# የኢዴፓ የፖለቲካ ፕሮግራም ትንታኔ

## ክፍል ሦስት (Volume - 3)

## የኢዴፓ የኢኮኖሚ ልማት መስመርና ስትራቴጂዎች

(ረቂቅ - ፩)

ሰኔ 1995 ዓ.ም

## ብርቱ ማሳሰቢያ፣

ይህ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለሕዝብ ይፋ የተደረገው በሰኔ ወር 1995 ዓ.ም ነው። ፖለቲካ በባህሪው የተለዋዋጭ ሂደቶች (Political Dynamism) ውጤት ነው። በዚህም ምክንያት ሰነዱ ከተዘጋጀ ወዲህ ባሉት ጊዜአት በሀገሪቱ በርካታ ሁኔታዎች ተስተውለዋል። እንደ ፖለቲካ ኃይል፤ ኢዴፓም የዚሁ ዳይናሚዝም ውጤት ነው። ስለሆነም፣ ፓርቲው ይህንን ሰነድ አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ የመጨረሻውን Version እስከሚያወጣ ድረስ፤ ይህንን ሰነድ የሚያነቡ ሁሉ የተጻፈበትን ወቅት የቋንቋ አጠቃቀምና ስነልቡና ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ በአክብሮት እናሳስባለን።

**(የኢዴፓ የውጭ ጉዳይ ዘርፍ)**

# ክፍል - 3

# የኢዴፓ የኢኮኖሚ ልማት መስመርና ስትራቴጂ

## 1. መግቢያ

በኢትዮጵያ ውስጥ መኖር የሚገባውን የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ልማት አቅጣጫ ይዘትና ባሕሪይ ለመወሠን በቅድሚያ አገሪቱ የሚያስፈልጋት ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት (Socio Economic System) ምን መሆን እንዳለበት ተለይቶ መታወቅ ይኖርበታል:: በአገሪቱ ውስጥ መገንባት የሚኖርበት የፖለቲካና ኢኮኖሚ ሥርዓት በግልፅ ካልታወቀ ዓላማና ግቡ በማያሻማ መንገድ የተቀመጠ የልማትና የዕድገት ፖሊሲ መንደፍ አስቸጋሪ ነው:: በአንድ አገር ውስጥ መገንባት ያለበትን ሥርዓት የመወሠን ኃላፊነት በሁሉም ዜጐች ትከሻ ላይ የሚወድቅ ቢሆንም አገሪቱና ሕዝቡ ያሣለፉትን ልምድ፣ አሁን የሚገኙበትን ተጨባጭ ሁኔታና የወደፊቱን መፃኢ ዕድል ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እየገመገሙ የተሻለውን አማራጭ በማቅረብ ረገድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ግንባር ቀደም ሚና አላቸው:: በመሆኑም የኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ (ኢዴአፓ) ከረጅም ጊዜ አንስቶ በዴሞክራሲ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር መጥፋት፣ ተከታታይነት ያለው ዘላቂ የልማትና የዕድገት እስትራቴጂ መታጣት የተነሣ ለጦርነት፣ ለበሽታ፣ ለመሃይምነት፣ ለርሃብና ለድህነት ሠለባ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ የኋላቀርነት አዙሪት ወጥቶ ዘላቂ ወደሆነ የዴሞክራሲና የልማት ደረጃ እንዲደርስ የራሱን ራዕይ ይዞ የተቋቋመ ፓርቲ ሲሆን ለዚህ ራዕይ እውን መሆን ይጠቅማል የሚለውን አማራጭ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ሥርዓት ምንነት በፕሮግራሙ ውስጥ አስፍሯል::

በኢዴፓ ፕሮግራም መግቢያና በሌሎች አምስት ክፍሎች ውስጥ በተለያዩ አንቀጾች የተዘረዘሩት የፓርቲው የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባሕል መስመሮችና አቅጣጫዎች በጥሞና ሲታዩ ፓርቲው በኢትዮጵያ እንዲገነባ ያቀረበው የፓለቲካና ኢኮኖሚ ሥርዓት ፍትሀዊ ካፒታሊዝም መሆኑን መገንዘብ ይቻላል:: ፓርቲው ይኸን ሥርዓት እንደ አማራጭ ሲያቀርብ በካፒታሊስት ርዕዮተ ዓለም ለመመራት፣ የዚህኑ ሥርዓት አጠቃላይ መርሆዎችና ድንጋጌዎች ተቀብሎ ለመስራት ፈቅዶና ውሣኔ አድርጐ መሆኑ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነገር አይደለም:: ይህ ሲባል መሠረታዊው የካፒታሊዝም መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታና ተጨባጭ እውነታ ያገናዘበ ያፈጻጸም እስትራቴጂና ስልት መንደፍና ተግባራዊ ማድረግ አያስፈልግም ማለት አይደለም::

የፓርቲውን መስመሮችና አቅጣጫዎች በሚመለከት አልፎ አልፎ ከሁለት የተለያዩ ማዕዘናት የሚነሱ ጥያቄዎች እንዳሉ ይታወቃል:: የመጀመሪያው የፓርቲውን ፕሮግራም ይዘት በጥልቀት ካለመረዳት ወይንም የበለጠ ግልፅነት እንዲኖር ከመፈለግ በሚመነጭ መንፈስ የሚቀርብ ገንቢ ጥያቄ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የፓርቲውን ፕሮግራም ይዘት ተረድቶ ነገር ግን የተዛባ ትርጉም ለመስጠትና ወይንም በሚገባ ተለይቶ የተቀመጠ አቅጣጫና ግብ የሌለው ድርጅት አድርጐ ውዥንብር በመንዛት የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት መሠሪ ተልዕኮ ካነገቡ ክፍሎች የሚመነጭ ነው::

በመጀመሪያዎቹ ወገኖች የሚነሣው ጥያቄ የፖርቲውን ጥንካሬና ዕድገት ከመፈለግ የሚመነጭ እንደመሆኑ ፕሮግራሙን ለማዳበር፣ የበለጠ ግልፅነትና ስፋት እንዲኖረው ለማድረግ በፓርቲው ውስጥና በሕዝቡ መካከል በሚከናወን ተከታታይ የፖለቲካ ሥራ መፍትሔ የሚያገኝ ሲሆን በሁለተኛዎቹ ወገኖች የሚነሣው ጥያቄ ደግሞ እልባት የሚያገኘው በፓርቲው መስመር ጥራት ብቻ ሳይሆን በሕዝቡ ውስጥ በሚሠራው ፖለቲካዊ ሥራ ብቃትና በሚያገኘው ተቀባይነት መጠን ነው:: የፓርቲውን መስመር አምኖ የሚቀበለውና በዚህ መስመር ዙሪያ የሚሠለፈው አባልና ደጋፊ የመስመሩ ተቀናቃኞች ሊያሰልፉት ከሚችሉት የበለጠ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የመስመሩ አሸናፊነት ይረጋገጣል:: እዚህ ደረጃ እስኪደረስ ድረስ ውዥንብሩና የተዛባ ትርጉም እየሠጡ የፓርቲውን መስመር ለመፈታተን የሚደረገው ርብርብ ይረግባል ተብሎ አይታሰብም::

በተለይም አሁን የመንግሥት ሥልጣን ይዘው የሚገኙ አብዮታዊ ዴሞክራቶችና ተባባሪዎቻቸው ከካፒታሊዝም ሥርዓት መርሆዎችና ድንጋጌዎች ጋር እንዳይስማሙ የሚያደርጋቸው ርዕዮተ-ዓለማዊና ፖለቲካዊ ባሕርይ ስላላቸው የኢ.ዴ.ፓን መስመር በተለያየ ሥልትና አቀራረብ ከመፃረር ይቆጠባሉ ተብሎ አይጠበቅም:: የሚከተሉት «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» የሚባለው አመለካከትና የፖለቲካ መስመር ለካፒታሊዝም ሥርዓት ተፃራሪና የዚሁ ሥርዓት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ንድፈ-ሃሳብ መሠረት በሆነው ሊበራል ዴሞክራሲ ማዕቀፍ ውስጥ ፈፅሞ ሊካተት የማይችል ነው::

«አብዮታዊ ዴሞክራሲ» የሚባለው ፅንሰ-ሃሳብ በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርዕዩተ-ዓለም ማዕቀፍ ውስጥ የሚታይና በዋናነት የሶሻሊዝም ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት የቆመባቸውን መርሆዎችና ሕግጋት የሚከተል ነው:: መሠረታዊ ትርጉሙም በማርክሲዝም ሌኒንዝም (ማሌ) መዝገበ ቃላት እንደሠፈረው ከከተማው ንዑስ ከበርቴ፣ ከገበሬውና ከምሁራን መካከል አብዮታዊ የፖለቲካ ንቃት ያላቸውን፤ በፀረ ፊውዳል፣ ፀረ-ኢምፔራያሊስትና ፀረ-ካፒታሊስት ትግል የተሠለፉትን ክፍሎች የያዘ፤ የእነዚህን ቡድኖች ጥቅምና ፍላጐት የሚወክሉ ፓርቲዎችን፣ ድርጅቶችንና ቡድኖችን ያቀፈ አመለካከት ማለት ነው:: ከዚህ ትርጉም መረዳት እንደሚቻለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚባለው አመለካከት የሚወክላቸው መደቦችና ጥቅሞች ያሉት፣ የሚፃረራቸውና የሚታገላቸው መደቦችና ጥቅሞችም ያሉት መሆኑን ነው:: ከሚፃረራቸው መካከል የካፒታሊዝም ሥርዓት አንዱ ነው:: ከእስካሁኑ የሕብረተሰብ ዕድገት ሂደት እንደታየው «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» በንድፈ-ሃሳብም ሆነ በተግባር የካፒታሊዝም ተፃራሪ ሆኖ ከመቆም የተለየ ገድል እንደሌለው የሚታወቅ ነው:: በተለይም ደግሞ ከፊል ካፒታሊስትና በአብዛኛው በቅድመ ካፒታሊስት የዕድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ አገሮች ሥልጣን በመያዝ ፀረ-ፊውዳል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ፀረ-ካፒታሊስት የሆነውን ትግል በማርክሳዊ-ሊኒናዊ ድርጅት ግንባር ቀደም መሪነት የሚያራምድ ኃይል ነው:: ከዚህ መሠረታዊ ትርጉም መገንዘብ የሚቻለው «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» የሶሻሊዝም ሥርዓት ርዕዮተ-ዓለም እንደሆነ በሚታወቀው ማርክሲስት-ሌኒኒስት ቲዎሪ ማዕቀፍ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር በሊበራል ዴሞክራሲ ማዕቀፍ ውስጥ የሚቆምበት ሥፍራ የሌለው መሆኑን ነው:: እንዲያውም የሊበራል ዴሞክራሲ እሴቶችንና መርሆዎችን በቀጥታ የሚንድ አመለካከት ነው:: በዚህም መሠረት በአብዮታዊ ዴሞክራሲ መርህ እየተመራ የተገነባ ካፒታሊዝም ከዚህ በፊት በሕብረተሰብ ታሪክ እንዳልታየ ሁሉ ወደፊትም ይኖራል ተብሎ አይታሰብም:: ምክንያቱም አብዮታዊ ዴሞክራሲንና ካፒታሊዝምን የሚያስተሳስር አንዳች ነገር ባለመኖሩ ነው::

የካፒታሊዝም ሥርዓት በሊበራል ዴሞክራሲ እሴቶች ላይ የተመሠረተና የራሱ የሆነ ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ ንድፈ-ሃሳብ ያለው ነው:: በተለምዶ የምዕራቡ ዓለም ዴሞክራሲ እየተባለ የሚጠራው ሊበራል ዴሞክራሲ የካፒታሊዝም ሥርዓት ርዕዩተ-ዓለምና የኢኮኖሚ ንድፈ-ሃሳብ መሠረት ነው:: ካፒታሊዝም በዋናነት በሊበራል ዴሞክራሲ እሴቶችና መርሆዎች ላይ የቆመ ሥርዓት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ እንደየ አገሩ ነባራዊና ልዩ ሁኔታ ተስማሚ የሆኑ ልዩ ልዩ የግንባታ አማራጮችን ሥራ ላይ በማዋል የሚገነባ ሥርዓት ነው:: እነዚህ ልዩ ልዩ የግንባታ (አፈፃፀም) አማራጮች የሊበራዝምን እሴቶች የሚያጠፉ ሳይሆኑ ይበልጥ የሚያዳብሩ፣ የሚያሰፉና ፈጠራ በተሞላበት መንገድ ከእያንዳንዱ አገር ተጨባጭ እውነታ ጋር የሚያጣጥሙ ናቸው::

የሊበራል ዴሞክራሲ ማዕከላዊ ነጥብ በሆነው የግለሰብ ነፃነት ላይ የቆመው የአሜሪካ ዴሞክራሲ ወይንም ሠፊ የማህበራዊ ደህንነት መረብ ዘርግቶ ሥራ ላይ በማዋል የሚታወቀው የአውሮፓ ሶሻል ዴሞክራሲ (በስካንዲናቪያን አገሮች፣ በጀርመንና በሌሎች አውሮፓ አገሮች ያለው ዴሞክራሲ) ወይንም ደግሞ በስዊትዘርላንድ፣ በቤልጅየምና በአውሮፓ ሕብረት ሥራ ላይ የዋለውና የተለያዩ አመለካከቶችንና ጥቅሞችን በማቻቻል መርህ ላይ የቆመው የድርድርና የስምምነት ዴሞክራሲ(Consensus Democracy) ሁሉም በሊበራል ዴሞክራሲ መሠረታዊ እሴቶች ላይ ተመሥርተው ከዚሁ ማዕቀፍ ሳይወጡ አጠቃላይ መርሆዎችን እንደራሣቸው ተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ የሚያደርጉ ናቸው:: በሁሉም የምዕራብ ዴሞክራሲዎች የተገነባው የካፒታሊዝም ሥርዓት የሊበራል ዴሞክሲን እሴቶችና መርሆዎች የጠበቀ በመሆኑ እንደየሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታ የስያሜና የአፈፃፀም ልዩነቶች ቢኖሩም እርስ በርስ ተፃራሪ የሚሆንበት ወይንም አንዱ ሌላውን የሚቃረንበት መንገድ የለም::

በእኛ አገር አሁን ሥልጣን የያዘው አገዛዝ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በሚያወጣቸው የፖሊሲ ሠነዶች ውስጥ የካፒታሊዝም ሥርዓትን ለመገንባትና የነፃ ገበያ ሥርዓትን ለመከተል እንደሚፈልግ የሚጠቁሙ ሀረጐችን መጠቀም ቢጀምርም በተግባር ግን ያንኑ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አቋሙን ከማራመድ እንዳልተገታ በግልፅ የሚታይ ነው:: በገዢው ፓርቲ የፖለቲካ ፕሮግራምና በመሠረተው መንግሥት ልዩ ልዩ የፖሊሲ ሠነዶች ውስጥ «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» ርዕዩተ-ዓለማዊ መርሁ ሆኖ ሠፍሯል:: የፖለቲካ ድርጅቱ መጠሪያ «የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር» ሲሆን የድርጅቱ ልሣንም «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» ተብሎ ነው የተሠየመው:: ሌላው ቀርቶ የአሁኑ አገዛዝ ግንባር ቀደም መሪና አስተባባሪ ኃይል ተደርጐ የሚወሰደው ሕዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ (ሕውሓት) አቋቁሞት የነበረው መሪ የፖለቲካ ድርጅት «ማርክሣዊ ሌኒናዊ ሊግ ትግራይ (ማሌሊት)» ተብሎ እንደሚጠራ ይታወቃል:: ይህ ድርጅት አሁን በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ በይፋ የተገለፀ ነገር ባይኖርም «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» የሚባለው መስመሩና ርዕዮተ-ዓለማዊ መመሪያው የአሁኑ መንግሥት የፖሊሲ ምንጭና መሠረት ሆኖ እያገለገለ ነው:: በዚህና በሌሎችም ተጨባጭ ምክንያቶች የተነሣ ገዢው ፓርቲ በተለያዩ ሠነዶች ውስጥ ስለ ሊበራሊዝም፣ ነፃ ገበያና ካፒታሊዝም ጥቂት ሀረጐችን እየጠቀሰ ለማስመሠል የጀመረው ጥረት ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ከባድ ጫና እንዳይደርስበትና የሥልጣኑ ማራዘሚያ የሆነው የምዕራቡ ዓለም ዕርዳታና ብድር እንዳይቋረጥበት የሚያደርገው ሽወዳ ነው:: ይህ አገዛዝ በአንድ በኩል የነፃ ገበያና ካፒታሊዝምን መፈክር እያስተጋባ በሌላ በኩል ደግሞ በተግባር ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር ዝንፍ ሳይል እየሠራ በሁለት የማይጣጣሙ አመለካከቶች መካከል ቆሞ የድብብቆሽ ጨዋታ ማካሄድን የመረጠ አገዛዝ ነው::

# 2. የካቲታሊዝም ሥርዓት መርህና አተገባበር

## 2.1 የካፒታሊዝም ሥርዓት ምንነትና ዋና ዋና ባህርያት

የካፒታሊዝም ሥርዓት መሠረታዊ ትርጉም የማምረቻ መሣሪያዎች በግል ሀብት ባለቤትነት የተያዘበት፣ አቅርቦትና ፍላጐት (Demand and Supply) በሚባሉት የገበያ ሚዛኖች የሚገዛ፣ አንፃራዊ በሆነ መንገድ ነፃና ተወዳዳሪ የሆነ ገበያ የሠፈነበት፣ አብዛኛው የሥራ ኃይል በመንግሥት ሳይሆን ለትርፍ በተቋቋመ የግል ድርጅት ውስጥ የተሠማራበት የኢኮኖሚ ሥርዓት ማለት ነው:: የቀድሞው ትርጉሙ በሌሴፌር አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ሆኖ መንግሥት በንብረት ባለቤትነት፣ በምርትና በንግድ ተግባር መግባትና ክልከላ ማድረግ አይገባውም የሚል ነበር:: ይሁን እንጂ የአሁኑ ዘመን ትርጉም ደግሞ መንግሥት ክልከላና የዘፈቀደ አሠራርን አስወግዶ በሕግ የተወሠነ ተሳትፎ ሊኖረው ይገባል የሚል ነው:: መንግሥት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረው ተሳትፎ የነፃ ገበያ ውድድርንና የትርፍ ዓላማን በማያጠፋ መንገድ የተቃኘ መሆን አለበት የሚል ነው::

ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው የካፒታሊዝም ሥርዓት በሊበራል አመለካከት ላይ የተመሠረቱ መርሆዎችንና ሕግጋትን ተከትሎ የሚገነባና በዚህ መሠረት የሚሠራ ሥርዓት ነው:: ከካፒሊዝም መሠረታዊ መርሆዎች መካከል አንደኛው የግል ሀብት ባለቤትነት መኖር ነው:: በካፒታሊስት ርዕዮተ-ዓለም መሠረት የግል ሀብት ባለቤትነት ከሰው ልጅ ነፃነት የማይነጠልና የተቀደሰው የሰው ልጅ መብት ተደርጐ የሚታይ ነው:: በካፒታሊስት ርዕዩተ-ዓለም መሠረት በሰው ልጅ ነፃነትና በግል ሀብት ባለቤትነት መካከል ያለው ግንኙነት ሊነጣጠል የማይችል ነው:: በዘመናችን የካፒታሊዝምን ሥርዓት የገነቡ አገሮች አሁን ከደረሱበት የዕድገትና የብልፅግና ደረጃ መድረስ የቻሉት የግል ሀብት ባለቤትነት መብትን ለማረጋገጥ በመቻላቸው መሆኑ ሠፊ ተቀባይነት አግኝቷል:: ከዚሁ የግል ሀብት ባለቤትነት መብት ጋር የተያያዘው ጠቃሚ ነጥብ የግል ባለሀብቶች ንብረት የሆኑ የምርት፣ የንግድና አገልግሎት ተቋሞች ነፃነት መኖር ነው:: በዚህም መሠረት ምን ዓይነት ምርትና አገልግሎት፣ በምን ዓይነት የሥራ ኃይል፣ በምን ያህል መጠንና ደረጃ፣ ለየትኛው ተጠቃሚ ማቅረብ እንዳለባቸው የሚወስኑት ራሣቸው ግለሰቦቹና ተቋሞች ሲሆኑ መንግሥት ክልከላና ገደብ በማድረግ ጣልቃ አይገባባቸውም:: ይህ አስተሳሰብ ሌላኛው የካፒታሊዝም መሠረታዊ መርህ ወደ ሆነውና ነፃ ገበያ ወደሚባለው አሠራር የሚያሸጋግር ድልድይ ነው::

ነፃ ገበያ የሚባለው የካፒታሊዝም መርህ ምርት የሚያመርቱ፣ አገልግሎት የሚሰጡና ንግድ የሚያካሂዱ ባለሀብቶችንና ተቋሞችን ብቻ ሳይሆን የተጠቃሚዎቹንም ነፃነት አካቶ የያዘ ነው:: የነፃ ገበያ መርህ ሲባል ሻጮችና ገዥዎች ገበያ እንዳይገበያዩ የሚከለክል ገደብ በሌለበት ሁኔታ የሚካሄድ የገበያ ግንኙነት ሥርዓት ማለት ነው:: በመሆኑም ገዢዎችና ሻጮች በሚፈልጉት መንገድ ለመግዛትና ለመሸጥ ሙሉ ነፃነት ያላቸው ሲሆን ዋጋ የሚወሠነው ወይንም በሌላ አገላለፅ ዋጋ የሚጨምረውና የሚቀንሰው ለሽያጭ በሚያቀርበው ምርትና አገልግሎት መጠንና የቀረበውን ምርትና አገልግሎት ለመግዛት ባለው ፍላጐት መጠን ይሆናል:: በአጭሩ ዋጋ የሚወሠነው በአቅርቦትና በፍላጐት እንጂ በመንግሥት ትዕዛዝ አይደለም ማለት ነው:: የነፃ ገበያ መርህ ግለሰቦችና ተቋሞች ሀብታቸውን የት ላይ ማዋል እንዳለባቸው፣ የትኛውን ምርትና አገልግሎት ማቅረብ እንደሚገባቸውና ለማንና በምን ዓይነት ሁኔታ ለሺያጭ ማቅረብ እንዳለባቸው ተጠቃሚዎችም የትኛውን ምርትና አገልግሎት፣ መቸ፣ የትና በምን ያህል መጠን መግዛት እንደሚገባቸው በነፃነት የሚወስኑበትን ሥርዓት የሚመለከት ነው:: አሁን በዓለም ደረጃ የሠፈነውና ግሎባላይዜሽን የሚባለውም የዘመናችን ክስተት የቆመበት መርህ የተመሠረተው በዚሁ የነፃ ገበያ አስተሳሰብ ላይ ነው:: የግሎባላይዜሽን ዋነኛ ባሕሪይ በየትኛ ውም የዓለም ክፍል የሚመረቱ ምርቶችና አገልግሎቶች የድንበር፣ ኮታና ታሪፍ እገዳ ሳይደረግባቸው ከአንዱ አገር ወደሌላኛው አገር በነፃ እንዲዘዋወር የሚፈቅድ፣ መንግሥት በነፃ ውድድር ሂደት ውስጥ ጣልቃ እየገባና ተፅዕኖ እያደረገ ድጐማና ማበረታቻ የሚሰጥበትን አሠራር እንዲያቆም የሚጠይቅ መሆኑ ነው::

ለገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት አስፈላጊ የሆነው ቅድመ ሁኔታ የውድድር መኖር ነው:: ውድድር ከሌለ የገበያ ኢኮኖሚ ጨርሶ የማይታሰብ በመሆኑ ውድድርና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት የማይነጣጠሉ ናቸው:: ተጠቃሚው የሚፈልገውን ምርትና አገልግሎት በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት የሚችለው በአምራቾችና አገልግሎት ሰጪዎች መካከል ውድድር ሲኖር ነው:: ጥራት ያለው ምርትና አገልግሎት በዝቅተኛ ዋጋ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ የቻለው ወገን በገበያው ላይ የመቆየት ዕድል ሲኖረው ተጠቃሚዎች የማይፈልጉትን ምርትና አገልግሎት ብቻ ሳይሆን ከመግዛት አቅማቸው በላይ በሆነ ዋጋ የሚያቀርበው ደግሞ ከገበያ ይወጣል:: በዚህ መንገድ አቅርቦትና ፍላጐትን በመከተል በነፃነት ላይ ተመሥርቶ የሚከናወን የገበያ ግንኙነት መኖር የካፒታሊዝም ሥርዓት አንድ ጠቃሚ መርህ ነው::

ከዚሁ የገበያ መርህ ጋር የተያያዘው ሌላ ቁም ነገር ትርፍ የማግኘት ጉዳይ ነው:: ትርፍ ማግኘ ት የገበያ ሥርዓት ዋነኛው አንቀሣቃሽ ሞተር እንደመሆኑ ትርፍ በሌለበትና የሕዝብ ጥቅም ብቻ ቅድሚያ በሚጠየቅበት ሁኔታ የገበያ ሥርዓት ውጤታማ ሊሆን አይችልም:: የካፒታሊዝም ርዕዮተ-ዓለም ትርፋማነት እንዲኖር የግል ሀብት ባለቤትነት መኖር አለበት ብሎ ያምናል:: ምክንያቱም ሀብትንና የኑሮ ደረጃን ማሳደግ የሚቻለው ትርፋማ በመሆን ነው:: የግል ባለሀብቶች ትርፍ ለማግኘት ጥረት ባደረጉ ቁጥር ተጠቃሚዎች በጣም የሚፈልጉትን ምርትና አገልግሎት በተሻለ ዝቅተኛ ዋጋ ለማቅረብ ይደፋፈራሉ:: በዚህም የተነሣ ሻጭና ገዢ ተጠቃሚ ይሆናሉ:: በአንፃሩ ተጠቃሚዎች የማይፈልጉትን ምርት በማምረት የተሠማሩት ባለሀብቶች በፍጥነት ከንግዱ ውድድር የመውጣት ዕድል ያጋጥማቸዋል:: የተወሠነ ሸቀጥ ለማምረት የሚወጣው ወጪ ተጠቃሚዎች ሊከፍሉት ከሚችሉት ዋጋ የበለጠ ከሆነ ትርፍ ሊገኝ ስለማይችል አምራቾች ያመራረት ዘዴያቸውን እንደገና ለመፈተሽ ይገደዳሉ:: በውጤቱም ባለሀብቶች ሁለቱንም ግዴታዎች ለመፈፀም ማለትም የሚገቡበትን አዲስ ገበያ ለመፈለግና የማምረቻ ዋጋቸውን ዝቅ ለማድረግ ተግተው ይሠራሉ:: ስለዚህ ከተጠቃሚው ፍላጐት አኳያ ሀብትን በከፍተኛ ብቃት ጥቅም ላይ የማዋል አዝማሚያ ይፈጠራል:: በመሆኑም ሻጭና ገዢ ሁሉም ተጠቃሚ ይሆናሉ::

በካፓታሊስት ርዕዮተ-ዓለም (አይዲዮሎጂ) መሠረት የካፒታሊስት ገበያ ኢኮኖሚ በባሕሪይው በነፃ ውድድር ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ አንድ ባለሀብት ከተገቢው በላይ ትርፍ ሊያገኝ አይችልም ተብሎ ይታመናል:: ምክንያቱም አንድ ምርት ከተገቢው ዋጋ በላይ በሽያጭ የሚቀርብበት ሁኔታ ከተፈጠረ ገዢዎች የመግዛት ፍላጐት አይኖራቸውም:: በምትኩ በሌላ ድርጅት የተመረቱትንና በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡትን ተመሣሣይ ምርቶች ይገዛሉ:: በዚህም የተነሣ በተመሣሣይ ምርት የሚወዳደሩ ኃይሎች ሀብትን (ሪሶርስን) ውጤታማ በሆነ መንገድ እየተጠቀሙ በገበያው ውስጥ ትርፋማ ለመሆን ይጥራሉ:: አንድ የማምረቻ ተቋም ለሠራተኞች ከመደበው ክፍያ በመቀነስ ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት ቢሞክር ምርጥ የሆኑት ሠራተኞቹ የተሻለ ክፍያ ወደሚያገኙበት ሌላ የማምረቻ ተቋም ጥለውት ይካሄዳሉ:: ይኸም የተቋሙ ምርት ጥራት

እንዲቀንስ ምክንያት ይሆናል፡፡ በመጨረሻም አንድም ከውድድሩ ይወጣል አሊያም ቢያንስ ለሠራተኛ ከፍተኛ የሆነ ክፍያ እንዲያወጣ ይገደዳል፡፡ ስለሆነም የዚህ ዓይነቱ ችግር እንደዳይከሠት ምርቱን በተገቢው ተመጣጣኝ ዋጋ በሽያጭ ያቀርባል፡፡ ሠራተኞችም ለድካማቸው ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያ ያገኛሉ፡፡ እንደዚህ ዓይነት አሠራር ሲኖር ሀብትን (ሪሶርስን) በብቃት ለመጠቀም ይቻላል፡፡ ባለሀብቱም ተመጣጣኝ ትርፍ፣ ገዢውም ከአቅሙ ጋር የሚመጣጠን ምርትና አገልግሎት ያገኛሉ፡፡ በዚህ መንገድ ባለሀብቱ፣ ሠራተኛውና ገዢው ሕብረተሠብ በአጠቃላይ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ ይፈጠራል የሚል መሠረታዊ ግንዛቤ አለ፡፡

ሌላው የዘመናችን የካታሊስት ሥርዓት ባህሪ በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የመንግሥት ተሣትፎ ተቀባይነት ማግኘት ነው፡፡ ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው ካፒታሊዝም ከመነሻው በጥቂት ባለሀብቶችና በነፃ ገበያ ውድድር ላይ የተመሠረት ሥርዓት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይኸውም አብዛኛውን ጊዜ ትክክለኛው የውድድር ኢኮኖሚ ሞዴል ተደርጐ ሲታይ ቆይቷል፡፡ የዚህ ሞዴል አንድ ገፅታ ደግሞ መንግሥት ምንም አይነት የማምረቻ ድርጅት ባለቤት እንዳይሆንና በማንኛውም መንገድ ኢኮኖሚውን የመምራትም ሆነ የመቆጣጠር ሚና እንዳይኖረው የሚጠይቅ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የወቅቱ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ባሕሪይ በሁለት መሠረታዊ ግንዛቤዎች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ እነዚህም አንደኛው ምርት የሚመረተው ለትርፍ ነው የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በከፊል የመንግሥት ቁጥጥር የሚደረግበት የግል ሀብት ባለቤትነት መኖር አለበት የሚል ነው፡፡ በካፒታሊዝም ሥርዓት ጠንካራ እምነት ያላቸው ወገኖች የዚህ ዓይነቱ የኢኮኖሚ አደረጃጀት መኖር የኢኮኖሚውን አሠራር ብቃት ያሣድጋል፣ ፖለቲካዊ ሊበራልዝምን ለመጠበቅና ዜጐች ሁሉ ማንኛውንም ዕድል በእኩል ደረጃ ለመጠቀም የሚችሉበትን በር ይከፍታል፤ የገበያ ኢኮኖሚ በሚፈጥረው ክፍተት ሊከሠት የሚችለውን ያለመመጣጠን ለመቀነስና የልዩነቱን ደረጃ ለማጥበብ ይረዳል ብለው ያስባሉ፡፡ ስለሆነም ለትርፍ የማምረት ዓላማን የማይፃረር፣ የገበያ ኢኮኖሚን የሚደግፍ፣ ውድድርን የሚያበረታታ፣ የግል ሀብት ባለቤትነት መኖርን እንደ መሠረታዊ የሰው ልጅ መብት የሚቀበልና ከግል ባለሀብቶች ጋር በአጋርነት ለመሥራት የተዘጋጀ መንግሥት በኢኮኖሚው ውስጥ ተሣትፎ ሊኖረው ይገባል የሚል ጠንካራ እምነት አላቸው፡፡ የመንግሥት ተሣትፎ የካፒታሊዝም ኢኮኖሚ ሥርዓት በነፃ ገበያ፣ በውድድርና ትርፍ በማግኘት መርህ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ታሣቢ ያደረገ ሆኖ በተለይም ለኢኮኖሚው ፍሬያማነት አስፈላጊ የሆኑትን የፖሊሲ ጉዳዮች ማሟላት፣ ሕግና ሥርዓትን ማስከበር፣ ሰላምና መረጋጋትን መፍጠር እንዲሁም ለግል ባለሀብቶች አትራፊ በማይሆኑትና ለሕዝቡ ጥቅም በሚሠጡት የኢኮኖሚ ልማትና የማኅበራዊ አገልግሎት መስኮች ተሠማርቶ ግንባር ቀደም ሚና በመጫዎት ላይ ማተኮር ይገባዋል ብለው ያምናሉ፡፡ በዚህም የተነሣ በግል ሀብት ባለቤትነት ላይ ብቻ የተመሠረተ ንፁህ የካፒታሊዝም ሥርዓት በዓለማችን የገነባ አገር ማግኘት ይከብዳል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የካፒታሊስት ገበያ ኢኮኖሚ በርዕዮተ-ዓለማዊ ትርጓሜው ተሟልቶ የሚገኝበት ሥፍራ በየትኛውም የአለም ክፍል ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡

በርዕዮተ ዓለም ደረጃ ለካፒታሊስት ኢኮኖሚ ሥርዓት ቁርጠኛ አቋም አላት የምትባለውን አሜሪካን ጨምሮ በብዙዎች የካፒታሊስት ኢኮኖሚዎች ውስጥ የመንግሥት ተሳትፎ ጨርሶ የተከለከለበት ሁኔታ የለም፡፡ በኢኮኖሚው ውስጥ መንግሥታት ቀላል የማይባል የቁጥጥር ሚና ይጫወታሉ፡፡ ለምሳሌ በእንግሊዝ ከፍተኛ ቁጥር ያለውን የሥራ ኃይል የያዙ ኢንዱስትሪዎች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር እንዲሆኑ የተደረገበትን ሁኔታ ማስታወስ ይቻላል፡፡ በካፒታሊስት ኢኮኖሚዎች ውስጥ የሚሠሩ ሞኖፓሊስቶች የራሣቸውን ጥቅም ለመጠበቅ ሲሉ የእርስ በርስ ውድድር ላለማድረግ የሚፈጥሩትን ቅንጅትና ስምምነት ለመከላከል ፀረ-ትረስት ሕግ አውጥተው ሥራ ላይ የሚያውሉ አገሮች አሉ፡፡ ለምሣሌ፣ የጀርመን የትብብር ሕግ ለመጀመሪያ ጊዜ እ.ኤ.አ በ1957 ወጥቶ በኋላም በየጊዜው እየተሻሻለ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ የዚህ ሕግ ዋና አላማ ውድድርን በመገደብ በገበያ ሁኔታ ላይ ተፅዕኖ የሚያሣድሩ ሁኔታዎች ለመፍጠር ሲባል የሚደረገውን ትብብር መከልከል ነው፡፡ ይኸንን ሕግ ተፈጻሚ የማድረግ ኃላፊነት በርሊን ለሚገኘው የፌደራል የካርቴል ቢሮና በየግዛቶቹ ለሚገኙት ፀረ ትረስት መምሪያዎች የተሠጠ ነው፡፡

የገበያ ኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ኃይል ትርፍ እንደመሆኑ ለግል ባለሀብቱ ትርፋማ ያልሆኑትንና ለሕዝቡ ከፍተኛ ጥቅም የሚያስገኙትን የኢኮኖሚ ክፍሎች መንግሥት በኃላፊነት ይዞ የሚያንቀሳቅስበት አሠራር በብዙዎቹ የካፒታሊስት ኢኮኖሚዎች ውስጥ የተለመደ ነው፡፡ ለምሣሌ በጀርመን በቀድሞው ምስራቅ ጀርመን ስር የነበሩና አሁን በአዲሲቱ የፌዴራል ግዛት

ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ተቋሞች ቀስ በቀስ ወደገበያ ሥርዓቱ ሊጠቃለሉ እንደሚችሉ ታሣቢ በማድረግ በመንግሥት በሚሠራ የትረስት ወኪል ሥር ሆነው ያለትርፍ እንዲሠሩ እየተደረገ ነው። በቀድሞው ምስራቅ ጀርመን ሥር የነበሩት ባቡር መንገድና ፓስታ ቤት አሁን በጀርመን ፌደራል ባቡር መንገድና ጠቅላይ ፖስታ ቤት ሥም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ናቸው። መንግሥት ይኸንን ኃላፊነት የወሠደው የባቡር መንገድ ማህበራዊ ተቀባይነት ያለው ዋጋ እንዲያስከፍልና ፖስታ ቤቱ ደግሞ ሩቅ መንደሮችን ከአገልግሎት ውጭ እንዳያደርግ ለመቆጣጠር እንዲቻል ነው። በዚህም መንገድ መንግሥት የገበያ ውድድር በትዕግሥት ሊታለፍ የማይችል ማኀበራዊ ውጤት አለማስከተሉን የማረጋገጥ ኃላፊነቱን ይወጣል። በሁሉም የካፒታሊስት ኢኮኖሚዎች ውስጥ መንግሥታት የገበያ ውድድር አደገኛ ውጤት እንዳይኖረው ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚወስዷቸው እርምጃዎች አሉ። ከእነዚህም መካከል እንደ ፀረ-ትረስት ያሉ የመከላከያ ሕጐችን ማውጣት፣ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሠቦች የኪራይ ድጋፍ መስጠት፣ የሕንፃ ፕሮጀክቶችን ማዘጋጀትና ቤቶችን ዘመናዊ ማድረግ የመሳሰሉት ይገኛሉ።

በመርህ ደረጃ የነፃ ገበያ ውድድር ባለባቸው በብዙዎቹ የኢኮኖሚ ክፍሎች ሕግ አውጭዎች ወደ ገበያ የሚገቡ ሰዎች የሚያሟሏቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ይደነግጋሉ። በዚህም መሠረት የዕደ ጥበብ ሠራተኞችና ችርቻሮ ነጋዴዎች ለምሣሌ የንግድ ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ተፈላጊው የሞያ ብቃት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። ሌሎች ሥራዎች ለምሣሌ በሕክምና፣ በሕግ፣ በሂሣብ አያያዝና የግብር አማካሪነት ሥራ የሚሠማሩ ልዩ ሥልጠና እንዲኖራቸውና አነስተኛ የዕድሜ መስፈርት እንዲያሟሉ ይጠበቃል። በአጠቃላይ አነጋገር ለምሳሌ አሜሪካ የካፒታሊስት ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ግንባር ቀድም አርአያ ተደርጋ የምትገመት ቢሆንም በተጨባጭ በአሜሪካ ኢኮኖሚ ውስጥ የንፁህ ካፒታሊስት ገበያ ሞዴል መግለጫ ያልሆኑ ብዙ ዓይነት ገፅታዎች ይገኛሉ። ዋና ዋናዎቹን ነጥቦች ለማንሣት አንደኛ የማምረቻ መሣሪያዎች ሁልጊዜ በግል ባለቤትነት የተያዙ ሆነው አይገኙም። በአሜሪካ ኢኮኖሚ ውስጥ በመንግሥት የባለቤትነት ይዞታ ሥር ሆነው የሚንቀሣቀሱ የኤሌክትሪክ ኃይል አከፋፋዮች አሉ። ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የሚገለፅና በንግድ ሥራ ውስጥ የሚታይ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት አለ። እንዲያውም እየተስፋፋ መሄዱን የሚጠቁሙ ብዙ ምልክቶች አሉ። ምርምርና መከላከያ፣ ኤሌክትሮኒክስና የነዳጅ ኢንዱስትሪዎች በከፍተኛ ደረጃ በመንግሥት ውጪ የሚደገፉ ናቸው። በውጤቱም መንግሥት የእነዚህ ተቋሞች ደጋፊ አጋር ሆኗል። በተለመደው የንፁህ ገበያ ኢኮኖሚ አሠራር አትራፊ ሊሆኑ የማይችሉትን ፕሮጀክቶች አብዛኛውን ጊዜ ከሕዝቡ በሚሳበሰብ ታክስ ለመደገፍ መንግሥት ጥረት የሚያደርግ ቢሆንም ሕዝቡ ግን ሁኔታውን በሙሉ ልብ እንዳልተቀበለው ይታወቃል። ከተጠቀሱት ነጥቦች አኳያ ሲታይ የአሜሪካ ኢኮኖሚ ያለማወላወል በትርፍ ፍላጐት ላይ ብቻ የተመሠረተ እንዳልሆነ አጠቃላይ ግንዛቤ መውሠድ ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ አብዛኛዎቹ የንግድ ኮርፖሬሽኖች በአንድ ባለሀብት እጅ ከመያዝ ይልቅ በብዙ ባለሀብቶች ባለቤትነት ሥር መገኘታቸው በትርፍ ፍላጐት ላይ ብቻ ተመሥርቶ ለመንቀሣቀስ ያለውን ዕድል ያዳክማል። ምክንያቱም የአገሪቱን አምራች ሀብቶች የሚያስተዳድሩት የግድ የእነዚያ አምራች ተቋሞች ባለቤት ስለማይሆኑ የተቻለውን ከፍተኛ ትርፍ የማግኘቱ ፍላጐት ጠንካራ አይሆንም። በእርግጥ በዘመናዊ ካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የኩባንያዎች ትብብር ዓላማ በተከታታይ ማደጉ ትርፍ የማሳደጉን ዓላማ እየተካው ነው ብለው ጥቂቶች ይከራከራሉ። የአሜሪካ ኢኮኖሚ የነፃ ካፒታሊስት ገበያ ሞዴል ማረጋገጫ እንዳይይሆን የሚያደርገው ሁለተኛው ነጥብ ባለሀብቶች ደስ ወደአላቸውና ወደፈለጉት ማንኛውም ዓይነት ገበያ ለመግባት ሁል ጊዜም ነፃ አለመሆናቸው ነው። ለዚህ ሁኔታ በምክንያትነት ከሚጠቀሱት ጉዳዮች መካከል ፋይናንስ አንደኛው ነው። በተወሠኑ የኢንዱስትሪ መስኮች የተሠማሩ የቢዝነስ ተቋሞች በከፍተኛ ደረጃ በማደጋቸው በአጠቃላይ አዲስ ካምፓኒ ወደ ዘርፉ ተመጣጣኝ በሆነ ውድድር እግሩን ለመትከል እንዳይችል አድርገውታል። ምክንያቱም ወደ እነዚህ ዘርፎች ለመሠማራት የሚፈልግ አዲስ ባለሀብት መጠነ ሠፊ የመነሻ ካፒታል ወጪ እንዲመድብ ይገደዳል። ምንም ዓይነት የገቢ ምንጭ ከማግኘቱ በፊት ፋብሪካዎችን ለመገንባትና ለመገጣጠም ረጅም ጊዜ ይወስድበታል። በተጨማሪም ትርፋማ የመሆን አቅም ያላቸውን የተወሠኑ ገበያዎች ለምሣሌ እንደ ባንክ፣ ቴሌቪዥን ጣቢያና ሌሎች ተመሳሳይ ተቋሞች ውስጥ ለመግባት መንግሥት ማነቆዎችን ያስቀምጣል። እነዚህ ተቋሞች ሥራ ከመጀመራቸው በፊት በመንግሥት ኤጀንሲ የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው የግድ አስፈላጊ ነው። እንዲሁም መንግሥት ወደሌሎች ገበያዎች ለመግባት እንዳይቻል በፈቃድ አሰጣጥ፣ በአመራረት ቁጥጥር በመሳሰሉት የተለያዩ ሕጋዊ የመቆጣጠሪያ ዘዴዎች እየተጠቀመ ከባድ ገደብ የሚጥልበት ሁኔታ አለ።

ባለሀብቶች ወደመረጡት ገበያ ለመግባት ሁልጊዜ ነፃ ለመሆን እንደማይችሉት ሁሉ ተጠቃሚዎችም የፈለጉትን ምርትና አገልግሎት ለመግዛት ሁልጊዜ ነፃ አይደሉም:: በሸማቾች ነፃነት ላይ ከሚታዮት ችግሮች መካከል ከፊሎቹ የሚመነጩት ከመግዛት አቅም ውስንነት ነው:: በተሟላ ነፃ ገበያ ሥርዓት መርህ መሠረት ሁሉም ሰው ለሚፈልገው ዕቃና አገለግሎት ገንዘቡን በመክፈል ድምፁን ለማሠማት ይችላል:: በዚህ መንገድ በሚያሳድረው ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ የመደመጥ ዕድል አለው:: ይሁን እንጂ ድሃውና ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ገቢ የሚተዳደረው ሰው በዚህ ዓይነቱ ስርዓት ለማለት የሚችለው ትንሽ እንደመሆኑ የተሠሚነቱም ደረጃ ዝቅተኛ ነው:: በመሠረቱ በአሜሪካ ገበያ ውስጥ ገንዘቡ ያላቸው ሸማቾች እንኳ ሣይቀሩ ለመምረጥ የሚቸገሩበት ሁኔታ አለ:: ለምሣሌ ብዙ ጊዜ በርካታ የማስታወቂያ በጀት ከመኖሩ ጋር በተያያዘ አብዛኛው የሸማቾች ፍላጐት የሚፈጠረው አርቲፊሻላዊ በሆነ ሁኔታ የመሆኑ ጉዳይ ነው:: የአሜሪካ ኢኮኖሚ ንፁህ የገበያ ሥርዓት ሞዴል እንዳይሆን ካደረጉት ምክንያቶች መካከል በመጨረሻ የሚጠቀሰው ሦስተኛው ነጥብ የአቅርቦትና የፍላጐት ኃይል ሁልጊዜም ዋጋን የማይወስን መሆኑ ነው:: ይህ ሁኔታ የሚፈጠረው ጥቂት ከፍተኛ ተቋሞች ብቻ ኢንዱስትሪውን በሚቆጣጣሩበትና በገበያ ውስጥ የፈለገው አይነት ምርትና አገልግሎት ቢኖርም ዋጋውን እነዚህ ተቋሞች የሚወስኑበት ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ ነው:: በኢኮኖሚስቶች ቋንቋ ኦሊጐፖሊ የሚባለው እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲፈጠር ሌሎች አቅራቢዎች ስለማይኖሩ ተጠቀሚዎችን የሚደግፍ ሁኔታ አይኖርም:: በተወሰኑ ባለኢንዱስትሪ አገሮች ውስጥ ኢንዱስትሪዎች በጥቂት ኩባንያዎች ቁጥጥር ሥር የገቡበትና ወሣኝ ኃይል ሆነው የወጡበት ሁኔታ መኖሩ በኢኮኖሚው ውስጥ በግልፅ ይታያል:: በተጨማሪ መንግስት የዋጋ ቁጥጥር ያደርጋል፣ ዝቅተኛውን የደመወዝ መነሻ ይወስናል:: በተወሠኑ ኢንዱስትሪዎች ደግሞ የመነሻ ዋጋ ወለል ይወስናል:: ትክክለኛ ከሆነው የገበያ ኢኮኖሚ ፍልስፍና የመራቅ ሁኔታ ቢኖርም አሜሪካም ሆነች ሌሎች የምዕራብ መንግስታት አሁንም መሠረታዊ የሆኑትን የካፒታሊዝም ዕሴቶች አጥብቀው ያምኑባቸዋል:: እነዚህ የካፒታሊዝም ዕሴቶች ማለትም፤ የግል ሀብት ባለቤትነት፣ ነጻ የግል ተቋሞችና ለትርፍ የማምረት ፍላጐት የአሜሪካና የሌሎች ካፒታሊስት ሀገሮች ኢኮኖሚ ሥርዓት መሠረታዊ የማዕዘን ድንጋዮች ተደርገው በስፋት ተቀባይነት አግኝተዋል:: ከዚህ ውጭ ያለው አማራጭ መንገድ የዕዝ ኢኮኖሚ ሥርዓት ነው::

## 2.2 በካፒታሊዝም ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ የሚታዮ አበይት ችግሮች

የካፒታሊዝም ኢኮኖሚ ሥርዓት የተመሠረተባቸውን ዋና ዋና መርሆዎች እንከን በሌለውና በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ እንቅፋት የሚሆኑ በርካታ ነባራዊ ችግሮች በተግባር መከሰታቸው ሊታበል የማይችል ነው:: ከእነዚህ ችግሮች መካከል ጥቂቶቹን ብቻ በማየት የችግሩን ባሕሪይ መረዳት ይቻላል::

የካፒታሊዝም ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት አንደኛው ችግር ተደርጐ የሚወሰደው ቁጥጥር የማይደረግበት የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ መኖር ያለመመጣጠን እንዲከሰትና እኩልነት እንዳይኖር የማድረግ አዝማሚያ ይፈጥራል የሚል ነው:: በተለይም ቁጥጥር የማይደረግባቸው ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች በአብዛኛው ወደ ሞኖፖሊነት እየተቀየሩ ስለሚሄዱ አነስተኛ የግል ሀብት ባለቤትነት ያላቸውን የሚጨፈለቁበት አሠራር እየሠፋ መምጣቱ የሥርዓቱ ልዩ ችግር ተደርጐ የሚታይ ነው:: ሁለተኛው ችግር ደግሞ በካፒታሊዝም ኢኮኖሚ ውስጥ የሚከሠቱ ሞኖፓሊስቶች በመካከላቸው ያለውን ውድድር ለማስቀረት ስምምነትና ቅንጅት የሚፈጥሩ መሆኑ ነው:: የስምምነቱ ዓላማ በመካከላቸው ያለውን ውድድር በማጥፋት በገበያ ሥርዓቱ ላይ ተፅዕኖ ማሣረፍና በሞኖፖሊው ውስጥ የሚሣተፉት ባለሀብቶች ብቻ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ዕድል መፍጠር ነው:: ይሽንን ሁኔታ በተሻለ ለመገንዘብ ጉዳዩን በመጠኑም ቢሆን ዘርዘር አድርጐ ማቅረብና ከአጀማመሩ አንስቶ አሁን እስከ ደረሠበት ደረጃ ያለውን ሂደት መቃኘት ያስፈለጋል::

ካፒታሊዝም በመነሻው ወቅት በግል ባለሀብቶች በነፃ ገበያ ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ሆኖ ግለሠብ ሠራተኞችን በተቻለ መጠን ርካሽ በሆነ ዋጋ መቅጠር የሚቻልበት ሥርዓት ነበር:: የወቅቱ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ባህርይ ደግሞ ለጥቂት የግል ባለሀብቶች ባለቤትነትና አሠራር ያዘነበለ ነው:: የዘመናችን ካፒታሊዝም ልዩ ባሕሪይ ጉልበት ቆጣቢ ዘዴ መጠቀም፣ ዘመናዊ የአመራረት ዘይቤ መከተል፣ መረጃን የሚያከማቹና የሚያሠራጩ ቴክኖሎጅዎችን መጠቀም፣ በዓይነትና በጥራት ከፍተኛ መጠን ያላቸውን ምርቶች የሚያመርቱ፣ የሚያሽጉና የሚያጓጉዙ

አውቶሜትድ ኢንደስትሪዎችን ማቋቋም ነው። ስለሆነም የዚህ አይነቱ አስደናቂ ቴክኒዎሎጅያዊ ዕድገት ልዩ በሆነ የቢዝነስ አደረጃጀት ለውጥ መታጀብ ስለሚገባው ከዚህ በፊት ያልነበረ ኢኮኖሚያዊ ድርጅት እንዲፈጠር ግድ ሆኗል። በዚህም የተነሣ ግዙፍ የሆኑ የካፒታሊስት ኮርፖሬሽኖች ተቋቁመዋል።

ኮርፖሬሽን ማለት ሥራ ላይ በዋሉና የተዓማኒነት ኃይል ባላቸው ሕጐች የተቋቋመና ከባለሀብቶቹና ሠራተኞቹ የተለየ ኃላፊነት ያለው ድርጅት ነው። ኮርፖሬሽን የራሱ መብት ያለው ሕጋዊ አካል ነው። በኮርፖሬሽኑ ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦች የሥራ ኃላፊዎችና የኮርፖሬሽን ፕሬዝደንቶች ሳይቀሩ ይሄዳሉ፣ ይመጣሉ። ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ ሕልውናውን ጠብቆ ይቀጥላል። በዚህ መንገድ የተደራጀ ቢዝነስ ደግሞ በርካታ ጥቅም የሚያስገኝ ሲሆን ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች መካከል ዋና ዋናዎቹ ከፍተኛ መጠን ያለው ካፒታል ለማንቀሳቀስ ማስቻሉ፣ በራሱ ባለቤትነት ሥር ያለውን ድርሻ ለመሸጥ ሕጋዊ መብት ማስገኘቱ፣ የኮርፖሬት ባለቤቶች ኃላፊነት ውስን በመሆኑ ምክንያት ክርክር ቢነሣና ኪሣራ ቢደርስ የግል ንብረታቸው ስለማይነካ በኮርፖሬሽን ውስጥ ኢንቨስት ለማድረግ ማራኪ መሆን ናቸው። ብዙ ኮርፖሬሽኖች በሺህዎች በሚቆጠሩ ባለሀብቶች ባለቤትነት ሥር ስለሚሆኑ እነዚህ ባለሀብቶች በጋራ ለቢዝነስ የሚያውሉት ሀብት ወሰን እጅግ ከፍተኛ ነው። እነዚህ ባለሀብቶች መጠኑ ሠፊ የሆነ ካፒታል ለማንቀሣቀስ ያላቸው ችሎታ በዘመኑ የከባድ ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽኖች ተገቢ ሥፍራ እንዲኖራቸው አስችሏቸዋል። በዚህም የተነሣ ኮርፖሬሽኖች በተቋቋሙብት አገር ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ኃይል ሆነዋል።

ለምሣሌ በአሜሪካ ውስጥ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ትላልቅ ኮርፖሬሽኖች የአገሪቱን ኢኮኖሚ ከፍተኛ ድርሻ ይቆጣጠራሉ። በርካታ ኢንዱስትሪዎች በጥቂት ትላልቅ ኮርፖሬሽኖች ተፅዕኖ ሥር ሆነዋል። በዚህ ሁኔታ ጥቂት ኮርፖሬሽኖች በአንድ አገር ውስጥ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጥንካሬ ሲቀዳጁ ከጥቅማቸው ጐን ችግርም ያስከትላሉ። በተለይም የተለየ ምርት ሙሉ በሙሉ አቅራቢ በሚሆኑበት ጊዜ ያለው አንድ ችግር በውድድር ገበያ ውስጥ እነዚህን ድርጅቶች ለመግራት የሚረዳ ልጓም ለማበጀት የማይቻልበት ልቅ ሁኔታ የሚፈጠር መሆኑ ነው። ስለሆነም ተጠቃሚዎች ብዙም ተፈላጊነት ወደሌለው ምርት ፊታቸውን ከማዞራቸው በፊት ምርቶቻቸውን በከፍተኛ ዋጋ ይሸጣሉ። ሠፊ የማስታወቂያ ሥራ በማከናወን ምርታቸው ያለውን ተፈላጊነት ጠብቆ እንዲቆይ ያደርጋሉ። የባለቤትነት ማረጋገጫ በመያዝ፣ ጥሬ ዕቃዎችን በመቆጣጠር፣ አንድም መግሥትን አሣምነው በውድድር ላይ ተፅዕኖ ለማሣረፍ ወይም አዳዲስ ተቋሞች ወደ ገበያው እንዳይገቡ ለመከላከል ከሌሎች ኮርፖሬሽኖችና ትላልቅ ተቋሞች ጋር ሆነው በማቀድና በመስማማት፤ ከእነሱ ምርት ተመሣሣይ ወይም የተለየ ምርት የሚያመርቱ ኩባንያዎችን፣ ተፎካካሪዎችንና አቅራቢዎችን ጠቅልሎ በመግዛትና ውክልና በመውሰድ ከፍተኛ መጠን ያለውን ሀብት (ሪሶርስ) እና የሥራ ኃይል ለመቆጣጠር ይችላሉ። ሌላው ችግር መቼና በምን ያህል መጠን ኢንቨስት ማድረግ እንደሚገባቸው የመወሠን ኃይል ስላላቸው በተጠቃሚው ሕዝብ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ። እናም የራሣቸውን ኢንደስትሪዎች የዕድገት ምጣኔ ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም ከእነርሱ ቢዝነስ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ኢንዱስትሪዎች ዕድገት ምጣኔ ይወስናሉ። የትኛው ምርት መመረት እንደሚገባውና መመረት እንደማይገባው እስከ መወሰን ድርስ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሣድራሉ ። ከዚህም ሌላ የትኛውም አዲስ ቴክኖሎጂ በምርምር ሲዳብር ሥራ ላይ መዋል እንዳለበት የመወሠን ነፃነትና ኃይል አላቸው። ይህ ደግሞ በሀገሮች የውጭ ፖሊሲ፣ በሕዝብ አሠፋፈር ሥርዓትና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ተፅዕኖ እንዲያሳድሩ ያስችላቸዋል። ለምሣሌ በኤሌክትሪክ ትራንስፖርት ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ቢወስኑ በግል አውቶሞቢል ተጠቃሚዎች ላይ በነዳጅ ግዢና ሽያጭ ግንኙነት ላይ ትልቅ ችግር ሊፈጠር ይችላል። በተጨማሪም በማዕከላዊና አካባቢ መንግሥት አካላት ላይ የፖለቲካ ጫና ለማሣደር የሚችሉበት ሁኔታ አለ። ይኸውም እነሱ የማይስማሙበትን ቀረጥ፣ የመንገድ ግንባታ፣ የኢንዱስትሪ ሕግ፣ ወዘተ ሕግ-አውጭው ቢወስን ኢንቨስትሜንት ከማካሄድ ራሣቸውን በመገደብ ሕጉ እንዳይሠራ ተፅዕኖ ያሣድራሉ። የሕዝብ ተመራጮች በውድድር ዘመቻ ወቅት ለማስታወቂያና ለመሣሠሉት ወጪዎች የሚያስፈልጋቸውን ከፍተኛ ገንዘብ በመሸፈን ፖለቲካዊ ሚና ይጫወታሉ።

በአገር ውሰጥ ከሚያሣድሩት ጫና በተጨማሪ በዓለም-አቀፍ ደረጃም ከፍተኛ ተፅዕኖ ያደርጋሉ። በአለም አቀፍ ደረጃ ኃይል ያላቸው ድንበር ዘለል ኮርፖሬሽኖች ጥሬ ሀብት፣ የሰው ጉልበትና ገበያ ለማግኘት በተለያዩ አገሮች የቢዝነስ ተቋም ከፍተው የሚንቀሳቀሱና በውክልና የሚሠሩ ሲሆን ተግባራቸውም በመግዛትና በመሸጥ የተወሠነ ብቻ ሳይሆን የቢዝነስ ተቋም በከፈቱበት

በእያንዳንዱ አገር ውስጥ የማምረት ሥራም ያከናውናሉ። በእነዚህ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ላይ የሚነሣው ወቀሣ እጅግ ግዙፍ፣ ሀብታምና ጠንካራ በመሆናቸው የተነሣ ብዙዎቹ ብሔራዊ መንግሥታት በእነዚህ ተቋሞች ላይ ቁጥጥር ለማድረግ ወደማይችሉበት ደረጃ ደርሰዋል የሚል ነው። አንዳንዶቹ ለምሣሌ እንደ ኤሪክሶንና ሞቢልን የመሣሠሉት በዓለም የታወቁ የዘይት ኩባንያዎች ወይም እንደ ጀኔራል ሞተርስ የመሳሰሉት አውቶ ካምፓኒዎች ወዘተ. ከምርት ሽያጭ የሚያገኙት ገቢ ቢዝነስ ከሚያካሂዱባቸው ብዙዎቹ አገሮች ጠቅላላ የአገር ምርት የበለጠ ነው።

አሁን የተፈጠሩት ግዙፍ ብሔራዊና ዓለም-አቀፍ ኮርፖሬሽኖች ከመፈጠራቸው በፊት በ19ኛው ክፍል ዘመን መጀመሪያ ላይ የግል ባለሀብቶች የራሣቸውን ቢዝነስ ያንቀሳቅሱ ስለነበር ሁሉንም ቁልፍ ውሣኔዎች የመወሠን፣ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴያቸው ያስገኘውን ትርፍ የመውሰድ ወይንም ያደረሰውን ኪሣራ የመሸከም ኃላፊነት የራሣቸው እንደነበር ይታወቃል። ከኮርፖሬሽኖች መፈጠር በኋላ ግን ባለቤትነትና የቢዝነስ ሥራ አመራር በመለያየታቸው የሥራ መሪዎቹ ትኩረት በረጅም ጊዜ በሚካሄድ ምርምርና ተቋሞችን በማዘመን ላይ ሳይሆን በአጭር ጊዜ ትርፍ በሚገኝበት ሁኔታ ላይ ነው። በዚህም የተነሣ የውህደትና የመቀላቀል ሂደት እየተስፋፋ በመምጣቱ ብዙዎቹ ካምፓኒዎች በሌሎች ካምፓኒዎች ቁጥጥር ሥር እየወደቁ መጥተዋል።

በአሁኑ ጊዜ በአሜሪካም ሆነ በአውሮፓ፣ በጃፓንም ሆነ በሌላ ሀገር የሚገኙ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች አለምን በጠቅላላ የሚመለከቱት እንደ አንድ የኢኮኖሚ ሥርዓት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ግሎባላይዜሽን የሚባለው የዘመናችን ክስተት ዋነኛ ባሕርይ ገደብ የማይጣልበት ክፍት የሆነ ዓለም-አቀፍ የገበያ ውድድርና ትስስር እንዲጠናከር ማድረግ በመሆኑ የድንበር ዘለል ኩባንያዎች ተፅዕኖ ተጠናክሮ እንዲቀጥል አስተዋፅዖ እያደረገ ነው። በዚህ ዓለም-አቀፍ የኢኮኖሚ ትስስር ሥርዓትና የሥራ ክፍፍል ውስጥ ድርሻቸው ጥሬ ዕቃ፣ ጉልበትና ገበያ በማቅረብ ብቻ የተወሠኑት ታዳጊ ሀገሮች ቦታ እንዲሻሻልና ፍትሃዊ ዓለም-አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት ሥርዓት እንዲሠፍን የሚነሣው ጥያቄ ገና ቁርጥ ያለ መፍትሔ ስላላገኘ ግፊቱ እንደቀጠለ ነው። ሦስተኛው የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ችግር ተደርጐ የሚታየው ነጥብ የገበያ ሥርዓት ዋነኛው አንቀሳቃሽ ሞተር ትርፍ ማግኘት እንደመሆኑ የግል ባለሀብቶች አትራፊ ባልሆኑ፣ ነገር ግን ለሕዝብ ጥቅም በሚሠጡ የኢኮኖሚ መስኮች መዋዕለ ንዋይ ለማፍሠስ ጠንካራ ፍላጐት የሌላቸው መሆኑ ነው። ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው የግል ሀብት ባለቤትነት መኖር የካፒታሊዝም ሥርዓት አንድ መሠረታዊ መርህ ነው። በዚህ መርህ መሠረት ሁሉም ለምርት ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ከእርሻ መሬት እስከ ዘይት ማጣሪያ ኢንዱስትሪዎች፣ ከትንሿ እስክርቢቶ እስከ ግዙፉ የኢንዱስትሪ ማሽን ማምረቻ ተቋሞች በግል ይዞታ ሥር እንዲሆኑ ይፈለጋል። ነገር ግን አትራፊ ሆነው በማይገኙበት ጊዜ የግል ባለሀብቶች በእነዚህ መስኮች ተሠማርቶ ለመሥራት አይደፋፈሩም።

## 2.3 የዕዝ ኢኮኖሚ ሥርዓት እንደ አማራጭ የሚቀርብበት ዕድል እየተመናመነ መምጣት

የዕዝ ኢኮኖሚ ሥርዓት የ19ኛው ክፍለ ዘመን ካፒታሊዝም ረጅም የሥራ ሰዓት፣ አነስተኛ ደመወዝ፣ አደገኛ የሥራ ሁኔታና የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ማስፈኑን ተከትሎ በእነማርክስ የተቀየሰ አማራጭ የኢኮኖሚ አስተሳሰብ ነው። በማርክስ አመለካከት ካፒታሊዝም ለኅብረተሰቡ መልካም ነገር በማምጣት ፋንታ በዋናነት የማምረቻ መሣሪያ ባለቤት ለሆኑት ባለሀብቶች ጥቅም የቆመ ሥርዓት ነው። የእነዚህ ባለሀብቶች ዋነኛ ፍላጐትም ትርፍ ማሳደግ በመሆኑ ሠራተኛው በስራው ላይ እንዲቆይ የሚያስችለው ደመወዝ ከመክፈል ያለፈ የሚያሣስባቸው ነገር የለም። ማሽኖች በስፋት ጥቅም ላይ በሚውሉበትና ጥቂት የሠለጠኑ ሠራተኞች እንደልብ በሚኖሩበት ጊዜ የተወሰኑ ሠራተኞች ደመወዝ በጣም ይቀንሣል። አንዳንድ ጊዜ ሠራተኞችና ቤተሰቦቻቸው በሕይወት መቆየት የሚያስችላቸውን ክፍያ ብቻ እያገኙ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ደረጃ ነው የሚኖሩት።

ማርክስ ሠራተኛውን በጥቅሙ ዙሪያ ለማንቃት፣ ለማስተማርና ለማደራጀት በሚካሄድ የረጅም ጊዜ ጥረት ፀረ-ካፒታሊስት አቋም እንዲይዝና የማምረቻ መሣሪያዎችን እንዲቆጣጠር በማድረግ በመጨረሻም ካፒታሊዝምን በመደብ አልባ ኅብረተሰብ መተካት ይቻላል የሚል አመለካከት ነበረው። ምንም እንኳ ይኸንን የጋርዮሽ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት በዝርዝር ባይገልጽም መሠረታዊ

ባህሪያቱን አመላክቷል:: በዚህም መሠረት ከካፒታሊዝም በኋላ የሚመሠረተው ሥርዓት አንደኛ የማምረቻ መሣሪያዎች በግል ሳይሆን በጋራ ባለቤትነት የሚያዙበት ሶሻሊስታዊ የኢኮኖሚ ሥርዓት ነው:: ሁለተኛ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች በገበያ እንዲወሠኑ የሚለቀቁበት ሣይሆን በማዕከላዊ ዕቅድ አውጭ አካል ቀጥጥር ስር የሚሆኑበት በኢኮኖሚስቶች አጠራር የእዝ ኢኮኖሚ ሥርዓት ነው:: ይህ ዕቅድ አውጭ ማዕከላዊ አካል ከሚያከናውናቸው ሥራዎች መካከል ኅብረተሰቡ ምን ዓይነት ምርት ማምረት እንዳለበት ይወስናል:: ምርት በምን ያህል መጠን መመረት እንዳለበት፣ የት መመረት እንዳለበት፣ እንዴት መመረት እንዳለበት፣ የተመረተው ምርት ለእነማንና በምን ዓይነት መንገድ መከፋፈል እንዳለበት ይወስናል:: ይህ ዓይነቱ ሥርዓት በቀድሞዋ ሶቭየት ሕብረትና ምስራቅ አውሮፓ ሶሻሊስት አገሮች የተሞከረ ቢሆንም በእነማርክስ እንደታሠበው ሶሻሊዝምን በተሟላ ሁኔታ ማስፈን አልተቻለም:: በተጠቀሱት አገሮች ሁሉም የማምረቻ መሣሪያዎችና የካፒታል ሀብት በመንግሥት ባለቤትነት ሥር ቢሆኑም አብዛኛዎቹ ቤቶች በግል የተያዙ ነበሩ:: የአቅርቦትና የገበያ ዘይቤዎችን ጨርሶ ለማስቀረት አልተቻለም:: ለምሣሌ አነስተኛ «የካፒታሊስት» የግል ይዞታዎች ስለነበሩ ገበሬዎች በራሳቸው አነስተኛ ማሳ ያለሙትንና ያመረቱትን ይሸጡ ነበር:: ሐኪሞች፣ አናፂዎችና የመሳሰሉት ግን የግል ሥራ ያካሂዱ ነበር:: በመጨረሻም ሀላፊነት የሚሸከሙ ሰዎችን ለመሳብ መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ማበረታቻ መክፈል እንደሚያስፈልግ ተገንዝበው ሥራ ላይ ሲያውሉ በካፒታሊስት አገሮች ከሚታየው ጋር የሚቀራረብና የሚመሳሰል የግል ባለሀብት ቀስ በቀስ እየተጠናከረ መጥቶ ነበር:: እናም ምዕራባዊያን ንፁህ ካፒታሊዝምን መፍጠር እንዳልቻሉት ሁሉ የምሥራቅ ሶሻሊስት አገሮችም ንፁህ የሆነ ሶሻሊዝምን ማስፈን አልቻሉም:: ይልቁንም ሶሻሊዝምን እንደ ሥርዓት ሕልውናውን ጠብቆ ማቆየት የሚያስችል ሁኔታ ባለመኖሩ ተንኮታክቶ ለመውደቅ ግድ ሆኖበታል:: ስለዚህ እንደ አማራጭ የሚቀርብበት ሁኔታ ተዘግቶ በታሪክ ማስታወሻነት ወደሚጠቀስበት ደረጃ ተሸጋግሯል::

የጋራ ንብረት ባለቤትነት፣ በአንድ ማዕከላዊ አካል የሚዘጋጅ ዕቅድና መደብ አልባ የሆነ ኅብረተሰብ የሚባሉት የሶሻሊዝም ሥርዓት እሴቶች ተግባራዊ ሊሆኑ ባለመቻላቸው የግል ንብረት ባለቤትነት፣ ያልተማከለና በእያንዳንዱ አምራች ወይም ተጠቃሚ የሚነደፍ ዕቅድ፣ በገበያ ሕግ የሚመራ ኢኮኖሚያዊ ስርዓትና እኩል የሆነ ዕድል መፍጠር የሚሉትና የመሳሰሉት የካፒታሊዝም ሥርዓት እሴቶች አሁንም ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጣቸውና ከሰው ልጅ መሠረታዊ መብትና ነፃነት ጋር የተጣጣሙ መሆናቸው ይበልጥ ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል:: ሁሉንም የኢኮኖሚ ሥርዓቶች ማለትም ሶሻሊዝምንም ይሁን ካፒታሊዝምን አንድ መሠረታዊ የሆነ ተመሳሳይ ችግር የሚያጋጥማቸው ቢሆንም በችግሩ አፈታት ላይ መሠረታዊ ልዩነት አላቸው:: የሁለቱም ሥርዓቶች የጋራ ችግር ተደርጐ የሚወሰደው ነጥብ ውስን ከሆነው ሀብት (ሪሶርስ) አንፃር ማለቂያ የሌለውን የሰው ልጅ ፍላጐት ማርካት የሚቻለው እንዴት ነው? የሚለው ጥያቄ ነው:: ውስን መሬት፣ ውሃ፣ ነዳጅ፣ ገንዘብ፣ የሥራ ፍላጐትና ዕውቀት ወዘተ. ባለበት ሁኔታ ይህንን የተመጠነ ሪሶርስ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዴት ማዳረስ እንደሚቻል ግልፅ መፍትሔ ከሌለ በስተቀር መውጫ በሌለው ዙሪያ ጥምጥም ችግር ውስጥ መዘፈቅ ይከተላል:: በሶሻሊዝም ኢኮኖሚ ስርዓት ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ከመደብ ጥቅምና ከኃይል አሠላለፍ ጋር በተያያዘ መመዘኛ ለአንዱ እየፈቀዱ ለሌላው መከልከል በመሆኑ ጠቃሚ መፍትሔ ሆኖ አልተገኘም:: በካፒታሊዝም ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ግን ሁሉም የሚፈልገውንና አቅሙ የሚችለውን እየሠራ እንዲጠቀም እኩል ዕድል በመስጠት መርህ ላይ የተመሠረተ መፍትሔ ስለሚቀርብ የተሻለው አማራጭ ሆኖ ተገኝቷል:: በመርህ ደረጃ በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ለአንዱ ግለሰብ፣ ቡድንና ተቋም በተለየ መንገድ የሚፈቀድና ለሌላው የሚከለከል ሀብት (ሪሶርስ) የለም:: በተግባርም ቢሆን የሚፈቀድ ነገር ካለ በእኩል ደረጃ ለሁሉም ክፍት የሚደረግ ሲሆን የሕግ ቁጥጥር የሚደረግበት ነገር ካለም ለሁሉም በእኩል ደረጃ ተፈፃሚ ይሆናል:: ልዩነት የሚፈጠረው ዕድሉን በመስጠትና በመከልከል አድሎ በማድረግ ሣይሆን ዕድሉን ያገኘው ግለሰብ፣ ቡድንና ተቋም በዕድሉ ለመጠቀም ባለው ፍላጐትና ብቃት ምክንያት ነው::

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የካፒታሊስት ስርዓት አስተሳሰቦች መሰረት በማድረግ ከሀገሪቱ ወቅታዊና ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘበና የተጣጣመ ፍትሀዊ የካፒታሊስ ሰርዓት ኢትዮጵያ ውስጥ መገንባት ይቻላል ብሎ ኢዴአፓ ያምናል::

# 3. አጠቃላይ የልማት እድገት ትርጉምና መለኪያዎቹ

## 3.1 የልማት እድገት ትርጉም

ለልማት የሚሰጠው ትርጉም የተለያየ የመሆኑን ያህል ስለልማት አመሰራረት ያሉት አስተሳሰቦችና ልምዶችም የተለያዩ ናቸው:: ከእነዚህ መካከል ለረጅም ጊዜ የቆየውና በተፈጥሮ ሀብት ላይ የተመሰረተው የእድገት ንድፈ ሀሳብና ልምድ አንዱ ነው:: ወንዞችን ተከትሎ በመስፈርና እርሻን በማረስ ወይም ማዕድንን ቆፍሮ በማውጣት የተመሰረተ የእድገት ልምድ አለ:: በንግድ ላይ በተለይም የውጭ ንግድ በማካሄድ የተመሰረተ የእድገት ንድፈ ሀሳብና ልምድም አለ:: ሌላው የእድገት ንድፈ ሃሳብና ልምድ በእደጥበባት መስፋፋትና በከተሞች እድገት ላይ የተመሰረተ ለረጅም ጊዜ የቆየ የእድገት አስተሳሰብ ነው:: ከኢንዱስትሪ አብዮትና ከካፒታሊዝም መምጣት በኋላ ደግሞ በቴክኖዮሎጂ ላይ የተመሰረተ የልማት ንድፈ ሀሳብና ልምድ አለ:: በአሁኑ ጊዜ በተራቀቀ ኢንዱስትሪና የመገናኛ ቴክኒዎሎጂ ላይ የተመሰረተ ልማት የማምጣቱ ሂደትም በአሜሪካ፣ በአውሮፓና በጃፓን እየተሰራበት ነው::

ከእነዚህ ለየት የሚለው የፖሊሲ መሣሪያዎችን በሚገባ ስራ ላይ በማዋል ልማት ማምጣት ይቻላል የሚለው ንድፈ ሀሳብና ልምድ ነው:: ይኸኛው የልማት ቲዎሪና ልምድ አስቀድሞ በተዘጋጀ እድቅና በእቅዱ አፈፃፀም ላይ የተለያዩ ተሳታፊ አካላትን በማስተባበር ተግባራዊ ሊሆን የሚችል አንድ አይነት ፕሮጀክት ነው ከሚለው አስተሳሰብ ጋር የሚደራረብ ነው:: በሌላ አገላለፅ በአንድ ሀገር ውስጥ ለልማት መሰረት የሚሆን የተፈጥሮ ሀብት፣ አስቀድሞ የተዘጋጀ ቴክኒዎሎጂና ካፒታል ኖረም አልኖረም ልማት ለማምጣት የሚያስችሉ የፖሊሲ መሣሪያዎችን (Policy Instruments) በመጠቀም ልማትን እውን ማድረግ ይቻላል የሚል ቲዎሪና ልምድ ነው::

ይኸኛው የልማት ንድፈ ሀሳብና ልምድ በአብዛኛው በምስራቅ ኤስያ የሚገኙት እነ ጃፓን፣ ደቡብ ኮሪያና ታይዋን ካስመዘገቡት የእድገት ልምድ ጋር ተያይዞ የሚነሳ ነው:: የእነዚህ ሀገሮች የልማት ልምድ ውሃን፣ የእርሻ መሬትን፣ ማዕድንን፣ ቴክኖዎሎጂን፣ ካፒታልን ወዘተ. መነሻ አድርጎ የተጀመረ ሳይሆን በዋናነት ሰውን በማልማት የፖሊሲ እርምጃ ላይ ተመስርቶ የተጀመረ ነው:: የሰውን አቅም በሁሉም ረገድ ከፍ የሚያደርግ የሞያና የእውቀት ግንባታ ፕሮግራም ዘርግተው ተግባራዊ በማድረግና ከሁሉም በላይ ለልማት ቆርጦ መሰለፍ የሚያስችል ስነልቦናዊ ዝግጁነት በዜጎቻቸው ውስጥ በሂደት እየፈጠሩ የገቡበት ልምድ ነው:: ልማት ለማምጣት የሚጠቅመውን ማንኛውንም እርምጃ ሳያመነታ የሚወስድ መንግስታዊ አመራር በቦታው ላይ ሆኖ ልማትን ለማምጣት የሚያግዙ ፈጣንና ተገቢ የፖሊሲ እርምጃዎችን በሚወስድበት አሰራር የተጀመረ ልምድ ነው:: አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ቦታ ሁሉንም ዓይነት የሰው ጉልበት (የሰለጠነም ያልሰለጠነም) ወይንም ለተወሰነ ተግባር ሆን ተብሎ እየሰለጠነና እየተዘጋጀ የሚወጣን ሞያተኛ እየተጠቀመ የማያቋርጥ ምርታማነትና የገቢ እድገት እንዲረጋገጥ የሚያስችል ልማት በማካሄድ ላይ የተመሰረተ የልማት ልምድ ነው:: የስራ እድል የሚፈጥሩ፣ ብሔራዊ ምርትንና ቁጠባን የሚያሳድጉ በርካታ ስራዎችን በመስራት ቁጠባን ወደማሳደግና ካፒታልን ወደ ማጎልበት የተሸጋገረ የልማት ልምድ ነው::

ምርታማነትንና የገቢ እድገትን፣ ቁጠባንና የካፒታል ምስረታን ቀጣይ የሚያደርጉ የገንዘብና የዋጋ ማረጋጊያ ፖሊሲዎችን አውጥቶ በስራ ላይ በማዋል የተገኘ የልማት ልምድ ነው:: የሀገረ ውስጥ አምራቾችን በመደገፍ፣ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ከሚተኩ የሀገር ውስጥ ምርቶች መካከል የተሳሰረና የማያቋርጥ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሊያስገኙ ይችላሉ ለሚባሉት ድጎማ በመስጠ ት ወይም የኤክስፖርት ገቢን በማሳደግ ለኢኮኖሚው የማይናቅ ድጋፍ ያደርጋል ለሚሉት የኤክስፖርት ምርቶች በመጠን፣ በጥራትና በአይነት እንዲያድጉና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችል ማበረታቻ በመስጠት የተገኘ የልማት ልምድ ነው:: በዚህ መንገድ ምርትና ምርታማነት፣ ገቢና ቁጠባ እያደገና የካፒታል ክምችት እየጎለበተ እንዲሄድ ከማድረግ ጎን ለጎን ትርፍና ገቢ በማያቋርጥ መንገድ እንዲጨምር ለማድረግ የሚረዳ የባንክ አሰራርና ተገቢ የብድርና የወለድ ስርዓት መኖሩን በማረጋገጥ ላይ የተመሰረተ የልማት ልምድ ነው:: የገበሬውን ምርታማነት ለመጨመር የሚያግዙ ተመጣጣኝ የታክስ ስርዓቶችን በማውጣት፣

ለኢንዱስትሪው ምርታማነትና ተወዳዳሪነት የሚያበረታቱ ድጋፎችን በመስጠት፣ ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎችን ይዘው ለማደግና ጠቅላለውን ኢኮኖሚ ለመደገፍ ጠቃሚ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ተብለው ለሚታመንባቸው ኢንዱስትሪዎች ድጎማ በመስጠት ላይ የተመሰረተ የልማት ልምድ ነው::

በምርምር መስክ የተሰማሩትንና ለኢኮኖሚው እድገት ቁልፍ አስተዋጽኦ የሚያደርጉትን ለይቶ የማበረታቻ ድጋፍ በመስጠት ብቻ ሳይወሰን የውጭ ቴክኒዎሎጂንና እውቀትን በማስገባት የእርሻንና የኢንዱስትሪን ምርታማነት ለማሳደግ በሚያስችሉ አሰራሮች ጥቅም እንዲሰጡ በማድረግ ጭምር የተገኘ የልማት ልምድ ነው:: በመንግስትና በግል ተቋሞች መካከል ቋሚ የመረጃ ልውውጥ በማድረግና ጠንካራ አጋርነትን በመፍጠር ላይ የተመሰረተ የልማት ልምድ ነው:: ሕዝቡን በከፍተኛ ብሔራዊ ስሜትና ልማትን ለማምጣት በሚያስችል ቁርጠኛ ተነሳሽነት አዘጋጅቶ በማሰማራት የተገኘ የልማት ልምድ ነው:: በአጭሩ የፖሊሲ መሳሪያዎችን በሚገባ በመጠቀም፣ መልካም አስተዳደርን በማስፈን፣ የማክሮ ኢኮኖሚ ማረጋጊያ እርምጃዎችን በመውሰድ፣ ምርትንና ምርታማነትን በማሳደግ፣ ሁሉንም ዓይነት የሰው ጉልበትን በመጠቀም፣ ቁጠባንና የካፒታል ምስረታን በማጠናከር፣ የሀገር አቅምን፣ የውጭ ካፒታልንና የቴክኒክ እውቀትን በማቀናጀት የተገኘ የልማት ልምድ ነው::

እስካሁን ድረስ ለማየት የተሞከረው በአለማችን ላይ ልማትን በሚመለከት ያሉትን የአተረጓጎም ልዩነቶችና ለእድገት መመስረት መነሻ ናቸው የሚባሉትን የተለያዩ የልማት ቲዎሪዎችና ልምዶችን ነው:: ከእነዚህ በርካታ የልማት ቲዎሪዎችና ልምዶች መካከል አንድ ሀገር አድጓል ወይም አላደገም ብሎ ለመመዘን ጭምር በአሁኑ ጊዜ አለም በሰፊው የሚጠቀምባቸውን ብቻ ለይቶ ማቅረብ በዚህ ረገድ የተሻለ ግልጽነት እንዲኖር ያስችላል:: በተለይም ከኮሎኒያሊዝም መውደቅ ጋር ተከትሎ በዓለም ደረጃ በተፈጠረው የኃይል አሰላለፍ ለውጥ ምክንያት ወደ መድረኩ ብቅ ያሉትን የ3ኛው አለም ሀገሮች የልማት ችግሮች ለመረዳት የተሻለ ስዕል የሚሰጡ -ትን ብቻ መርጦ ለማየት መሞከር ጠቃሚ ነው:: ምክንያቱም ስለኢትዮጵያ የወቅቱ ሁኔታ ግምገማ ለማድረግም ሆነ ስለወደፊቱ እድገቷ አቅጣጫ ለመምረጥ የሚቻለው እነዚህን አለም በሰፊው የሚጠቀምባቸውን የልማት መመዘኛ ንድፈ ሀሳቦችና ልምዶች ከራሳችን ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ነው:: በእነዚህ መመዘኛዎች ኢትዮጵያ የምትገኝበትን ደረጃ ለማየት ከመሞከር በተጨማሪ ወደፊት ሁነኛ እድገት እንድታመጣ ምን አይነት የልማት አቅጣጫ መቀየስ ይገባታል የሚለውንም ጥያቄ ለመመለስ ይረዳል::

## 3.2 የልማት እድገት መለኪያዎች

አንድ ሀገር እድገት አስመዝግቧል ወይንም እድገት ማስመዝገብ ተስኖታል ለሚሉት ፈታኝ የልማት ጥያቄዎች መልስ ከሚገኝባቸው በአለማችን በሰፊው ከሚሰራባቸው የልማት ቲዎሪዎችና ልምዶች መካከል የመጀመሪያው ልማትን ከኢኮኖሚ ለውጥ ጋር በማያያዝ ለመግለፅ የሚሞክረው ቲዎሪና ልምድ ነው:: ይህ ቲዎሪና ልምድ የአንድን ሀገር አጠቃላይ ብሔራዊ ምርትና (GNP) የዜጎችን የነፍስ ወከፍ ገቢ በማሳደግ ረገድ በተገኘ አሃዛዊ ውጤት ላይ ተመስርቶ ልማትን ለመግለፅ የሚሞከርበት ነው:: ሁለተኛው ደግሞ ልማትን ከመዋቅራዊ ሽግግር (Structural Transformation) ጋር በማያያዝ ለመግለጽ የሚሞክረው ቲዎሪና ልምድ ነው:: ይኸኛው ቲዎሪና ልምድ ለምሳሌ ከገጠር አኗኗርና አሰራር ዘይቤ ወደ ከተማ አኗኗርና አሰራር ዘይቤ ወዘተ. በሚደረግ ሽግግር ላይ በመመስረት ልማትን ለመግለጽ የሚሞከርበት ነው:: በሶስተኛ ደረጃ ሊጠቀስ የሚገባው ምንአልባትም ከተለያየ ምንጭ የሚነሳና በተለያየ የአቀራረብ ዘዴ የሚገለፅ በመሆኑ ምክንያት እንደ አንድ ወጥ ቲዎሪና ልምድ ባይወሰድም ቢያንስ እንደ አንድ አማራጭ የልማት መግለጫ መታየት ያለበት ልማትን የሰው ልጅ ፍላጎት ማዕከል ከማድረግና ካለማድረግ ጋር በማያያዝ ለመግለፅ የሚሞከርበት አመለካት ነው:: ይህ አመለካከት ልማትን ለመግለፅ የሚሞክረው የተገኘው ልማት የሰውን ልጅ ፍላጎት ማዕከል ያደረገ (Human need centered development) ነው ወይንስ አይደለም ከሚል አቀራረብ በመነሳት ነው::

የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ የልማት መግለጫ ቲዎሪዎችና ልምዶች እ.ኤ.አ እስከ 1970ዎቹ ድረስ ስለልማት በተወሳ ቁጥር እንደዋነኛዎቹ የልማት መሪ ሀሳቦች መለኪያዎች ተደርገው ሲወሰዱ

ቆይተዋል። አንድ ሀገር ልማት አስመዘገበ ሊባል የሚችለው አጠቃላይ ብሔራዊ ምርትና የነፍስ ወከፍ ገቢ ሲያድግ ነው ከሚለው አስተሳሰብ ጎን ለጎን ልማት መኖሩ የሚረጋገጠው መዋቅራዊ ሽግግር ሲደረግ ነው የሚለው አመለካከት እየቀረበ አንዱ ከሌላው የተሻለ የልማት ቲዎሪ ሆኖ ለመገኘት ሰፊ የሀሳብ ፍጭት ተካሂዷል። እዚህ ላይ ሁለቱም ቲዎሪዎች ጠቃሚ የልማት መለኪያ ሆነው ማገልገላቸው ባይካድም እያንዳንዳቸው በተናጠል ብቸኛ መለኪያ እንደሆኑ ተደርጎ የመታየት ችግር እንዳለባቸው መገንዘብ ጠቃሚ ነው። ለምሳሌ የአጠቃላይ ብሔራዊ ምርትና የነፍስ ወከፍ ገቢ እድገትን እንደ አንድ የልማት መለኪያ አድርገን ብንመዝነው የአንድን ሀገር ልማት በተሟላ ሁኔታ ለመግለፅ የማያበቁትን በርካታ ድክመቶች ማየት እንችላለን። የመጀመሪያው ድክመቱ ይህ የልማት ስሌት በዋናነት የሚመሰረተው በተደራጀ የልውውጥ መስመር ውስጥ ገብተው መደበኛ ልውውጥ በሚካሄድባቸው የሸቀጦችና የአገልግሎቶች እሴት ላይ ብቻ መሆኑ ነው። ሌሎች በዚህ የልማት መለኪያ ስሌት ውስጥ የማይገቡ የቤት ውስጥ ስራዎች፣ በመረጃ እጥረት ምክንያት በብሔራዊ አካውንት ውስጥ የማይመዘገቡ የእደ ጥበብና ጥቃቅን የንግድ እንቅስቃሴዎች የማህበራዊና አካባቢ ጥበቃ ዋጋዎች ወዘተ. ስለሚኖሩ የተማከለ የልማት ማሳያ እንዳይሆን ያደርገዋል።

ሁለተኛው ድክመት የሀገር ምርትና ገቢ ስለሚከፋፈልበት ሁኔታ በተሟላ መንገድ ሊገልፅ አለመቻሉ ነው። በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች፣ በተለያዩ ክልሎች፣ ገጠሮችና ከተሞች ወዘተ. ያለውን የሀብት ክፍፍል ቁልጭ አድርጎ አያሳይም።

አጠቃላይ ብሔራዊ ምርትና የነፍስ ወከፍ ገቢ አደገ ወይም ቀነሰ የሚለውን አሃዛዊ መረጃ ለማወቅ ካልሆነ በስተቀር ከተገኘው ምርት ምን ያህሉ ለየትኛው ሕብረተሰብና አካባቢ ደረሰው፣ የትኛው አካባቢና ሕብረተሰብ በልማቱ ተጠቀመ፣ የትኛው ጉዳት ደረሰበት የሚለውን አያመለክትም። በዚህም የተነሳ የአጠቃላይ ብሔራዊ ምርትና የነፍስ ወከፍ ገቢ እድገት ማለት ትክክለኛ የሀብት ክፍፍል መኖሩ የሚታይበት ሊሆን ስለማይችል የልማትን ሙሉ ስዕል የማሳየት ችግር አለበት። በአጠቃላይ ከብሔራዊ ምርትና ከየነፍስ ወከፍ ገቢ ረገድ በአሃዝ ሊገለፅ የሚችል የመጠን እድገት በሚታይበት ሁኔታ በክፍፍል ችግር ምክንያት ሕዝቡ የሚደኸይበት አጋጣሚ መኖሩ በተደጋጋሚ ጊዜ በተለያዩ ሀገሮች ታይቷል። በዚህም ምክንያት የአጠቃላይ ብሔራዊ ምርትና የነፍስ ወከፍ ገቢ እድገት ንድፈ ሀሳብ ልማትን በመለካት ያሉበትን ድክመቶች ለማስወገድ ሲባል በ1970ዎቹ ተጨባጭ የኑሮ ደረጃ አመልካቾች እንደ አማራጭ የልማት መለኪያ እንዲያገለግሉ ማድረግ ተጀመረ። ከእነዚህ አመልካቾች (physical quality of life index) መካከል አማካይ በሕይወት የመቆያ እድሜ፣ የሕፃናት ሞት መጠን፣ እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ሕፃናት የትምህርት ተሳትፎ ወዘተ. የመሳሰሉት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም (UNDP) ካወጣው የሰብዓዊ ልማት አመልካች (Human developemnt Index) ጋር በማቀናጀት የተለያዩና የተወሳሰቡ የኑሮ ሁኔታ ገጽታዎችን ከአጠቃላይ ብሔራዊ ምርትና የነፍስ ወከፍ ገቢ ጋር እያነፃፀሩ ልማትን ለመለካት ተሞክሯል። እነዚህም ተጨምረው እንኳ ሁሉንም የኑሮ ገጽታ የመለካት ጉደለት እንዳለባቸው የታወቀ ነው። እነዚህ አማራጭ የልማት አመልካቾች ራሳቸው የሕዝቡን ባህላዊ ሁኔታ የማካተት ችግር ስላለባቸው የተሟላ የልማት መመዘኛ ለማግኘት ያለውን ክፍተት በአስተማማኝ የሚሞሉ አይደሉም። በእርግጥ አጠቃላይ ብሔራዊ ምርትና የነፍስ ወከፍ ገቢ እድገትን ከሰው ልጅ ተጨባጭ የኑሮ ሁኔታና ከሰብዓዊ ልማት አመልካቾች ጋር ድጋፍ ንጽጽር እያደረጉ የአንድን ሀገር ልማት ለማየት መሞከር በአጠቃላይ ብሔራዊ ምርትና የነፍስ ወከፍ ገቢ እድገት ላይ ብቻ ተመስርቶ ከሚገኘው ምዘና የተሻለ ጥቅም እንዳለው መካድ አይቻልም።

የአጠቃላይ ብሔራዊ ምርትና የነፍስ ወከፍ ገቢ እድገትን ከሰው ልጅ ተጨባጭ የኑሮ ሁኔታና ሰብዓዊ ልማት አመልካቾች ጋር በማነፃፀር የሚገኘውን ውጤት መነሻ በማድረግ የተወሰኑ ሀገሮችን ልምድ እንደምሳሌ አድርገን ብንመለከት የሁለቱ መመዘኛዎች ቅንጅት ምን ያህል የተሻለ የልማት መለኪያ ሊሆን እንደሚችል መረዳት አያዳግትም። ቻይናና ሲሪላንካ ከሌሎች ሀገሮች ጋር ሲነፃፀሩ ዝቅተኛ ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ ቢኖራቸውም የተሻለ ተጨባጭ የኑሮ ሁኔታና የሰብዓዊ ልማት እድገት አሳይተዋል። እንደ ሳውዲ አረቢያና አረብ ኤምሬትስ የመሳሰሉት ነዳጅ አምራች ሀገሮች እንዲሁም ብራዚልንና ሜክሲኮን የመሳሰሉ ሀገሮች ከፍተኛ ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢና ዝቅተኛ የሰብዓዊ ልማትና ተጨባጭ የኑሮ ደረጃ የሚታይባቸው

ናቸው:: ኢትዮጵያንና ባንግላዲሽን የመሳሰሉት ሀገሮች ደግሞ በዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢም ሆነ በሰብአዊ ልማትና ተጨባጭ የኑሮ ሁኔታ እድገት እጅግ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ሲሆኑ በአንፃሩ የስካንዲናቪያንስ ሀገሮች፣ ሌሎች የአውሮፓ ሀገሮችና አሜሪካ በዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢም ሆነ በሰብዓዊ ልማትና በተጨባጭ የኑሮ ሁኔታ እድገት በጣም ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ ናቸው:: ስለዚህ የአጠቃላይ ብሔራዊ ምርትና የነፍስ ወከፍ ገቢ ማደግ ብቻውን የተሟላ የልማት ማሳያ ሊሆን አይችልም ማለት ነው::

ይህንን ሀሳብ ግልፅ ለማድረግ ትንሽ ነገሩን ዘርዘር ማድረግ ይጠቅማል:: አጠቃላይ ብሔራዊ ምርትና የነፍስ ወከፍ ገቢ ስለአንድ ሀገር ልማት ምንም አይነት መረጃ አይጠሰጡም ማለት አይደለም:: ለምሳሌ የአንድ ሀገር ሕዝብ ድህነትና የኑሮ ደረጃ ከሚወስንባቸው ነጥቦች መካከል የነፍስ ወከፍ ገቢ መጠን አንደኛው ነው:: ነገር ግን ይህ ብቸኛ የተሟላ መመዘኛ ሊሆን አይችልም:: የተሟላ እንዲሆን በገቢው ክፍፍል ላይ ያለው የልዩነት ደረጃም መታየት ይኖርበታል:: በአንድ የተወሰነ የነፍስ ወከፍ ገቢ ድርሻ መጠን ከፍተኛ የገቢ ክፍፍል ልዩነት ካለ የድህነቱም ደረጃ ከፍተኛ መሆኑ የማይቀር ነው:: የገቢ ክፍፍል ልዩነቱ ዝቅተኛ ከሆነ ደግሞ የድህነቱም ደረጃ ዝቅተኛ ይሆናል::

ከኢኮኖሚ እድገት፣ ከገቢ፣ ከማህበራዊ ሕልውናና ከድህነት ጋር የተያያዘው ሌላው ጠቃሚ ነጥብ እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች የሚወሰኑት በአንድ ነገር ብቻ ሳይሆን በብዙ ጉዳዮች መሆኑ ነው:: ለምሳሌ እንደመሬት፣ ካፒታልና ወዘተ. የመሳሰሉት ለምርት አስፈላጊ የሆኑ ሀብቶች ለዜጎች በሚከፋፈሉበት ጊዜ ከመነሻው በተዛባ መንገድ ከተከፋፈሉ አጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት በሚታይበት ሁኔታም ቢሆን የከፋ የኑሮ ደረጃ ልዩነት መኖሩ የማይቀር ነው:: እንዲያውም ለማስተካከል በሚያስቸግር ሁኔታ ልዩነቱ እየተባባሰ ሊሄድም ይችላል:: ምክንያቱም በቅድሚያ ከፍተኛ ድርሻ ያገኙት የተሻለ የኢኮኖሚ እድገት እድል የሚኖራቸው ሲሆን በቅድሚያ ዝቅተኛ ድርሻ ያገኙት ደግሞ ያነሰ የኢኮኖሚ እድገት እድል ስለሚኖራቸው ነው:: ምንም ያላገኙት ደግሞ በሕይወት ለመቆየትም የሚያስችል እድል እንደተነፈጋቸው የሚቆጠሩ ናቸው:: መሬት በቅድሚያ በተወሰኑ ሰዎች እጅ እንዲሰባሰብ ከተደረገ እነዚህ ሰዎች የኮሜርሻያል እርሻ አስፋፍተው ከሀገር ውስጥ ገበያ በተጨማሪ ወደ ውጭ የሚላኩ የእርሻ ምርቶችንም ለማምረት እድል ያገኛሉ:: ይኸንን እድል በቅድሚያ ያላገኙት ደግሞ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ የእርሻ ስራ ተወስነው ለመኖር ይገደዳሉ:: ስለዚህ የኢኮኖሚ እድገት የገቢ መጠንና የኑሮ ሁኔታ በሀብት ክፍፍሉ ይወሰናሉ ማለት ነው::

በኢኮኖሚው እድገት ጸባይም ሊወሰኑ ይችላሉ:: ለምሳሌ የገጠሩን እድገት ችላ የሚልና በከተማው ላይ የተለየ ትኩረት የሚሰጥ ወይንም ከተማውን ችላ ብሎ ገጠሩን ብቻ ማዕከል ያደረገ እድገት እንዲኖር ከተደረገ በከተማና በገጠር የሚኖሩ ሰዎች የገቢና የኑሮ ሁኔታ ልዩነት እየሰፋ ይሄዳል:: በካፒታል ላይ ከተመሰረተው ኢንዱስትሪ ይልቅ በጉልበት ለተመሰረተው የተለየ ትኩረት ከተሰጠ በካፒታል የተመሰረተው ኢንዱስትሪም ይወድቅና ተያይዞ ድህነት ይመጣል::

በመሰረታዊ ማህበራዊ አገልግሎቶች አቀራረብ ላይ መንግስት በሚከተለው ፖሊሲም ሊወሰኑ ይችላሉ:: የመንግስት የትምህርት ፖሊሲ ለገጠሩና ለድሃው ሕዝብ ትኩረት የማይሰጥ ከሆነ፣ ወይም በጤናና በምግብ አገልግሎት አቀራረብ ያለው ፖሊሲ የተዛባ ከሆነ የገቢና የኑሮ ልዩነት ሁኔታዎች ይበልጥ ይባባሳሉ:: በዚህ መሰረት ድህነትና የኑሮ ልዩነት በፖለቲካ ሂደት ይወሰናሉ ማለት ነው:: እዚህ ላይ በገበያ ሂደት ላይ ተመስርቶ የሚፈጠር የካፒታል ክምችት የሚያስገኘው የኢኮኖሚ እድገት ከገቢ፣ ከኑሮ አለመመጣጠንና ከድህነት ጉዳዮች ተለይቶ መታየት እንዳለበት መረዳት ተገቢ ነው:: ምክንያቱም በገበያ ሂደት የሚፈጠር የካፒታል ክምችት የገበያ ሕግ በሚፈቅደው አሰራር ላይ ተመስርቶ የሚካሄዱ በአድሎና በተዛባ የሀብት ክፍፍል ሳይሆን ለሁሉም እኩል የተሳትፎ እድል በሚፈቅድ ውድድር የሚገኝ በመሆኑ ነው:: እዚህ ውስጥ ወሳኙ ፍላጎትና አቅርቦት የሚሉት የገበያ ኃይሎችና የእነዚህን ኃይሎች ሕግ ተከትሎ ብቁ ተወዳዳሪ መሆንና አለመሆን እንጂ መንግስት ወይም ሌላ አድሎ መስራት የሚፈልግ አካልና ግለሰብ አይደሉም::

መዋቅራዊ ሽግግርን በማረጋገጥ ላይ የተመሰረተው የልማት ቲዎሪና ልምድ ዋነኛ ይዘት ደግሞ በሆነ መንገድ ሊፈፀም በሚችል መዋቅራዊ ሽግግር ልማትን ማምጣት ይቻላል በሚል አመለካከትና እምነት ላይ የተመሰረተ መሆኑ ነው። ይህ አስተሳሰብ መዋቅራዊ ሽግግር ምንም አይነት ሰቆቃ ሳያስከትል ቢፈፀም ተቃውሞ የለውም። ነገር ግን በመዋቅራዊ ሽግግር ወቅት የተለያየ ገጽታ ያላቸው ችግሮች ጨርሶ እንዳይከሰቱ ማድረግ አይቻልም የሚል እምነት በመኖሩ ችግሮችና ሰቆቃዎች ኖሩም አልኖሩ፣ መስዋዕትነቱ ከበደም ቀለለ ልማት መመዝገብ ይኖርበታል በሚል ጠንካራ አቋም ላይ የቆመ አስተሳሰብ ነው። በመሆኑም የበለፀጉት ሀገሮች ከደረሱበት ደረጃ መድረስ ይቻላል የሚል ማጠንጠኛ ሀሳብ በመያዝ መዋቅራዊ ሽግግር በማድረግ ልማትን ማምጣት እንደዋነኛ ግቡ አድርጎ የሚመለከት ቲዎሪና ልምድ ነው። የበለፀጉት ሀገሮች ከደረሱበት ደረጃ ለመድረስ የሚደረገው ሽግግር ደግሞ በሁሉም ዘርፍ መፈፀም አለበት የሚል ነው። ለምሳሌ እርሻን ወደ ኢንዱስትሪ፣ አነስተኛ እደጥበብን ከፍ ወዳለ ኢንዱስትሪ፣ የተበጣጠሰና በአነስተኛ አቅም የሚካሄድ እርሻን ሰፊ ወደሆነ ሜካናይዝድ እርሻ፣ ከእጅ ወደ አፍ የሆነን እርሻ ወደኮሜርሻል እርሻ፣ የቆዩና ያረጁ ባህሎችን፣ ልማዶችን፣ አስተሳሰቦችንና አሰራሮችን ወደ አዲስ አስተሳሰብና አሰራር፣ አገዛዝን ወደዴሞክራሲ ወዘተ. ማሸጋገር ከተቻለ እውነተኛ ልማት እንደተመዘገበ ይቆጠራል የሚል ነው። ይህ የልማት ቲዎሪና ልምድ እጅግ ጠቃሚ የልማት አስተሳሰቦችን ያዘለ መሆኑ ባያጠራጥርም ምንም ዓይነት ጉድለቶች የሌሉበት እንደሆነ አድርጎ ማየት ግን ተገቢ አይሆንም።

በእርግጥ የመዋቅራዊ ሽግግር ልማት ቲዎሪ ከአጠቃላይ ብሔራዊ ምርትና ገቢ እድገት ቲዎሪ በተለየ መንገድ ልማትን በአሃዛዊ መመዘኛዎች ከመለካት ባሻገር ተጨባጭ በሆኑ የሽግግር ገጽታዎች መመዘን የሚቻልበትን መንገድ መክፈቱ እንደ መልካም ነገር የሚታይ ነው። አንድ ሀገር ከእርሻ ወደ ኢንዱስትሪ መሸጋገሩን ወይንም ከአገዛዝ ወደ ዴሞክራሲ ስርዓት መለወጡን አሊያም ከተበጣጠሰና ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ እርሻ ወደ ሜካናይዝድና ኮሜርሻያል እርሻ መሸጋገሩን ወዘተ. በማየት እድገት የሚመዘንበትን ተጨባጭ መለኪያ መነሻ ስለሚያደርግ ጥሩ የልማት ማሳያ ነው ሊባል ይችላል። ይሁን እንጂ ይኸም ቢሆን በሕዝቡ የዕለት ከዕለት አኗኗር ጋር ለተሳሰሩ አነስተኛ ጥረቶች የሚገባን ትኩረት የመስጠት ችግር አለበት።

በሽግግሩ ወቅት በሕዝቡ ውስጥ ሰፊ ድህነትና የኑሮ ልዩነት መፈጠሩን የማይቀር አድርጎ በመውሰድና መፍትሔውም የሚመጣው በተራዘመ ሂደትና ቀስ በቀስ ነው ከሚል ግንዛቤ በመነሳት ግለሰቦችና ቡድኖች በአነስተኛ አቅም ለሚያከናውኗቸው እንቅስቃሴዎች ሚዛን የሚደፋ ትኩረት አይሰጥም። በመሆኑም በአጭር ጊዜ ውስጥ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኘው ሕዝብ ድህነት እንዳይባባስና የከፋ የኑሮ ሁኔታ ልዩነት እንዳይከሰት ለመከላከል የሚረዳ ተጨባጭ መፍትሔ መኖሩን የማሳየት ጉልህ ድክመት አለበት። በመዋቅራዊ ሽግግር ቲዎሪ አመለካከት መሰረት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኘው ሕብረተሰብ የልማት ፍሬዎችን የሚቀምሰው ዘግይቶ ስለሚሆን እስከዚያ መስዋዕትነት መክፈል ይገባል የሚል እምነት አለ። ልማት ለማምጣት የሚቻለው አባጣ ጎርባጣ የበዛበት ጉዞ እያለፉ እንጂ በተለሳለሰ መንገድ እየተጓዙ ስላልሆነ ወይንም በረጅም ጊዜ የሚገኘውን የልማት ፍሬ ለመቅመስ እስከዚያ የሚጋጥመውን ሰቆቃ በትዕግስት በማሳለፍ ስለሆነ በሂደቱ ተጠቃሚና ተጎጂ መኖሩን መቀበል እንደ ግዴታ ተደርጎ የሚታይ ነው። በመሆኑም በዚህ አስተሳሰብ እምነት አሳድረው ራሳቸውን መስዋዕት ለማድረግ የሚወስኑት እጅግ አነስተኛዎቹ ሲሆኑ አብዛኛው በገጠመው ከባድ የኑሮ ፈተናና መረሳት ስለመጪው መልካም ነገር ተስፋ ማሳደሩን ይተወዋል።

የአጠቃላይ ብሔራዊ ምርትና ገቢም ሆነ የመዋቅራዊ ሽግግር ቲዎሪዎች ልማትን ለማሳካት በርካታ ግብዓቶችንና አካላትን አቀናጅቶ መስራት እንደሚገባ ያምናሉ። ከበለፀጉት ሀገሮች ወደ አልበለፀጉት ሀገሮች ካፒታልንና ቴክኖዎሎጂን በማሸጋገር፣ የውጭ እርዳታና ብድር በማቅረብና አለም አቀፍ የንግድ ተሳትፎን በማጠናከር፣ በዚህ ተግባር ወሳኝ ሚና መጫወት ለሚገባቸው ብሔራዊ መንግስታት አቅም ማሳደጊያ የሚሆኑ ቴክኒካዊና የምክር ድጋፎችን በመስጠት ያላደጉትን ሀገሮች ማልማት ይቻላል የሚል እምነት አላቸው። ይኸንኑ እምነት በመከተል ብድርና እርዳታ፣ የልማት እቅድና የእድገት ማሳኪያ ያሉትን ምክር ይዘው አይ.ኤም.ኤፍ፣ የአለም ባንክና ሌሎችም የተባበሩት መንግስታት ወኪሎችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ምሁራን ወደ 3ኛው ዓለም ሲጎርፉ ቆይተዋል። በዚህ መንገድ ያላደጉ ሀገሮችን ወደ ተረጋጋ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና ፖለቲካዊ እድገት ማድረስ ይቻላል በሚል እምነት በመላው ዓለም ሰፊ

እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል፡፡ ይሁን እንጂ በተግባር እንደታየው ነገሮች ሁሉ በታሰበው መንገድ ሊሄዱ አልቻሉም፡፡ ያላደጉት ሀገሮች ለልማት ማሳኪያ እንዲሆን ከውጭ ወደ ሀገር የሚያስገቡትን ብድርና ወለድ ለመክፈል ወደ ውጭ የሚልኩት እየበዛ በመምጣቱ ከጥቅሙ ጉዳቱ አመዝኗል፡፡ የተከፈለውን ሁሉ መስዋዕትነት ተከፍሎ ልማት ተገኝቷል በተባለባቸው ሀገሮች ሳይቀር ሕዝቡ የፍሬው ተጠቃሚ ለመሆን ያልቻለበት ሁኔታ ታይቷል፡፡ የፖለቲካ ስልጣን የጨበጡ ነጣቂዎች በዙሪያቸው ካሰለፏቸው ጥቂት የውጪና የውስጥ ግብረ በላዎቻቸው ጋር የተገኘችውን እየተቀራመቱ አብዛኛው ሕዝብ የበይ ተመልካች ሆኖ ቀርቷል፡፡ ተገኘ የተባለው የኢኮኖሚ እድገት ሀብት ባገኙትና ባላገኙት መካከል ያለውን ልዩነት ይበልጥ አሰፋው እንጂ አላጠበበውም፡፡

የድህውን ሕዝብ ድህነት አባባሰው እንጂ አልቀነሰውም፡፡ በዴሞራሲያዊ ተሳትፎና በተረጋጋ ፖለቲካዊ ሥርዓት ምትክ ፈላጭ ቆራጭ የሆኑ አገዛዞች የስልጣን መዘውሩን ጠቅልለው የያዙበትም አጋጣሚ ታይቷል፡፡ በዚህም የተነሳ አንዳንዶቹ የከፍተኛ ማህበራዊ ብጥብጥና ቀውስ መናኸሪያ ለመሆን ተገደዋል፡፡ እነዚህና የመሳሰሉት እውነታዎች ከተጠቀሱት የልማት ቲዎሪዎች ለየት ያለ አዲስ አመለካከት በአማራጭነት እንዲቀርብ አስገዳጅ ሁኔታ ፈጥረዋል፡፡

አዲሱ የልማት አመለካከት «የሰውን ልጅ ፍላጎት ማዕከል ያደረገ ልማት» የሚለው ሲሆን ዋነኛ ትኩረቱም ቀደም ሲል የተጠቀሱት የልማት ቲዎሪዎች ችላ ሲሏቸው በቆዩት ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ ይህ አመለካከት ከአጠቃላይ ብሔራዊ ምርትና የነፍስ ወከፍ ገቢ እድገት እንዲሁም ከመዋቅራዊ ሽግግር ቲዎሪዎች በስተጀርባ የተዘነጉትን ሰብአዊ ፍጡሮች ማህበራዊ ደህንነት የሚያካትት ልማት መምጣት አለበት በሚል ነጥብ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው፡፡ አዲሱ አመለካከት የቀድሞዎቹ እሳቤዎች የዘነጓቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች ሕይወት ለማሻሻል ስራዬ ብሎ ትኩረት የሚሰጥና መፍትሔ የሚያስገኝ ልማት ካልተመዘገበ በስተቀር እንደ ተሟላ ልማት ሊቆጠር አይገባውም በሚል እምነት ላይ የቆመ ነው፡፡ ልማት የተሟላ ሊሆን የሚችለው በዝቅተኛ ደረጃ ላለው እያንዳንዱ ሰው ማህበራዊ ደህንነት ፋይዳ ያለው ነገር ማስገኘት ከቻለ ነው በሚል መሰረታዊ ግንዛቤ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ልማት የስራ እድል ከማስገኘቱ ጋር፣ መሰረታዊ ፍላጎቶችን ከማሟላት ጋር፣ ሀብትን ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ከማከፋፈል ጋር፣ ለትላልቅ ፕሮጀክቶች ብቻ ሳይሆን በዝቅተኛው ሕብረተሰብ ደረጃ በአነስተኛ አቅም ለሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ከሚሰጠው ትኩረት ጋር ወዘተ. አብሮ መታየት አለበት የሚል አስተሳሰብ ሲሆን እ.ኤ.አ ከ1970ዎቹ መጀመሪያ አንስቶ እስካሁን በሰፊው እየተሰራጨ ነው፡፡

የሰውን ልጅ ፍላጎት ማዕከል ያደረገ ልማት ማረጋገጥ የሚለው አመለካከት ምንጩ የተለያየ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በዙሪያው የሚነሱት ነጥቦችም የተለያዩ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉም የሚጋሩት ማዕከላዊ ነጥብ የተሟላ ልማት መኖሩ የሚረጋገጠው ለሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች መሟላት ትኩረት በመስጠት፣ ሰዎች እኩል እድል እንዲያገኙ (በትምህርት፣ በጤና፣ በምግብ፣ በፖሊሲ አወጣጥ፣ በፖለቲካ ውሳኔ፣ ወዘተ.) በማድረግና የስራና ሌሎች ማህበራዊ ዋስትናዎች እንዲኖሯቸው በማስቻል ረገድ መልካም ውጤት የተገኘ እንደሆነ ነው የሚል ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ይኸንን አመለካከት መሰረት አድርገው እድገት ለማምጣት በመላው አለም የሚረባረቡ ወገኖች ብዙ ናቸው፡፡ ብሔራዊ መንግስታትና ሕዝቡ ከሚያደርጉት ጥረት ጎን በርካታ አለም አቀፍ ድርጅቶች ለምሳሌ እንደ አለም የስራ ድርጅትና አለም አቀፍ ፋውንዴሽኖች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና አካዳሚሽያንስ ወዘተ. ይኸንን አመለካከት ደግፈው እድገት እንዲመጣ እየሰሩ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ አመለካከት አኳያ የልማት ጥያቄ ሲነሳ ዋነኞቹ የትኩረት ነጥቦች የአጠቃላይ ብሔራዊ ምርትና የነፍስ ወከፍ ገቢ እድገት ወይም መዋቅራዊ ሽግግር ብቻ ሳይሆኑ ድህነትን በሚመለከት ምን ሁኔታ አለ? ሥራ አጥንትንና የኑሮ ደረጃ ልዩነትን ወዘተ. የሚመለከቱ ሁኔታዎች ምን ይመስላሉ የሚሉት ጭምር ናቸው፡፡

እዚህ ላይ በጥንቃቄ መረዳት የሚያስፈልገው ይህ የልማት አስተሳሰብ የአጠቃላይ ብሔራዊ ምርትና የነፍስ ወከፍ ገቢ እድገት ወይንም የመዋቅራዊ ሽግግር ቲዎሪዎች ልማትን በማምጣት ወይም በመለካት ምንም አይነት ጥቅም የላቸውም በሚል እምነት ላይ የቆመ አለመሆኑን ነው፡፡ ይልቁንም ከእነዚህ ቲዎሪዎች የሚለየው ልማት መለካት ያለበት ለእያንዳንዱ ሰው ሕይወት

መሻሻል ሲባል በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙት ክፍሎች በሚሰጠው ትኩረት ሊሆን ይገባል በሚለው ነጥብ ነው:: ለእነዚህ ጉዳዮች ዝቅተኛ ግምት እስካልተሰጠ ድረስ የአጠቃላይ ብሔራዊ ምርትና የነፍስ ወከፍ ገቢ ወይም የመዋቅራዊ ሽግግር ቲዎሪዎች ስለልማት ያላቸው አስተሳሰብ በስራ ላይ ቢውል ተቃውሞ የለውም:: ዋናው ነገር ልማቱ የስራ አጥነትን ለመቀነስ ረድቷል ወይስ አልረዳም፣ አንፃራዊ በሆነ መንገድ እኩል ተጠቃሚነትን አስገኝተዋል ወይስ አላስገኙም፣ ሴቶች እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው አስችሏል አላስቻለም፣ ሀገሮች ከጥገኝነት ተላቀው እውነተኛ ብሔራዊ ነፃነት እንዲቀዳጁ አግዟል ወይስ አላገዘም፣ የሰዎች ፖለቲካዊ ሕይወት ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን አስችሏል ወይስ አላስቻለም ወዘተ. ተብሎ ከሰው ልጅ ፍላጎቶች መሟላት አንፃር ሊመዘን ይገባዋል የሚለው ነው::

ይኽንን አስተሳሰብ መነሻ በማድረግ የሚካሄድ ልማት የተለያዩ ስያሜዎች ቢሰጡትም በተለያዩ አቀራረቦች ቢገለፅም ዞሮ ዞሮ ማዕከላዊ ነጥብ ተደርገው የሚወሰዱት ጉዳዮች ቀደም ሲል የተገለፁት ናቸው:: የሰውን ልጅ ፍላጎት ማዕከል ያደረገ ልማት አንዳንዴ አሳታፊ ልማት ሌላ ጊዜ ደግሞ ሕዝብን ማዕከል ያደረገ ልማት እንዲሁም አማራጭ ልማት ወዘተ የሚል መጠሪያ ቢኖረውም የሚያቀነቅናቸው አስተሳሰቦች ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ናቸው::

በሌሎቹ የልማት ቲዎሪዎችና ልምዶች ላይ ከየአቅጣጫው እንደሚነሳው ትችት በዚህኛው የልማት አስተሳሰብም ላይ የሚቀርቡ ትችቶች መኖራቸውን ማስታወስ ተገቢ ነው:: በዚህ አስተሳሰብ ዙሪያ የሚነሳው የመጀመሪያ ትችት አስተሳሰቡ ልማት በምን መንገድ ተፈፃሚ እየሆነ ነው ከሚለው ይልቅ እንዴት ተፈፃሚ ሊሆን ይገባዋል በሚል ምኞት ላይ ያተኩራል የሚለው ነው:: አሁን በመፈፀም ላይ ካለው የልማት ተግባር ይልቅ ወደፊት እንዲፈፀም በሚፈለገው ላይ ስለሚያተኩር አስተሳሰቡ የሞራልና የፖለቲካ ግምገማ ከመሆን ያለፈ ተጨባጭነት የለውም የሚል ትችት ይቀርብበታል:: በሰባዊነት ላይ ተመስርቶ የሁሉም ልማት ግብ ሰውን ማልማት መሆን አለበት ወይም የሰውን ፍላጎት ማሟላት ሊሆን ይገባል ወይንም የሰውን አቅምና ችሎታ በጥቅም ላይ ማዋል ሊሆን ይገባል ከማለት ባሻገር ይኽንን ግብ ለማሳካት የሚያስችሉ ተጨባጭ የልማት እቅዶችና መፍትሔዎችን የማቅረብ ችግር አለበት የሚል ትችት ይቀርብበታል::

በኢኮኖሚ እድገትና መዋቅራዊ ሽግግር ንድፈ ሀሳቦች ላይ ያሉትን ቅራኔዎች፣ ድክመቶችና ጠ ንቆች ከመተቸትና ከማጋለጥ ባሻገር አልፎ የሚሄድ ተደማጭነት መፍጠር አይችልም የሚል ወቀሳም ይቀርብበታል:: የሰውን ልጅ ፍላጎት ማዕከል ያደረገ ልማት የሚለው አስተሳሰብ በአለም ውስጥ ባሉ ትላልቅ ድርጅቶችና ተቋሞች እንደመፈክር የሚነሳ ቢሆንም ድህነትን ይበልጥ እንዲባባስ አስተዋፅኦ ከማድረግ አልፎ ሲያስወግድ ማየት አልተቻለም የሚል ወቀሳ አለ:: ለምሳሌ የዓለም ባንክ ይኽንን መፈክር ወስዶ የራሱ አድርጎታል:: የአለም ባንክ ደግሞ የአለም አቀፍ ካፒታል ማናጀር ተደርጎ የሚቆጠር ነው:: ካፒታሊዝም በዋናነት በገበያ ኢኮኖሚ ላይ ተመስርቶ የካፒታል ክምችትና እድገት እንዲመጣ የሚሰራ ስርዓት እንጂ ድህነትን የሚቀንስ ወይንም እኩልነትንና ሀብትን የማከፋፈል ተልዕኮ ያለው ባለመሆኑ በአለም ባንክ የሚሰማውና የሰውን ፍላጎት ማዕከል ያደረገ ልማት የሚለው መፈክር ትርጉም የለውም የሚል ወቀሳ በአንዳንድ ክፍሎች ይሰማል::

በሌሎች ወገኖች ደግሞ የሚቀርበው አስተያየት ከዚህ የተለየ ነው:: ይኸውም በአለም ውስጥ ስለሚታየው ድህነት ከአለም ባንክ የበለጠ ትኩረት ሰጥቶ ጥናቶችን፣ የምርምር ሰነዶችንና የመፍትሔ እርምጃዎችን ያቀረበ የለም የሚል ነው:: ይህ መፈክር ጎልቶ በወጣበት በ1970 የአለም ባንክ በከፍተኛ አድናቆት ደግፎ የተቀበለውን ያህል አሁንም ቢሆን የሕዝብን አቅም ለማሳደግ፣ የፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ፣ ዘላቂ ልማትና የአካባቢ ጥበቃ እንዲተሳሰሩ ለማድረግ ከአለም ባንክ የበለጠ ድምፅ የሚሰማ ሌላ አካል ማግኘት ይከብዳል የሚል አስተያየት አላቸው:: አንዳንዶች በዚህ የልማት አስተሳሰብ ላይ ትችት የሚቀርብበት ዋናው ምክንያት በኢኮኖሚ እድገትና በመዋቅራዊ ሽግግር ንድፈ ሀሳቦች ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ ለመቀነስ ሲባል ነው የሚል አስተያየት ሲያቀርቡ ሌሎች ደግሞ ይህ አስተሳሰብ ከመነሻው የነበረውን ጠንካራ ጎን በሂደት እያጣና በኢኮኖሚ እድገትና በመዋቅራዊ ሽግግር ንድፈ ሀሳቦች እየተዋጠ የመጣ ነው ይላሉ::

ሌላው ትችት የሰውን ልጅ ፍላጎት ማዕከል ያደረገ ልማት የሚለው አስተሳሰብ አላማውና ግቡ እንዴት ተፈፃሚ እንደሚሆን ግልፅ ካለመሆኑም በላይ አሁን ባለው የኃይል አሰላለፍና የስልጣን አወቃቀር ተግባራዊ የመሆን እድሉ ጥያቄ ውስጥ የወደቀ ነው የሚል መንፈስ አለው:: የሀብት ክፍፍል፣ እኩልነት፣ ድህነትን ማስወገድ ወዘተ. የሚሉ አስተሳሰቦች አብዮታዊ አፈፃፀም የሚጠይቁ ሆነው ሳለ በብሔራዊና አለምአቀፋዊ ደረጃ ስርነቀል የሆነ አብዮታዊ ለውጥ ሳይኖር ተግባራዊ የመሆን እድላቸው የመነመነ ነው የሚል አስተያየት ያላቸው ወገኖች አሉ:: ስለሆነም የሰውን ልጅ ፍላጎት ማዕከል ያደረገ ልማት የሚለው አስተሳሰብ አሁን ባለው አለም አቀፍ የስራ ክፍፍልና የስልጣን አወቃቀር ተጨባጭ ሁኔታ ሊፈፀም የማይችል ከንቱ ምኞትና ተስፋ ብቻ ነው የሚል ትችት ይቀርብበታል::

## 3.3 ማጠቃለያ

በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የሚነሱ ልዩ ልዩ ትችቶችና አስተያየቶች እንዳሉ ሆነው የልማት ጥያቄ አለም አቀፍ ባህሪይ ያለው ትልቅ አጀንዳ መሆኑ የማይካድ ነው:: የማንኛውም ልማት ውጤት የሚመዘነው ደግሞ አሁን በቀረቡት መመዘኛዎች መሆኑ የማይቀር ነው:: አንድ ሀገር ልማት አምጥቷል ወይንስ አላመጣም ለማለት አንድም የተመዘገበ የኢኮኖሚ እድገት መኖር አለመኖሩ መታወቅ አለበት:: አልያም ደግሞ የሚጨበጥ መዋቅራዊ ሽግግር ማድረጉና አለማድረጉ መረጋገጥ አለበት:: ወይንም ደግሞ ለሰው ልጅ ፍላጎቶች መሟላት ያደረገው ጥረትና ያስመዘገበው ውጤት መኖር አለመኖሩ መታየት አለበት::

የሀገራችንም ልማትና ውድቀት ከእነዚህ መሰረታዊ መመዘኛዎች ውጭ የሚገመገምበት ሌላ አማራጭ መንገድ ሊኖር አይችልም:: በኢትዮጵያ ውስጥ ልማት መኖር አለመኖሩን ለማየት የተመዘገበ የኢኮኖሚ እድገት አለ ወይንስ የለም ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው:: ከዚህም ሌላ ምን አይነት መዋቅራዊ ሽግግር አለ ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ ነው:: ከሁሉም በላይ ደግሞ የተመዘገበው የኢኮኖሚ እድገትና የታየው መዋቅራዊ ሽግግር የዜጎችን ምግብ የማግኘት፣ መጠለያ የማግኘት፣ ልብስ የማግኘት፣ ስራ የማግኘት፣ ትምህርትና ሕክምና የማግኘት ወዘተ. ፍላጎቶች አሟልቷል ወይንስ አላሟላም ብሎ መገምገም የማይታለፍ ጉዳይ ነው:: በእነዚህ ከሞላ ጎደል አለም አቀፍ ተቀባይነት ባላቸውና የሀገሮች ልማት መመዘኛ ሆነው በሚያገለግሉ መስፈርቶች የሀገራችን ልማት ሲመዘን የሚገኘው ውጤት አዎንታዊ አይደለም:: በሁሉም አይነት የልማት መመዘኛዎች ኢትዮጵያ የመጨረሻውን ደረጃ እንደያዘች ናት::

በመሆኑም ከዚህ ሁኔታ ለመውጣት እንዲቻል ለሀገራችን እድገት የሚበጅ ብሔራዊ (አገር አቀፍ) የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ማቅረብ የማይታለፍ ጥያቄ ነው:: እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ሶስት ዋና ዋና የልማት መለኪያዎች ያቀናጀ አሰራር ተግባራዊ ማድረግም ለሀገራችን ጠቃሚና አስፈላጊነው ብሎ ኢዴፓ ያምናል::

# 4. ግሎባላይዜሽን በልማት ምርጫ ላይ የሚጫወተው ሚና

የዘመናችን ዋነኛ ዓለም አቀፍ ክስተት ግሎባላይዜሽን ነው:: ግሎባላይዜሽን ማለት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተፈጠረና ባለብዙ ፈርጅ የግንኙነት መረብ ማለት ነው:: በሌላ አገላለጽ የእያንዳንዱ ሀገር ሕዝብና ግለሰብ ሕይወት ከእርሱ በከፍተኛ ርቀት በሚገኙ ክስተቶች ተጽዕኖ ስር የወደቀበት ሁኔታ ማለት ነው:: በአሁኑ የግሎባላይዜሽን ዘመን የመልክዓ ምድራዊ ርቀት፣ በሀገሮች መካከል የተሰመሩ የግዛት ክልሎችና በመኖሪያዎች መካከል የተገነቡ አጥሮች ግንኙነትን የሚገድቡበት አቅም በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል::

ግሎባላይዜሽን ራሱ የብዙ ክስተቶች እድገት ውጤት ሲሆን በተለይ ደግሞ የመገናኛ ቴክኒዎሎጂዎች ተሻጋሪ የንግድ እንቅስቃሴዎች ማደግና የመሳሰሉት ሁኔታዎች ለዚህ ክስተት መፈጠርና ዓለም አቀፍ ገጽታ መያዝ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል:: ግሎባላይዜሽን እንደገና በተራው ለእርሱ መፈጠር መነሻ የሆኑ ጉዳዮች ይበልጥ እንዲቀላለፉና በመላው ዓለም በፍጥነት እንዲሰፋፉ አስችሏል:: እንዳውም ከ20ኛው ክፍለ ዘመን 2ኛ አጋማሽ ጀምሮ ለተከሰቱ

ውስብስብና መልከ ብዙ ለውጦች ምክንያት ለመሆን በቅቷል። ግሎባላይዜሽን በሀገሮች መካከል ፈጣን የሆነ የምርትና ካፒታል ዝውውር፣ የፖለቲካና የባህል ትስስር እንዲኖር ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። የኢንተርኔት፣ የሳተላይትና የኬብል ቴሌቪዥን መስፋፋት ጎልቶ በሚታይበት አስደናቂ የመገናኛ ቴክኒዎሎጂ ሊታገዝ በመቻሉ አለምአቀፋዊ የኢኮኖሚ ትስስር ብቻ ሳይሆን ፖለቲካዊና ባህላዊ ትስስርም እንዲኖር አድርጓል። ለድንበር ዘለል ኩባንያዎች መጠናከር ብቻ ሳይሆን ለባህል መወራረስ፣ ለፖለቲካዊ እሴቶች ዓለም አቀፍ ባህርይ መያዝ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። በዚህም የተነሳ በአሁኑ ጊዜ ግሎባላይዜሽን የማይነካው የሕይወት ዘርፍ የለም ለማለት ይቻላል።

በዚህ ዓለም አቀፍ ክስተት ይዘትና አስፈላጊነት ላይ ሰፊ የአስተሳሰብ ልዩነቶችና ክርክሮች እንዳሉ የታወቀ ቢሆንም ዋናው ነገር ከዚህ የዓለም ተጨባጭ ሁኔታ ውጭ ለመሆንና ጉዳዩን በገለልተኝነት ለማየት የማይቻልበት ደረጃ ላይ መደረሱ ነው። ግሎባላይዜሽንን በሚመለከት ከሚነሱት ክርክሮች መካከል በብሔራዊ መንግስታት ፖለቲካ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው የሚለው አስተያየት አንደኛው ነው። ግሎባላይዜሽን ብሔራዊ መንግስታት ተግባራቸውን በነፃነት እንዳይሰሩና ከቁጥጥራቸው በላይ በሆኑ ውጫዊ ሁኔታዎች ተፅዕኖ ስር እንዲወድቁ አድርጓል የሚል የከረረ ወቀሳ ይደመጣል። በእርግጥም የኢንተርኔት፣ የሳተላይት ቴሌቪዥንና የመሳሰሉት የመገናኛ ቴክኒዎሎጂዎች አንዳንድ አምባገነን መንግስታት የራሳቸውን አመለካከት ብቻ ለማሰራጨትና የተቃዋሚዎቻቸውን ለማፈን እንዳይችሉ አድርጓቸዋል። በመረጃዎች ስርጭት ላይ ቁጥጥር ለማድረግ እንዳይችሉና ከድንበራቸው ውጭ ከሚገኙ ማሰራጫዎች የሚተላለፈውን ማንኛውም ነገር ከቁጥጥር አቅማቸው በላይ እንዲሆን አድርጎታል።

በዚህና በሌሎችም ሁኔታዎች የተነሳ በዓለም አቀፉ ተፅዕኖ ስር ሙሉ በሙሉ ወድቀው ነፃነታቸውን እንደተነጠቁና ለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ እንደተጋለጡ አድረገው የሚያስቡ አሉ። በግሎባላይዜሽን ዘመን የሚታየውን ሰፊ የባህል ልውውጥ እንደባህል ወረራ የሚመለከቱ አሉ። በተለይም የግሎላይዜሽን ኢኮኖሚያዊ ገጽታ በድሃ ሀገሮች ላይ ከባድ ተጽዕኖ እያደረገ ነው የሚሉት ወገኖች ጥቂት አይደሉም። በኢንዱስትሪ ያደጉ ሀገሮች የድንበር ዘለል ኩባንያዎች የሚያካሂዱት ዓለም አቀፍ ንግድና የካፒታል ዝውውር ዋነኛ ተጠቃሚዎች በመሆናቸው፣ የተራቀቀ ቴክኒዎሎጂ ምንጭ ብቻ ሳይሆኑ ግንባር ቀደም ተጠቃሚቹም እነርሱ ስለሆኑ ግሎባላይዜሽን የሀብታሞቹን ጥቅም እየጠበቀ ድሃዎቹን ደግሞ ይበጥል እንዲደኸዩ የሚያደርግ ውጤት ያስከትላል የሚለው ስጋት በሰፊው ይንፀባረቃል።

ለስጋቱ ማስረጃ ተደርገው ከሚቀርቡት መካከል ዋና ዋና የሚባሉትን ጥቂት ነጥቦች መጥቀስ ጠቃሚ ነው። የመጀመሪያው ነጥብ ከብሔራዊ መንግስታት ፖለቲካዊ ሉዓላዊነት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ነው። ይኸውም ማንኛውም ድሃ ሀገር የራሱን እድል በራሱ ለመወሰንና የማንም ውጫዊ አካል ጣልቃ ገብነት ሳይኖር የራሱን ጉዳይ ለመቆጣር ያለው ችሎታና ስልጣን ከግሎባላይዜሽን ክስተት ጋር በተፈጠረው የብሔራዊ መንግስታት ትስስር የተነሳ ተሸርሽሯል የሚል ነው። ከዚህ በፊት በብሔራዊና ዓለምአቀፋዊ ፖለቲካ መካከል የነበረው ልዩነት ቀስ በቀስ እየጠፋና ትስስሩ ደግሞ በፍጥነት እየጨመረ በመምጣቱ በግንኙነቱ ሂደት ጠንካራ ተሰሚነት የሌላቸው የድሃ ሀገሮች መንግስታት በራሳቸው መንገድ ነፃ ሆነው ለመስራት ያላቸው ችሎታ አደጋ ላይ እንደወደቀ አድርገው ይመለከቱታል።

የግሎባላይዜሽን አንዱ ገጽታ መንግስታት ወንዝ ተሻጋሪ በሆኑ መንግስታዊ ትስስሮች ውስጥ እየተጠቃለሉ መምጣታቸው ነው። ለምሳሌ የአውሮፓ ሕብረት፣ የአፍሪካ ሕብረት ወዘተ. ተመስርተዋል። ይሁን እንጂ የአውሮፓ ሕብረት ጠንካራ ፖለቲካዊ ተደማጭነትና የኢኮኖሚ አቅም ያላቸውን መንግስታት ያስተሳሰረ እንደመሆኑ ከአፍሪካ ህብረት ጋር በእኩል ደረጃ ለመታየት የማይችልባቸው በርካታ ሁኔታዎች አሉ። የአውሮፓ ሕብረትና የአፍሪካ ሕብረት ለአባል መንግስታት የሚያስገኙት ጥቅም እኩል አይደለም። የአውሮፓ ሕብረት በዓለም አቀፉ ትስስር ውስጥ መሪ ሚና ያላቸው ሀገሮች ሕብረት እንደመሆኑ እንደ አፍሪካ ባሉ ድሃ ሀገሮች የተመሰረቱ ሕብረቶች ከሚያስገኙት የበለጠ ጥቅም እንዳለው የታወቀ ነው። ጥቅማቸውን የሚጎዳ አቋም ያራምዳል በሚሉት መንግስትና ሀገር ላይ የሞራል ግፊት ከማድረግ ጀምሮ ፖሊሲ ለማስቀየር የሚረዳ ማዕቀብ በመጣል፣ ከዚያም በላይ ዓላማቸውን ለማሳካት ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት እስከመፈፀም የሚደርስ የማስገደጃ ዘዴ ይጠቀማሉ። የዚህ ዓይነቱን እርምጃ

በመውሰድና ውጤት በማምጣት ረገድ ባደጉትና ባላደጉት ሀገሮች መካከል ሰፊ ልዩነት አለ፡፡ ያደጉት ይበልጥ ውጤታማ ተፅዕኖ ማሳደር የሚያስችል ዓለም አቀፍ ጥንካሬ ገንበተዋል፡፡ ያላደጉት ደግሞ ይኸ ችሎታ የላቸውም፡፡ በመሆኑም የወንዝ ተሻጋሪ መንግስታት ትስስር ይበልጥ ተጠቃሚ የሆኑት ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ መሰረትና የንግድ የበላይነት የመሰረቱት ሲሆኑ ይበልጥ ተጎጂ የሆኑት ደግሞ ዓለም አቀፍ አቅምና ተደማጭነት ያልገነቡት ድሃ ሀገሮች ናቸው የሚለው ስጋት ምክንያታዊ ነው፡፡

ሁለተኛው ነጥብ ከአለምአቀፋዊው የኢኮኖሚ ትስስር ጋር በተያያዘ የሚነሳው ነው፡፡ በግሎባላይዜሽን ዘመን ሁሉም ሀገሮች ለጋራ ጥቅም በሚበጅ ትብብር ዙሪያ እንዲሰለፉ በማደፋፈር እያገለገሉ ካሉት ልዩ ልዩ መደበኛ ተቋሞች /እንደ ተ.መ.ድ. ያሉ/ በተጨማሪ የድሃ ሀገሮችን ወሰን አስፈላጊነት የሚሸረሽሩ አለም አቀፍ ክስተቶችም እያደጉ መጥተዋል የሚለው ስጋት ተደጋግሞ የሚሰማ ነው፡፡ በዘመኑ ንግድና ፋይናንስ ዓለማቀፋዊ ባህርይ ምክንያት የተከሰተው አለምአቀፋዊ የኢኮኖሚ አስተሳሰብ የተመሰረተው የእያንዳንዱ ሀገር ኢኮኖሚ እንደ አንድ ሀገራዊ ኢኮኖሚ ሳይሆን እርስ በርስ የተሳሰረው የአለም ኢኮኖሚ አካል ሆኖ መታየት አለበት በሚል ግንዛቤ ላይ ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ የአንድ ሀገር ወይም የወተሰኑ ሀገሮች የኢኮኖሚ ውጤታማነትና ውድቀት በመላው አለም በሚገኙ ሌሎች ሀገሮች ላይ ወሣኝ አንደምታ አለው ለሚለው ነጥብ አጽንኦት የሚሰጥ ነው፡፡ የእያንዳንዱን ድሃ ሀገር ወሰን አስፈላጊነትና ሉዓላዊነት በመሸርሸር መሪ ሚና ይጫወታሉ የሚል ወቀሳ ከሚቀርብባቸው የዘመናችን ኢኮኖሚያዊ ክስተቶች መካከል አለም አቀፍ ንግድ፣ ሕብረ ብሔራዊ ኩባንያዎችና የውጭ እርዳታ ዋነኞቹ ናቸው፡፡

እያንዳንዱን ክስተት በመጠኑም ቢሆን ለማየት መሞከር በዚህ ዙሪያ ከሚነሳው ክርክር ጀርባ ያለውን እውነታ ለመረዳት ያግዛል፡፡ የዘመኑ ዓለም አቀፍ ንግድ ሁሉም ብሔራዊ መንግስታት በሚያካሂዱት እንቅስቃሴ ላይ የተወሰነ ተፅዕኖ እንደሚኖረው ቢታወቅም ተፅዕኖው ይበልጥ የሚበረታው በድሃዎቹ ላይ ነው የሚለው መከራከሪያ ቀላል መልስ የሚገኝለት አልሆነም፡፡ ለምሳሌ የአውሮፓ ሕብረት (EU) ወይም ጠቅላላ የታሪፍና የንግድ ስምምነት (GATT) አባል ሀገሮች አንዳቸው የሌላውን አባል መንግስት ጥቅም የሚጎዳ የታሪፍ ጥበቃ ፖሊሲ አውተው ስራ ላይ እንዳያውሉ የሚከለክል ስምምነት አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ ስምምነቱ ስራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ድሃ ሀገሮች የሚጠቀሙበት እድል መፈጠሩን በተጨባጭ ለማረጋገጥ የሚያስችል ውጤት አለመገኘቱ ለዓለም አቀፍ ንግድ ፍትህ አልባነት እንደ አንድ ማስረጃ ሆኖ የሚቀርብበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ እንዲያውም ያደጉት ሀገሮች የአለም ንግድ ስርዓቱን በተባበረ መንገድ የሚቆጣጠሩበትን መንገድ ከመፍጠሩ በስተቀር ለድሃዎቹ ሀገሮች ያስገኘው ፋይዳ የለም ከሚለው ወቀሳ አላመለጠም፡፡

የአለምን የንግድ ስርዓት ለመቆጣጠር ከዚህ የሰፋ ስምምነትም ተፈጥሯል፡፡ ይህ ስምምነት ከሚገለጽባቸው መድረኮች መካከል ጂ-7 (ቡድን 7) እየተባለ የሚጠራውና አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ኢጣሊያ፣ ካናዳ፣ ጀርመንና ጃፓን በአባልነት የሚገኙበት የሰባቱ በኢንዱስትሪ የበለፀጉ ሀገሮች ሕብረት አንደኛው ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሶቭየት ሕብረትንም እንዲያካትት በመደረጉ ጂ-8 (ቡድን 8) እየተባለ መጠራት ጀምሯል፡፡ ይህ መድረክ እያንዳንዱ አባል ሀገር በኢኮኖሚ ፖሊሲ ረገድ በተናጠል ሊደርግ የሚችለውን ጥረት በተወሰነ ደረጃ የሚገድብ ተደርጎ ቢገመትም የበለፀጉት ሀገሮች የዓለምን ንግድ በመቆጣጠር ያላቸውን ጥቅም እንዲያቻችሉ በመርዳት የሚያስገኘው ውጤት የበለጠ ነው የሚል ግምገማ ከተለያየ አቅጣጫ ይቀርባል፡፡ እያንዳንዱ አባል መንግስት አንድ አይነት የፖለቲካ ውሳኔ ሲያስተላልፍ በሌሎች አባል መንግስታት የፋይናንስ ገበያ ላይ ሊከሰት የሚችለውን ገንቢም ሆነ አፍራሽ ውጤት አስቀድሞ እያገናዘበ መሆን እንዳለበት በስምምነት የተቀመጠው ግዴታ የውስጥ ነጻነቱን በተወሰነ ደረጃ እንደሚገድብ ቢታመንበትም ከዚህ ይልቅ በዓለም አቀፍ ንግድ ያላቸውን የመሪነት ሚና በቅንጅት ለመወጣት የሚያስችል የጋራ መድረክ ሆኖ በማገልገል የሚሰጠው ጥቅም የበለጠ ዋጋ አለው፡፡ ይህ መድረክ የበለፀጉት ይበልጥ እንዲበለጽጉና ወደ ኋላ የቀሩት ደግሞ ባሉበት እንዲዳክሩ ከማድረግ ያለፈ ውጤት ባለማምጣቱ የዓለም አቀፍ ንግድ ፍትሃዊነት የሚረጋገጥበት ዘመን ቅርብ እንደሚሆን ተስፋ ለማድረግ እንኳ የሚያስችል

ምልክት አላሳየም ብለው የሚያማርሩት ብዙ ናቸው:: ይልቁንም የበለፀጉት ሀገሮች የጋራ መድረኮች የድሃዎቹን ሀገሮች ሉዓላዊነት ይበልጥ አዳክመዋል ባይ ናቸው::

በተደጋጋሚ ጊዜ እንደሚገለፀው መጠነ ሰፊ የሆነ ካፒታልና የንግድ እንቅስቃሴ መሰባሰብ ሕብረ ብሔራዊ ኩባንያዎች እንዲመሰረቱ ረድቷል:: እነዚህ ኩባንያዎች ዋና ጽህፈት ቤታቸውን በአንድ ሀገር ውስጥ ያድርጉ እንጂ የእንቅስቃሴያቸው አድማስ ግን መላውን ዓለም የሚያዳርስ ነው:: ለዚህ ዓለምአቀፋዊ እንቅስቃሴ የሚደፋፈሩበት ዋነኛ ምክንያት ደግሞ በተለይም በታዳጊ ሀገሮች ያሉት ተቋሞቻቸው ጥሬ ዕቃና ርካሽ የሰው ጉልበት እንደልብ ስለሚያገኙ ነው:: እነዚህ ሕብረ ብሔራዊ ኩባንያዎች ካፒታላቸውን ኢንቨስት ባደረጉባቸው ሀገሮች መንግስታት ነፃ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ጫና ያሳርፋሉ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ነፃነታቸውን አደጋ ላይ ይጥሉታል የሚል ክስ ይቀርብባቸዋል:: ሕብረብሔራዊ ኩባንያዎቹ ለፈጠሩት የስራ እድልና ለሚያስገኙት የቀረጥ ገቢ ምትክ ኢንቨስትሜንት ያካሄዱበት ሀገር መንግስት ልዩ ወሮታ እንዲከፍላቸው ይጠይቃሉ ከሚል ወቀሳ አላመለጡም:: የዚያ ሀገር መንግስት ፖሊሲ ከኩባንያቸው ጥቅም ጋር የሚጋጭ አለመሆኑን ለማረጋገጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሀገሪቱን ፖለቲካዊ ስርዓት ለመቆጣጠር ከፍተኛ ፍላጎት ስለሚያድርባቸው በዚህ የተነሳ በሚከሰተው አለመግባባት ጉዳት አጋጥሞናል የሚሉ መንግስታት አሉ:: እናም የድሃ ሀገሮችን ሉዓላዊነት በመሸርሸር ረገድ ሕብረብሔራዊ ኩባንያዎች ወሳኝ ሚና እንደሚጫወቱ የሚነሳው ቅሬታ ሁነኛ መፍትሔ አግኝቷል የሚባል አይደለም::

ድሃ ሀገሮች የውጭ እርዳታ ተቀባይ የመሆናቸው ጉዳይ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለሚመጣ ልዩ ልዩ ዓይነት ተፅዕኖዎች የተጋለጡ አድርጓቸዋል:: የእርሻና ኢንዱስትሪ ልማትን ለማነቃቃት ወይም ደህንነታቸውን ለመጠበቅ የሚያስፈልጋቸውን ገንዘብ በአብዛኛው በሀገር ውስጥ የመፍጠር አቅም ስለሌላቸው ከውጭ በሚገኝ ብድርና እርዳታ ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ ይገደዳሉ:: የሚገኘው ብድርና እርዳታ ከመንግስት ጋር በተናጠል በሚፈፀም ባይላተራል ግንኙነት ወይንም እንደ አለም ባንክና አለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ከመሳሰሉት ዓለም አቀፋዊ አካላት ጋር በሚደረግ መልቲ ላተራል ግንኙነት የሚመጣ ነው::

በዚህ መንገድ የሚገኝ ብድርና እርዳታ ተቀባይ የሆኑ መንግስታት እንዲያሟሏቸው በሚፈለጉ በርካታ ቅድመ ግዴታዎች የታጀበ ነው:: ከግዴታዎቹ መካከል አንዱ መሰረታዊ የውስጥ ፖሊሲዎችን መቀየር ሊሆን ይችላል:: በዚህም ምክንያት በውጭ እርዳታና ብድር ላይ የሚተማመኑ ሀገሮች ከጥገኝነት ነፃ ሆኖ ለመኖርና ለመስራት ያላቸው እድል አነስተኛ ነው:: በአበዳሪዎች የሚጠየቁት የወለድ መጠንና ብዙ ዓይነት ቅድመ ሁኔታ የተበዳሪ ሀገሮችን ሉዓላዊነት ከመሸርሸሩም በላይ የዜጎቻቸውን ሕይወት ይበልጥ ጎስቋላ እንዲሆን ማድረጉ የብድርና የእርዳታውን ዓላማ ትክክለኛነት ጥያቄ ውስጥ አስገብቶታል:: ተበዳሪ ሀገሮች የወሰዱትን ብድር ከእነወለዱ ለመክፈል የእርሻ ምርቶቻቸውን በገፍ ወደውጭ ለመላክ ስለሚገደዱ በተገኘው ብድር ተጠቃሚ መሆን ቀርቶ የሀገራቸውን ሕዝብ ከረሃብ ለማዳን እንኳ አልቻሉም:: የዓለም አቀፍ ብድር ጥገኛ መሆናቸው በኢኮኖሚ ልማት መከተል የሚገባቸውን ተገቢ አቅጣጫ በነፃነት ለመወሰን የማይችሉና በደካማ አቋም ላይ እንዲገኙ አድርጓቸዋል:: የዚህ ዓይነቱ ግንኙነት ድሃዎቹ ሀገሮች ላደጉት ባለኢንዱስትሪ ሀገሮች ለረጅም ጊዜ ጥሬ እቃ አቅራቢና የሸቀጥ ማራገፊያ ብቻ ሆነው እንዲያገለግሉ አድርጓቸዋል:: ድሃዎቹ ሀገሮች በእርሻና በተፈጥሮ ማዕድን ላይ ብቻ  እንዲያተኩሩና በኢንዲስትሪ ለመልማት ያላቸው እድል የጠበበ እንዲሆን ስላደረገው የኢኮኖሚ ልማት ስርዓታቸው በቀላሉ በማይቃናበት ሁኔታ ተዛብቷል:: በአጭሩ ያደጉት ባለኢንዱስትሪ ሀገሮች ያላቸው ዓለም አቀፍ የገበያ፣ የቴክኒዎሎጂና የካፒታል የበላይነት ያላደጉትና ድሃዎቹን ሀገሮች ለውጭ ብድርና እርዳታ ጥገኛ እንዲሆኑ ስላደረጋቸው በዚህ ዓይነቱ የተዛባ ዓለም አቀፍ ግንኙነት ውስጥ የሚጠቀሙት እነዚያው ቀድመው የበለፀጉት ብቻ ናቸው የሚለው ክርክር እንደቀጠለ ነው:: ስለዚህ ከግሎባላይዜሽን ክስተት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጥያቄ የድሃዎቹን ሀገሮች ኢኮኖሚያዊ ነፃነት የሚያረጋግጥ ፍትሃዊ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት እንዲመሰረት ያግዛል ወይንስ በበለፀጉትና በደኸዩት መካከል የነበረውን ልዩነት ይበልጥ ያሰፋል በሚሉት ጉዳዮች ዙሪያ የሚሽከረከር ነው::

በግሎባሌይዜሽን ክስተት ምክንያት ከተደቀነው የሉዓላዊነት የኢኮኖሚ ነፃነትና የባህል ጥበቃ ስጋት ጎን ለጎን የሚነሳ ገንቢ አስተያየት መኖሩንም መጥቀስ ተገቢ ነው:: ግሎባላይዜሽን

በኢንዱስትሪ ያደጉ ሀገሮች ለራሳቸው የሚጠቅሙ የንግድ ሕጎችን ለማስፋፋት የሚችሉትና በድሃ ሀገሮች ላይ ተፅዕኗቸውን የሚጠብቁበት ክስተት ብቻ ተደርጎ መታየት አይገባውም ከሚለው ወገን የሚነሳው ክርክር የሚመሰረትባቸው የራሱ መነሻዎች አሉ፡፡ የመጀመሪያው መነሻ ሀሳብ አለም አሁን በደረሰችበት የተራቀቀና ዓለም አቀፋዊ ባህርይ ባለው የኢንፎርሜሽን አብዮት ዘመን ግሎባላይዜሽን (ዓለምአቀፋዊ ትስስርን) ወደጎን እየተው መራመድ አይቻልም የሚለው ነው፡፡ ስለሆነም ዓለምአቀፋዊው ትስስር የሚያስገኛቸውን በጎ ውጤቶች ለመጠቀም እየሞከሩ የሚያሳድራቸውን ጎጂ ተፅዕኖዎች ለመቀነስ መሞከሩ እንጂ ሊገቱት ወይንም ጨርሶ ሊያስወግዱት የማይችሉትን ነባራዊ እውነታ በመርገም ብቻ ከችግሩ መገላገልና መፍትሔ ማግኘት እንደማይቻል መቀበል ያስፈልጋል የሚል ነው፡፡

ሁለተኛው ነጥብ የግሎባላይዜሽን ክስተት ቢያንስ አሁን በሚገኝበት ደረጃ የብሔራዊ መንግስታት ሙሉ በሙሉ በትልቁ አለምአቀፋዊ ኢኮኖሚ ትስስር የተዋጡበትና ምንም ነገር ለማድረግ እንዳይችሉ ሁሉም በሮች የተዘጉባቸው መሆኑን አያመለክትም የሚል ነው፡፡ በዚህ አመለካከት መሰረት አሁን የሚታየው አለምአቀፋዊ ትስስር የብሔራዊ መንግስታት ከነአካቴው የማያስፈልጉ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሳይሆን የቀድሞ ሚናቸው የተቀየረ መሆኑን ነው፡፡ ይኸውም የብሔራዊ መንግስታት የወቅቱ ሚና አንድ ሊያስወግዱት የማይችሉት አለምአቀፋዊ ነባራዊ ክስተት መፈጠሩን ተቀብለው በዚህ ሁኔታ ውስጥ ለመኖር ደግሞ በውድድር መስራት አስፈላጊና ግዴታም መሆኑን አምነው በፍጥነት እየሰፋ በሚሄደው ዓለምአቀፋዊ ውድድር ውስጥ ለብሔራዊ ልማት የሚበጅ ተገቢ ስትራቴጂ እያወጡ መንቀሳቀስ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ ብሔራዊ መንግስታት የልማት ስትራቴጂ በሚያወጡበት ጊዜ እንደ ድሮው አለምአቀፋዊ ወይም ውጫዊ ሁኔታን በቀላሉ እንደሚቆጣጠሩት (እንደሚቋቋሙት) ጉዳይ አድርገው ለመመልከት አይችሉም፡፡ በልማት ሂደት ውስጥ ስኬታማ የመሆናቸው ወይም የመውደቃቸው ጉዳይ የሚወሰነው በሀገራቸው ነባራዊ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን በዓለምአቀፋዊው (በውጫዊው) ተጨባጭ ሁኔታም ጭምር መሆኑን ማወቅ የግድ ነው፡፡ የአሁኑን ዓለምአቀፋዊ ሁኔታ እንደፈለገው ይሁን ብሎ ለመተው የሚቻልበት ዘመን አለመሆኑን ማወቅ ይገባል፡፡ ግሎባላይዜሽንን በዚህ መንገድ መረዳት ከተቻለ ከበጎ ጎኖቹ ይበልጥ ተጠቃሚ ለመሆን እድሉ ዝግ አይደለም፡፡

በግሎባላይዜሽን ዘመን እያንዳንዱ ሀገር በራሱ የውስጥና የውጭ ጉዳዮች ላይ ትርጉም ያለው ቁጥጥር ለማድረግ ምንም አይነት እድል የለውም የሚለው አቋም የተሳሳተ ነው፡፡ በዚህ የግሎባላይዜሽን ዘመን እያንዳንዱ ብሔራዊ መንግስት የሀገሩ ኤኮኖሚና አሰራር ለዓለምአቀፋዊው ተፅዕኖዎችና ተጨባጭ ሁኔታዎች የተጋለጠ መሆኑን አምኖ ነገር ግን የራሱን ኢኮኖሚ ተወዳዳሪ ለመሆን በሚያስችለው የፖሊሲ አቅጣጫ እየቃኘ መምራት ይችላል፡፡ የየሀገሩ ሕግ አውጭዎች አሁንም የሀገራቸውን ታክስ፣ የወለድ መጠን፣ የወጪና የገቢ ንግድ ሕጎች ወዘተ. ከሀገራዊውና አለምአቀፋዊው ሁኔታና ከገበያ ሕጎች ጋር በተጣጣመ መንገድ የመወሰን ስልጣናቸውን እንደጠበቁ ናቸው፡፡ አለም አቀፍ የንግድ ድርጅት (WTO) የሚባለው አለምአቀፋዊው ተቋም ለሁሉም ሀገሮች ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ክፍት የሆነ ንግድ እንዲኖርና ለታዳጊ ሀገሮች ኢኮኖሚ ማደግ አስተዋጽኦ ያለው ሚና ለመጫወት በሚያስችለው ደረጃ እንዲንቀሳቀስ ለመገፋፋት እድሉ አላቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የዴሞክራሲ ስርዓት ያልገነቡ ሀገሮች ግሎባላይዜሽን የዴሞክራሲ እሴቶች በመላው አለም እንዲስፋፉ የፈጠረውን ምቹ ሁኔታ ተጠቅመው የዴሞክራሲ ባህል በየሀገራቸው ስር እንዲሰድ ለማድረግ ፍላጎትና ዝግጁነት ማሳየት ከቻሉ በዚህም ረገድ ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ፡፡ የአሁኑ የግሎባላይዜሽን ክስተት በዘር ላይ የተመሰረተ ፖለቲካና ጎሰኝነት የሚቆምበትን መሰረት የሚንድ ትስስር እንዲፈጠር ስለሚያስገድድ የዘር ልዩነቶችን ለማጥበብና እያቻቻሉ በትብብር ለመስራት የሚያስችል በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ አንድነት የሚፈጥር መሆኑ ሌላው ጠቃሚ ጎኑ ነው፡፡ ለቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ለተቀላጠፈ አለም አቀፍ መረጃ ዝውውር፣ ለተቀላጠፈ አለም አቀፍ ግንኙነትና ለወጪ ቁጠባ ወዘተ. የሚስገኘው ጥቅም እጅግ የላቀ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የአለም አቀፉ አንድ አካል እንደመሆኗ ከግሎባላይዜሽን ክስተት ራሷን ገለልተኛ ማድረግ አይቻላትም፡፡ እንደዚህ ዓይነት አስተሳሰብ መከተልና አቋም መያዝ አይገባም፡፡ በአሁኑ

የአለም አቀፍ ተጨባጭ ሁኔታ ራስን ከተጨባጩ እውነታ ለማግለል ቢፈለግም ውጤቱ አደገኛ ነው:: ነባራዊውን እውነታ እንዳላዩና እንዳልሰሙ በመቁጠር ራስን ለማግለል መሞከር በአለምአቀፋዊው ትስስር ምክንያት ይደርሳል ከሚባለው ችግር የባሰ ሁኔታ ይፈጠራል:: ኢትዮጵያ ከዚህ የትስስር መረብ ራሷን ለማውጣትና የዳር ተመልካች ለመሆን ብትፈልግ ከትስስሩ ልታገኝ የምትችለውን ጥቅም እያጣችም በትስስሩ ምክንያት ከሚፈጠረው ልዩ ልዩ ዓይነት ተፅዕኖ ሙሉ በሙሉ ነፃ ለመሆን አይቻላትም:: በመጀመሪያ ደረጃ ግሎባላይዜሽን (አለምአቀፋዊ የትስስር መረብ) ኢትዮጵያን ጨምሮ ማንኛውም ሀገር ፈልጎ ያመጣው ነገር አይደለም:: የተለያዩ ታሪካዊና ነባራዊ ምክንያቶች ውጤት እንደመሆኑ አንድ ሀገር ስለፈለገው ብቻ የተከሰተ፣ ሌላ ሀገር ስለጠላው ብቻ ወደጎን እየገፋው በሌላ አቋራጭ ሊጓዝ የሚችልበት ክስተት አይደለም:: በሁለተኛ ደረጃ ይኸንን በተራቀቀ የመገናኛ ቴክኖዎሎጂ ማዕበል የሚታገዝ አለምአቀፋዊ የትስስር መረብ ኢትዮጵያን ጨምሮ ማንኛውም ሀገር ሊገታው ወይንም ሊያስቀረው የሚችለው ክስተት አይደለም:: ስለዚህ ፈራ ተባ በማለት ወይንም የጎሪጥ በመመልከት ኢትዮጵያ ልታገኘው የምትችለው ጥቅም ይኖራል ብሎ ለመገመት ያስቸግራል:: በእርግጥ ኢትዮጵያ የምትገኝበት እጅግ አሳዛኝ የድህነት ደረጃ በዚህ ዓለም አቀፍ የትስስር መረብ ውስጥ ገብታ ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን ያላትን አቅም ውስን እንደሚያደርገው የታወቀ ነው:: ይሁን እንጂ ራሷን በማግለልና እጇን አጣጥፋ በመቀመጥ የምትገነባው አቅምና የምታሻሽለው የእድገት ደረጃ ስለማይኖር ድህነቷና አቅሟን የተገነዘበ የልማት ስትራቴጂ አውጥታ፣ መወዳደር የምትችልባቸውን መስኮች በጥንቃቄ መርጣና የወደፊት እድገት ተስፋዋን ከግምት ውስጥ አስገብታ በትስስሩ ውስጥ ለመሳተፍ መሞከር ይኖርባታል::

በዚህ አለምአቀፋዊ ትስስር በጎ ገጽታዎች ሁሉ በመጠቀም የመረጃ ቴክኒዎሎጂ ደረጃዋን በፍጥነት ለማሻሻል የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ ይገባታል:: የቴክኒዎሎጂ ሽግግር እንዲስፋፋ የሚረዳትን የፖሊሲ አቅጣጫ መከተል ይጠበቅባታል:: ወደውጭ የሚላኩ ምርቶቿን በአይነት፣ በመጠንና በጥራት ለማሻሻል የሚረዳ ስትራቴጂ መከተል ይገባታል:: የኤክስፖርት አቅሟን በማሻሻል ብቻ ሳይሆን የውጭ ምርቶችን የሚተኩ እንቅስቃሴዎችን በማስፋፋት የውጭ ምንዛሬ ግኝቷን ማሳደግ፣ የተገኘውን የውጭ ምንዛሬ በቁጠባና ለዘላቂ እድገት መሰረት በሚሆን ልማት በሚውልበት አግባብ መጠቀም ይኖርበታል::

የዘመኑ የመረጃ ቴክኒዎሎጂ የፈጠረውን ቀልጣፋ የግንኙነት ስርዓት በብቃት ስራ ላይ በማዋል ያላትን ውስን ሪሶርስ በቁጠባና በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል አቅጣጫ መከተል ይገባታል:: ይህ ዓለም አቀፍ የትስስር መረብ የዜጎችን ትምህርት፣ ጤና፣ ድህነትና የኑሮ ድቀት ለማሻሻል በሚያስችል መንገድ ሀገሪቱን እንዲጠቅማት ከተፈለገ ግርር ያለ የፖሊሲ አቅጣጫ በመከተል ፋንታ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን በፍጥነት ለመገንዘብና ከዚህ ጋር የሚጣጣሙ ማስተካከያዎችን ለማድረግ የሚያስችል አካሄድ መኖር አለበት:: በአለምአቀፋዊው የትስስር መረብ ውስጥ ገብቶ ለመወዳደር እንቅፋት የሚሆኑ ፖሊሲዎችንና አሰራሮችን በተገቢ ጥናትና ትኩረት ላይ ተመስርቶ በወቅቱ ማሻሻል፣ ማስተካከልና በአዳዲስ ፖሊሲዎች መተካት ይጠይቃል:: በዚህ የመውደቅና የመነሳት ትግል ውስጥ ገብተው ስኬታማ ለመሆን የሚችሉ ሀገራዊ ባለሀብቶች እንዲበራከቱና እንዲጠናከሩ የቴክኒክ፣ የምክር፣ የፋይናንስ፣ የፖሊሲ ጥበቃና ሌሎችንም የማበረታቻ ድጋፎች ሁሉ በተገቢው ጊዜና ሁኔታ የሚያሟላ አመራር ያስፈልጋል:: በኃላፊነትና ተጠያቂነት መንፈስ የሚሰራ፣ በሕዝብ ፍላጎትና ፈቃድ የተመረጠ ዴሞራሲያዊ መንግስት ያስፈልጋል:: ከሙስኝነትና ፍትህ አልባነት የፀዳ መልካም አስተዳደር ይጠይቃል:: ቀልጣፋና ፍትሃዊ የሲቪል ሰርቪስ፣ የቢሮክራሲና የዳኝነት ስርዓት ይጠይቃል:: በአጠቃላይ ለዜጎች መብትና ለሀገሪቱ ብሔራዊ ጥቅም በጽናት የሚቆም፣ የእድገት ራዕይና ቁርጠኛ የልማት ዝግጁነት ያለው ዴክራሲያዊ መንግስት በመፍጠር ለዘላቂ እድገት መሰረት የሚሆን ሰላምና መረጋጋት በመላ ሀገሪቱ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት እንዲኖር የሚያስችል ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መፍጠር በአለም አቀፉ ትስስር ውስጥ ኢትዮጵያ ብቁ ተወዳዳሪ እንድትሆን ስለሚረዳ ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገር እንድትኖርም መሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ ነው::

አለመታደል ሆኖ በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ በዚህ ሁኔታ ላይ አይደለችም:: የዴሞክራሲ ስርዓት ለመገንባት ባለመቻሏ በአለም አቀፉ የትስስር መረብ ውስጥ ገብታ ለመወዳደር ቀርቶ የውስጥ አንድነቷን የሚስተሳስሩ መረቦች እንኳ እንዳይበጣጠሱ መጠበቅ ተስኗታል:: በውስጥ የጎሳ

መሳሳብ እንድትወጠር በሚያደርግ አገዛዝ ስር በመውደቋ በአለምአቀፋዊው የትስስር መረብ ውስጥ ገብታ ለመወዳደር የሚያስችላትን የሰው ኃይል፣ ጊዜ፣ ፋይናንስና ጉልበት እንድታባክን ተገዳለች። በዚህ የተባበረ ጠንካራ ርብርብ በሚጠይቅ አለም አቀፍ ውድድር ውስጥ ገብታ ትርጉም ያለው ውጤት ማምጣት ቀርቶ ዜጎች የእለት ምግባቸውን የሚያሟሉበት ምቹ ሁኔታ በመጥፋቱ በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ሰብዓዊ እርዳታ ስር ከወደቀች በርካታ አስርት ዓመታት እየተቆጠሩ ነው። በአሁኑ አለምአቀፋዊ የትስስር መረብ ውስጥ ገብቶ ለመወዳደር ደግሞ እየተባባሰ በሚሄድ ፍጹም ድህነት ውስጥ ወድቆና ጥቅም በሌለው የጎሳ ፖለቲካ ተወጥሮ የሚሳካ ነገር አይደለም። የተሻለ አቅም ገንብቶና የተባበረ አቋም ይዞም በቀላሉ የማይወጡት ፈተና ነው። ስለዚህ በአሁኑ ዓለምአቀፋዊ የትስስር መረብ ውስጥ ተወዳዳሪ ለመሆን ኢትዮጵያ በቅድሚያ የሚያስፈልጋት ለዚህ የሚመጥን ዴሞክራሲያዊ ሰርዓት መፍጠር ነው።

# 5. የኢትዮጵያ የወቅቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ገጽታ

ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ያለችበት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታ በታወቁት አለም አቀፍ የእድገት መመዘኛዎች ሲታይ በሁሉም መስክ እጅግ አስከፊ በሆነ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ለዚህ ሁኔታ መፈጠር እንደ ምክንያት ሊቀርቡ የሚችሉ በርካታ የውስጥና የውጭ ምክንያቶች ቢኖሩም ዋነኞቹ ግን አንደኛ ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት አመቺ የሆነ የዴሞክራሲ ስርዓትና መልካም አስተዳደር በሀገሪቱ ውስጥ አለመፈጠሩ፣ ሁለተኛ ደግሞ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ እየተባባሰ የመጣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ውድቀት ያስከተለው ስር የሰደደ ድህነት ነው። እነዚህንም ዘርዘር አድርገን እንያቸው።

## 5.1 ለልማት የሚመች የዴሞክራሲ ስርዓትና መልካም አስተዳደር መታጣት

ኢትዮጵያ ባለመታደል በዚህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ እንኳ ከጭቆና አገዛዝ ለመገላገል ባለመቻሏ ሌላው የዓለም ክፍል ከደረሰበት ከፍተኛ ስልጣኔ በስተጀርባ እንደተቀመጠች ለመቆየት ተገዳለች። በሀገሪቱ የረጅም ዘመን የመንግስት ታሪክ ውስጥ አንደኛው አገዛዝ በሌላኛው አገዛዝ ሲተካ፣ አንደኛው ጨቋኝ በሌላ ጨቋኝ ሲቀየር ከመኖሩ በስተቀር የዴሞክራሲ ስርዓት ሊፈጠር ባለመቻሉ ሕዝቡ ከድህነት ወደ ድህነት እየተሸጋገረ ከመኖር የተለየ እድል አላገኘም። ኢትዮጵያ ለእድገትና ለልማት የተመቸ የተፈጥሮ ሀብት ቢኖራትም ይኸንን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል የተዘጋጀ መልካም አስተዳደር መፍጠር ስለተሳናት ሳታጣ ያጣች ሆናለች።

ጥሩ የተፈጥሮ ሁኔታ መኖር ብቻውን የረባ ውጤት ሊያስገኝ እንደማይችል ከኢትዮጵያ የተሻለ ምሳሌ የለም። ይኸ ነው የሚባል የተፈጥሮ ሀብት የሌላቸው ነገር ግን ለእድገትና ለልማት መልካም ራዕይና ቁርጠኝነት ያለው መልካም አስተዳደር መፍጠር የቻሉ ሌሎች ሀገሮች ከኢትዮጵያ ኋላ እየተነሱ በሚያስደንቅ ፍጥነት እየቀደሟት ሄደዋል። የኢትዮጵያን ችግር አስከፊ የሚያደርገው ከችግሯ መንጥቆ ሊያወጣ የሚችል የዴሞክራሲ ስርዓት ገና ያልፈጠረች መሆኗ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም አሁን በሀገሪቱ የነገሰው አገዛዝ ከበፊቶቹ ሁሉ የባሰ አፋኝና ከፋፋይ በመሆኑ ነው።

የአሁኑን አገዛዝ ከበፊቶቹ የከፋ ያደረገው የመንግስት ስልጣን በጠመንጃ ኃይል መያዙ ብቻ አይደለም። ይህ ለአሁኑ አገዛዝ ብቻ የተለየ መገለጫ ባህርይ ሊሆን አይችልም። ከዚህ በፊት የነበሩትም አገዛዞች የመጡበትና የሄዱበት መንገድ ነው። የኋላ ታሪኩ ከኮሙኒዝም አመለካከት ጋር የተቆራኘ መሆኑ ብቻም አይደለም። በመላው አለም የኮሙኒዝምን ባንዲራ ሲያውለበልቡ የከረሙ በርካታ ቡድኖችና ተቋሞች ዛሬ አሰላለፋቸውን ቀይረው ቆመዋል። የዚህ አገዛዝ ችግር ከዚህ ለየት ያለ ነው። አንደኛው የችግሩ ገጽታ ካለፈው አቋሙና ባህርይው ጨርሶ ለመላቀቅ በማያስችል የዞረ ድምር (hangover) የታሰረ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛውና ነገር ግን እጅግ አደገኛው ችግር ጫካ ውስጥ ተኮትኩቶ ባደገው አምባገነንነት ላይ መንግስታዊ ሙሰኝነትን ሊደርብ መቻሉ ነው። የአሁኑ አገዛዝ የነፃ ገበያ ስርዓት ደጋፊና አፍቃሪ ካፒታሊዝም

ለመምሰል ቶሎ ብሎ ጭንብል ቢያጠልቅም ለዚህ ስርዓት የሚገዛ ግልጽነትና የአሰራር ዲስፕሊን በተግባር ማሳየት አልቻለም።

በድርጅት ፕሮግራሞቹና በመንግስት የፖሊሲ ሰነዶች ውስጥ ያሰፈራቸው አብዮታዊ ዴክራሲያዊ አቋሞቹ ለነፃ ገበያና ለካፒታሊዝም ስርዓት ግንባታ ባዕድ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ፍፁም ተፃራሪ መሆኑን የሚያመላክቱ ናቸው። ከዚህ ሁኔታ በመነሳት መገመት የሚቻለው አገዛዙ ነፃ ገበያና የካፒታሊዝም ስርዓት ተቀብያለሁ የሚለው ምርጫ በማጣት እንጂ ለሀገር እድገትና ልማት ይጠቅማል ከሚል እምነት አለመሆኑን ነው። በአሁኑ ጊዜ ነጻ ገበያንና ካፒታሊዝምን ከፊት ለፊት እየተጋፈጡ የመንግስት ሥልጣን ይዞ መቆየት እንደማይቻል በመገመትና ከምዕራቡ ዓለም ብድርና እርዳታ ለመለመን ሳይወድ በግድ ያንጠለጠለው መፈክር እንጂ ለልማት የሚያዋጣ መንገድ ነው ከሚል እምነት ተነስቶ በቁርጠኝነት የያዘው አቋም አይደለም። በመሆኑም ካለፈው ኮሚኒስታዊ አመለካከት ጨርሶ የተቆራረጠና ለሌላ አዲስ ራዕይ በሙሉ ልብ የተሰለፈ መሆኑን በእርግጠኝነት ለመረዳት በሚያስቸግር ሁኔታ ራሱን ደብቆ የተቀመጠ አገዛዝ ነው። እንዲህ ዓይነት መንታ አቋም የያዘ አመራር የኢትዮጵያን ችግር ሊፈታ ቀርቶ ራሱንም ከችግር ማውጣቱ አጠራጣሪ ነው።

የአሁኑ አገዛዝ ወደ ስልጣን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ መፈክሮችን ሲያነሳና ሲጥል ቢከርምም የሀገሪቱን ችግር ከማባባስ በስተቀር ያስገኘው መሻሻል የለም። በተለያዩ ጊዚያት የመዋቅር ማሻሻያ፣ የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም፣ የተሃድሶ እርምጃ፣ የድህነት ቅነሳ ወዘተ. የሚሉትን አጀንዳዎች ይዞ ላይ ታች ሲል የከረመውም በውጭ መንግስታትና በአለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ግፊት እንጂ ልማት ለማምጣት ካለው ፍላጎትና ዝግጁነት በመነሳት አልነበረም። እነዚህን አጀንዳዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሙሉ እምነት፣ አደረጃጀትና አሰራር በሌለበት ሁኔታ «ይህንን አድርግ» የሚል ውጫዊ ጫና በተፈጠረ ቁጥር የራሱ ያልሆነ አጀንዳ አንጠልጥሎ በመሮጥ የሚሻሻል መዋቅር፣ የሚታደስ አመራርና የሚቀነስ ድህነት ሊኖር አይችልም። የመዋቅር ማሻሻያም ይሁን የአመራር ተሃድሶ ወይንም የድህነት ቅነሳ እንዲኖር በቅድሚያ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትና መልካም አስተዳደር በቦታው ላይ መገኘት አለባቸው። የአሁኑ አገዛዝ ደግሞ ከዴሞክራሲና ከመልካም አስተዳደር መሰረታዊ መርሆዎች የተነጠለ አገዛዝ ነው። የዚህ አገዛዝ እውነተኛ መገለጫዎች በጠመንጃ ኃይል የተመሰረተ የፖለቲካ ስልጣንና በዚህ ሕገወጥ ስልጣን ላይ የተገነባ ተቋማዊ ሙስና ናቸው።

## 5.2 በኃይል የተመሰረተ የፖለቲካ ስልጣን መኖር

በመጀመሪያ ደረጃ ሕዝቡ ልዩ ልዩ ጥቅሞቹንና መብቶቹን አቻችሎ ለመኖር የሚያስችለውን ሕገመንግስታዊ ስርዓት በነፃነት እንዲመሰርት እድል አልተሰጠውም። አሁን በኃይል የፖለቲካ ስልጣን የወሰደው አገዛዝ እንደመሰለው ጽፎ በግድ በጫነበት የአንድ ፖለቲካ ቡድን ሕገመንግስት ታስሮና ታፍኖ ለመቀመጥ የተገደደ ሕዝብ ነው። አገዛዙ የመንግስት ስልጣን ምንጭና ባለቤት ሕዝብ መሆኑን ለመቀበል የተዘጋጀ አይደለም። በመሆኑም ሕዝቡ የራሱን ተወካዮች መርጦ ዴክራሲያዊ መንግስት ለመመስረት ባለመቻሉ እስካሁን ድረስ በጠመንጃ ኃይል በተመሰረተ አገዛዝ ስር እንደወደቀ ነው። የሕግ የበላይነት ባለመኖሩ ራሱን ከሕግ በላይ ያስቀመጠ አገዛዝ አድራጊና ፈጣሪ ሆኖ ቁጭ ብሏል። አገዛዙ ሁሉን ነገር በጫካ ሕግ ለመምራት ስለወሰነ የሕዝቡን መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚያስችል የሕግና የሞራል ስርዓት በሀገሪቱ የለም። የአገዛዙ ቅሞችና ፍላጎቶች እንዲሟሉ ሲባል ሕግ በመረገጡ ኃይልና ስልጣን በሕግ ቦታ ተተክተዋል። በሀገሪቱ ውስጥ ፍትህና ዳኝነት በሕግ ላይ ሳይሆን በኃይልና በስልጣን ላይ እንዲመሰረቱ ተደርገዋል። የፍትህና የዳኝነት ስርዓቱ በኃይል ለተመሰረተ ስልጣን መሣሪያ እንዲሆኑ ስለተፈለገ የፍትህና የዳኝነት መዋቅሩ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ መርህ እንዲዋቀሩና እንዲሰሩ ተደርገዋል።

በዚህ መዋቅር ውስጥ የሚመደቡት ደግሞ የአገዛዙ ካድሬዎች እንዲሆኑ ተደርጓል። የገዥው ፓርቲ አባላት በዳኝነት፣ በዓቃቤ ሕግ፣ በፖሊስና በደህንነት መዋቅር ውስጥ ገብተው በፍትህና በዳኝነት ስም የፖለቲካ ውሳኔ እየሰጡ የሕግን የበላይነት ከመሰረቱ ነቅለው እንዲጥሉት እየተደረገ ነው። የገዥው ፓርቲ አባላት ያልሆኑ ዳኞች አቃቤ ሕጎችና ፖሊሶች የፈለገውን

ያክል የሕግ እውቀትና ልምድ ቢኖቸውም አገዛዙ ጥቅሜንና ፍላጎቴን አይጠብቁም ብሎ ስላመነ በሰበብ አስባቡ ከፍትህና ከዳኝነት ስራ እንዲወጡ አርጓቸዋል፡፡ የሚሰጡትን ዳኝነት፣ በአደባባይ ከማውገዝ አልፎ ያለፈው ስርዓት ቅሪቶች፣ ኢሠፓ፣ ሌቦች ወዘተ. የሚል ስም እየተሰጣቸው ይባረራሉ፡፡ የሚገርመው ግን አገዛዙ በፖለቲካ ምክንያት በሚያባርራቸው ዳኞች፣ ዓቃቤ ሕጎችና ፖሊሶች ምትክ የሚመድባቸው የራሱን ፓርቲ አባላት መሆኑ ነው፡፡

በእዚህ መንገድ ነፃ ዳኝነትና የሕግ የበላይነት በሀገሪቱ ውስጥ እንዳይኖር በመደረጉ በመንግስት ወይም በአንድ የመንግስት ባለስልጣን ላይ መብቴ ተደፈረ ብሎ ማንም ዜጋ አቤቱታ የሚያቀርብበትና ፍትህ የሚያገኝበት እድል የተዘጋ ነው፡፡

በአሁኑ አገዛዝ የፍትህና የዳኝነት ሥርዓቱ በአስፈፃሚው ቀጥተኛ ተፅዕኖና ቁጥጥር ስር የወደቀ በመሆኑ ዜጎች በነፃነት እየሰሩ ለመኖር አንድም ሕጋዊ መተማመኛ የላቸውም፡፡ የመንግስት አስፈፃሚው አካል የፈለገውን አዋጅ ማውጣትና ያልፈለገውን ደግሞ መጣል ይችላል፡፡ አዲስ የፀረ ሙስና አዋጅ ባወጣ ማግስት የዜጎችን የዋስትና መብት እንዲከለክል አድርጎ ያሻሻለበትን አሰራር በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ዜጎች ካለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ቤታቸውንና ንብረታቸውን እንዳይነጠቁ የተደነገገውን የሕግ ስርዓት በማፍረስ የገቢዎች ሚኒስቴርና ባንኮች የዜጎችን ንብረት እንዲወርሱና በሀራጅ እንዲሸጡ አዋጅ ያወጣበትን ሁኔታ ማየት ይቻላል፡፡ ዜጎች ሀሳባቸውን በነፃነት ለመግለጽና ማወቅ የሚፈልጉትን መረጃ ለማወቅ ያላቸውን መብት የሚቀማ ከሴንሰር ሸፐ ጋር የሚመሳሰል ስልጣን ለማስታወቂያ ሚኒስቴር የሚሰጥ አዋጅ ያወጣበትን ሁኔታ ማየት ይቻላል፡፡ እነዚህ አዋጆች ለስሙ በፓርላማ የፀደቁ ናቸው ይባላል እንጂ ፓርላማው ራሱ በአስፈፃሚው ቁጥጥርና ተፅዕኖ ስር እንዲወድቅ ሆኖ የተቋቋመ ስለሆነ አስፈፃሚው አካል የሚፈፅመውን ሕገወጥ ተግባር ለመከላከልና ለማስወገድ የሚያስችል አቅም የለውም፡፡

በአሁኑ አገዛዝ በነፃነት መደራጀት አይቻልም፡፡ ነፃ ድርጅት ለመመስረት የሞከሩ ዜጎች የገጠማቸው ሁኔታ አሳዛኝ ነው፡፡ ነፃ ሆነው የተደራጁ ወገኖች ለሞት፣ ለእስራት፣ ለግርፋት፣ ከስራና ከመኖሪያ ቤታቸው ለመባረር፣ ለስደት፣ ለአፈናና ለመሳሰሉት አደጋዎች የተጋለጡ ናቸው፡፡ አንድ ነፃ ድርጅት ከተመሰረተ ወዲያውኑ አገዛዙ ሌላ የራሱን ተለጣፊ ድርጅት ከጎን አቋቁሞ ማተራመሱን ይቀጥላል፡፡ በፓርቲ ላይ ፓርቲ፣ በማህበር ላይ ማህበር እየመሰረተ ነገሮችን ሁሉ ለማቆላለፍ ከመሞከር በስተቀር ገንቢ የሆነ አመለካከት እንኳ የለውም፡፡ በመምህራን ማህበር ላይ የራሱን መምህራን ማህበር፣ በሰራተኛ ማህበር ላይ የራሱን ሰራተኛ ማህበር፣ በጋዜጠኞች ማህበር ላይ የራሱን የጋዜጠኞች ማህበር ወዘተ. እየፈጠረ የሕዝቡን በነፃነት የመደራጀት መብት ሲቀማና እርስ በርስ የሚናከሱ ተፎካካሪ ማህበራትን ሲያበዛ ማየት የተለመደ ነው፡፡

ሀሳብን በነፃ መግለጽና ሰላማዊ ተቃውሞ ማድረግ በአሁኑ አገዛዝ ዘመን ያስገድላል፣ ያሳስራል፣ ለከባድ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር ያጋልጣል፡፡ ሀሳባቸውን በግል ጋዜጦችና መጽሔቶች የገለጹ ዜጎች ያጋጠማቸውን መከራ በማየት የችግሩን ስፋት መረዳት ይቻላል፡፡ ሰላማዊ ተቃውሞ ያሰሙ ተማሪዎች፣ ገበሬዎች፣ ነጋዴዎች፣ የከተማ ነዋሪዎች፣ ማህበራትና የፖለቲካ ድርጅቶች ላይ በተለያዩ ጊዜያት የተፈፀሙትን ግድያዎችና ጨካኝ እርምጃዎች በማየት የሁኔታውን አደገኛነት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በማንኛውም የሕዝቡን ጥቅም በሚመለከት የፖሊሲ ጉዳይ ላይ ሕዝቡ አስተያየት እንዲሰጥና የውሳኔ ሀሳብ በማፍለቅ ነፃ ተሳትፎ እንዲያደርግ መብት አልተሰጠውም፡፡ ገዥው ፓርቲ በራሱ መንገድ ፖሊሲ አውጥቶና መርሃ ግብር ቀርፆ ከጨረሰ በኋላ ለይስሙላ የሚካሄዱ ስብሰባዎችን ከማዘጋጀት በስተቀር በሕዝቡ ሀሳብና ፍላጎት ላይ ተመስርቶ የሚቀረፅ ፖሊሲና መርሃ ግብር የለም፡፡

አገዛዙ በሕዝብ የተመረጠ ባለመሆኑ የአሰራር ግልፅነት፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት የሌለበት አገዛዝ ነው፡፡ የፈለገውን ሕገወጥ ስራ ቢሰራ የሚጠይቀው፣ የሚቆጣጠረውና ከጥፋቱ እንዲመለስ የሚያደርገው ኃይል የለም፡፡ እያንዳንዱ ባለሥልጣን ለሾመው ሌላ ባለስልጣን ታማኝ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ በሕግ እጠየቃለሁ፣ በሕዝብ እወቀሳለሁ ብሎ የሚሰጋበት ሁኔታ የለም፡፡ አገዛዙን የሚጎዳ ነገር እስካልፈፀመ ድረስ ማንም ባለስልጣን ሕግ ጥሰሃል፣ የሰው መብት ደፍረሃል ተብሎ የሚከሰስበት አሰራር የለም፡፡ ምንአልባት አንድ ባለስልጣን የሚወቀሰው አገዛዙን የሚጎዳ ነገር ፈጽሚል ከተባለ ብቻ ነው፡፡ እሱም የሕግን አግባብ ተከትሎ በፍርድ ቤት

የሚፈፀም ሳይሆን ድርጅታዊ ስብሰባ በሚባለው ዝግ ችሎትና ግምገማ በሚባለው አፍርሣታ ነው፡፡ በእነዚህ መድረኮች ሂሱን የተቀበለ ባለሥልጣን በጥፋቱ እንደተቀጣና እንደታደሰ ስለሚቆጠር ተመልሶ እዛው ስልጣኑ ላይ ይቀመጣል፡፡ በአንድ ባለሥልጣን ላይ የሚወሰደው ከባድ ቅጣት በግምገማ (በአፈርሳታ) መውቀስና ግለሂስ እንዲያካሂድ ማድረግ በመሆኑ የአሁኑ አገዛዝ ካድሬዎች ወንጀል እየፈፀሙ ግለሂስ ማድረግን እንደዋነኛ ስራ አድርገው ይጠቀሙበታል፡፡ መታሰር፣ ከስራ መባረርና መከሰስ የሚመጣው ሕግን በመጣስና የሰውን መብት በመድፈር ሳይሆን ከፖለቲካ ስልጣን ፉክክር ጋር በተያያዘ ሁኔታ ብቻ ነው፡፡ የሀገር ሀብት በመዝረፍና የዜጎችን መብት የሚጎዳ ወንጀል በመስራት ቢሆንማ ኖሮ በአሁኑ አገዛዝ ውስጥ ከዚህ ዓይነቱ ጥፋት ነጻ የሚሆን ሰው ማግኘት ስለማይቻል ከሳሽና ተከሳሽን ለመለየት ባልተቻለ ነበር፡፡

ስለዚህ በሕዝብ ነፃ ፍላጎትና ነፃ ውሳኔ ላይ የተመሰረተ ሕገመንግስታዊ ስርዓት፣ ነፃ ምርጫ፣ ነፃ ዳኝነት፣ የመደራጀት ነፃነት፣ ሀሳብና ተቃውሞን የመግለፅ ነፃነት፣ የአሰራር ግልፅነት፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት በሌለበት አገዛዝ ስር ዜጎች ለልማት የሚሰለፉበት ሁኔታ ቀርቶ በሕይወት ለመኖር እንኳ ምንም ዓይነት የሕግ መተማመኛና ዋስትና የላቸውም፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነው እውቀታቸውን፣ ጉልበታቸውንና ሀብታቸውን ለልማት እንዲያውሉ የሚደፋፈሩበት መንገድ የለም፡፡ በሕይወት ለመኖር እንኳ ነፃነት የሚሰጥ ስርዓት በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ሆነው በስጋትና በተስፋ ቢስነት ከተከበቡ ዜጎች የልማት ተነሳሽነት ይኖራል ማለት የማይቻል ነው፡፡ የሕግ የበላይነት በጠፋበትና የጠመንጃ ኃይል ራሱ ሕግ በሆነበት አገዛዝ ስር ሆኖ ልማት መፍጠር ይቅርና ልማትን ማሰብ እንኳ ከባድ ነው፡፡

## 5.3 ሕገወጥ ሥልጣን የወለደው ተቋማዊ ሙስና መስፈን

በሁለተኛ ደረጃ መጠቀስ ያለበትና የአሁኑ አገዛዝ ከዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር የተነጠለ መሆኑ የሚረጋገጥበት ሁኔታ በሀገሪቱ ውስጥ የነገሰው ሙስና ነው፡፡ የአሁኑ አገዛዝ የቦናፓርቲዝም ባህሪያትን የተላበሰ አገዛዝ ነው ሲባል ዝም ብሎ ተቀፅላ ስም ለመስጠት በመፈለግ የሚባል ጉዳይ አይደለም፡፡ በተጨባጭ ማስረጃዎችና በትክክለኛ ምዘናዎች ላይ ተመስርቶ የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡ ቦናፓርቲዝም ስሙ ከውጭ ሀገር ቋንቋና የአገዛዝ ስርዓት የተቀዳ ቢሆንም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እራሳቸውን ከደሙ ንፁህ አድርገው አጣመው ሊጠቀሙበት ከሞከሩበት በተለየ ሁኔታ ቦናፓረቲዝም አሁን ኢትዮጵያን ለሚገዛው መንግስት ባህርይ መገለጫ ተደርጎ ቢወሰድ አያስኬድም የሚባል አይደለም፡፡ ቦናፓርቲዝም እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1850ዎቹ መጀመሪያ ወደ ስልጣን ከመጣውና የናፖሊዮን ቤተሰብ ከሆነው ከሉዊ ቦናፓርቲ አገዛዝ በመነሳት የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡ ይኸንን ስያሜ አጉልቶ ያወጣው ካርል ማርክስ «18ኛው ብሩ ሚየር» በሚል እ.ኤ.አ በ1872 በፃፈው መጽሐፍ ውስጥ ስለሉዊ ቦናፓርቲ አገዛዝ ባህርይ ባቀረበው ግምገማ ቢሆንም ይኸንን አስተያየትና ስያሜ የሚሰሩ ሌሎች ወገኖችም በተለያየ ጊዜ ተጠቅመውበታል፡፡ የስያሜው መነሻ አገዛዙ በወቅቱ በፈረንሳይ ተጨባጭ ሁኔታ ያሳየው ባህርይ ሲሆን ጉዳዩን በአጭሩ አብራርቶ ማለፍ በኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ስልጣን የያዘው አገዛዝ አንድ ዋነኛ ባህሪይ ተቋማዊ ሙስና ነው የሚለውን ግምገማ ትክክለኛነት ለማገናዘብ ይረዳል፡፡

ሉዊ ቦናፓርቲ ወደ ሥልጣን በመጣበት ጊዜ በፈረንሳይ የቡርዧ አብዮት ትልቅ ለውጥ ያሳየበትና ከመሬት ባለቤትነት ጋር የተያያዘው የመሬት ከበርቴና የጭሰኛ ግንኙነት እየተሰባበረ የመጣበት ወቅት ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ በፈረንሳይ ውስጥ በአንድ በኩል ታዳጊ ካፒታሊስትና ታዳጊ ሰራተኛ የሕብረተሰብ ክፍል መፈጠሩ በግልፅ የታየበትና በሌላ በኩል ደግሞ ገበሬው ከመሬት ባለቤቶች ተፅዕኖ ስር እየወጣ የመጣበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን በወቅቱ የሕዝብን ጥያቄ የሚደግፍ በመምሰል የመንግስት ስልጣን የያዘው የሉዊ ቦናፓርቲ አገዛዝ በፈረንሳይ ቡርዧ አብዮት አስተዋፅኦ የነበረውን ታዳጊ ካፒታሊስትና ከመሬት ባለቤቶች ጭቆና በመላቀቅ ላይ የነበረውን ገበሬ ሕብረተሰብ ጥቅም እንደሚያስጠብቅ እየማለና እየተገዘተ ሥልጣኑን ማጠናከር ያዘ፡፡ ገበሬው መሬቱን እያረሰ በነፃነት ለመኖር የተገባለትን ተስፋ በማመን በሉዊ ቦናፓርቲ አገዛዝ ላይ ተፅዕኖ ማድረጉን ሲተወው ታዳጊ ካፒታሊስቱም ገና የተጠናከረ አቅም ባለመገንባቱ ለጊዜው ከሉዊ ቦናፓርቲ በኩል የተሰጠውን የተወሰነ ድጋፍ

በፀጋ እየተቀበለ ካፒታሊዝምን በጠንካራ መሰረት ላይ ለማቆም ከመሞከር በስተቀር የቦናፓርቲን መንግስት አታስፈልገኝምና ዘወር በል ለማለት የሚችልበት ሁኔታ አልነበረም። ከካፒታሊስቱ የሕብረተሰብ ክፍልም በአደረጃጀትም ሆነ በቅንጅት ገና በቂ አቅም ያልፈጠረ በመሆኑ በቦናፓርቲ አገዛዝ ላይ ተከታታይና ጠንካራ ጥያቄዎችን እያነሳ ለማስጨነቅ በሚያስችል ደረጃ ላይ አልነበረም። በዚህ አብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል በቦናፓርቲ አገዛዝ ላይ ጠንካራ ተፅዕኖ ለማሳረፍ የሚያስችል ከፍተኛ አቅም ባልገነባበት ጊዜ የቦናፓርቲ አገዛዝ ጥያቄ የሌለበት፣ ከሕግና ከሕዝብ ቁጥጥር ውጭ የሆነ ነጣቂ ስርዓት በመሆን ስልጣኑን አደላድሎ ቁጭ አለ። ከገበሬው፣ ከታዳጊ ካፒታሊስቱ፣ ከሰራተኛውና ከጠቅላላው ሕዝብ ከፍተኛ መጠን ያለው ታክስና ግብር መሰብሰብ ያዘ። ከታክስና ከሌላም ምንጭ የሚገኘውን የመንግስት ገንዘብ ሉዊ ቦናፓርቲና ቤተሰቡ ወደግል ካዝናቸው አዞሩት።

በስልጣናቸው ከተለያየ አቅጣጫ እየነጠቁ በሚሰበስቡት ገንዘብና ንብረት አማካይነት የማምረቻና የአገልግሎት መስጫ ከፍቶ እየነገደና የካፒታል ክምችት እየፈጠረ ለማደግ ከሚሞክረው ታዳጊ ካፒታሊስትም የበለጠ ሀብት ማካበት ቻሉ። ስልጣንን የሀብት ማግኛ አድርገው ተጠቀሙበት። የቦናፓርቲና ቤተሰቡ የሀብት ማፍሪያ ፋብሪካዎች ከማንም ተፅዕኖ ውጭ በሆነ መንገድ በሞኖፖል የያዙት ስልጣን ሆነ። ከላይ እስከታች የተዘረጋና በራሳቸው ቁጥጥር ስር የወደቀ ቢሮክራሲ አቋቁመው ይኸንኑ የነጠቃ ስራ በሚገባ እንዲፈፅም ተልዕኮ ሰጡት። የፍትህና የዳኝነት ስርዓቱንም ለዚህ ዓላማቸው በሚያገለግል መንገድ አዋቀሩት። የፖለቲካ ስልጣን፣ ሀብትና ፍትህ በቦናፓርቲ መዳፍ ስር ተጠቃለው ገቡ። የፍትህና ዳኝነት መሰረቱ ስልጣን ሆነ። የቦናፓርቲ የሞኖፖል ስልጣን የሀብት ምንጭና የሕግ መሰረት በመሆኑ ቦናፓርቲ ማለት ራሱ ሀብትና ሕግ ማለት ሆኖ ቁጭ አለ። ቦናፓርቲን የሚጠይቅ፣ የሚወቅስና የሚከስ ወንጀለኛ ተባለ። የቦናፓርቲ ስልጣን ሕግ ሆነ ሕግም ቦናፓርቲ ሆነ። ሉዊ ቦናፓርቲ የሕዝቡን ስልጣን፣ ሀብትና መብት ነጥቆ በእጁ በማስገባቱ የእሱ ስርዓት ቦናፓርቲዝም ከመባል በስተቀር ሌላ ስም የሚወጣለት አልነበረም። በዚያ ዘመን በፈረንሳይ የነገሰውን የነጠቃ አገዛዝ በራሱ በነጣቂው ስም ከመጥራትና ቦናፓርቲዝም ከማለት ሌላ የተሻለ መጠሪያ መስጠትና የሁኔታውን ሀቀኛ ባህርይ መግለፅ እንደማይቻል በመገመት ብዙዎች ይኸንን ስያሜ ሲጠቀሙበት ቆይተዋል።

በኢትዮጵያ አሁን ሥልጣን ላይ ያለው አገዛዝ ጠያቂ የሌለበት፣ ሁሉንም ነገር በሞኖፖል ጠቅልሎ የያዘና ተቋማዊ ሙስናን የገነባ በመሆኑ ከቦናፓርቲዝም ጋር የሚመሳሰሉት በርካታ ባህርያት ያሉት ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ አሁን በሥልጣን ላይ ያለው አገዛዝ ራሱን ከሕግ በላይ ያስቀመጠ በመሆኑ በሕግና በህዝብ የሚጠየቅበትና መንገድ መዘጋቱ ቀደም ሲል በሚገባ የተገለፀ ስለሆነ መድገም አያስፈልግም። ከዚህ ይልቅ በሀገሪቱ የነገሰው ሕገወጥ አገዛዝ የፈጠረውን ተቋማዊ ሙስና (Institutional corruption) ዋና ዋና መገለጫዎች በማየት ያለውን እውነታ በአግባቡ ለመረዳት መሞከር የተሻለ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ ያለው ሙስና በድብቅ የሚካሄድና በግለሰቦች የሚፈፀም ተራ ሌብነት ተደርጎ የሚታይ ቀላል ነገር አይደለም። አሁን ያለው ሙስና የፖለቲካ ድጋፍ ያለውና በይፋ የሚካሄድ የተደራጀ ዘረፋ ነው። ሀገሪቱ ውስጥ የነገሰው የፖለቲካ ስልጣን አወቃቀርና አሰራር ይኸንን በይፋ የሚያስፈፅም ሙስናን ማስፋፋት በሚያስችል አቅጣጫ የተቃኘ ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ የአገዛዙ መርህ ስልጣንን ጠብቆ ለመቆየት በሁሉም ዘርፍ የድርጅትን ጥቅም ማስቀደምና የበላይነትን መያዝ ይገባል በሚል አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ነው። በመሳሪያ ኃይል የተገኘውን የፖለቲካ ስልጣን የበላይነት እንደገና በኢኮኖሚ መስክ በሚገኝ የበላይነት መደገፍ ይገባል የሚል ነው። ሕግና ስርዓትን ጠብቆ ስልጣን በማግኘትና ሀብት በማፍራት በሁሉም መስክ የበላይነት ለማግኘት የሚደረግ ቢሆን ኖሮ ባልከፋ ነበር። ችግሩ በሁሉም መስክ የበላይነትን ለማረጋገጥ ሲባል በሀገርና ሕዝብ ኪሳራ እያተረፉና ሕገወጥ በሆነ የኃይልና የነጠቃ አሰራር እየተመሩ የሚፈፀም ከመሆኑ ላይ ነው። የአሁኑ አገዛዝ ሀገር ስትለማ አብሮ የመልማት ሀሳብ የለውም። ከሀገር በፊት አገዛዙ ራሱን በቅድሚያ ማልማት ይፈልጋል። ሀገር እንድትለማ ሁሉም በሚችለው መስክ ተሰልፎ የሚሰራበትን እድል መፍጠር አይፈልግም። አገዛዙ

የሚፈልገው አንድም ተፎካካሪ በሌለበት ሜዳ ብቻውን መጋለብ ነው፡፡ በልማት ተሳትፎ ለማድረግ የሚፈልጉትን የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች እንደ ጠላት የሚመለከታቸውና በማያላውስ የፖሊሲ መሰናክል እየጠለፈ የሚጥላቸው በዚህ የተነሳ ነው፡፡

አገዛዙ የሀገሪቱን ሲቪል ሰርቪስ እንዴት አድርጎ እንዳዋቀረውና እንደሚመራው በማየት የመንግስት ድጋፍ ያለው ተቋማዊ ሙስና የተገነባ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ በየደረጃው ባሉት የሲቪል ሰርቪሱ መዋቅሮች የሚገኙትን ቁልፍ የሀላፊነት ቦታዎች በሹመት በሚመድባቸው ካድሬዎች አገዛዙ ከላይ እስከታች በቁጥጥሩ ስር አድርጓቸዋል፡፡

ማንም ዜጋ በየትኛውም የሲቪል ሰርቪስ መዋቅር ውስጥ ጉቦ ሳይሰጥ ጉዳይ ለማስፈፀም የማይቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ጉቦ መክፈል ግዴታ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ጉቦ የሚጠይቁት ከታች እስከላይ የሚገኙት ልዩ ልዩ የስራ ክፍሎች መሆናቸውና የሚጠይቁትም መጠን ከፍተኛ መሆኑ ነገሩን ሁሉ የበለጠ አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ ከሕዝብ በሚሰበሰብ ግብርና ታክስ የሚተዳደር የሲቪል ሰርቪስ ተቋምና ሰራተኛ ካለጉቦ አገልገሎት የማይሰጥበት ሁኔታ መፈጠሩን የኢትዮጵያ መንግስት ቀርቶ ከውጭ የሚመጡ ባለሀብቶችና አበዳሪ መንግስታት ሁሉ የሚያውቁት ቢሆንም አገዛዙ አምኖበት የፈጠረው ነገር ስለሆነ ሊስተካከል አልቻለም፡፡ በሲቪል ሰርቪሲ የተሰገሰገው የአንድ ፓርቲ ሠራዊት ከተገልጋዩ በሚቀበለው ጉቦ ብቻ የሚጠግብ ባለመሆኑ የመንግስትን ንብረትና ገንዘብ በተለያየ መንገድ እየመዘበረ ይጠቀማል፡፡

እገዛዙ ሙስናን እንዴት እንዳስፋፋ ለመረዳት የሚቻልበት ሌላው መንገድ ፕራይቬታይዜሽን የሚለው ፕሮግራም ነው፡፡ በቀድሞው መንግስት ባለቤትነት ስር የነበሩ የልማት ድርጅቶችን ወደግል ለማዛወር በተጀመረው ፕሮግራም አማካይነት ግልፅ ሙስና እንደሚፈፀም የታወቀ ነው፡፡ መንግስት በአዋጅ ስልጣን የተሰጠው የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እቋቋምኩ ካለ በኋላ የዚህን ኤጀንሲና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የሚባለውን ተቋም በራሱ ካድሬዎች ሙሉ ኃላፊነት ቁጥጥር ስር እንዲመሩ አድርጎ አዋቅሯቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የገዥው ፓርቲ ካደሬዎች ከዚህ ፓርቲ ጋር በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ትስስር ያላቸው ሰዎች የተጠና የስራ ክፍፍል አድርገው ከፊሎቹ የጨረታ አባል በመሆን ሽያጬን እንዲያካሂዱ፣ ከፊሎቹ ደግሞ ተጫራቾች ሆነው እየተመዘገቡ ግዥ እንዲፈፅሙ እየተደረገ ወደግል ንብረትነት ተዛወሩ ከተባሉት የመንግስት ንብረቶች ውስጥ ሼክ መሀመድ አላህሙዲን፣ ቢጂአይ ኢትዮጵያና ሌሎች ጥቂት የውጭና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ከገዟቸው በስተቀር ሌሎቹ በአብዛኛው ከገዥው ፓርቲ አባላት፣ የትግል አጋሮችና ዘመድ አዝማዶች በአነስተኛ ዋጋ የተዛወሩ በመሆናቸው በስጦታ እንደተሰጡ የሚቆጠሩ እንጂ እንደተሸጡ ተደርገው የሚታዩ አይደሉም፡፡

በዚህ አገዛዝ የተመሰረተውን ተቋማዊ ሙስና ለማየት የሚያስችለው ሌላ ነጥብ ስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ የራሱ የንግድ ኩባንያዎች ሕገወጥ በሆነ መንገድ የከፈተበት ሁኔታ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሀገሪቱ ካላት አጠቃላይ ሀብትና ንብረት የሚበልጥ ካፒታል ያለው ትልቅ ባለሀብት ስልጣን በኃይል የያዘው ገዥ ፓርቲ ነው፡፡ በእርግጥ ገዥው ፓርቲ የፖለቲካ ስልጣንና የፓርቲ ንግድ ስራን አንድ ላይ ይዞ በጣምራነት እያካሄደ በመሆኑ የሀገሪቱ ድርሻ የትኛው እንደሆነና የገዥው ፓርቲ ደግሞ የትኛው እንደሆነ ለመለየት የማይቻልበት ሁኔታ መፈጠሩን መካድ አይቻልም፡፡ ዋናው ነገር ከመንግስት ስልጣኑ በተጨማሪ ፓርቲው በከፍተኛ የካፒታል መጠን በይፋ የሚያንቀሳቅሰው የራሱ ንግድ ስራም ያለው መሆኑ ነው፡፡ የገዥው ፓርቲ ንብረት ናቸው በሚባሉት ኩባንያዎች ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉት ነጥቦች ብዙ ቢሆኑም በዚህ ጽሑፍ ለማየት የሚሞከረው ዋና ዋና የሚባሉትን ብቻ ነው፡፡

የመጀመሪያው ነጥብ የኩባንያዎቹ መነሻ ካፒታል የተገኘበት ምንጭ ነው፡፡ ለእነዚህ ኩባንያዎች መነሻ የሆነው ካፒታል በዋናነት የተገኘው አሁን የመንግስት ስልጣን የጨበጠው አገዛዝ አማፂ በነበረበት ጊዜ ከመንግስት፣ ከሕዝባዊ ማህበራት፣ ከአገልገሎት አምራቾች የህብረት ሥራ ማህበራት፣ ከከነማ ሱቆች፣ ከግለሰቦች፣ ወዘተ. በኃይል ከተወሰደ ገንዘብና ንብረት ነው፡፡ በትግራይ ሕዝብ ስም ከተገኘ የውጭ እርዳታም የተሰበሰበና የድርጅቱ ንብረት የሆነ እንዳለ ይታወቃል፡፡ ድርጅቱ ከአባላት፣ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ደጋፊዎቹ ያገኘው ገንዘብና ንብረት ብቻ ከጦርነት ማካሄጃ ተርፎ ለንግድ ኩባንያ ማቋቋሚያ ለሚሆን ካፒታል የሚበቃ

እንዳልነበርም ይታወቃል፡፡ ስለዚህ የኩባንያዎቹ ካፒታል ምንጭ በአብዛኛው በንጥቂያና በዘረፋ የተሰበሰበ ገንዘብና ንብረት በመሆኑ ሕጋዊነት የሌለው ነው፡፡ ገንዘቡና ንብረቱ ለሕጋዊ ባለቤቶቹ መመለስ የሚገባ እንጂ ለአንድ ፓርቲ የግል ንግድ ማካሄጃና የስልጣን መደገፊያ የሚውልበት እንዲያውም ቀጥተኛ በሆነ አገላለፅ ለግፍ አገዛዝ እድሜ ማራዘሚያ የሚያገለግልበት በቂ ምክንያት የለም፡፡

ሁለተኛው ነጥብ ኩባንያዎቹ የተቋቋሙበትና የሚሰሩበት አግባብ ከሕግ ጋር የሚጣጣም አለመሆኑ ነው፡፡ እነዚህን ተቋሞች ኢንደውሜነት ናቸው በሚል ገዥው ፓርቲ ሕጋዊ መሰረት ያላቸው ለማስመሰል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መጠነ ሰፊ ጥረት እያደረገ ነው፡፡ በአንዳንድ የፖሊሲ ሰነዶቹ ላይ ሳይቀር ለሕዝብና ለሀገር ልማት ታስበው የተቋቋሙ ሕጋዊ አደረጃጀቶች መሆናቸውንና ከየአቅጣጫው የሚነሳባቸው ተቃውሞ ተገቢ አለመሆኑን በማብራራት አቋሙን ይፋ አድርጓል፡፡ ይህ አገላለፅ የአገዛዙን ፖለቲካዊ አቋም ከማሳየት በስተቀር የኩንያዎቹን ሕገወጥነት የሚያስቀር አይደለም፡፡ ምክንያቱም ለሀገርና ለሕዝብ ጥቅም የሚሰጡ ናቸው እንዳይባል እነዚህን ኩባንያዎች በባለቤትነት የሚያስተዳድሯቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች የታወቁ ናቸው፡፡ ኩባንያዎቹ የሼር ባለቤትነት ባላቸው የግል ባለሀብቶች የተመሰረቱ ናቸው እንዳይባል የሼር ድርሻ ይዘው የተመዘገቡ ግለሰቦች የፓርቲዎቹ ከፍተኛ ባለስልጣኖችና መሪ ካድሬዎች ሲሆኑ ይኸንን ያክል ኩባንያ በሽርክና ለመክፈት የሚያስችል የግል ሀብትና ንብረት እንዳልነበራቸው (ምክንያቱም 17 ዓመት ትግል ላይ ነበሩ) የሚታወቁ ናቸው፡፡ አብዛኞቹ ከፓርቲያቸው ጋር ጫካ ውስጥ የነበሩ እንጂ ፋብሪካ አቋቁመው፣ እርሻ አልምተውና ንግድ አካሂደው ገንዘብና ንብረት ሲያከማቹ የቆዩ አልነበሩም፡፡ የኩባንያዎቹ ስራ አስኪያጆችና አመራሮች ኩባንያዎቹን በበላይነት የሚያስተዳድሩ ቦርዶች መሪዎችና አባላት እነዚያው የፓርቲው መሪ ካድሬዎች ሹማምንት ናቸው፡፡ ድርጅቶቹም በህዝብ ስም የንግድ ፈቃድ ያልወጣላቸው ከመሆኑም በላይ ገቢያቸውና ወጪያቸው የሚመረመርበትና ለሕዝብ ይፋ የሚደረግበት ሁኔታም ፈፅሞ የለም፡፡

በኢትዮጵያ ፍትህ ብሔር ሕግ አንቀጽ 483 እንደተደነገገው ኢንደውሜንት ማለት ትርፍ ለማግኘት ሳይሆን ለሕዝብ ጥቅም በሚያስገኝ የተወሰነ ዓላማ ላይ የዋለ፣ የማይመለስ ቀጣይ የሆነ አገልግሎት እንዲሰጥ የተመደበ ገንዘብና ንብረት መሆኑ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ እነዚህ ኩባንያዎች ግን ከፍተኛ ትርፍ በሚገኝባቸው የተመረጡ የስራ መስኮች የተሰማሩና ለትርፍ የተቋቋሙ በመሆናቸው ኢንደውሜንት የሚባሉበት ምንም አይነት ሕጋዊ መስመር የሌለ ከመሆኑ በተጨማሪ በሀገሪቱ ሕግ መሰረት ተቀባይነት የሌለው ሕገወጥ ድርጊት እየፈፀሙ ናቸው፡፡

ገዥው ፓርቲ ኢንደውሜንት ናቸው፣ ለንግድ የተቋቋሙ የሼር ኩባንያዎች ናቸው ወዘተ. የሚል ስም መስጠት የፈለገበት ዋናው ምክንያት ደግሞ ፓርቲዎች ለትርፍ የሚሰራ ኩባንያና ንግድ እንዳይከፈቱ በሕግ የተከለከሉ ስለሆኑ ከዚህ ማምለጫ ዘዴ የፈጠረ መስሎት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በሁሉም ሁኔታ መውጫ በሌለው ሕገወጥ መንገድ የተቋቋሙና የሚሰሩ በመሆናቸው በእስካሁኑ አደረጃጀትና አሰራር የሚቀጥሉበት እድል የተዘጋ ነው፡፡ ይኸንን በመገንዘብ ይመስላል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ገዥው ፓርቲ አንድ አዲስ ስልት መጀመሩ ግልፅ እየሆነ መጥቷል፡፡ ይኸውም እነዚህ ኩንያዎች ከሀገር ውስጥና ከውጭ ባለሀብቶች ጋር በጋራ የሚሰሩበትና በሰብ ኮንትራት መልክ ትስስር የሚፈጥሩበት አካሄድ እየተከተለ ነው፡፡ እንዲህ አይነት ትስስር ከተፈጠረና የባለቤትነት መብቱን ከሌሎች ጋር መጋራት ከተቻለ በእያንዳንዱ የገዥው ፓርቲ ኩባንያ ንብረትና ገንዘብ ላይ የተለየ ጥያቄ ለማንሳት የማያስችል ውስብስብ ሁኔታ ስለሚኖር ቀስ በቀስ ተቃውሞው እየተዳከመ ይጠፋል በሚል ሂሳብ የተነሳ ነው፡፡

ይኸኛውም ስልት ወንዝ የሚያሻገር አይደለም፡፡ እንዲያውም ከሌሎች የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች ጋር የሚመሰረቱ ሽርክናዎች የገዥውን ፓርቲ ኩባንያዎች ካፒታል በዓይነትና በመጠን እየለዩ ለማወቅ የሚያስችሉ ግልጽ መረጃዎችን ከእስከዛሬው በተሻለ ለማግኘት ስለሚረዱ ሕገወጥ በሆኑት የፓርቲ ኩባንያዎች ላይ የሚነሳውን ሕጋዊ ጥያቄና ተቃውሞ ለማጠናከር አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል፡፡

የገዥው ፓርቲ ኩባንያዎች ሕገወጥነት በካፒታል ምንጫቸውና በተቋቋሙበት ሁኔታ ላይ ብቻ የተመሰረተ ሳይሆን በአሰራራቸውም ላይ የሚንፀባረቅ ነው፡፡ ይኸውም በችርቻሮና በጅምላ፣ በአስመጭነትና በላኪነት፣ በሕንፃ፣ በመንገድና በግድብ ኮንስትራክሽን፣ በኃይል ማመንጫ ግንባታና በኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ፣ በባንክና በኢንሹራንስ፣ በሕትመትና በማስታወቂያ፣ በሕዝብ ትራንስፖርትና በጭነት ማጓጓዣ፣ በገጠርና በከተማ አነስተኛ ብድር ተቋማት፣ በእርሻ ግብዓቶች ስርጭት፣ በትምህርትና በጤና አገልግሎት፣ በኪነጥበብና በመገናኛ ብዙሃን ወዘተ. ያልገቡበት መስክ የለም፡፡ እነሱ በገቡበት መስክ ሌሎች የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች እንዳይሳተፉ ከፍተኛ የፖሊሲና የቢሮክራሲ መሰናክሎች ይፈጠሩባቸዋል፡፡ ይኽንን ሁሉ ተፅዕኖና መሰናክል አልፈው ወደመስኩ ለመግባት ከቻሉ ደግሞ ከፓርቲ ኩባንያዎች ጋር በነፃነት መወዳደር እንዳይችሉ ልዩ ልዩ እንቅፋቶች ሆን ተብለው ይደቀኑባቸዋል፡፡ አማልጋሜትድ ኢትዮጵያ የሚባለው የግል ኩባንያ የእርሻ ግብዓቶችን በማቅረብ የገዥው ፓርቲ ኩባንያ ከሆኑት ከእነ አምባሰል ጋር እየተወዳደረ እንዳይሰራ በፌዴራልና በክልል የመንግስት አካላት ተከታታይ የሆነ ከባድ ተፅዕኖ ስለተደረገበት ከውድድሩ ለመውጣት የተገደደበትን ተጨባጭ ማስረጃ ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ገበሬው በጥራትና በዋጋ የተሻለውን መርጦ ለመግዛት እንዳይችል ተደርጓል፡፡

የገዥው ፓርቲ ኩባንያ የሆኑት ሱርና ላሊበላ ኮንስትራክሽን ድርጅቶች ሌሎች የሀገር ውስጥ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች ሊያገኙት ያልቻሉትን የስራ እድል እንዲያገኙ የሚደረግላቸውን የተለየ እንክብካቤ በማስረጃነት ማየት ይቻላል፡፡ የገዥው ፓርቲ ኩባንያ የሆነው ትራንስ ኢትዮጵያ ሌሎች የግል ባለሀብቶችና የመንግስት የጭነት ማጓጓዣ ተቋሞች እየተከለከሉ በውጭ ምንዛሬ የትራንስፖርት ክፍያ እያገኘ ከውጭ የሚገቡ እርዳታዎችንና ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን እንዲያጓጉዝ የሚደረግለትን ልዩ ድጋፍ በምሳሌነት ማንሳት ይቻላል፡፡ የገዥው ፓርቲ ኩባንያ የሆነው ጉና የንግድ ድርጅት ቡናን ወደ ውጭ በመላክ ከሌሎች የግል ባለሀብቶችና ከመንግስት ቡና ላኪ ድርጅት የበለጠ ሚና እንዲጫወት የሚደረግለትን ልዩ ድጋፍ በምሳሌነት ማንሳት ይቻላል፡፡ የገዥው ፓርቲ ኩባንያ የሆነው የስኳር አቅራቢ ድርጅት የሀገሪቱን የስኳር ምርት በሞኖፖል ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ እንዲያቀርብ የሚደረግለትን ልዩ እንክብካቤ መጥቀስ ይቻላል፡፡ የግል ባንኮች ተቀማጭ ካፒታላቸው እስከ 75% ካልደረሰ አንድም ይቀላቀላሉ አሊያም ይዘጋሉ የሚል ሕግ ቢኖርም ይኸንን ሕጋዊ ግዴታ ያልተወጣውና የገዥው ፓርቲ ኩባንያ የሆነው ወጋገን ባንክ ከሕግ ውጭ ስራውን እንዲሰራ የተደረገለትን ልዩ ድጋፍ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለሌሎች የግል ባለሀብቶች በከባድ ውጣ ውረድና ከጠየቁት እጅግ ባነሰ መጠን የሚገኝ የመንግስት ባንኮች ብድር የገዥው ፓርቲ ኩባንያ የሆኑት ኤፈርት፣ ጉና፣ አምባሰልና ሌሎቹም በቀላሉ እንዲያገኙ የሚደረግላቸውን ልዩ ድጋፍ መጥቀስ ይቻላል፡፡ የግል ባለሀብቶች የብድር መክፈያ ጊዜ እንዲራዘምላቸው የሚያቀርቡት ሕጋዊ ጥያቄ እየታጠፈ ንብረታቸው ሲወረስና በሀራጅ ሲሸጥ የፓርቲው ንግድ ኩባንያዎች ያልከፈሉት እዳ እንደተቆለለ ሌላ ተጨማሪ ብድር እንዲያገኙ የሚያደረጋቸውን እንክብካቤ መጥቀስ ይቻላል፡፡ በተለያዩ ጨረታዎች አስቀድመው የጨረታ ምስጢርና የማሸነፊያ ምክር ስለሚያገኙ ከገዥው ፓርቲ ኩባንያዎች ጋር ተወዳድሮ ለማሸነፍ የተቻለበት እድል እጅግ የመነመነ መሆኑን መጥሰቅ ይቻላል፡፡ የመንግስት ትምህርት መሣሪያዎች አቅራቢ ድርጅትና ሌሎች የግል ሕትመት ድርጅቶች የሚሳተፉበት እድል ተዘግቶ የሜጋ አሳታሚ ድርጅት የሚለው የገዥው ፓርቲ ኩባንያ የተማሪዎችንና የመምህራንን መፃህፍት በብቸኝነት እያተመ እንዲያሰራጭ ብቻ ሳይሆን ከውጭ የሚገቡ መፃህፍትንም በሞኖፖል እንዲያስገባና እንዲያሰራጭ የሚደረግለትን ልዩ ድጋፍ በአስረጅነት ማንሳት ይቻላል፡፡ የብሮድካስቲንግ አዋጅ በስራ ላይ እንዲውል ሳይደረግና የግል ባለሀብቶች በዚህ ዘርፍ እንዲሳተፉ የሚያስችል ፈቃድ መስጠት ሳይጀመር የገዥው ፓርቲ ኩባንያ የሆነው ሬዲዮ ፋና በሕገወጥ መንገድ የሬዲዮ ማሰራጫ አየር ሞገድ ያገኘበትን ሁኔታ መጥቀስ ይቻላል፡፡ የገዥው ፓርቲ ኩባንያ የሆነውና ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል የሚባለው የዜና አገልግሎት ተቋም የመንግስት ዜና አገልግሎት ከሆነው ኢዜአ የበለጠ ዜና ከውስጥና ከውጭ እንዲሰባሰብ እንዲገዛና እንዲሸጥ የሚደረግለትን ልዩ ድጋፍ መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህ የፓርቲ ኩባንያዎች በሚያካሂዱት ስራ የሚጠቀሙበትን የመሬት፣ የቤትና ሌሎች የመሰረተ ልማት አገልግሎት ኪራይ ክፍያዎች፣ የስራ ግብርና ታክስ ለመንግስት የሚከፍሉ መሆናቸው በግልጽ አይታወቅም፡፡

ከዚህም የባሰው ሙስና ለግብርና ግብዓት ከውጭ አበዳሪ ድርጅቶች መንግስት በሀገሪቱ ስም የሚገኘውን ብድርና እርዳታ ለገዥው ፓርቲ ኩባንያዎች ንግድ ማካሄጃ እንዲሆን የሚሰጥበት ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡ ይኸንን በሀገር ስም የተገኘ ብድር እነአምባሰል እየወሰዱና የግብርና ግብዓት ከውጭ ገዝተው ለገበሬው በውድ ዋጋ እየሸጡ ትርፉን ወደፓርቲው ካዝና ያስገባሉ፡፡ እዳውን ሀገሪቱ ትከፍላለች፡፡ ለገጠርና ለከተማ አነስተኛ ብድርና ቁጠባ አገልግሎት እየተባለ በገዥው ፓርቲ የተከፈቱ ተቋሞች በብድርና በእርዳታ ከተገኘ ገንዘብ ወይም ለሌላ ዓላማ በመንግስት ባንክ ከተቀመጠ ገንዘብና ከመንግስት መደበኛ በጀት እያዞሩ በብድር መልክ ካከፋፈሉ በኋላ ትርፉን ወደ ገዥው ፓርቲ ካዝና ያገባሉ፡፡ እዳውን ድሃው ሕዝብ ከጉሮሮው እየተነጠቀ ይከፍላል፡፡ ጉና ንግድ የሚባለው የገዥው ፓርቲ ኩባንያ ቡና ሸጦ ካገኘው የውጭ ምንዛሬ፣ ወይም ትራንስ ኢትዮጵያ እቃ በውጭ ምንዛሬ ክፍያ አጓጉዞ ካገኘው የውጭ ምንዛሬ ምን ያህሉን ለብሔራዊ ባንክ ምን ያህሉን ወደገዥው ፓርቲ ካዝና ገቢ እንደሚያደርግ በግልፅ አይታወቅም፡፡ በዚህ ዓይነት መንገድ ሁሉም የሀገር ሀብትና ንብረት ለሁሉም ዜጎች መገልገያ ወደሆኑት የመንግስት ካዝናዎችና እቃ ግምጃ ቤቶች ሳይሆን ወደገዥው ፓርቲ ቋት እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

በዚህ መንገድ ተዘርዝረው የማያልቁ የሙስና ገጽታዎችን መጥቀስ ቢቻልም ዋናው ነገር በሀገሪቱ አሁን የተከሰተው ሙስና የገዥው ፓርቲ ሙሉ እውቅናና ድጋፍ የሚደረግለት ይፋ የሆነ ተቋማዊ ሙስና እንጂ በግለሰብ ደረጃ የሚካሄድና በድብቅ የሚፈፀም ተራ ሌብነት አለመሆኑ ነው፡፡ ይኸንን ሁሉ ግልፅ ዘረፋ ሲያካሂድ የሚጠየቅበት ወይንም የሚከሰስበት መንገድ ሁሉ የተዘጋና ራሱን ከሕግ በላይ አስቀምጦ በአፈናና በንጥቂያ የሚኖር ጠያቂ የሌለው አገዛዝ መሆኑ ነው፡፡

ስለዚህ እንዲህ ዓይነት ተቋማዊ ሙስና በነገሰበት፣ ነፃ የገበያና የፍትህ ሥርዓት በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ስለሀገር ልማት፣ ስለኢንቨስትሜንት መስፋፋትና ስለ ግል ባለሀብቶች ተሳትፎ ማሰብ የማይቻል ነው፡፡ ይኸንን ተቋማዊ ሙስና ከመሰረቱ የሚያስወግድ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሳይመሰረት ኢትዮጵያን ከድህነት ሰልፍ ማውጣትና የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታ የሚያሻሽል ልማት ማምጣት እጅግ አስቸጋሪና የማይቻልም ነው፡፡

## 5.4 ፈርጀ ብዙ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ድቀት ያስከተለው ስር የሰደደ ድህነት

በኢትዮጵያ ውስጥ በቂ የተፈጥሮ ሀብት ቢኖርም ሕዝቡ ከርሃብ፣ ከተመጽዋችነት፣ ከድህነትና ከኋላቀርነት ሊወጣ አልቻለም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁን የሚገኝበት ሁኔታ በማንኛውም አለም አቀፍ ተቀባይነት ባለው መመዘኛ ቢለካ በሁሉም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘርፍ በዓለም ውስጥ እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን ሀገሪቱም የመጨረሻዎቹ ድሃ ከሚባት አገሮች መካከል የመጀመሪያውን ስፍራ ይዛለች፡፡ ይህ ለማንኛውም ሀገሩን ለሚወድ ዜጋ ሁሉ እንቅልፍ የሚነሳ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር በረጅም ጊዜ ሂደት ውስጥ እየተከማቸ የመጣና ስር የሰደደ ነው፡፡ የችግሩም ዓይነትና መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሚሄድ እንጂ የመቀነስ አዝማሚያ የሚታይበት አይደለም፡፡ ይበልጥ አሳሳቢው ጉዳይ ደግሞ ይኸንን ስር የሰደደ ችግር የሚቀለብስ አቅጣጫ በሀገራችን ገና ያልተተለመ መሆኑ ነው፡፡ አሁን የተያዘው ጉዞ ነባሮቹን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች የሚያባብስ ብቻ ሳይሆን አዳዲስ ተጨማሪ ችግሮች እንዲበራከቱ ያደረገ ነው፡፡ የሀገራችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ደረጃ እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡ የመሰረተ ልማት ደረጃዋና የቴክኒዎሎጂ ልማቷም እንደዚሁ ቀርፋፋ ነው፡፡ ማቆሚያ ያጣ የሕዝብ መራብና እያደገ የሚሄድ ስራ አጥነት የሀገሪቱ መሰረታዊ ችግሮች ሆነዋል፡፡

በኢኮኖሚው ውስጥ ቁልፍ ችግር ከሚባሉት መካከል የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት፣ ዝቅተኛ የሠራተኛ ምርታማነት፣ ዝቅተኛ የቴክኖዎሎጂ ደረጃ፣ እድገት የማይታይበት የገቢና ቁጠባ ሁኔታ፣ የካፒታል እጥረት፣ ደካማ የኢንቨስትመንት ልማት፣ የተዳከመ ንግድ፣ ኋላቀርና የዝናብ ጥገኛ በሆነ የተበጣጠሰ መሬት ላይ የሚካሄድ እርሻ፣ እየጨመረ የሚሄድ የውጭ እዳ ክምችት፣ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር እድገት፣ በኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሳይሆን በርዕዮተ ዓለማዊ

እይታ ብቻ የተቃኘ የመሬት ፖሊሲ፣ ዝቅተኛ የመሰረተ ልማት ደረጃና ከእነዚህ ጋር የተሳሰረው አጠቃላይ ድህነት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

በሀገራችን ውስጥ የሚታየውን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ድቀት እንዲሁም ከዚሁ ጋር የተያያዘውን ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃና ስር የሰደደ ድህነት በሚገባ ለመገንዘብ እንዲቻል ጥቂት ማነፃፀሪያዎችን በአስረጅነት ማቅረብ አስፈላጊ ነው:: በመንግስት የኢኮኖሚ ዘገባዎች መሰረት የሀገሪቱ አጠ ቃላይ ብሔራዊ ምርት በየዓመቱ 6% እድገት ማሳየቱ እውነት ሆነም አልሆነ የድህነቱን አስከፊነትና የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ማሽቆልቆል እንዳላስቀረው አሳማኝ ማስረጃዎችን ለማቅረብ ከባድ አይደለም::

በመንግስት የሚቀርበው የአጠቃላይ ብሔራዊ ምርት እድገት ዘገባ እንደ ትክክለኛ ተደርጎ ቢወሰድ እንኳ በሌሎች ሁኔታዎች ከሚታየው ውድቀት ጋር ሲነፃፀር ሚዛን የሚደፋ ነገር አይደለም:: በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙውን ጊዜ ተመዘገበ የሚባለው እድገት ከዝናብ መምጣትና መቅረት ጋር ከተያያዘ የእርሻ ምርት በሚገኘው ውጤት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ዘላቂነቱ ሁልጊዜም አስተማማኝነት የሌለው ነው:: በዚህ ላይ አሁን ባለው የመሬት ባለቤትነት ፖሊሲ ችግር ምክንያት በግብርናው ዘርፍ ፈጣን እድገት ለማምጣት የማያስችሉ ከባድ ማነቆዎች መኖራቸው ሲጨመርበት የእድገቱ ተከታታይነትና ዘላቂነት ተስፋ የሚጣልበት ሊሆን አይችልም::

በተደጋጋሚ ጊዜ የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያረጋግጡት ካለፉት 50 ዓመታት ወዲህ የገጠሩ ሕዝብ ራሱን የመመገብ አቅሙ እየመነመነ መጥቷል:: የሚለማ ተጨማሪ የእርሻ መሬት በሌለበት ሁኔታ የሕዝቡ ቁጥር በዓመት ወደ 3% ገደማ እየጨመረ ነው:: የአንድ ገበሬ የይዞታ መጠን ከግማሽ ሄክታር በታች ወርዷል:: ከሕዝቡ ቁጥር በፍጥነት መጨመር፣ ከይዞታው እያነሰ መሄድና ከመሬት ባለቤትነት ዋስትና ዕጦት ጋር ተያይዞ የመሬቱ ምርታማነት በየጊዜው እየቀነሰ መጥቷል:: ከ40 ዓመታት በፊት በ1 ሄክታር በአማካይ 11 ኩንታል ማምረት ይቻል የነበረ ሲሆን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ለዚያውም የምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች በተሻለ ደረጃ ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው በሚባልበት ጊዜ ማምረት የተቻለው በ1 ሄክታር በአማካይ ከ10 ኩንታል አይበልጥም:: እያንዳንዱ ገበሬ በነፍስ ወከፍ የሚያመርተው ምርት ከ20 ዓመት በፊት በአማካይ 174 ኪሎ ግራም የነበረ ሲሆን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን ከ97 ኪሎ ግራም የሚበልጥ አይደለም:: በእንስሳት ምርት ያለውም ሁኔታ በተመሳሳይ እድገት የሚታይበት አይደለም:: ባለፉት 3 አስርት ዓመታት በሀገሪቱ ውስጥ በቋሚነት ለከብት ግጦሽና እርባታ ይውል የነበረው 46 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከ20 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በታች ወርዷል:: ከግጦሽ መሬት እያነሰ መሄድ፣ ከእንስሳት ህክምና አለመስፋፋትና በተከታታይ ከሚከሰተው ድርቅ ጋር ተያይዞ የእንስሳት ቁጥር በከፍተኛ መጠን ቀንሷል:: ከ10 ዓመት በፊት የነበረው 30 ሚሊዮን አካባቢ የእንስሳት ቁጥር በአሁኑ ጊዜ ከ20 ሚሊዮን እያነሰ ነው:: ከእንስሳት የሚገኘው የወተት፣ የስጋና የቆዳ ምርት መጠንም እየቀነሰ እንጂ እየጨመረ አልሄደም:: በዚህም የተነሳ ላለፉት 15 እና 20 ዓመታት በእርዳታ ብቻ የሚኖሩ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ ነው:: ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ1992 በርሀብ ተጠቅቶ የነበረው ሕዝብ ቁጥር 6.1 ሚሊዮን የነበረ ሲሆን አሁን በያዝነው 2002/003 ውስጥ በርሃብ የተጠቃው ሕዝብ ቁጥር ከ14 ሚሊዮን በላይ ነው::

የእርዳታ ፈላጊው ቁጥር መጨመር የሚያሳየው የድህነቱን እየተባባሰ መምጣት ነው:: በዚህ ሁኔታ እየሞተ በሚገኝ የግብርና ኢኮኖሚ ላይ በመመስረት ተመዘገበ የሚባለው እድገት ለአጠ ቃላዩ ኢኮኖሚ መሻሻልና ለድህነት መቀነስ ትርጉም ያለው ድጋፍ ሊያስገኝ ቀርቶ ዜጎች በምግብ እህል ራሳቸውን ችለው እንዲኖሩ ለማድረግ እንኳ የሚያስችል አይደለም:: ሌላ ሩቅ ቦታ መሄድ ሳያስፈልግ 6% ዓመታዊ የኢኮኖሚ እድገት ተመዝግቧል በሚባልበት በአሁኑ ወቅት ከ14 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የሚልሱትና የሚቀምሱት አጥተው በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ሰብዓዊ እርዳታ እየኖሩ መሆናቸውን በማየት ተመዘገበ የሚባለው እድገት ትርጉም አልባ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል::

*ሀገሪቱ የምትገኝበትን ዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታና አስከፊ ድህነት ለማየት እንዲቻል የታወቁ የእድገት መለኪያዎችን በመጠቀም ከተመረጡ ጥቂት የአፍሪካ አገሮች ጋር ኢትዮጵያን በማነፃፀር ነገሩን ግልፅ ማድረግ ይገባል፡፡ ለምሳሌ አሁን ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአጠቃላዩ ብሔራዊ ምርት የሚያገኘው ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ድርሻ* 100 *ዶላር ነው፡፡ በዚሁ ወቅት የአፍሪካ አማካይ የነፍስ ወከፍ ድርሻ* 800 *ዶላር ሲሆን ከኢትዮጵያ ስምንት ጊዜ እጥፍ ነው፡፡ በተናጠል የተወሰኑ ሀገሮችን ብንመለከት ደግሞ ኬንያ* 360 *ዶላር፣ ሱዳን* 330 *ዶላርና ግብፅ ደግሞ* 1390 *ዶላር ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ አላቸው፡፡*

*የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከ*100 *ኢትዮጵያዊያን መካከል ወደ* 50 *ገደማ የሚጠጉት ከድህነት ወለል በታች ናቸው፡፡ የምስራቅና ደቡብ ምስራቅ ኤሽያን ብንመለከት ከ*40 *ዓመታት በፊት* 35% *የሚሆነው ሕዝብ ብቻ ነው በፍጹም ድህነት ደረጃ ላይ የነበረው፡፡ ይሁን እንጂ በ*20 *ዓመት ውስጥ ይኸንን ቁጥር ወደ* 10% *ዝቅ ለማድረግ ችለዋል፡፡ በእኛ ሀገር ግን እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ መሄድ አልቻለም፡፡ እነሱ ባደጉበት ፍጥነት በየዓመቱ እድገት ማስመዝገብ ብንችል እንኳ የሀገራችንን ፍጹም ድሃዎች ቁጥር የተጠቀሱት ሀገሮች ከ*40 *ዓመት በፊት ወደነበሩበት* 35% *ደረጃ ዝቅ ለማድረግ በቀላሉ ወደ* 40 *ዓመት ገደማ ይወስድብናል፡፡*

*ከዚህ ባነሰ ጊዜ በፍጹም ድህነት ውስጥ የገቡትን ዜጎች ደረጃ ለማሻሻል ከተፈለገ ቢያንስ ለ*20 *ተከታታይ ዓመታት በእያንዳንዱ ዓመት* 8% *የኢኮኖሚ እድገትና በየዓመቱ ለ*1 *ሚሊዮን ገደማ ዜጎች የስራ እድል የሚያስገኝ የልማት እንቅስቃሴ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡*

*በሀገራችን ከጠቅላላው ሕዝብ ውስጥ ከ*15% *ትንሽ ከፍ ያለ ሕዝብ በከተማ የሚኖር ሲሆን ከሰሀራ በታች ባሉ ሌሎች ሀገሮች ግን* 34% *ይደርሳል፡፡ ድህነት በሀገሪቱ ገጠርና ከተማ በጠ ቅላላው የተስፋፋ ሲሆን በገጠር ያለው ሁኔታ ደግሞ ከከተማው የባሰ ነው፡፡ ለዚህ ዋና ዋና ከሚባሉት ምክንያቶች መካከል የመሬት ባለቤትነት ፖሊሲው ለገበሬውና ለመሬቱ ምርታማነት መጨመር የማያግዝ መሆን፣ በቂ የእርሻ መሬት አለመኖር፣ የሕዝቡ ቁጥር መጨመር፣ የትምህረት፣ የጤና፣ የንጹህ መጠጥ ውሃና የመሳሰሉት ማህበራዊ አገልግሎቶች አለመስፋፋት፣ ተደጋጋሚ ድርቅ ወዘተ. ይገኙበታል፡፡ የዛሬ* 5 *ዓመት ገደማ በተደረገ ጥናት በሀገር ደረጃ ከጠ ቅላላው ፍጆታ ውስጥ* 60% *የሚሆነው ለምግብ ፍጆታ የሚውል ሲሆን በገጠር ደግሞ ለምግብ ፍጆታ የሚውለው መጠን ከ*60% *የበለጠ ነው፡፡ በአለም የጤና ድርጅት የሚታመንበት የካሎሪ መጠን ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው በቀን* 2200 *ካሎሪ ሲሆን በእኛ ሀገር አንድ ሰው በቀን የሚያገኘው መጠን ከ*954 *ካሎሪ አይበልጥም፡፡ በዚሁ ጥናት መሰረት ከሁለት ሶስተኛው የሚበልጡት ሕፃናት እድገታቸው የቀጨጨ ነው፡፡ በወንድና በሴት መካከል ከፍተኛ ልዩነት በሌለው ሁኔታ ከገጠሩ ሕዝብ መካከል ከአንድ አራተኛ የሚበልጡት በምግብ እጥረት መጎዳት የደረሰባቸው ናቸው፡፡ ይኸ ቁጥር በአሁኑ* 2002/2003 *ውስጥ በጣም ጨምሯል፡፡*

*የሕፃናትና ከ*1 *ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ሞት በኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ*1998 *በተደረገ ጥናት ከአንድ ሺህ ልጆች ውስጥ* 173 *እና* 107 *ነበር፡፡ በሌሎች ከሰሀራ በታች ባሉ ሀገሮች ይኸ ቁጥር እንደቅደም ተከተላቸው* 151 *እና* 92 *ብቻ ነው፡፡ በሌላ መረጃ ደግሞ ከሚወለዱት ሕፃናት መካከል ከ*10% *በላይ የሚሆኑት አንድ ዓመት ሳይሞላቸው ይሞታሉ፡፡ ከ*8% *በላይ የሚሆኑት ደግሞ አምስት ዓመት ሳይሞላቸው ይሞታሉ፡፡ ይኸ ቁጥር ከሰሀራ በታች ካሉ ሌሎች ሀገሮች ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ነው፡፡*

*ከ*5 *ዓመት በታች የሆኑ የሀገራችን ሕፃናት የምግብ እጥረት መጠን* 48% *ሲሆን ይህ ከሰሀራ በታች ባሉ ሌሎች ሀገሮች ከ*33% *አይበልጥም፡፡ በአሁኑ ጊዜ የሀገራችን አማካይ የእድሜ መጠ ን ለወንዶች* 47 *እና ለሴቶች* 49 *ገደማ ነው፡፡ ይህ ከሰሀራ በታች ካሉ ሌሎች ሀገሮች ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ደረጃ ነው፡፡*

*በተጨባጭ የኑሮ ሁኔታ አመልካቾች የሀገራችንን ሁኔታ ከሌሎች ሀገሮች ጋር ለማነፃፀር ቢያስፈልግ እ.ኤ.አ በ*1997 *በተገኘ መረጃ ኢትዮጵያ በየአንድ ሺህ ሰው* 3 *ሰዎች ብቻ ስልክ፣* 6 *ሰዎች ብቻ ቴሌቪዥን፣* 196 *ሰዎች ብቻ ሬዲዮ፣ ወደ ዜሮ መጠን የሚጠጋ የሰዎች ቁጥር ሞባይል ነበራቸው፡፡ ይህ ሁኔታ እንደ ቅደም ተከተሉ በኬንያ ሲታይ* 9፣ 22፣ 104 *እና* 1

ነው:: በተመሳሳይ ቅደም ተከተል በሱዳን ያለው ሁኔታ ሲታይ 3፣ 173፣ 271 እና 0 ነው:: በዚሁ ቅደም ተከተል መሰረት በግብፅ ያለው ሁኔታ ደግሞ 9፣ 183፣ 160 እና 3 ነው:: በጠቅላላው በአፍሪካ ያለው ሁኔታ በተመሳሳይ ቅደም ተከተል ሲታይ በአማካይ 18፣ 59፣ 214 እና 14 ነው::

በዚሁ ዓመት ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው ከመሃይምነት በተላቀቁ ሰዎች ቁጥር፣ በልጆች የርሃብ ጉዳት፣ በመጠለያ ችግር፣ በንጽህና አገልግሎት አለመኖርና በመሳሰሉት የኑሮ ሁኔታ አመልካቾች ከሰሀራ በታች ከሚገኙ ሀገሮች መካከል ኢትዮጵያ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች::

በሰብዓዊ ልማት መመዘኛዎች ማለትም በምርታማነት፣ በእኩል ተጠቃሚነት፣ በዘላቂ የልማት እድገት፣ በፖሊሲ አወጣጥና አወሳሰን ረገድ ባለ ተሳትፎና በመሳሰሉት የኢትዮጵያ እድገት 25% አካባቢ ነው:: ይህ ነጥብ ከአለም አማካይ ነጥብ አንድ ሶስተኛ ብቻ ሲሆን ከታዳጊ ሀገሮች አማካይ ነጥብ ደግሞ ከግማሽ ያነሰ ነው:: በጣም ወደ ኋላ የቀሩ አገሮች ካገኙት አማካይ ነጥብ በሶስት አራተኛ ዝቅ ያለ ነው:: በሰብዓዊ ልማት ረገድ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም ስለኢትዮጵያ የሚያወጣቸው መረጃዎች በየጊዜው ወደታች የማሽቆልቆል ካልሆነ በስተቀር የነበረውን ሁኔታ እንኳ ይዞ ለመቆየት እንዳልተቻለ የሚያሳዩ ናቸው:: ለምሳሌ እ.ኤ.አ 1991 ኢትዮጵያ በሰብዓዊ ልማት ረገድ የነበረችበት ደረጃ 138ኛ ነበር:: በ1998 ደግሞ ወደ 171ኛ ደረጃ አሽቆለቆለ:: በ2002/2003 ደግሞ ከዚህ በበለጠ ደረጃዋ ዝቅ ብሏል::

እነዚህ ሁኔታዎች በቅርብ ጊዜ ይሻሻሉ ይሆናል ብሎ ተስፋ ለማድረግ እንዳይቻል ከአጠቃላይ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሩ በባሰ ፍጥነት የሕዝብ ብዛት 69 ሚሊዮን እየተጠጋ ነው:: ይህ ቁጥር ከአፍሪካ ውስጥ ከናይጀሪያ ቀጥላ በ2ኛ ደረጃ በአለም ደግሞ በዘጠነኛ ደረጃ እንድትቀመጥ አድርጓታል:: በሕዝቧ ብዛት መጨመር የተነሳ በአንድ ስኩየር ኪሎ ሜትር የሚኖረው ሰው ቁጥር ከ63 በላይ ነው:: ከሰሀራ በታች ባሉ ሀገሮች ግን 27 ሰው በ1 ስኩየር ኪሎ ሜትር ውስጥ ይኖራሉ:: የሕዝቡ አሰፋፈር ደግሞ ቆላማው የሀገሪቱ ክፍል አነስተኛ የዝናብ መጠን፣ ደካማ የመሰረተ ልማት ፋሲሊቲና አደገኛ የጤና ችግር ስላለው አነስተኛ ሕዝብ በተበታተነ ሁኔታ የሰፈረበት ሲሆን በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ በተጠጋጋ ሁኔታ በደጋማው የሀገሪቱ ክፍል የሰፈረ ነው::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር በአሁኑ ጊዜ ወደ 3% ገደማ ዓመታዊ እድገት የሚታይበት ነው:: እ.ኤ.አ በ1980 38 ሚሊዮን የነበረ ሲሆን በአሁኑ 2002/2003 69 ሚሊዮን ደርሷል:: አሁን በየዓመቱ በሚታየው 3% ጭማሪ የሚቀጥል ከሆነ በየ23 ዓመቱ በእጥፍ ስለሚጨምር እ.ኤ.አ በ2026 ወደ 138 ሚሊዮን ይደርሳል:: የኢትዮጵያ ሴቶች በአማካይ እስከ 6 ልጆች እንደሚወልዱ የቅርብ ጊዜ መረጃዎች ያመለክታሉ::

ከሀገሪቱ ጠቅላላ ሕዝብ ውስጥ ወደ ግማሽ የሚጠጋው እድሜው ከ16 ዓመት በታች ነው:: እድሜያቸው 60 እና ከዚያ በላይ የሆኑት ቁጥር ከ5% አይበልጥም:: እ.ኤ.አ ከ1990-98 ባሉት ዓመታት ከ15-49 ዓመት እድሜ ካላቸው ያገቡ ሴቶች መካከል የወሊድ መቆጣጠሪያ የሚጠቀሙት በአማካይ 4% ብቻ የሚሆኑት ናቸው:: እነዚህ መረጃዎች የሚያሳዩት ቢኖር ከፍተኛ የወሊድ ሁኔታ መኖሩንና ዝቅተኛ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት መኖሩን ነው:: የቤተሰብ ምጣኔ ቢስፋፋ ውልደትን ስለሚቀንስ የሕዝብ ቁጥር እድገቱን ፍጥነት ለመቀነስና ሁኔታውን ለመቀልበስ ይቻላል ብሎ ተስፋ ለማሳደር እድል ይገኝ ነበር:: ነገር ግን ሁኔታው ይኸንን አያሳይም::

የሀገሪቱ ሕዝብ የእድሜ ስብጥር እንደሚያሳየው በርካታ የቤተሰብ ጥገኝነት መኖሩንና ሳይሰራ የሚቀለበው ቁጥር ከጠቅላለው ሕዝብ ቁጥር ከ50% የሚበልጥ መሆኑን ነው:: የእድሜ ስብጥሩ መዛባትና የሚወለዱ ልጆች ቁጥር መብዛት የምግብ ፍጆታ መጠንን ስለሚያሳድገው አንድ ቤተሰብ ለመጠባበቂያ የሚያቆየውን የምግብና የገንዘብ መጠን ያሳንሰዋል:: የሚቆጠብ ጥሪት ሳይኖር የሚመረተው ነገር አብዛኛው ለፍጆታ ብቻ ከዋለ ትርፍ የሚያስገኝ ነገር በመስራት በቂ ምርትና ሀብት ለማፍራት አይቻልም:: እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ልጆችን ለማስተማር የሚበቃ ትምህርት ቤት እንዲስፋፋ መንግስት ከፍተኛ ሀብት ለመመደብ ይገደዳል:: ይህ በተራው በሌላ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ሊመደብ የሚገባን የመንግስት በጀት ይሻማል::

ከዚህ በላይ በአጭሩ የቀረቡት ማሳያዎች ሀገሪቱ የምትገኝበትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ድቀት ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተባባሰውን ድህነት ስፋትና ጥልቀት ለመረዳት መጠነኛ ግንዛቤ የሚሰጡ ናቸው:: የችግሩ ዓይነትና መጠን ከዚህም የከፋ መሆኑን ለመረዳት ደግሞ በምንኖርበት አካባቢና የስራ ቦታ በየዕለቱ የምናያቸውን በልመና የተሰማሩ ዜጎች፣ በረንዳ ላይ የወደቁትንና በየስርቻ ካላአንዳች ምግብና መጠለያ ራቁታቸውን የሚውሉትንና የሚያድሩትን ወገኖች በዓይነ ሕሊናችን ማሰብ በቂ ነው:: ሀገሪቱ የምትገኝበት ድህነት በአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚገለጽና በቀጥር እየተሰላ ሊቀርብ የሚችል አይደለም:: በተወሰኑ የኢኮኖሚና የኑሮ ሁኔታ ማሳያዎች ከሚገለፀውና በቁጥር ከሚቀርበው በላይ የሚዘገንን ድህነት በሀገሪቱ ውስጥ ተንሰራፍቷል::

ድህነት ላይ ላዩን ሲያዩት የገንዘብ እጦት ብቻ ይመስላል እንጂ ክብርን የሚያዋርድና ብዙ ጠ ንቆችን አስከትሎ የሚመጣ ክስተት ነው:: ያልተመጣጠነ ምግብ፣ ያልተሟላ ጤንነት፣ የትምህርት እድል ማጣት፣ በማይረባ ቤት ውስጥ መኖር፣ ስራ ማጣት፣ በማይጠቅም ስራ መሰማራት፣ ፍትህ ማጣት፣ የሕግና የፖለቲካ መብትን መነፈግ፣ ወዘተ. እነዚህ ሁሉ የድህነት ገጽታዎች ናቸው:: ድህነት በሌላ ሁኔታም ሊገለጽ ይችላል:: ለምሳሌ አንድ ሰው የራሱን ሕይወት በራሱ ለመቆጣጠርና የወደፊት እድሉንም ለመወሰን ካልቻለ፣ ሰብአዊ ክብሩን ለማስጠ በቅ አቅም ካጣ፣ እያደር በሚያከሳ የተስፋ መቁረጥ ስሜት ከተዋጠና በነገው ተስፋ እምነት ካጣና ሁሉ አይጥምሽ ለመሆን ከተገደደ እነዚህ ሁሉ የድህነት መገለጫዎች ናቸው:: ብዙ ጊዜ የተለያየ ዓይነት ችግር የሚያጠቃው እነዚያ ድህነት አስሮ ተብትቦ የያዛቸውን ወገኖች ነው:: ለምሳሌ በስራ ማጣት የተነሳ የገቢ ማነስ፣ ረሀብ፣ ጤና ማጣት፣ የመጠለያ ችግር፣ ልብስ ማጣትና የሌሎችም ማህበራዊ አገልግሎቶች መጥፋት በአንድ ላይ ተከታትለው ይከሰታሉ:: የተመጣጠነ ምግብ አለመመገብ አካላዊ ጥንካሬን የሚጎዳና የአእምሮን መዳበር የሚገድብ ነው:: የጤና ጉድለት ደግሞ የአካል ጉድለትን በማስከተል ብቻ ሳይወሰን የኋላ ኋላ አኗኗርን ማቃናት እስከሚሳን ድረስ ከባድ ጉዳት የሚያስከትል ነው:: የቤተሰብ የስራ ሁኔታና የኑሮ ደረጃ በልጆች አስተዳደግ፣ ትምህርት፣ ጤንነትና የወደፊት አኗኗር ላይ ተፅዕኖ አለው:: የእናትና የልጅ በምግብ መጎዳት ለመጪው ሕይወት መጥፎነት እንደ መጀመሪያ ምልክት ማረጋገጫ የሚታይ ነው:: የተቸገሩ ወላጆች የልጆቻቸውን ጤንነት አሟልተውና በትምህርት አንፀው ለማሳደግ ያዳግታቸዋል:: ራሳቸው ያልተማሩ ከሆኑ ደግሞ ልጆቻቸውን በትምህርት እንዴት መርዳት እንደሚችሉ ለማወቅ ይቸገራሉ::

በአጠቃላይ አነጋገር ድህነት ብዙ መልኮችና ባህርያት ያሉት ውስብስብ ጉዳይ ነው:: በሀገራችን የተንሰራፋው ድህነት እንዲሁ በቀላሉ መፍትሔ ይገኝለታል የሚባል አይደለም:: በተለይ ደግሞ የዴሞክራሲ ስርዓትና መልካም አስተዳደር በሌለበት ሁኔታ ከድህነት መውጣት የሚቻል ጉዳይ አይደለም:: የሀገራችን ድህነት ስር የሰደደውና ከዚህ አስከፊ ደረጃ ላይ የደረሰው ሀገሪቱ ድህነትን ለማስወገድ የሚረዳ፣ ተከታታይ እድገትንና ዘላቂ ልማትን ለማስገኘት የሚችል የተፈጥሮ ሀብት ስለሌላት አይደለም:: ለልማት ሊሰለፍ የሚችል የሰው ጉልበት ስለቸገራትም አይደለም:: ችግሯን የሚገነዘብላትና ድጋፍ ሊያደርግላት የሚችል አጋርና ተባባሪ ስላጣችም አይደለም:: በእርግጥ የሰለጠነ የሰው ኃይል፣ የቴክኖሎጂና የካፒታል ችግር ያለባት ሀገር መሆኗ ባይካድም እንዲህ ዓይነት ችግር ያለበት ሀገር ድሃ እንደሆነ ይቀራል ማለት አይደለም:: በተፈጥሮ ሀብት፣ በሰለጠነ የሰው ኃይል፣ በቴክኒዎሎጂና በካፒታል ችግር ከኢትዮጵያ በከፋ ሁኔታ ውስጥ የነበሩ ብዙ ሀገሮች ከድህነት ሰልፍ ወጥተው ዘላቂ በሆነ የእድገትና የልማት መስመር ውስጥ መግባት ችለዋል:: የእኛ ሀገር ችግር በአብዛኛውና ከምንም በላይ ከዴሞክራሲ ስርዓትና ከመልካም አስተዳደር መጥፋት ጋር የተያያዘ ነው:: በሀገሪቱ ውስጥ ከድህነት የሚጠ ቀም አገዛዝ በመተከሉ ድህነትን በማስወገድ ፋንታ እንዲጎለብትና ስር እንዲሰድ አድርጎታል:: የአገዛዝ ስርዓቶች ሁሉ አንድ የጋራ ባህርይ አላቸው:: ይኸውም ሀገርና ሕዝብ ሲለማ ጥቅማችን ያጓድላል ብለው ይሰጋሉ:: በድህነት ውስጥ የሚኖር ሕዝብ ለአገዛዝ ይመቻል ብለው ያስባሉ:: በዚህ እምነታቸው በመመራት ድህነትን ያባብሱታል እንጂ አያስወግዱትም:: ሕዝቡ ጻቦ ጠግቦ ካደረ ለሥልጣናችን ስጋት ይሆናል ብለው ስለሚሰጉ በድህ ሕዝብ ጀርባ እንደታዘሉ ለመኖር የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ:: ድህነት ከጠፋ በብድርና በእርዳታ ስም ከየማዕዘኑ የሚቃርሙት ገንዘብ ምንጩ እየመነመነ ስለሚሄድ በድሃ ሕዝብ መሀል የገነቡት የድሎትና የምቾት ደሴት አደጋ ላይ ይወድቃል ብለው ይጨነቃሉ:: ከዚህ ሁሉ ጣጣ ሀገርና ሕዝብ ይበልጥ እየደኸዩ የእነሱ ስልጣን ይበልጥ እየተደላደለና ምቾታቸው እየጨመረ እንዲሄድ ይፈልጋሉ:: ማንም በግልፅ እንደሚያውቀው የበለጸጉ ሀገሮችን ከሚመሩ ፕሬዚዳንቶች፣ ጠቅላይ ሚኒስትሮች፣

ሚኒስትሮች የበለጠ በትላልቅ ባንኮች ውስጥ ተቀማጭ ወርቅና ዶለር ያላቸው እጅግ ድሃ ሀገሮችን የሚገዙ ፕሬዚዳንቶች፣ ጠቅላይ ሚኒስትሮች፣ ሚኒስትሮች ናቸው:: የኢትዮጵያ ሁኔታም ከዚህ የተለየ ሊሆን አይችልም:: አገዛዝ በስልጣን መንበሩ ላይ እስከተቀመጠ ድረስ ኢትዮጵያና ሕዝቧ ከድህነት ይወጣሉ ብሎ ማሰብ በሕልም ቅቤ እንደመብላት የሚቆጠር ነው::

# 6. የኢዴፓ አገር አቀፍ የልማት መስመርና ስትራቴጂ አጠቃላይ ይዘት

## 6.1 የኢዴፓ አማራጭ የልማት መስመር፣ የፖሊሲና የስትራቴጂ መሰረታዊ ትርጉም

ለሀገራችን የሚያስፈልጋት ብሔራዊ የልማት መስመርና ስትራቴጂ ይዘት የሚወሰነው ለመገንባት በሚፈለገው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሥርዓት ባህርይ ነው:: ኢትዮጵያ ውስጥ ሊገነባ ይገባዋል ብለን የመረጥነው ሥርዓት ፍትሀዊ የካፒታሊዝም ሥርዓት ነው:: ሀገራችን ይኸንን ሥርዓት ገንብታ ከድህነትና ከኋላቀርነት ተላቃ የበለፀገችና በሁሉም ረገድ የተሳካ የልማት ውጤት ባለቤት መሆን ትችላለች የሚል ትልቅ ራዕይ አለን:: ፍትሀዊ የካፒታሊዝም ሥርዓት የመገንባት ዓላማችን እንዲሳካ ለማድረግ በምንችልበት ጊዜ ልንደርስበት የምንፈልገው የመጨረሻ ግብ ኢትዮጵያ ሀገራችን ድህነትና ኋላቀርነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የተወገዱባትና ዘላቂ በሆነ ፈጣን የልማት ጎዳና ውስጥ ገብታ ወደፊት የምትገሰግስ ሀገር ማድረግ ነው:: ይኸንን አላማና ግብ ለመጨበጥ ከካፒታሊዝም ሥርዓት ባህርይ ጋር የተጣጣመ የልማት መስመር፣ ፖሊሲና ስትራቴጂ መንደፍ ያስፈልጋል::

የልማት መስመር ስንል በዋነኛነት የምንከተለውን የልማት ፕሪንስፕል (መርህ) ለማመልከት ሲሆን ይኸውም የፓርቲያችን የልማት መሰረተ ሀሳብ የሚመሰረትበትና የሚመራበት አጠ ቃላይና ሳይንሳዊ የሆነ ሕግ ነው:: ፓርቲያችን የሚከተለውን የልማት አቅጣጫ የሚገዛ አጠ ቃላይ መርህ ማለታችን ነው:: ፖሊሲ ስንል ደግሞ የፓርቲያችን የልማት እምነቶችና አስተሳሰቦች የሚገኙበትን አጠቃላይ የተግባር እቅድ የያዘ በረጅም ጊዜ የሚፈፀም ሀሳብን ለማመልከት ነው:: ለምሳሌ የሀገራችን ሲቪል ሰርቪስ ብቁ ሞያ ያላቸውን ሰራተኞች እንዲቀጥር ማድረግ እንደ አንድ የፓርቲያችን የፖሊሲ ሀሳብ ተደርጎ ቢወሰድ ይህ ሀሳብ በመጀመሪያ ደረጃ አጠቃላይ ነው:: ምክንያቱም እንዴት፣ መቼና በማን አማካይነት ወዘተ. ብቁ ባለሙያ መቀጠር እንዳለበት ዝርዝሩን አያሳይም:: በሁለተኛ ደረጃ ይኸ የፖሊሲ ሀሳብ በአንድ ቀን፣ ወርና ዓመት ተሰርቶ የሚቆም ነገር አይደለም:: ብቁ ሞያተኛ በሀገሪቱ ሲቪል ሰርቪስ ውስጥ መቅጠር የሚለው የፖሊሲ ሀሳብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለውጥና ማስተካከያ እየተደረገበት ተገቢነቱን እንደጠበቀ ለረጅም ጊዜ እየተሰራበት የሚቆይ ቀጣይነትና ተከታታይነት ያለው ነው::

ለኢትዮጵያ ዘላቂ ልማት ለማምጣት የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን በየዘርፉ ለማውጣት ዋና ዋና የሚባሉትን የሀገሪቱን ቁልፍ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች በቅድሚያ ለይቶ ማቅረብ ተገቢ ነው:: ከዚህ ሌላ ፖሊሲን በመቅረፅና በመፈፀም ሂደት ውስጥ መሟላት ያለባቸውን ዋና ዋና ጉዳዮች ማመልከት አስፈላጊ ነው:: በሀገራችን ውስጥ ግልፅ ፖሊሲ ስለሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሀሳብ ከመቅረቡ በፊት የፖሊሲ ገፅታዎችንና ደረጃዎችን ማስቀመጥ ይገባል::

ፖሊሲ ፍላጎት፣ ተግባርና ውጤት ተቀናጅተው የሚገለፁበት ሀሳብ ነው:: በፍላጎት ገጽታው ሲታይ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ፣ መንግስት፣ የንግድ ተቋም ወዘተ. ለመስራት የሚፈልገውን ሀሳብ የሚገልጽበት አቋም ነው:: በተግባር ገጽታው ሲታይ አንድ ፓርቲ፣ መንግስት፣ የቢዝነስ ተቋም ወዘተ. በተጨባጭ መደበኛ እንቅስቃሴው ወቅት በሚከናውነው ድርጊት የሚገለጽ ነው:: በውጤት ገጽታው ሲታይ ደግሞ አንድ ፓርቲ መንግስት፣ የቢዝነስ ተቋም ወዘተ. ባስገኘው አወንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት የሚገለጽ ነው::

የፖሊሲ ሀሳብ ከሚወጠንበት አንስቶ በተግባራዊ አፈጻጸም ወቅት ያስገኘው ውጤት እስከሚመዘንበት ጊዜ ድረስ አራት ተከታታይነትና ተያያዥነት ያላቸውን ደረጃዎች ማለፍ አለበት፡፡ የመጀመሪያው ደረጃ ፖሊሲ የማመንጨት እርከን ሲሆን አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም መንግስት በሕዝብ እንዲመከርበትና ሀሳብ እንዲሰጥበት በመነሻነት የሚቀርብ ፖለቲካዊ አጀንዳ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በዚህ ደረጃ የሚቀርብ የፖሊሲ ሀሳብ በሕዝብ ዘንድ ታይቶ ተቀባይነት ሊያገኝም ላያገኝም ይችላል፡፡

ሁለተኛው ደረጃ ፖሊሲ የመቅረጽ እርከን ነው፡፡ ይህ እርከን በፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ውስጥ እጅግ ጠቃሚና ወሳኝ ደረጃ ነው፡፡ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ በሚደረገው ክርክር፣ ውይይት፣ ትንተናና ክለሳ አማካይነት ፖለቲካዊ አጀንዳዎች ወደቋሚ ብሔራዊ ፖሊሲነት ስለሚያድጉ ነው፡፡ የተሳካ ፖሊሲ ለመቅረፅ በዚህ እርከን የተለያዩ የሕብረተሰብ ተወካዮች እንዲሳተፉ በማድረግ የተሻለ መድረክ መፍጠር የሚቻልበት ይህ የፖሊሲ ቀረፃ እርከን በመሆኑ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ነው፡፡

ሶስተኛው ደረጃ ፖሊሲ የመፈፀም እርከን ነው፡፡ ይህ እርከን ፖሊሲው ተግባራዊ የሚሆንበትን ሂደት የሚያካትት ነው፡፡ በመሆኑም ይህ እርከን አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም መንግስት በወረቀት ያሰፈራቸውንና በተግባር የሚፈፅማቸውን ተጨባጭ ሁኔታዎች በማነፃፀር እውነተኛ ባህርይውንና ማንነቱን ለማወቅ የሚቻልበት ነው፡፡

አራተኛውና የመጨረሻው ደረጃ የፖሊሲ ግምገማ እርከን ነው፡፡ በዚህ እርከን የአንድ ፓርቲ ወይም መንግስት ፖሊሲ በስራ ላይ በሚውልበት ጊዜ የታየውን ሁኔታ፣ የተከሰተውን አዎንታዊና አሉታዊ ውጤት ለመመዘን የሚቻልበት ነው፡፡ ከግምገማው የተገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ የፖሊሲ ማሻሻያ ሀሳቦች ሊመነጩ ይችላሉ፡፡ በኢዴአፓ እምነት በሀገራችን የሚዘጋጁ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲዎች እነዚህን ደረጃዎች በጠበቀ መንገድ ቢሰሩ በመሰረታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ መግባባት እንዲደረስ የሚያስችል የተሳካ ፖሊሲ ለማውጣት የተሻለው አማራጭ ነው፡፡

ከፖሊሲ አዘገጃጀትና አፈፃፀም ጋር አብሮ መታየት የሚገባው ነጥብ ስትራቴጂ የሚለው ፅንሠ ሀሳብ ምንነት ነው፡፡ ፓርቲያችን ስትራቴጂ በሚልበት ጊዜ አጠቃላይ የልማት አላማችንን ለማሳካት የምንከተለውን ቅደም ተከተል፣ ለፖሊሲዎቻችን ተግባራዊነት የሚያስፈልገውን ሪሶርስ አደረጃጀትና ዝግጅት የሚመለከት ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ስትራቴጂ የምንለው የታቀደ አላማን ደረጃ በደረጃ በማሳካት በረጅም ጊዜ ሊጨበጥ ይገባል ተብሎ ከታሰበው ግብ ለመድረስ አስፈላጊ የሆነውን ሪሶርስ የማዘጋጀት፣ የማደራጀትና የማንቀሳቀስ ሂደትን ለማመልከት ነው፡፡ ዓላማን ለማሳካትና ከታሰበው ግብ ለመድረስ የሚያስችል ቀልጣፋና ቀላል የሆነ ዘዴ ጥቅም ላይ በማዋል ለአፈፃፀም የሚረዱ ስርዓቶችን፣ አሰራሮችንና አደረጃጀቶችን ብቁና ውጤታማ እንዲሆኑ አድርጎ ማዘጋጀትን የሚመለከት ነው፡፡ ስትራቴጂም ቢሆን የረጅም ጊዜ አላማና ግብ እንዲሳካ የሚያስችል ሪሶርስ የሚገኝበትን፣ የሚዘጋጅበትና የሚደራጅበትን አጠቃላይ ማዕቀፍ ያስቀምጣል እንጂ መቸ ምን መሰራት እንዳለበትና በእነማን መሰራት እንደሚገባው ዝርዝር ጉዳዮችን አያሳይም፡፡ እንዲህ አይነቶቹ ዝርዝሮች በተግባር መርሃ ግብሮች በመሳሰሉት ውስጥ ተካተው የሚቀርቡ ናቸው፡፡

ስለዚህ በኢዴፓ ያቀረበው ብሔራዊ የልማት መስመርና ስትራቴጂ በዚህ ግንዛቤ ላይ የተመሰረተ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ኢዴፓ የመንግስት ሥልጣን የያዘ ሳይሆን ገና አማራጭ ፖሊሲ ሀሳቦችንና ስትራቴጂዎችን ለሕዝብ አቅርቦ ነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የመራጩን ሕዝብ ፈቃድና ውክልና በማግኘት የመንግስት ስልጣን ለመያዝ የሚታገል የፖለቲካ ድርጅት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ሰነድ የቀረቡት የፖሊሲ ሀሳቦች የልማት መስመርና ስትራቴጂዎች በፖሊሲ ማመንጨት ደረጃ ላይ ሊቀርቡ የሚችሉ የመነሻ ሀሳቦች እንጂ ሁሉንም ዝርዝር ጉዳዮች ሙሉ በሙሉ ያካተቱ ተደርገው መታየት የሚገባቸው አይደሉም፡፡ ዝርዝር ጉዳዮች በሕዝብ ተመርጦ የመንግስት ስልጣን የያዘ ፓርቲ የሀገሪቱን የሞያተኛ፣ የፋይናንስና የመረጃ አቅም ሙሉ በሙሉ እየተጠቀመ የሚያዘጋጃቸው እንደሚሆኑ በማመን በአጠቃላይ ጉዳዮች ላይ የመነሻ ሀሳቦችን በዚህ ሰነድ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ ይሁን እንጂ በአንዳንድ መሰረታዊ ጉዳዮች ደግሞ በመነሻነት ከሚታዩ አጠቃላይ ሀሳቦች ባሻገር የተወሰኑ ዝርዝር ነጥቦችን ለማቅረብና የፓርቲውን አቋም የበለጠ ግልፅ አድርጎ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

## 6.2 የልማት መስመርን በመምረጥና በመወሰን ሂደት ልንከተላቸው የሚገቡ መርሆዎች

ኢትዮጵያ ልትገነባው የሚገባት ስርዓት ፍትሀዊ ካፒታሊዝም መሆን እንዳለበት በግልፅ ተቀምጧል። ለሀገሪቱ የሚያስፈልጋት ስርዓት ፍትሀዊ የሆነ ካፒታሊዝም ቢሆን ይሻላል የሚል አማራጭ ማቅረብ ግን ብቻውን በቂ አይደለም። ይኸንን ስርዓት ለመመስረት መከተል የሚገባትን የልማት አቅጣጫና መርህ በሚገባ መለየት ያስፈልጋል። ተደጋግሞ ለማብራራት እንደተሞከረው የካፒታዝም ስርዓት ባህርይ ዋነኛ መገለጫዎች በአብዛኛው በግል ሀብት ባለቤትነት ላይ የተመሰረተ፣ በገበያ ውድድር የሚመራና ትርፍ በማግኘት ዓላማ ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚያዊ ስርዓት መሆን ናቸው። ነገር ግን ይኸንን ስርዓት የተቀበሉ ሀገሮች ሁሉ በእኩል የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ባለመሆናቸውና በተለይም ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ገና ወደ ካፒታሊዝም ስርዓት ግንባታ እንዲገቡ በሚጠበቁ ሀገሮች ያለው ሁኔታ የተለየ በመሆኑ ምክንያት ማንኛውንም ጉዳይ ለመፈፀም ሲፈልጉ ከዋሽንግተንና ከቶኪዮ ወይንም ከበርሊንና ከለንደን እየተዘጋጀ በሚወጣ አንድ አይነት መመሪያ እየተመሩ ይሰራሉ ማለት አይደለም። አንድ ወጥ ሆነው በተዘጋጁ የእድገት አቅጣጫዎችና መርሆዎች ከመመራት በስተቀር ወደግራም ወደቀኝም ወይንም ወደኋላም ወደፊትም ማየት እንዳይችሉ ሆነው ተሸብበዋል ማለትም አይደለም። ይህ የካፒታሊዝም ስርዓት መሰረታዊ ባህርይ አይደለም።

የካፒታሊዝም ስርዓት እሴቶችና ዋነኛ መገለጫዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንም ሀገር የሚጠቅመውን አቅጣጫና የአሰራር መርህ ለመከተል የሚያስችል መብት አለው። ማንም ሀገር እንደሚገኝበት ተጨባጭ ሁኔታ የሚስማማውን መንገድ መርጦ በሚስማማው ፍጥነትና መጠን ቢጓዝ የሚከለክል አስገዳጅ ሕግ የለም። ለምሳሌ አሜሪካ ከፍተኛ የቴክኒዎሎጂና የካፒታል አቅም ስለገነባች ለመጪው እድገቷ የምትመርጠው አቅጣጫና መርህ ይኸንኑ ነባራዊ አቅም ከግምት ውስጥ ያስገባና የካፒታሊዝምን መሰረታዊ እሴቶች የሚያጠናክር ነው። ኢትዮጵያ ደግሞ የካፒታልና የቴክኒዎሎጂ ድህነት ስላለባት የሰው ጉልበትና መሬትን በሰፊው የሚጠቀም የልማት አቅጣጫና መርህ ብትከተል በካፒታልና በቴክኒዎሎጂ ላይ ያልተመሰረተ የልማት አቅጣጫ ስለሆነ ከካፒታሊዝም ሕግ ወጥተሻል የምትባልበት መንገድ የለም። ስለዚህ ኢትዮጵያ መከተል የሚገባት የልማት አቅጣጫና መርህ ከራሷ አቅምና ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም መሆን አለበት። ኢትዮጵያ የምትከተለውን የልማት አቅጣጫ የምትመርጠውና የምትወስነው በራሷ አቅምና ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመስርታ ነው ሲባል ሌሎች ውጫዊ ሁኔታዎችን ችላ ማለት አለባት ወይንም አሁን ከምትገኝበት ሁኔታ ውጭ ስለወደፊቱ አስቀድማ ማሰላሰልና አርቃ መመልከት አይገባትም ማለት አይደለም። እነዚህ ሁሉ በልማት አቅጣጫ ምርጫና ውሳኔ ላይ በከፍተኛ ትኩረት ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው።

ኢትዮጵያ ወደ ካፒታሊዝም ሥርዓት ለመጓዝ የሚያስችላትን አቅጣጫና መርህ ለመወሰን ስታስብ የሌሎችን ሀገሮች ልምዶች የማገናዘብ መብት አላት። በአለማችን ብዙ ዓይነት የልማት ንድፈ ሀሳብ ሞዴሎችና ተሞክሮዎች አሉ። አንዳንዶቹ በተግባር ተፈትሸው ድክመታቸውና ጥንካሬያቸው ተለይቶ የታወቀ ናቸው። የውጤት ሞዴል ሆነው የሚታዩ የመኖራቸውን ያህል የውድቀት ሞዴል ሆነው የሚጠቀሱም አሉ። ጨርሰው ያልተፈተሹና ሰፊ አካዳሚያዊ ውይይት የሚካሄድባቸው ንድፈ ሀሳባዊ አስተሳሰቦችም አሉ። ኢትዮጵያ ከእነዚህ ሁሉ የሚበጃትን አገናዝባና ለራሷ እንደሚስማማት አስተካክላ ልትጠቀም ትችላለች። ከዚህ ላይ በጥንቃቄ መታየት ያለበት ለአንዱ ሀገር ውጤት ያስገኘ የልማት ሞዴል ለሌላውም ውጤት ያስገኛል ማለት አይደለም። በልምድነት የሚወሰደው የልማት ሞዴል ውጤታማነትና ውድቀት ልምዱን በሚቀስመው ሀገር ውስጥ በሚገኙ ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ሊወሰን የሚችል ነው። የልማት ልምዶች ከሌላ ሀገር ሲቀሰሙ እንደወረደ ተቀድተው የሚወሰዱበት ሁኔታ የለም። ለአዲሱ ሁኔታ እንደሚስማማ ሆነው ከዳበሩና ተገቢው ማሻሻያ ከተደረገባቸው በኋላ ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው። የልማት ልምዶችና ሞዴሎች ሲቀሰሙ በአንድ ሀገር ልምድ ላይ ብቻ መወሰን ግዴታ ስላልሆነ የተለያዩ ሀገሮችን በአማራጭነት ማየት የተሻለው መንገድ ነው።

ከተለያዩ ሀገሮች ልምዶች ለራስ ሁኔታ የሚስማሙትን እየመረጡ በመውሰድ አቀናጅቶ ስራ ላይ ማዋል ይችላል። ልምዶችና ሞዴሎች ሲቀዱ በርዕዮተ ዓለማዊ እይታ ብቻ የሚመዘኑበትን መንገድ መከተል ተገቢ አይደለም። የእድገት አቅጣጫን የመወሰን ጉዳይ ሁልጊዜ በርዕዮተ ዓለማዊ እይታ ብቻ የታጠረ እንደሆነ አድርጎ መመልከት ስህተት ነው። ቻይና ለዚህ ተገቢ ምሳሌ ተደረጋ ልትጠቀስ ትችላለች። ቻይና የኮሚኒዝምን ስርዓት እየተከተለች ከካፒታሊዝም ስርዓት የልማት ልምዶችና ተሞክሮዎች በሰፊው የምትጠቀም ሀገር ነች። የዚህ ዓይነቱ የመተጣጠፍ ችሎታዋ ላስመዘገበችው ከፍተኛ እድገት እንደአንድ ጠቃሚ ልምድ የሚታይ ነው። ቻይና ራሷን በርዕዮተ ዓለማዊ መመዘኛና እይታ ሸብባ ባለማስቀመጧና ለካፒታዝም የልማት ሞዴሎችና ልምዶች ፍፁም ገለልተኛ ባለመሆኗ ፈጣን እድገት እያስመዘገቡ ካሉ ሀገሮች ጎራ በግንባር ቀደምነት ለመሰለፍ ችላለች። ስለዚህ ኢትዮጵያ የልማት አቅጣጫዋን በምትመረጥበት ጊዜ ከአንድ ሀገር በተቀዳ ልምድ ብቻ ወይም በርዕዮተ ዓለማዊ እይታ ብቻ በታጠረ ሁኔታ እንድትፈጽመው የሚያስገድዳት ሕግ የለም። የእድገት አቅጣጫ ስትመርጥና ስትወስን ግርር ባለ አቋም ላይ ተመስርታ ሳይሆን በመተጣጠፍና ዙሪያ ገባውን ለመቃኘት በሚያስችላት ፈጠራ የተሞላበት ሁኔታ ላይ ተመስርታ መሆን አለበት።

ኢትዮጵያ የሌሎችን የልማት ሞዴሎችና ልምዶች በመቅሰም ለራሷ የልማት አቅጣጫ እንደሚጠቅም አድርጋ ሰራ ላይ በምታውልበት ጊዜ ከአሁኑ የውስጥና የውጭው ነባራዊ እውነታ ጋር ያላቸውን ትስስር ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባታል። ለምሳሌ ለታይዋንና ለደቡብ ኮሪያ ፈጣን እድገት ማስመዝገብ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደነበረው የሚታመንበት የቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት የሀይል አሰላለፍ አሁን በአለማችን ላይ አይታይም። ያኔ ዓለም በሁለት የተለያዩ ጎራዎች ተከፍላ ተሸናፊውና አሸናፊው ባልተለየበት ጊዜ የካፒታዝምን እድገት የተከተሉት ታይዋንና ደቡብ ኮርያ በቅርብ ከከበቧቸው ኮሚኒስት ቻይናና ሰሜን ኮርያ የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ከካፒታሊስቱ ጎራ የተደረገላቸውን ከፍተኛ ድጋፍ ዓይነት ለማግኘት በአሁኑ ጊዜ የሚታሰብ አይደለም። ኢትዮጵያ የካፒታሊዝምን ስርዓት ለመገንባት ስለወሰነች ብቻ ለእድገቷ መፋጠን የሚጠቅማትንና የምትፈልገውን ድጋፍ ሁሉ በምትፈልገው መጠንና ዓይነት፣ በፈለገችው ጊዜና ሁኔታ አሟልቶ የሚሰጣት እንዳለ ፍፁም የሆነ እምነት ልትጥል አትችልም። በመጀመሪያ ደረጃ ዋናው ኃላፊነት የራሷ መሆኑን ታሳቢ ያደረገ አቅጣጫ መምረጥ አለባት።

የሌሎችን የልማት ልምድና ሞዴሎች ለመቅሰም በሚሞከርበት ጊዜ አንድም ነጥብ ሳይጎድል ተግባራዊ ለማደረግ መወሰን ተገቢ ሊሆን አይችልም። ለምሳሌ አሁን በኢንዱስትሪ የበለፀጉት ሀገሮች ከእርሻ ወደ ኢንዱስትሪ ከመሸጋገራቸው በፊት የእርሻ ስራቸውን ምርታማነት ለማሻሻል ኬሚካል ማዳበሪያዎችን፣ ፀረ-ተባይ መከላከያዎችንና የመሳሰሉትን ከእነጉድለቶቻቸው ተጠ ቅመውባቸዋል። በአሁኑ ጊዜ ደግሞ እነዚህን የእርሻ ግብዓቶች መጠቀም በሰዎች ጤንነት፣ በሰብሎችና በእጽዋት እድገት ላይ በአጠቃላይ በአካባቢ ደህንነት ላይ ጠንቅ እያስከተሉ ነው በሚል በሌሎች ለአካባቢ ደህንነት ከባድ ጉዳት በማያስከትሉ ግብዓቶች ቀይረዋቸዋል። እኛ ግን ከዛሬ 50 እና 60 ዓመት በፊት ሌሎች ሀገሮች ተጠቅመው እድገት አግኝተውበታል በሚል ግርር ያለ አቋም በሰፊው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ከፍተኛ ፍላጎት አለን። አሁን ተሻሽለው በወጡትና ለአካባቢ ደህንነት ከባድ ጉዳት በሌላቸው የእርሻ ግብዓቶች ለመጠቀም ከመሞከር ፋንታ የቀድሞዎቹ የተጓዙበትን ጠመዝማዛ መንገድ አንድ እርምጃም ሳይቀነስ እንጓዘው ካልን ተገቢ አቅጣጫ ተከትለናል ለማለት አይቻልም። የራሳችንን ባህላዊ የእርሻ ማዳበሪያ ሚዛናዊ በሆነ አሰራር እያሻሻልን እንዳንጠቀም ወይንም ሌላ አዲስ አቋራጭ ፈልገን እንዳንጓዝ የተጣለብን ግዴታ ያለ ይመስል ሌሎች በተጓዙበት መንገድ ስንንቀረፈፍ መክረም ትክክለኛ የእድገት አቅጣጫ አይደለም። በሌላ አቅጣጫ ተጉዘን ወደካፒታዝም ስርዓት መድረስ እንደምንችል እርግጠኛ እስከሆንን ድረስ የግድ አሜሪካ በወጣችበት ዳገትና ጃፓን በወረደችበት ቁልቁለት ስናዘግም የመክረም ግዴታ የለብንም። ጀርመን የረገጠችውን እያንዳንዱን አሻራ ደግመን ለመርገጥ ግዴታ የሚጥልብን የለም። እንዲያውም እኛ ከእነሱ ልምድ ለመማር የታደልን በመሆናችን ለእነሱ የረዘመውን በማሳጠር፣ ለእነሱ አድካሚ የነበረውን ቀላል በማድረግ መራመድ የሚያስችለንን የልማት አቅጣጫ በመጓዝ እነሱ የገነቡትን ካፒታሊዝም ለመገንባት መሞከር ይኖርብናል። ስለዚህ የእድገት ልምዶችንና ሞዴሎችን ቀስመን የራሳችንን የተሻለ የልማት አቅጣጫ ለመከተል ስንነሳ መመዘኛዎቻችን መሆን ያለበት በተግባር የተፈተሹትን፣ ብዙ አደጋና ውስብስብነት የሌላቸውን፣ ለራሳችን ተጨባጭ ሁኔታ፣ አቅምና ፍላጎት

የሚስማሙትን መምረጥ ነው:: ከዚህ ውጭ ያሉትን ለመምረጥ ፈጽሞ አይቻልም የሚባል ነገር ባይሆንም የእኛ ሁኔታ ይኸንን ለማድረግ እድል የሚሰጥ አይደለም:: እንቅልፍ በሚነሳና ፋታ በማይሰጥ ድህነት ውስጥ የሚገኝን ሀገርና ሕዝብ ባልተፈተሹ ወይም ተፈትሸው ጥሩ ውጤት ባላመጡ ወይም ብዙ ዓይነት አደጋዎችና ውስብስብ ውጤት ሊያመጡ በሚችሉ ሞዴሎች ላይ የተመሰረተ አቅጣጫን መከተልና ሀገሪተን በቤተሙከራነት እንድታገለግል ማድረግ እጅግ አደገኛ ምርጫና ውሳኔ ነው::

አሁን ስልጣን ላይ ያለው ሕወሓት/ኢህአዴግ ያደረገው ምርጫና ውሳኔ ኢትዮጵያን የልማት አቅጣጫ ቤተሙከራ የሚያደርግ ነው:: አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከዚህ በፊት በሌሎች ሀገሮችና በከፊል በእኛም ሀገር ለሶሻሊዝም ስርዓት ግንባታ ተሞክሮ ውጤት ያልተገኘበት ሲሆን በአብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚመራ ካፒታሊዝም ደግሞ ጭራሽ በዓለም ታይቶና ተሰምቶም የማይታወቅ ነው:: ቻይናዎች ከካፒታሊዝም ጠቃሚ ልምዶች እየወሰዱ ለቻይና ኮሙኒዝም ግንባታ ማሳደጊያ አደረጉት እንጂ የእኛዎቹ አብዮታዊ ዴሞክራቶች ሊያደርጉ እንደሚፈልጉት በኮሚኒዝም ርዕዮተዓለም የሚመራ ኮሚኒዝም ለመገንባት ሳይሆን ለዚያው ለመረጡት ስርዓት የሚጠቅመውን ወስዶ ስራ ላይ ለማዋል ነው:: ስለዚህ የሚመሰርቱትን ስርዓት እሴቶችና መሰረታዊ መርሆዎች የሚሸረሽር ተቃራኒ አቅጣጫ የያዙበት ሁኔታ የለም:: ኢትዮጵያን አሁን የሚገዛው ፓርቲ ደግሞ በኮሚኒዝም እሴቶች ርዕዮተ ዓለማዊ መርሆዎች የተቃኘ ካፒታሊዝም መገንባት ይቻላል በሚል የካፒታሊዝምን እሴቶች የሚፃረር የእድገት አቅጣጫ መርጦ ሀገሪቱን ቤተሙከራ አድርጓታል:: በሁለት የማይጣጣሙ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ስርዓቶች መሀል ቆማ እንድትቀር በማድረግ ብሩህ ተስፋ የሌላትና በጨለማ ውስጥ የምትዳክር ሀገር አድርጓታል:: ሀገሪቱን በዚህ አላማውና ግቡ ግልፅ ሆኖ በማይታይና ወዴት እንደሚያደርስ ለመገመት በሚያስቸግር መንታ አቅጣጫ ውስጥ አስገብቶ ከድህነትና ከኋላቀርነት ለመውጣት በሚጓጓ ሕዝብ ላይ ትልቅ ግፍ እየፈፀመ ነው:: ለዚህ መያዣ መጨበጫ ለሌለውና አብዮታዊ ዴሞክራሲ ይገነባል ለሚባለው የውሸት ካፒታሊዝም የዚህች ድሃ ሀገር ውስን ሪሶርስ እየባከነ ነው:: በዚህች ድሃ ሀገርና ሕዝብ ስም የሚሰበሰብ የውጭ ብድርና እርዳታ ውሃ እየበላው ነው:: ሕዝቡና ሀገሪቱ ወደባሰ ድህነትና ውድቀት በሚያሽቆለቁሉበት ጊዜ አምባገነኖች እየበለፀጉና ዓለም አቀፍ ቱጃር እየሆኑ ነው::

የኢትዮጵያ የልማት አቅጣጫ ምርጫና ውሳኔ መካሄድ ያለበት ሕልውናቸው በአንድ ወይም በሌላ መንገድ በጉዳዩ በሚነካው በመላው የሀገሪቱ ዜጎች ነው:: በአንድ ፖለቲካ ፓርቲ መልካም ፈቃድ ወይም በአንድ ቅን አሳቢ ግለሰብ ፍላጎት ሊወሰን አይገባውም:: በአንድ ፓርቲ ወይም በአንድ ግለሰብ የሚቀርበው አማራጭ የልማት አቅጣጫ የፈለገውን ያክል ጠቃሚ ቢሆንና የፈለገውን ያክል በቅን መንፈስ ላይ የተመሰረተ ቢሆን እንኳ ዜጎች ሕልውናቸውን በሚመለከት ጉዳይ ላይ ተወያይተው የመወሰን መብታቸውን በሚነካ ሁኔታ እንዲፈፀም ማድረግ አይገባም:: አንድ ለሕዝብ ጥቅም ቆሜ እታገላለሁ የሚል ፓርቲ ወይም አንድ ለሀገሩ እድገት የሚቆረቆር ቅን ዜጋ መውሰድ የሚችለው የመጨረሻ እርምጃ ይጠቅማል ብሎ ያመነበትን አማራጭ ዜጎች በነፃነት ተወያይተው ከፈለጉ እንዲቀበሉት፣ ካልፈለጉ እንዲተዉት ወይንም እንዲያሻሽሉትና እንዲያዳብሩት ማድረግ ነው::

## 6.2.1 በውድድር መርህ የተቃኘ የገበያ ስርዓት መከተል

የልማት መስመራችንን ይዘት በተለያየ መንገድ ማቅረብ የሚቻል ቢሆንም ቁልፍ የሆኑትን ጉዳዮች ብቻ ለአብነት በማንሳት ነገሮችን ግልፅ ማድረግ የተሻለ ነው:: በሀገራችን ውስጥ የካፒታሊዝም ስርዓት መገንባት እንደሚገባው ግልፅ አቋም በመያዛችን በአማራጭነት የምናቀርበው የልማት መስመር በዚህ አጠቃላይ አቋም ማእቀፍ ስር የሚጠቃለል እንደሚሆን የታመነ ነው:: ኢዴፓ የካፒሊዝም ስርዓት ለኢትዮጵያ ያስፈልጋታል የሚል አቋም የወሰደው አንዳንዶቹ ብልጣብልጦች እንዳደረጉት ምርጫ በማጣትና ሳይወድ በግድ እጁን ተጠምዝዞ በመያዙ አይደለም:: የሀገራችንንና የምንኖርበትን አለም ተጨባጭ ሁኔታ በሚገባ ገምግሞና ተገንዝቦ የተሻለው የእድገት አማራጭ የካፒታዝም ስርዓትን መገንባት እንደሆነ በማመን ነው:: ስለሆነም የፓርቲያችን የልማት መስመር በይዘቱ ይኸንን አቋም የተከተለ መሆኑ አግባብ ነው::

ሀገራችን ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ለረጅም ጊዜ ግልፅ የሆነ የእድገት ራዕይና የልማት መስመር የሌላቸው አገዛዞች ሲፈራረቁበት በመቆየቷ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አደረጃጀታችንና የምንገኝበት የእድገት ደረጃችን ካፒታዝምን በቀላሉና በፍጥነት ለመገንባት የሚያመች አይደለም:: በየዘርፉ መዋቅራዊ ሽግግር ማድረግና አያሌ ውጣ ውረድ ማለፍ ይኖሪብናል:: በመጀመሪያ ትኩረት ከምንሰጣቸው ጉዳዮች መካከል በሀገራችን ኢኮኖሚ እንቀስቃሴ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ሲሰራበት የቆየውንና አሁንም ያልተወገደውን የመንግስት ሞኖፖሊ በማስቀረት በምትኩ የገበያ ኃይሎች ተገቢ ሚናቸውን የሚጫወቱበትና በውድድር መርህ የተቃኘ የገበያ ስርዓት ማስፈን ነው:: ይህ ተግባር በቀላሉ ይሳካል ተብሎ የሚታመን ባይሆንም የተከፈለው መስዋዕትነት ሁሉ ተከፍሎ መፈፀም የሚገባው ጠቃሚ ጉዳይ ነው:: መንግስት የፈለገውን እየሰጠና ያልፈለገውን እየነፈገ በኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ላይ ብቸኛው አዛዥ ናዛዥ ሆኖ በተቀመጠበት ሁኔታ ሀብት፣ እውቀትና ጉልበት ጠቃሚ በሆነ ልማት ላይ ተሰማርተው የተሳካ እድገት ሊገኝ የሚችልበት እድል የመነመነ ነው::

ፈጣን ልማት ማምጣትም ሆነ የካፒታዝምን ስርዓት በአስተማማኝ መሰረት ላይ ለማቆም የሚቻለው በውድድርና በገበያ ስርዓት እንጂ በመንግስት ትዕዛዝና ውሳኔ አይደለም:: የተሳካ ልማት አስመዝግበው ከፍተኛ የስልጣኔና የብልፅግና ደረጃ የደረሱት ሀገሮች ልምድ ያረጋገጠ ውም ይኸንኑ ነው::

መንግስት በገበያው ውስጥ ለሚሳተፉት ወገኖች የተስተካከለ የጨዋታ ሜዳ (level play ground) የመፍጠር ኃላፊነቱን በሚገባ እየተወጣ የገበያ ኃይልና ሚዛን የሆኑት (አቅርቦትና ፍላጎት) ሚና እንዲጠናከር መፍቀድ አለበት:: ይኸ ሲባል አንዱን ለመጥቀምና ሌላውን ለመጉዳት የፖሊሲ ማነቆዎችንና አስተዳደራዊ መሰናክሎችን በማበጀት ፋንታ በገበያ ውስጥ መግባት ለሚፈልጉት እኩል እድል መስጠት ይገባል ማለት ነው:: ካፒታዝም በመርህ ደረጃ ጥቂቶች ብቻ እንዲሳተፉና እንዲበለጽጉ ብዙዎቹ ደግሞ እንዲገለሉና እንዲደኸዩ የሚያደርግ አላማ አይከተልም:: ስርዓቱ ለሁሉም እኩል እድል በመስጠትና በውድድር መርህ የሚመራ ነው:: የካታሊዝም ስርዓት በነፃ ገበያና በውድድር መርህ ላይ የተገነባ በመሆኑ በዚህ ውስጥ መውደቅና መነሳት ይኖራል:: ነገር ግን ውድድር ስላለ ጥቂቶች ይጠቀማሉ ብዙዎቹ ይጎዳ ማለት ትክክል አይደለም:: በውድድር የተቃኘ የገበያ ስርዓት እንዲኖር የሚፈለገው አንድ ወገን ብቻ እንዲጠ ቀም በማሰብ አይደለም:: በዚህ ሂደት የሚፈጠረው ጥቅም የጋራ ነው:: አምራችና ተጠቃሚ፣ አገልግሎት አቅራቢና ተገልጋይ፣ ሻጭና ሸማች በውድድር መርህ በሚመራ የገበያ ስርዓት የየበኩላቸውን ጥቅም ያገኛሉ::

ነፃ ገበያና ውድድር ሲኖር ሻጭ ብቻ ሳይሆን ገዥም በተመጣጠኝ ዋጋ ጥራት ያለው ምርትና አገልግሎት የመሸመት እድል ያገኛል:: ሻጭም በቂ የግዥ ፍላጎት መኖሩን እርግጠኛ ሲሆን የምርትና አገልግሎት አቅርቦቱን መጠንና ጥራት በማሳደግ ተፈላጊውን ትርፍ ያገኛል:: በዚህ ሂደት ጠንክሮ የሚወጣና ደክሞ ከውድድሩ የሚወጣ ሊኖር ይችላል:: በዚህ መልክ በሚደረግ ውድድር አሸናፊውና ተሸናፊው የሚወሰነው አሁን በሀገራችን የመንግስት ስልጣን የያዙት አብዮታዊ ዴሞክራቶች እንደሚያደርጉት በዘርና በርዕዮተ ዓለም አመለካከት አይደለም:: አሸናፊውና ተሸናፊው የሚወሰነው ግልፅ ሆኖ በተቀመጠ የገበያ ውድድር ስርዓትና ሜዳ ላይ ነው:: በድርጅታዊ ስራና የጨረታ ሰነድ እየሰረቁ በማቀበል በሚካሄድ ሙስና ሳይሆን በግልፅ ጨረታና በሕጋዊ ውድድር ነው::

ካፒሊዝም አንድን ግለሰብ ወይም ቡድን ከሌሎቹ ለይቶ ለመጥቀም ሲባል የሚመሰረት ስርዓት አይደለም:: በካፒታሊዝም ስርዓት ከሚፈጠረው ልማት ጥቂቶች እየተጠቀሙ ብዙዎቹ የበይ ተመልካች እንዲሆኑ አላማው አድርጎ የሚሰራ ስርዓት አይደለም:: በካፒታሊዝም ስርዓት ውስጥ የልማት ማዕከል ሰው በመሆኑ በሰዎች መካከል ልዩነት የሚያደርግና በአድሎ ላይ የተመሰረተ አይደለም:: ልማት ለማንኛውም ሰው ጥቅም እንዲያስገኝ ታስቦ የሚካሄድ እንደመሆኑ ልማትን ለማምጣት መሳተፍ ለሚፈልጉት ሁሉ እኩል እድል መፍቀድ በካፒታሊዝም ስርዓት ተቀባይነት ያለው መርህ ነው:: በልማቱ እንቅስቃሴ ሂደት ውስጥ የተሻለ ዝግጅት፣ አቅምና ብቃት ማሟላት የቻለው በውድድሩ አሸናፊ ሆኖ ይዘልቃል:: ያልቻለው ደግሞ አቅሙና ችሎታው ወደሚፈቅድለት ሌላ መስክ ይሰማራል እንጂ እኛ ሀገር ሥልጣን በኃይል የያዙ አብዮታዊ

ዴሞክራቶች እንደሚያደርጉት የሰዎች የመደብ ጀርባ እየተመረመረ የፊውዳል ቅሪት፣ ነፍጠኛ ወዘተ. የሆነ የተሳትፎ እድል እየተነፈገው አብዮታዊ ዴሞክራት፣ የጎሣ ፖለቲካ ካድሬ ልዩ ድጋፍ እየተደረገለት የሚከናወን አይደለም። እንዲህ አይነት አብነቶችን እየጠቀሱ በውድድር የተቃኘ የገበያ ስርዓት ጥቅምና አስፈላጊነት በሰፊው ሊገለፅ ቢችልም ለተነሳንበት አላማ ይኸው በቂ ማሳያ ሊሆን እንደሚችል ይታመናል።

እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት መሰረታዊ ነጥብ ቢኖር የገበያ ጉድለቶችን በማስተካከል መንግስት የሚጫወተው አንዳችም ሚና አይኖርም ማለት አለመሆኑን ነው:: መንግስት ገለልተኛ መሆንና ለገበያ ኃይሎች እድል መስጠት ይገባዋል ሲባል ምን ማለት እንደሆነ በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል። መንግስት ገለልተኛ ይሁን ሲባል በአጭሩ አድሎ መፈፀም አይገባውም ማለት ነው:: አንዳንድ መንግስታት ቀደም ሲል የተፈፀመን አድሎ እናስተካክላለን በሚል ሽፋን ነባሩን አድሎ በአዲስ አይነት አድሎ የሚተኩበት ሁኔታ በተደጋጋሚ ጊዜ ሲፈፅሙ ይታያሉ። ልክ ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን እየተፈፀመ እንዳለው አሰራር ስህተትን በስህተት እያረሙ ልማት ማምጣት የሚቻል አይደለም። የመንግስት ሚና አንዱን እየደገፉ ሌላውን መጉዳት እስከሆነ ድረስ ትርጉም ያለው ልማት መፍጠር የማይታሰብ ነው:: እንዲያውም የመንግስት ቀዳሚ ኃላፊነት ሁሉም ዜጎች በሰላም ሰርተው እንዲኖሩ የሚያስችል ሕጋዊ ስርዓት ማስፈን ነው:: ለሁሉም ዜጎች እኩል ተፈፃሚነት ያለው ሕግ ማውጣትና አፈፃፀሙንም መቆጣጠር ነው:: የመንግስት ኃላፊነት በዚህ ብቻ የተገደበ አይደለም። ለልማት አመቺ የሆኑ የመሰረተ ልማት አገልግሎቶችን የማስፋፋት ከፍተኛ ኃላፊነት አለበት። በውድድር የተቃኘ የገበያ ስርዓት ሁልጊዜ ጉድለት የሌለበትና ሙሉ በሙሉ ውጤታማ ሊሆን ስለማይችል በዚህ በኩል የሚፈጠሩ ጉድለቶችን ሁሉ የመሸፈን ሚና መጫወት ይኖርበታል። ከዚህም በላይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ገና ወደ ካፒታሊዝም ስርዓት ግንባታ ማቅናት በሚጀምሩ ሀገሮች ያለ መንግስት የገበያ ጉድለቶችን መሸፈን ብቻ ሳይሆን ጉድለቶቹ ከቁጥጥር ውጭ ሄደው ከባድ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ እንዳያስከትሉ የማክሮ ኢኮኖሚ ማረጋጊያ እርምጃዎችን በሕጋዊ አግባብ መውሰድ ይኖርበታል። የዚህ አይነቱ የመንግስት ሚና እንደኢትዮጵያ ባሉ ሰፊ የገበያ ጉድለት ሊያጋጥማቸው በሚችሉ ድሃ ሀገሮች ቀርቶ የዳበረ ካፒታዝም በገነቡትም ሳይቀር የሕግን ስርዓት በተከተለና የገበያ ኃይሎችን ድርሻ ጨርሶ በማያጠፋ አሰራር ተግባራዊ የሚሆን ነው።

## 6.2.2 በሕግ አግባብ የሚመራ የመንግስት ተሳትፎን መፍቀድ

የካፒታሊዝም ስርዓት ግንባታ ልምዶች በሕግ የሚመራ የመንግስት ተሳትፎ መኖር ከካፒታዝም ስርዓት መርሆዎች ጋር ተጣጥሞ ሊሄድ የሚችልበት እድል መኖሩን በሚገባ አስመስክረዋል።

በነፃ ገበያ የሚያተርፉ አምራቾችንና አገልግሎት አቅራቢዎችን የሚያደፋፍራቸው አቅርቦትና ፍላጎት ብቻ ስለሆነ መንግስት እጁን ማስገባት አይገባውም የሚለው አስተሳሰብ እ.ኤ.ኤ በ1928/29 በካፒታሊስት ሀገሮች የታየው ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ እስከተከሰተበት ጊዜ ድረስ የቆየ አስተሳሰብ ነበር። ይሁን እንጂ ከተከሰተው የኢኮኖሚ ቀውስ ለመውጣት ብቻ ሳይሆን በዘለቄታው የተረጋጋና አስተማማኝ የኢኮኖሚ ሁኔታ እንዲኖር መንግስት ምትክ የማይገኝለት ሚና መጫወት ይገባዋል በሚል ኬይንስ የተባለው እንግሊዛዊ ኢኮኖሚስት ያቀረበው አዲስ አስተሳሰብ ተቀባይነት በማግኘቱ መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ በሕግ ስርዓት በግልጽ የተቀመጠ ሚና መጫወት ጀመረ። ከዚያ በኋላ የካፒታዝም ስርዓት ዋነኛ ባህርይ የሆኑትን የግል ሀብት ባለቤትነት መኖርን የነፃ ገበያ ውድድር ማካሄድና ለትርፍ የሚዘጋጅ ምርትና አገልግሎት ማቅረብን የሰው ልጅ መብት አድርጎ የሚቀበልና የግል ባለሀብቶችን እንደ አጋር የሚመለከት መንግስት በገበያ ኢኮኖሚ ውስጥ ጠቃሚ ተሳትፎ ማድረጉ ከሞላ ጎደል በሁሉም የካፒታሊዝም ስርዓት በገነቡ ሀገሮች የሚሰራበት ሆኗል። ስለዚህ በገበያ ኢኮኖሚው ውስጥ የሚፈጠሩትን ክፍተቶች በመድፈን፣ የግል ባለሀብቶች ትርፋማ ሆነው በማያገኟቸውና በቂ ተሳትፎ በማያደርጉባቸው የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች፣ በአጠቃላይ ለኢኮኖሚው መረጋጋት ቁልፍ አስተዋፅኦ ባላቸው የማክሮ ኢኮኖሚ እርምጃዎች መንግስት የሚያደርገው በሕግ የሚገዛ ተሳትፎ የገበያ ሕግን የሚፃረር ተደርጎ የሚወሰድበት ሁኔታ የለም።

በካፒታሊዝም ስርዓት ውስጥ የመንግስት ቀዳሚ ተግባር ሕግና ስርዓትን ማስከበር ቢሆንም በገበያ ሊሸፈኑ ያልቻሉትን የገበያ ጉድለቶች የመሸፈን ኃላፊነትም አለበት፡፡ ነገር ግን መንግስት የገበያ ጉድለቶችን የመሸፈን ሚናውን በሚጫወትበት ጊዜ ሁሉንም የገበያ ሕጎች እንዳይሰሩ እንቅፋት እየፈጠረ ወይንም እነሱን እየተካ ሊሆን አይገባም፡፡ ይልቁንም የመንግስት ሚና መሆን ያለበት ክፍተቶችን መሙላት፣ ገበያው በሚገባ መስራት በሚችልበት ሁኔታ ደግሞ እጁን መሰብሰብ ነው፡፡ በትዕዛዝና በመመሪያ ብቻ ሁሉም ነገር እንዲመራ በማድረግ ሳይሆን ለገበያ ኃይሎች እድል እየሰጠ የመንግስት ተሳትፎ ካልተጨመረበት ሊሟላ በማይችለው ጉደለት ላይ በሕግ በተወሰነ ስርዓት በመሳተፍ የገበያ ስርዓቱን የማጠናከር ሚና መጫወት ይገባዋል፡፡

አማራጭ የልማት መስመራችን መንግስት ዜጎች ባላቸው አቅም ሰርተው እንዲጠቀሙ፣ በሰላም ወጥተው እንዲገቡ፣ ምርትና አገልግሎት በሚያቀርቡና በተጠቃሚዎች መካከል ያለው ግንኙነት ሕጋዊ በሆነ መንገድ እንዲቀላጠፍ፣ የገበያ ውድድሩን የሚያደናቅፉ ችግሮች እንዲቃለሉ፣ የሌሎችን እድል የሚዘጋ ሞኖፖሊ እንዳይፈጠር፣ በልማት እንቅስቃሴና በአካባቢ ደህንነት መካከል ጤናማ ግንኙነት እንዲኖር የማድረግ ሚና ሊጫወት እንደሚችል ታሳቢ ያደረገ መስመር ነው፡፡ መንግስት ለካፒታሊስት ኢኮኖሚ መጠናከር የሚረዱ አሰራሮችን፣ አደረጃጀቶችንና ይኸንኑ በኃላፊነት የሚያስተባብሩ ዴሞክራሲያዊ ተቋሞችን የመፍጠር ሚናም ሊኖረው ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ የመንግስት ሚና በዚህ ብቻ የታጠረ መሆን የለበትም፡፡ ከዚህም በላይ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ የመፍጠር ሚና ሊጫወት ይገባዋል፡፡

መንግስት ማክሮ ኢኮኖሚን የማረጋጋት ተግባር የሚያከናውንበት የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም ዋና ዋናዎቹ ለገበያ ውድድሩ ብቻ ሊተው የማይገባቸውን የስራ አጥነትን ለመከላከል፣ የዋጋ ግሽበትን ለመቆጣጠር፣ የኢኮኖሚ እድገት መገታት እንዳይከሰት ለመከላከልና ጤናማ ያልሆነ የገቢና የወጪ ክፍያ ሚዛንን ለመቆጣጠር ነው፡፡ ይኸንን ዓላማ ለማሳካት ከሚያስችሉ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ መሣሪያዎች መካከል ደግሞ ከመንግስት ገቢና ወጪ ጋር የተያያዘው የፊስካል ገንዘብ ነክ ፖሊሲ፣ የውጭ ምንዛሬ ፖሊሲ፣ የገቢ ፖሊሲና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

በካፒሊዝም ስርዓት ውስጥ መንግስት እነዚህን የማክሮ ኢኮኖሚ ማረጋጊያ መሳሪያዎች በደንብ ካልተጠቀመ የኢንቨስትሜንት ፍሰት ይቆማል፡፡ የምርት ተግባርና ሀብት የማፍራት ስራ ይታወካል፡፡ ያልተጠበቀ የዋጋ መውጣትና መውረድ፣ የገቢ መቀነስ፣ የወጪና የገቢ ክፍያ ሚዛን አለመስተካከል፣ የስራ አጥነት መበራከትና ሌላም በርካታ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ያጋጥማሉ፡፡ ከዚህም አልፎ የሰላምና መረጋጋት መጥፋት፣ የማያባራ ብጥብጥና የፖለቲካ ቀውስ መከሰቱ የማይቀር ይሆናል፡፡ እነዚህን አደጋዎች ለመከላከልና ለማስወገድ የሚቻለው መንግስት የማክሮ ኢኮኖሚያዊ ማረጋጊያ መሳሪያዎችን በአግባቡ መጠቀም ከቻለ ነው፡፡

የፊስካል ፖሊሲ የሚለውና ከመንግስት ገቢና ወጪ ጋር የተያያዘው የማክሮ ኢኮኖሚ ማረጋጊያ መንግስት ከፍተኛ የስራ እድል እንዲፈጠርና የኢኮኖሚ መረጋጋት እንዲኖር የሚያስችለው ጠ ቃሚ መሳሪያ ነው፡፡ ኢኮኖሚው የመዝቀጥ አዝማሚያ በሚያሳይበት ጊዜ የስራ እድልንና ገቢን ለማሳደግ ሲባል መንግስት የታክስ ቅነሳ ለማድረግ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ ይጠ በቅበታል፡፡ ኢኮኖሚው የማንሰራራት አዝማሚያ ሲያሳይ ደግሞ የመንግስት ወጪን የሚቀንሱ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርበታል፡፡ በአጠቃላይ የታክስና /የገቢ/ የወጪ ስርዓቱን እንደሁኔታው ለማስተካከል በሚያስችል የፊስካል ፖሊሲ መሣሪያ ተጠቅሞ ኢኮኖሚውን የማረጋጋት ተግባር ያከናውናል፡፡

የገንዘብ ነክ ፖሊሲ መሣሪያን (monetary policy instrument) በመጠቀም መንግስት የሚዘዋወረውንና የሚቀመጠውን ገንዘብ አቅርቦት እንዲሁም የወለድን መጠን በመቆጣጠር የዋጋ ሁኔታንና በአጠቃላይ ኢኮኖሚውን የማረጋጋት ሚና መጫወት ይገባዋል፡፡ መንግስት የዋጋ ማረጋጊያ እርምጃ መውሰድ ያለበት ያለምክንያት አይደለም፡፡ ዋጋ ሲጨምር የገንዘብ ግሽበት ይከሰታል፡፡ የዚህ አይነቱ ክስተት በዜጎች ዘንድ ስጋት ስለሚፈጥር ሰዎች ያላቸውን ገንዘብ በማውጣት ለዛሬ ብቻ ሳይሆን ለነገና ከተነገ ወዲያ የሚያስፈልጋቸውን እቃ በአንዴ ለመግዛት ይጥራሉ፡፡ በገንዘብ መልክ የሚስቀምጡት ስለማይኖር ወደ ምርት ኃይል ሊቀየር የሚችል መዋዕለ ነዋይ በምርት ተግባር ለመመደብ አይቻልም፡፡

የዋጋ መናር በሸማቾች ላይ ከባድ ጉዳት እንደሚያስከትል ሁሉ የዋጋ መውደቅም አምራቾችን ስለሚጎዳ የማምረት ተግባር እንዲታወክና ምርት እንዲቀንስ ያደረጋል። የዋጋ መናር የሚከሰተው ምርት ሲያንስና የፈላጊው ቁጥር ሲበዛ ነው። የገበያ ዋጋ የሚወድቀው ብዙ ምርት ሲኖርና የፈላጊው ቁጥር ሲያንስ ሲሆን በዚህም ምክንያት የምርት መቀነስ ይከተላል። በውጤቱም የሰራተኛ ከስራ መቀነስና የስራ አጥነት ችግር መባባስ ይመጣል። ይኸንን አደጋ ለመከላከል በመንግስት የሚወሰዱ እርምጃዎች መኖር አለባቸው። መንግስት ገንዘብ የማሳተም ስልጣን የእሱ ከሆነ ወይንም ይህ ተግባር በብሔራዊ ባንክ የሚከናወን በሚሆንበት ጊዜ ከዚሁ ተቋም ጋር በመቀናጀት የሚዘዋወረውን የገንዘብ አቅርቦት ይወስናል። የገበያ ዋጋ እንዳይጨምር የመጀመሪያው ጠቃሚ እርምጃ ምርትን መጨመር ነው። ሌላው ኢኮኖሚው እንዳይጎዳ፣ የገበያ ዋጋ እንዲረጋጋ፣ ኢንቨስትመንት እንዲጠናከርና ስራ አጥነት እንዲቀንስ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚዘዋወረውን የገንዘብ መጠን በሚፈልገው ልክ እንዲሆን ማድረግ ነው። እንደዚሁም ወለድን ለቆጣቢዎች (ለአስቀማጮች) በሚጠቅም ሁኔታና ገንዘብ ያላቸውም ሆኑ ከባንክ ተበድረው በልማት ተግባር ለመሰማራት የሚፈልጉትን ለማበረታታት በሚያስችል መጠ ን መወሰን ያስፈልጋል።

ከዚህ በተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ ከውጭ ለምናስገባቸው ምርቶች አገልግሎቶች እንዲሁም ለውጭ እዳ ክፍያ የሚያገለግል እንደመሆኑ በዚህም ረገድ መንግስት የሚጫወተው ሚና ቀላል አይደለም።

መንግስት ማክሮ ኢኮኖሚን የሚያረጋጋበት ሌላው የፖሊሲ መሣሪያ ገቢ (Income) ነው። የሀገሪቱ ዜጎች በአብዛኛው ገቢያቸውን የሚያገኙት ከተሰማሩበት የእርሻና የንግድ ስራ ነው። ከዚህ ቀጥሎ ከፍተኛው የዜጎች የገቢ ምንጭ ደመወዝና የስራ ክፍያ ነው። ከጡረታ አበል በሚገኝ ገቢም የሚተዳደሩ አሉ። ከአክሲዮን በሚገኝ ድርሻ፣ ከኪራይ፣ ከመንግስት በሚሰጥ እርዳታ ገቢ የሚያገኙ የተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች አሉ። በዚህ መንገድ ዜጎች ከሚያገኙት ገቢ ለታክስና ለማህበራዊ ዋስትና የሚከፍሉት መዋጮ ተቀንሶ የሚቀረው መጠን የአንድ ቤተሰብ የተጣራ የግል ገቢ ነው። በሀገራችን በአማካይ ከ5 የማያንስ ቤተሰብ ያለው የቤተሰብ ኃላፊ የወር ገቢ ስምንት የአሜሪካ ዶላር ገደማ ነው። ከዚህ ውስጥ 60% በላይ ለዕለት ፍጆታ የሚውል በመሆኑ ለቁጠባ የሚሆን ተቀማጭ ነገር የለም ማለት ይቻላል። ከጉልበቱ በስተቀር በአስቀመጠው ጥሪት የሚጠቀመው እጅግ አነስተኛ ነው፡ የመኖሪያ ቤት መስራት እንደ መሰረታዊ ነገር መሟላት ሳይሆን የሀብትና የማህበራዊ ቦታ መለያ ተደርጎ ነው የሚታየው። መኪና ካለ ደግሞ የሀብት ደረጃ ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል። በተመሳሳይ መንገድ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ቪዲዮ፣ ማቀዝቀዣና የልብስ ማጠቢያ ማሽን ያለው ሰው ባለጸጋ ተደርጎ ነው የሚታየው። በሀገራችን ውስጥ እነዚህን ጥሪቶች ማሟላት የቻሉት ዜጎች መጠን እጅግ አነስተኛዎቹ ብቻ ናቸው።

ከእነዚህ መካከል አብዛኞቹ በከተማ ውስጥ የሚኖሩ ናቸው። ለቤት ግንባታ፣ ለጥሪት መግዣና ለአደጋ ጊዜ መጠባበቂያ የሚሆን ቁጠባ የሚያደርጉ ዜጎች ቁጥር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ሰራተኞች ከደሞዛቸውና ከተለያዩ የማህበራዊ ዋስትና መዋጮዎች ቁጠባ እንዲያደርጉ፣ የባንክ ተቀማጭ እንዲኖራቸውና የጥሪት ክምችት እንዲያፈሩ የሚያደፋፍር አሰራር በሀገቱ ውስጥ የለም። የቤት ግንባታ፣ ለሚያካሂዱ፣ የማህበራዊ ዋስትና መዋጮ ለሚከፍሉና ለመሳሰሉት ዜጎች ካፒታል ማፍራት እንዲችሉ ማበረታቻ እርምጃ መውሰድ ይገባል። በመንግስት በኩል ምርታማነትን የሚያሳድጉና ገቢን የሚጨምሩ እርምጃዎችን ከመውሰድ ጎን ለጎን የታክስ ቅነሳ፣ ጉርሻና የመሳሰሉ ፕሮግራሞች ተቀርፀው በስራ ላይ ካልዋሉ ካፒታል የመፍጠር አቅም ሊፈጠርና ሊጠናከር አይችልም። ለሰራተኞቻቸው ጥሪት ክምችት ተጨባጭ ጥረት ለሚያደርጉ፣ ከሰራተኞቻቸው ጋር በሚያደርጉት የሕብረት ስምምነት ለካፒታል ክምችትና ቁጠባ የሚረዳ እርምጃ ለሚወስዱ ባለሀብቶችም ሆነ ለቤት መስሪያና ለማህበራዊ ዋስትና መዋጮ በባንክና በሕብረት ስራ ማህበራት አማካይነት ቁጠባ ለሚያደርጉ ሰራተኞች የማበረታቻ ጉርሻና የታክስ ቅነሳ ድጋፍ ካልተደረገላቸው ዜጎች ጥሪት በማፍራትና ካፒታል በማከማቸት ሕይወታቸውን ሊለውጡ አይችሉም።

የዜጎች የኑሮ ደረጃ የሚወሰነው በገቢያቸው ብቻ ሳይሆን በዋጋ ሁኔታም ጭምር ነው፡፡ የተረጋጋ የዋጋ ሁኔታ መፍጠር ለዜጎች ሕይወት መረጋጋት ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ የገንዘብ ምንዛሬ በየጊዜው የሚወድቅ ከሆነ የዋጋ አለመረጋጋትና የኑሮ መወደድ ስለሚፈጠር ዜጎች ለከፋ የኑሮ ሁኔታ ይጋለጣሉ፡፡ ለምሳሌ የቡና ዋጋ በአለም ገበያ መውደቅና በሌሎችም ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ተፅዕኖ ወይንም በቀረጥ መጨመርና በፍላጎት ማደግ ወዘተ. የተነሳ የግሽበት መጠን ከጨመረ የኑሮ መወደድና የመግዛት አቅም መውደቅ ይፈጠራል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ እንዳይፈጠር የማክሮ ኢኮኖሚ ማረጋጊያ እርምጃዎች መውሰድ ከመንግስት የሚጠበቅ ነው፡፡ የፊስካል፣ የብድር፣ የውድድር ፖሊሲዎችን እንደሁኔታው ለችግሩ መፈታት በሚጠቅም መንገድ ስራ ላይ ከማዋል ጎን ለጎን ዋጋ በገበያ ኃይሎች እንዲወሰን መፍቀድ ተገቢ ነው፡፡ መንግስት የማረጋጊያ እርምጃዎች ሊወስድ ይገባል ሲባል የገበያ ኃይሎችን ሙሉ በሙሉ ከጨዋታ ውጭ አድርጎ ዋጋን እንደፈለገው እሱ ብቻ ይወስን ከተባለ ከቀውስ መውጣት አይቻልም፡፡

በገበያ ኢኮኖሚ የማይፈለግ እድገት ሊከሰት ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ክስተት ለመቆጣጠር መንግስት የበጀትና የታክስ የገንዘብ አቅርቦት፣ የወለድ፣ የገቢና የዋጋ ማረጋጊያ ፖሊሲዎችን በመጠቀም የማስተካከል እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለበት፡፡ የኢኮኖሚ ማረጋጊያ ሕግ አውጥቶ ሁኔታውን ጤናማ ማድረግ ይገባዋል፡፡ ምንም እንኳ ሁሉንም በአንድ ጊዜ ማሳካት ባይቻልም ፈጣንና በቂ በሆነ የእድገት ሁኔታ ውስጥ የተረጋጋ ዋጋ፣ የስራ እድልና ሚዛኑን የጠበቀ የውጭ ኢኮኖሚ እንዲፈጠር ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ ይኸንን መንገድ መከተል የሚገባው መንግስት ብቻ ሳይሆን የገንዘብ አቅርቦት ኃላፊነት የተሸከመው ነፃ የፌዴራል ባንክ፣ ለኢኮኖሚው ሰፊ የኃላፊነት ድርሻ የተሸከሙት የሰራተኛ ማህበርና የአሰሪዎች ማህበርም ይኸንኑ ጠቃሚ ሚና እንዲጫወቱ ይጠበቃል፡፡ የገንዘብ ነክና ፊስካል ፖሊሲን በማስተባበር ተሳትፎ ማድረግ የሚገባቸው ክፍሎች ማለትም የኢኮኖሚ ፖሊሲ የማውጣት ሕጋዊ ኃላፊነት ያለባቸው ወይም የፋይናንስ እቅድ የሚያወጡ ክፍሎች የአጠቃላዩን ኢኮኖሚ አዝማሚያ የሚገመግሙ ሞያተኞችና የመሳሰሉት ሁሉ ናቸው፡፡

በየጊዜው የሚመዘገብ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት መልሶ እንዳይቀለበስ ወይም ተጨማሪ እድገት በተከታታይ እንዲኖር ለማድረግ በሳይንስና ቴክኒዎሎጂ መስክ የተመዘገቡ ፈጠራዎችን ማዋሃድ ይገባል፡፡ ከአለም ገበያ ሁኔታ ጋር ራስን እያስተካከሉ መጓዝም እንደዚሁ በማያቋርጥ መንገድ መከናወን የሚገባው ነው፡፡ በርግጥ ይህ ቀላል ተግባር ተደርጎ የሚታይ አይደለም፡፡ ለምሳሌ የቡና ዋጋ በአለም ገበያ በሚወድቅበት ጊዜ ሁሉም ነገር አብሮ ቀጥ እንዳይል ፈጣን የማስተካከያና የጉድለት ማካካሻ እርምጃዎችን መውሰድ ይገባል፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ስራ አጥ በበዛበት ሀገር የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠርና ገበያውን ለማረጋጋት በገበያ ውስጥ የሚዘዋወረውን ገንዘብ ከመቀነስ ይልቅ የተሻለው መፍትሔ ምርትን ማሳደግ ነው፡፡

ሥራ አጥነትን መቀነስ የመንግስት ፖሊሲ ማዕከላዊ ተግባር እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡ ተጨማሪ የስራ እድል እንዲኖር ደግሞ ቁልፍ ጉዳይ ኢንቨስትሜንትን ማጠናከር ነው፡፡ ኢንቨስተሮች አትራፊ ሆነው እንዲሰሩና ተጨማሪ ኢንቨስትሜንት እንዲሳብ ለማድረግ በስራ ብቃታቸው መጠን ለእያንዳንዱ ኢንቨስተር በመንግስት በኩል የማበረታቻ ድጋፍ መስጠትና የገበያ ኃይሎች ይበልጥ እንዲደፋፈሩ መርዳት አለበት፡፡ ይህ ሲባል መንግስት በኢኮኖሚው ላይ ያለው ተፅዕኖ ከሚፈለገው በላይ መለጠጥ አለበት ማለት አይደለም፡፡ ለገበያ እንቅስቃሴ እንቅፋት የሆኑ የመቆጣጠሪያ ስርዓቶችን እያበዛ ነፃ ገበያውን እንዳይላወስና አዳዲስ እድገት እንዳይመዘገብ በሩን ሁሉ መያዝ አለበት ማለት አይደለም፡፡

ለዓለም ገበያ ከፍተኛ ምርት የሚያቀርቡ ሀገሮች ከኤክስፖርት የሚያገኙት ጥቅም እንዳይጓደል ማንኛውንም ዓይነት ጥበቃ የሚቃወሙትንና ነፃ የዓለም ንግድ እንዲኖር የሚጥሩትን ያክል አስፈላጊ ሆኖ በሚያገኙት ጊዜ የራሳቸውን ምርትና አምራቾች ለመጠበቅ የሚያስችል እርምጃ ይወስዳሉ፡፡ ጠንካራ የኤክፖስርት አቅም የሌላት ኢትዮጵያ ደግሞ የሀገሪቱን ባለሀብቶች ከውድድር ውጭ የሚያደርግ ኪሳራ እንዳይደርስባቸው ጥበቃ በማድረግ የራሷን ጥቅም የመከላከል ኃላፊነት እንዳለበት መረዳት ይገባል፡፡

## 6.2.3 **ኢንዱስትሪን ዋነኛ የልማት አንቀሳቃሽ ሞተርና ውጤት ሊያደርግ የሚችል ስትራቴጂ**

በኢዴፓና በአብዮታዊ ዴሞክራቶች (በኢህአዴግ) መካከል ካሉት በርካታ መሰረታዊ ልዩነቶች መካከል አንዱና ዋነኛው በዚህ አቅጣጫ ረገድ ያሉን አቋሞች የተራራቁ መሆናቸው ነው:: ኢዴአፓ ኢንዱስትሪን የልማታችን ዋነኛ ሞተርና የልማት ውጤት ሊያደርግ የሚችል ስትራቴጂ መከተል ያፈልጋል ሲል አብዮታዊ ዴሞክራቶች ከሚያቀነቅኑት ገጠርን ማዕከል ካደረገ የግብርና መር ስትራቴጂ የተለየ አቋም እንዳለው የሚያሳይ ነው:: ኢንዱስትሪን የልማታችን ዋነኛ ሞተርና የልማት ውጤት ያደረገ ስትራቴጂ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከመዘርዘራችን በፊት የአብዮታዊ ዴሞክራቶችን የግብርና መር ስትራቴጂ ለምን እንደማንደግፍ ግልፅ ማድረግ ያስፈልጋል::

አብዮታዊ ዴሞክራቶች ግብርና መር ስትራቴጂ ለመከተል የወሰኑበትን ምክንያት በተደጋጋሚ ጊዜ ሲገልፁ እንደሚሰማው ከኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል 85% የሚሆነው ኑሮ የተመሰረተው በግብርና ላይ ስለሆነ ነው የሚለው አንደኛው ምክንያት ነው:: ይሁን እንጂ መተዳደሪያው ግብርና የሆነው አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ አስከፊ የሆነ ሕይወት ከመግፋት በስተቀር ከኢህአዴግ የልማት ፖሊሲ እስካሁን የተረፈው ነገር እንደሌለ የሚታወቅ ነው:: ሌላኛው ምክንያታቸው ከሀገር ውስጥ አጠቃላይ ምርት 50% የሚሆነው ከግብርና የሚመጣና ከሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ግኝት ውስጥ 90% የሚመነጨው፣ እንዲሁም ለሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች 70% የጥሬ እቃ ምንጭ የሆነው ግብርና ስለሆነ ነው የሚል ነው:: ነገር ግን የኢትዮጵያ ግብርና እጅግ ኋላቀር በሆነ የምርታማነት ደረጃ ላይ የሚገኝ እንደመሆኑ ከዚህ ዘርፍ የሚገኘው ድርሻ ከሀገሪቱ ጠቅላላ ምርት ውስጥ ያለው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑ የምንገኝበትን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ችግር ከሚያሳይ በስተቀር ለልማት የተሻለ መነሻ ሊሆን እንደሚችል አያመለክትም::

85% የሚሆነው ሕዝብ የሚተዳደርበት የሀገራችን ግብርና ለጠቅላላው የሀገሪቱ ዜጎች አስተማማኝ የምግብ ዋስትና ሊያገኝ ቀርቶ በቀጥታ በግብርና ለተሰለፉትም በምግብ ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግ አልቻለም:: ከዚህ ዘርፍ የምናፈራው የውጭ ምንዛሬ ግኝትም ለዘላቂ ልማት የሚያግዝ በቂ የውጭ ምንዛሬ ባለቤት ሊያደርገን ቀርቶ መሰረታዊ ለሆኑ ምርትና አገልገሎት ግዥ ለማካሄድ ከውጭ የምናስገባውን ብድር መጠን እንድንቀንስ እንኳ በበቂ ሁኔታ አላገዘንም:: ከግብርና በሚገኝ ጥሬ እቃ እየተጠቀሙ የሚያመርቱ የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎቻችን ሁኔታ ደግሞ በመጠንም ሆነ በጥራት በአለም ተወዳዳሪ መሆን ቀርቶ የሀገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ፍላጎታችንን እንኳ የማያሟሉ ከመሆናቸውም በላይ ሰፊ የስራ እድል፣ ትርጉም ያለው ቁጠባና የካፒታል ምስረታ ለማድረግ የሚችሉ አይደሉም:: ከግብርና የሚገኘው ምርት ከእጅ ወደ አፍ ከመሆን አልፎ ገቢን የሚያሳድግ፣ ቁጠባንና የካፒታል ክምችትን የሚያጠናክር አይደለም:: የቴክኒሎጂ ሽግግር እንዲኖር እድል የማይሰጥና ኋላቀር በሆነ መንገድ የሚከናወን በመሆኑ ለመጭው ጊዘ ብሩህ የልማት ተስፋ ለመጨበጥ የሚቻልበት አይደለም::

ሌላው የሚያቀርቡት ምክንያት ሀገሪቱ ከፍተኛ የካፒታል እጥረት ያለባት ስለሆነ በቀላሉ ማግኘት የምንችለውና የተጨበጠው የልማት መሳሪያችን የሰው ኃይልና መሬት በመሆኑ:: የሰው ኃይልንና የመሬትን ምርታማነት በማሳደግ ፈጣን የልማት እድገት አስመዝግበን የካፒታል አቅም እንፈጥራለን የሚል ነው:: በዚህ ሂደት ለንግድና ኢንዱስትሪ የሚሆን የካፒታል ክምችት በመፍጠር የሰራተኛ ጉልበትና የጥሬ እቃ ምንጭ በመሆን ግብርናው ሌሎችን የኢኮኖሚ መስኮች እየመራ ወደ ኢንዱስትሪ እንሸጋገራለን የሚል ነው:: ይሁን እንጂ በግብርናው መስክ የተሰማራውን የሰው ኃይልና የመሬትን ምርታማነት ለመጨመር የካፒታል ወጪ ሳይወጣ የሚሳካ ነገር አይደለም:: የካፒታል ወጪ ሳይኖር የገበሬ ማሰልጠኛዎችን ማስፋፋት፣ የተሻሻሉ የምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን ማቅረብ፣ የአፈር ማዳበሪያና የአካባቢ ጥበቃ ቴክኒሎዎጂን ማሟላት፣ ለመሬት ምርታማነትና ለግብርና ምርት እድገት የሚረዳ ምርምርና ስርፀት ማምጣት የሚቻል አይደለም:: በግብርና ስራ የተሰማራውን ገበሬ የትምህርትና የጤና አገልገሎት የካፒታል ወጪ ሳይኖር ማሟላት የሚቻል አይደለም:: የገበሬውን አመጋገብ የሚያሻሽሉ ሁኔታዎችን ለመፍጠር አነሰም በዛ የካፒታል ወጪ የሚጠ

ይቁ እንቅስቃሴዎች መኖራቸው አይቀርም:: የገበሬውን ምርት ወደ ገበያ ለማድረስና ለግብርና ስራ የሚያስፈልጉ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ለገበሬው ለማቅረብ የሚሰሩ የመንገድ ስራዎች ገበሬው የመስኖ እርሻ እንዲያስፋፋ የሚካሄዱ ግንባታዎች፣ ንፁህ የመጠጥ ውሃ ለማዳረስ፣ የተሻለ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመፍጠር ወዘተ. የሚከናወኑ የመሰረተ ልማት ስራዎች የካፒታል ወጪ የሚጠይቁ ናቸው:: እነዚህ ሁኔታዎች ካልተሟሉ ጉልበትን ብቻ በመጠቀም ፈጣን ልማት ማምጣትም ሆነ የካፒታል አቅም መፍጠር የማይታሰብ ነው::

መሬትን በሰፊው በመጠቀም ብቻ ፈጣን እድገት ማምጣትና የካፒታል ክምችት መፍጠር አይቻልም:: የመሬትን ምርታማነት የሚጨምሩ ግብዓቶችን ለማሟላት የሚረዳ ካፒታል ጥቅም ላይ ሳይውል የሀገሪቱ መሬት ከጫፍ እስከጫፍ ቢታረስ የሚገኝ ፈጣን እድገት የለም:: የመሬት ምርታማነት ለመጨመር አነሰም በዛም የካፒታል ወጪ መመደብ ይጠይቃል:: በአጭሩ በግብርናው ዘርፍ የተሰማራውን የሰው ኃይልና የመሬትን ምርታማነት ለመጨመር ከፍተኛ የካፒታል ወጪ ሳይመደብ የሚከናወን ቀላል ስራ አይደለም:: ከዚህ የከፋው ነገር ደግሞ ይኽ ሁሉ የካፒታል ወጪና ድካም በግብርናው ዘርፍ ከተካሄደ በኋላም እንኳ ቢሆን የሀገሪቱን ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ችግሮች በመፍታት ወደ ዘላቂ ልማት ወይም ወደ ኢንዱስትሪ ደረጃ እንደሚያሸጋግር እርግጠኛ መሆን አለመቻሉ ነው::

## 6.2.4 ግብርና ኢኮኖሚያችንን ሊመራ እንደማይችል ያሉን ተጨባጭ ልምዶች

ግብርናው የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ችግሮች ሊፈታና ወደዘላቂ ልማት ሊሸጋገር እንዳልቻለ ሁለት መሰረታዊ ነጥቦችን ብቻ በማንሳት ሁኔታውን መገምገም በቂ ነው:: የመጀመሪያው ነጥብ ላለፉት አራት አስርተ ዓመታት ገደማ በግብርናው ላይ ተመስርቶ ወደዘላቂ ልማት ለመሸጋገር የተደረጉ ሙከራዎች ውጤታማ ሳይሆኑ መቅረታቸው ሲሆን 2ኛው ነጥብ ደግሞ የሀገራችን ግብርና ለዘላቂ ልማት መረጋገጥ ዋስትና ሊሆን የሚችልበት ተስፋ የተመናመነ መሆኑ ነው::

የመጀመሪያውን ነጥብ አጠር ባለ መንገድ ለመገምገም እ.ኤ.አ ከ1950ዎቹ ጀምሮ በንጉሱ ጊዜ የተደረጉትን ሙከራዎች፣ በኋላም እ.ኤ.አ ከ11974 ጀምሮ በደርግ ጊዜ የነበሩትን ጥረቶች፣ እንደገና እ.ኤ.አ ከ1991 ወዲህ በህወሓት/ኢህአዴግ ጊዜ ከልማት ጋር በተያያዘ ያሉትን ልምዶች በመጠኑም መዳሰስ ያስፈልጋል::

### 6.2.4.1 ግብርና በንጉሱ ዘመን

በንጉሱ ጊዜ የተቀየሱትን ብሔራዊ የኢኮኖሚ አላማዎች የተከተሉ ልዩ ልዩ ስትራቴጂዎች ወጥተው ተሞክረዋል:: የመጀመሪያው ስትራቴጂ ኤክስፖርትን በማስፋፋት (export promotion) ላይ የተመሰረተ የልማት ስትራቴጂ ሲሆን ይኽም በወቅቱ ከነበረው ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታ በመነሳት የሀገሪቱን ልማት ለማፋጠን የተሻለው አማራጭ ነው ተብሎ ስለተገመተ የተቀየሰ ስትራቴጂ ነው:: በአንድ በኩል ሀገሪቱ ሰፊ የእርሻ መሬት ያላት በመሆኑ ይኽንን ሀብት ጥቅም ላይ በማዋል የውጭ ንግድ ቢስፋፋ ፈጣንና ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችል የተመቻ ውስጣዊ ሁኔታ አለ ከሚል ስሌት የተነሳ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከ2ኛው ዓለም ጦርነት ማብቂያ ጀምሮ ኢትዮጵያ ከውጭው አለም ጋር ያላትን ግንኙነት በማጠናከሯና ለሌላው አለም ክፍት እንድትሆን በመደረጓ የውጭ ንግድ በማስፋፋት ፈጣንና ዘላቂ ልማት የሚያስገኝ ምቹ ውጫዊ ሁኔታ ተፈጥሯል ከሚል እምነት በመነጨ የተቀየሰ ስትራቴጂ ነው:: በዚህም መሰረት ብዙዎቹ የመሰረተ ልማት ስራዎች ይኽንኑ የውጭ ንግድ እድገት ከማስገኘት እንቅስቃሴ ጋር እንዲያያዙ ተደረጉ:: ከጠቅላላው ኢንቨስትሜንት ውስጥ 60% የሚሆነው የውጭ ንግድን ለማስፋፋት በሚያስችል መሰረተ ልማት ግንባታ ላይ ተመደበ:: ሰፊ የእርሻ ክልል ለኤክስፖርት ገበያው የሚሆኑ ሰብሎችን ለማምረት ተግባር እንዲውል ተደረገ:: በዚያን ወቅት የሀገሪቱ የውጭ ንግድ የተመሰረተባቸው ዋነኛ መስኮች ቆዳና ሌጦ እንዲሁም ቡና ነበሩ:: በዚህ ስትራቴጂ መሰረት ዋነኛው ትኩረት የመሰረተ ልማት ግንባታ ቢሆንም ዞሮ ዞሮ ልማትን ለማፋጠን ከእርሻ ስራ የሚገኝ ምርት ኤክስፖርት በማድረግ ዓላማ የተቃኘ ነበር ማለት ይቻላል::

ሌላኛው ስትራቴጂ ከውጭ የሚገባውን ምርትና አገልግሎት በሀገር ውስጥ የመተካት (Import substitution) ስትራቴጂ ነበር፡፡ ይኸኛው ስትራቴጂ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት የውጭ ምንዛሬን መቆጠብና ለካፒታል እቃዎች ግዥ የሚሆን አቅም መገንባት፣ የሀገር ውስጥ ምርቶች እንዲስፋፉና ቁጠባ እንዲበረታታ በማድረግ ኢንቨስትሜንትን ማስፋፋት፣ በሀገር ውስጥ የሰው ኃይል ስልጠናና የቴክኒዎሎጂ መሻሻል እንዲጠናከር ማድረግ ወዘተ. ዓላማዎች ያሉት ስትራቴጂ ነበር፡፡ ይኸንን ስትራቴጂ ውጤታማ ለማድረግ እ.ኤ.አ. ከ1960ዎቹ መጀመሪያ አንስቶ የጨቅላ ኢንዱስትሪዎችን ጥንካሬ ለመጠበቅ በገቢ ንግድ ላይ ተከታታይ የታሪፍ ቁጥጥር ስራ ላይ ዋለ፡፡ በውጭ ንግድ ላይም እንደዚሁ የቁጥጥር ስራዎች ተግባራዊ ሆኑ፡፡

ኤክስፖርትን የማስፋፋቱም ሆነ ከውጭ የሚገቡትን በሀገር ውስጥ የመተካት ስትራቴጂዎች የአሰራር ቅደም ተከተልና የትኩረት አሰጣጥ ሁኔታ ልዩነቶች ቢኖራቸውም ሁለቱም የግብርናን ልማት በማሳደግ ወደ ፈጣንና ዘላቂ ልማት ማምራት ይቻላል በሚል አስተሳሰብ ላይ የተመሰረቱ ነበሩ፡፡ በመሆኑም የመንግስት የልማት እቅዶች ከዚህ አስተሳሰብ ጋር ተጣጥመው እንዲወጡ ተደረጉ፡፡ በንጉሱ ጊዜ እ.ኤ.አ ከ1957 እስከ 1973 የቆዩ ሶስት (3) የአምስት ዓመት እቅዶች የነበሩ ሲሆን ሁሉም የተጠቀሱትን ስትራቴጂዎች በመከተል የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ከ1957 - 1962 የቆየው የመጀመሪያው የአምስት ዓመት እቅድ ለኤክስፖርት መስፋፋት የሚያግዝ መሰረተ ልማት በመዘርጋት ላይ ያነጣጠረ ስለነበር ለቤት፣ ለትራንስፖርት፣ ለመገናኛ፣ ለግብርና ኢንቨስትሜንት ወዘተ. ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቷል፡፡ ከ1963 - 1968 የቆየው ሁለተኛው የአምስት ዓመት እቅድ ደግሞ መሰረታዊ ይዘቱ ከመጀመሪያው ያልተለየ ቢሆንም በቀጥታ ምርት ለማምረት በሚያስችል ኢንቨስትሜንት ላይ በማነጣጠር ለኢንዱስትሪ፣ ለማእድን፣ ለኃይል ማመንጫ፣ ለግብርና ጥናት፣ ለግብርና መረጃና ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ ለትምህርትና ስልጠና ትኩረት ሰጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ ከሌሎቹ ዘርፎች ጋር ሲነፃፀር በቀጥታ ለግብርናው የተመደበው ድርሻ ከጠቅላላው ኢንቨስትሜንት ውስጥ 6% ብቻ ስለነበር በዘርፉ መሰረታዊ ለውጥ አልታየም፡፡ ከ1968 እስከ 1973 የቆየውና 3ኛው የአምስት ዓመት እቅድ ከበፊቶቹ በተሻለ ሁኔታ ለግብርናው ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ የግብርናውን ልማት ያሻሽላሉ የሚባሉ በርካታ ሙከራዎች ተደርገዋል፡፡

በሶስተኛው የአምስት ዓመት እቅድ ለግብርናው የተለየ ትኩረት የተሰጠው እያደገ የመጣውን የሀገር ውስጥ ፍላጎት ለማሟላት በግብርና ምርት ረገድ ፈጣን እድገት ማምጣት እንደሚገባ ስለታመነበት፣ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን ብቻ ሳይሆን የውጭ ኢንቨስትመንትን በመሳብ የግብርና ምርቶችን በብዛት ኤክስፖርት በማድረግ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን የማስፋፋትና ኢኮኖሚውን በገንዘብ የማጠናከር አጣዳፊ ፍላጎት በመከሰቱ፣ ከ1960ዎቹ 2ኛ አጋማሽ ጀምሮ በተለያዩ ሀገሮች «አረንጓዴ አብዮት» በሚል ልማትን የሚያፋጥን ሰፊ ጥረት መጀመሩ በተወሰነ ደረጃ በኢትዮጵያ ውስጥ የመነቃቃት መንፈስ እንዲፈጠር በማድረጉና በመሳሰሉት ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች ግፊት ነበር፡፡ ለግብርናው ልማት ቅድሚያ የሚሰጥና በዚህ ላይ ተመስርቶ ፈጣንና ዘላቂ ልማት ማረጋገጥ የሚያስችል ፖሊሲ መከተል እንደሚገባ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ ግብርናውን በሁለት ዋና ዋና አቅጣጫዎች የማልማት ጥረት ተጀመረ፡፡ አንደኛው አቅጣጫ ጥቅም ላይ ያልዋለውን መሬት ለባሀብቶች በማከራየት ካፒታልን በሰፊው የሚጠቀም ሰፊ ኮሜርሻያል ፋርም ማስፋፋት ሲሆን ዓላማውም ግብርናውን ዘመናዊ በማድረግ ለገበያ የሚቀርብ ምርት እንዲጨምር ማድረግ ነበር፡፡

ሁለተኛው አቅጣጫ ደግሞ የተለያዩ ፓኬጆችን በማውጣትና የሰው ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀም የኤክስቴንሽን ስራ በገበሬዎች እርሻ ላይ በማስፋፋት የእርሻ መሳሪያዎችን የማሻሻል፣ የግብርናን ምርትና ምርታማነት የማሳደግ፣ የነፃ ገበያን የማስተዋወቅና የመሳሰሉት ዓላማዎች የነበሩት ነው፡፡

በኮሜርሻል ፋርም ሀብታቸውን ኢንቨስት ለሚያደርጉ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች ከ3-5 ዓመታት ከታክስ ነፃ በማድረግ፣ የእርሻ ማሽነሪዎችን ከቀረጥ ነፃ እንዲያገቡ በመፍቀድ፣ በአነስተኛ ወለድ የባንክ ብድር እንዲያገኙ በመርዳት፣ ከ200,000 ብር በላይ ኢንቨስት ላደረጉ የውጭ ባለሀብቶች ከገቢያቸው ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ወደ ውጭ ለማሸጋገር እንዲችሉ

በመፍቀድና በመሳሰሉት ዘዴዎች ማበረታቻዎችን እንዲያገኙ ተደረገ። እነዚህን ማበረታቻዎች እየተጠቀሙ ባለሀብቶች በስምጥ ሸለቆ በተለይም በአዋሽ ሸለቆና በሌሎችም የተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ኮሜርሻል እርሻዎችን ከፍተው እንቅስቃሴ ጀመሩ። ጠቃሚ የልማት ተሞክሮዎችን ያገኙና የግብርናውን ዘርፍ የማነቃቃት ሚና የተጫወቱ መሆናቸው ባይካድም የኢኮኖሚውን መዋቅር በመቀየርም ሆነ ወደዘላቂ ልማት በማሸጋገር ወሳኝ ድርሻ ይኖራቸዋል በሚል ተጥሎባቸው የነበረው ተስፋ ተጨባጭ ከመሆኑ በፊት በ1974 ሕዝባዊ አብዮት በመቀጣጠሉ በጅምር ቀሩ። በግል ባለሀብቶች ተጀምረው የነበሩት ኮሜርሻል ፋርሞች ወደመንግስት ንብረትነት ተዛውረው የመንግስት እርሻ ሆነው እንዲሰሩ ተደረገ።

በገበሬዎች እርሻ ላይ የተመሰረቱ ፓኬጆችን በማውጣት ኤክስቴንሽንን ለማስፋፋት የተያዘው አቅጣጫ ደግሞ ሁለት አይነት አቀራረቦች ነበሩት። እነዚህም አንደኛው አጠቃላይ ፓኬጅ ፕሮጀክት (comprehensive package project) የሚባለውና ሁለተኛው ደግሞ አነስተኛ ፓኬጅ ፕሮጀክት (minimum package project) የሚባለው ነው። የፓኬጅ አሰራር ማለት በመርህ ደረጃ ተግባራዊ እንቅስቃሴንና ልዩ ልዩ ሪሶርስን አቀናጅቶ ውጤታማ ለመሆን የሚያስችል እምቅ አቅም ባለባቸው መስኮች ላይ መጠቀም ማለት እንደመሆኑ የአጠቃላይም ይሁን የአነስተኛ ፓኬጅ ፕሮጀክቶች በዚህ መንፈስ የተቃኙ ነበሩ። በመሆኑም አጠቃላይ ፓኬጅ ፕሮጀክት በሁለት ደረጃዎች ተከፍሎ የተከናወነ ሲሆን የመጀመሪያው ከ1967 እስከ 1970 ሁለተኛው ደግሞ ከ1970 - 1975 የዘለቀ ነው። በዚህ ፓኬጅ ድጋፍ እ.ኤ.አ በ1967 የጭላሎ ግብርና ልማት አሀድ ካዱ (Chilalo Agricultural Developemnt Unit) በሚል ተጀመረ። የፕሮጀክቱ የመጀመሪያው ደረጃ እስከ 1970 ከተከናወነ በኋላ ከ1970 - 1975 ሁለተኛው ደረጃ የካዱ ፕሮጀክት ቀጠለ። ይኸንን አጠቃላይ ፓኬጅ ፕሮጀክት ተከትሎ በአለም ባንክ ድጋፍ የወላይታ ግብርና ልማት አሀድ ዋዱ (WADU) ፣ በአሜሪካ አለም አቀፍ ልማት እርዳታ የአድአ ወረዳ ልማት ፕሮጀክት አዲፕ (ADDP) እንዲሁም የታች አዲያቦና ሀድጊት ልማት አሀድ ታህዱ (TAHDU)፣ የደቡብ ክልላዊ ልማት አሀድ ፕሮጀክት ሶርዴፕ (SORDEP)፣ የሁመራ ግብርና ልማት ፕሮጀክት ሃድፕ (HADP) ተግባራዊ እንዲሆኑ ተሞክሯል።

የእነዚህ ፕሮጀክቶች አጠቃላይ አላማዎች 20 ሄክታርና ከዚያ በታች መሬት ያላቸውን ገበሬዎች ገቢ ማሳደግ፣ ዝቅተኛ የሆነ ገቢ ባላቸው ገበሬዎች ላይ ትኩረት በመስጠት የገቢ ልዩነት እንዲጠብ ማድረግ ተጨማሪ የስራ እድል መፍጠር፣ የገበሬዎችንና የአካባቢ መንግስት አካላትን የልማት ተሳትፎና ጥረት ማሳደግ፣ በሀገር ደረጃ የገጠር ልማትን ለማስፋፋት የሚያስችል ዘላቂ ዘዴ ለመፍጠር ተከታታይ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ ለወደፊቱ የተሻሉ ፕሮጀክቶችን ለመንደፍ የሚያስችል መረጃ ማሰባሰብ ናቸው። ከእያንዳንዱ ፕሮጀክት ልዩ ባህርይ ጋር የተያያዙ ዝርዝር አላማዎች ቢኖሩም ሁሉም የሚጋሯቸውና ዋና ዋና የሚሉት ጉዳዮች በሰብልና በእንስሳት ምርት ላይ ተግባራዊ ምርምር ማካሄድ፣ የተሻለ የእርሻ አሰራር መፍጠር፣ የተፈተሹ የቴክኒዎሎጂ ፈጠራዎችን በኤክስቴንሽን ፕሮግራም አማካይነት ማሰራጨት፣ የእርሻ ብድርና የገበያ አገልግሎት ማቅረብ፣ መጋቢ መንገዶችና የገጠር ውሃ አቅርቦት የመሳሰሉ የመሰረተ ልማት ስራዎችን መስራት፣ የአፈር ጥበቃ ማካሄድና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት፣ አርብቶ አደሮችን ማስፈርና ዘላቂ ኑሮ እንዲመሰርቱ ማስቻል የሚሉት ነበሩ። እነዚህን አላማዎች ለማሳካት ከፍተኛ ጥረት ከተደረገ በኋላ በተወሰኑት ጉዳዮች ላይ ውጤት ሲገኝ በሌሎቹ ደግሞ እንደታሰበው ሳይሆን ቀረ። ለምሳሌ የካዱም ሆነ ሌሎች የፕሮጀክት ሙከራዎች የፓኬጅ አሰራር እንዲለመድ ረድተዋል። በተለይም አነስተኛ እርሻ በማረስ ላይ የተመሰረቱ ገበሬዎችን ለመድረስና ለመደገፍ የፓኬጅ አቀራረብ ውጤታማ መሆኑን አሳይተዋል። የእርሻ ስራ ምርታማ እንዲሆን የግድ ሜካናይዝድ መሆን እንደሌለበት በቴክኒዎሎጂ ማሻሻያ ምርምሮች ተረጋግጧል። የደጋማው ገበሬዎች ለእርሻ ስራ ፈጠራዎችና ማበረታቻዎች ገንቢ ምላሽ እንደሚሰጡ በሚገባ አስመስክረዋል። እንደማዳበሪያና የተሻሻሉ የእርሻ መሳሪያዎችን በማሰራጨት ጠቃሚ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

እነዚህ ፕሮጀክቶች የመሬት ዋጋ ከፍ እንዲል ማድረጋቸው ተረጋግጧል። በሌላ በኩል ውጤታማ ያልሆኑባት ሁኔታዎች ነበሩ። ለምሳሌ የፓኬጅ ፕሮጀክቶችን በሀገር ደረጃ ለማስፋፋት ወድ ሆነው ተገኙ። ካዱ በ7 ዓመታት ውስጥ 37 ሚሊዮን ብር በመጠየቁ ከታሰበው በላይ ውድ መሆኑ ተረጋገጠ። የዋዱ ሰፈራ ወጪም ቢሆን የገጠር ስራ ለመፍጠር

የሚያስችል ርካሽ ዘዴ አለመሆኑ ታየ። በሁሉም ፕሮጀክቶች ፍትሃዊ የገቢ ክፍፍል የመፍጠር አላማ ውጤታማ ሳይሆን ቀረ። ከ15-20 ዓመታት ባለው ጊዜ ውስጥ 90% የሚሆነውን የሀገሪቱን ገበሬ በተመሳሳይ ፓኬጆች ለማዳረስ የታቀደው ሀሳብ በታቀደው ጊዜ ውስጥ እንደማይሟላ ተረጋገጠ። በእነዚህ ፓኬጆች ምክንያት በርካታ ጭሰኞችና አርብቶ አደሮች ከቦታቸው ተፈናቀሉ። ለምሳሌ ከካዱ የፕሮጀክት ክልል ብቻ የተፈናቀሉት ከጠቅላለው ነዋሪ ውስጥ ከ13-15% የሚሆኑት ናቸው። በዚህም የተነሳ ተጨማሪ የስራ እድል መፈጠሩ ቀርቶ ስራ አጥነት ተጠናከረ፣ በፕሮጀክቱ የተጠናከረው የእርሻ ሜካናይዜሽን ለግጦሽ መሬት መመናመን አስተዋፅኦ አደረገ።

የአነስተኛ ፓኬጅ ፕሮጀክቶች በተመሳሳይ ሁኔታ በሁለት ደረጃዎች የተከናወኑ ሲሆን የመጀመሪያው እ.ኤ.አ ከ1971 - 1978 ተግባራዊ ከተደረገ በኋላ ሁለተኛው ደግሞ እ.ኤ.አ ከ1981 - 1985 የቀጠለ ነበር። የመጀመሪውን ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የኤክስቴንሽንና የፕሮጀክት አፈፃፀም ልማት ኤፒድ በሚል አቀራረብ ተሞከረ። ይህ ፕሮጀክት እ.ኤ.አ ከ1971 እስከ 1985 የቆየ ሲሆን አላማውም በካዱና በዋዱ ከታየው ባነሰ ወጪ እያንዳንዱ ገበሬ የተሻለ እንዲያመርት ማድረግ፣ ባህላዊ እርሻን ማሻሻል፣ በልማት ወኪሎች አማካይነት በሚዘረጋ ኤክስቴንሽን፣ የተለያዩ የእርሻ ግብዓቶችንና የብድር አገልግሎችን ለተመረጡ ወረዳዎች በማቅረብ ዘዴ የግብርና አገልግሎትን ማስፋፋት ነበር። በዚህም መሰረት በአንድ የአነስተኛ ፓኬጅ ፕሮጀክት ስር አምስት የኤክስቴንሽን አካባቢዎችን በማቀፍ አንድ ሄክታር የሙከራና ሰርቶ ማሳያ ጣቢያ በማቋቋም፣ የገበያ ማዕከል በመመስረትና የተማሩ ገበሬዎችን እንደ ሞዴል በመውሰድ በአነስተኛ እርሻ ላይ የተሰማሩ ገበሬዎችን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ጥረት ተደረገ። የኢፒድ አፈፃፀም የገበሬዎችን የልማት ተሳትፎ እንዲጨምር አደረገ። የተሻሻሉ ግብዓቶች በገበሬው እንዲለመዱ በማድረግ የምርትና ገቢ መጠን እንዲጨምር አስቻለ። የአነስተኛ ፓኬጅ ፕሮጀክት ማዕከላትን የማቋቋም ግቡን አሳካ። ብዙሃኑ የተሻለ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስቻለ። በሞዴልነት የተመረጡ ገበሬዎችን መጠቀም በገጠር የተማሩ ሰዎች ቁጥር እንዲጨምር አገዘ። ይሁን እንጂ ከካዱና ዋዱ ባነሰ ወጪ ለመስራት የታቀደው ሳይሳካ ቀረ። በመልክዓምድራዊ ተፅዕኖዎች ሳቢያ የተወሰኑ የፓኬጅ አካባቢዎች ያሳዩት ፈጠራ ውስን ሆኖ ቀረ። ኢፒድ ባህላዊ ተግባሮችን ለማሻሻልና የማዳበሪያ መጠንን ለማለማመድ ያደረገው ሙከራ በሚገባ ተግባራዊ ሳይሆን ቀረ። የመሬት ይዞታ ማሻሻያዎች ባለመደረጋቸው የፕሮግራሙ ውጤታማነት የታሰበውን ያህል እንዳይራመድ አደረጉት። ተቋማዊ ሁኔታዎችና የአመራር ድክመቶች እንዲሻሻሉ ባለመደረጋቸው ፕሮጀክቱ ውጤታማ ሳይሆን ቀረ። የገቢ ልዩነት ከቀድሞውም በባሰ ሁኔታ ሰፋ። ግብዓቶችን መጠቀም ምርትን እንደሚጨምር በተግባር በመረጋገጡ ሜካናይዜሽን እንዲጠናከርና ጭሰኞች ከይዞታቸው እንዲፈናቀሉ ግፊት አደረገ።

የዚሁ አነስተኛ ፓኬጅ ፕሮጀክት ሁለተኛው ደረጃ እ.ኤ.አ የ1974ን ሕዝባዊ አብዮት ተከትሎ በመጣው የመሬት አዋጅ ምክንያት ተቋርጦ ከቆየ በኋላ እ.ኤ.አ ከ1981 - 1985 የቀጠለ ቢሆንም ከመጀመሪያው የተለየ ውጤት ለማምጣት ሳይችል አበቃ። በዚህኛው ፕሮጀክት የተማሩ ግለሰብ ሞዴል ገበሬዎች ሳይሆኑ የገበሬ ማህበራትና የአምራቾች ሕብረት ስራ ማህበራት እንዲሆኑ ተደረገ። የመሬት ባለቤትነትም ወደመንግስት የተዛወረ እንደመሆኑ እያንዳንዱ ገበሬ በአፈር ጥበቃና በአካባቢ እንክብካበ ያለው ተነሳሽነት እየሞተ ሄደ። በዚህ ላይ በምርምርና በኤክስቴንሽን ስራ መካከል ያለው ግንኙነት ከጊዜ ወደጊዜ እየላላ በመምጣቱና የምርምር ውጤቶችን የማባዛትና የማሰራጨት አቅም ከጊዜ ወደጊዜ ከመቀነሱም በላይ ፕሮጀክቱ እንደተፈለገው ውጤታማ ሳይሆን በመቅረቱ እ.ኤ.አ በ1985 ተቋረጠ።

## 6.2.4.2 ግብርና በደርግ ዘመን

እ.ኤ.አ ከ1974 ሕዝባዊ እንቅስቃሴና የመንግስት ለውጥ በኋላ እስከ እ.ኤ.አ 1991 ድረስ በግብርና ላይ ተመስርቶ ፈጣንና ዘላቂ ልማት ማምጣት ይቻላል በሚል አስተሳሰብ የተደረገው ሙከራ በተመሳሳይ መንገድ ውጤታማ ሳይሆን መቅረቱ የታወቀ ነው። በእርግጥ ይኸኛው በንጉሱ ዘመን የተጀመረውን የውጭ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት የመተካት (import substitution) የልማት ስትራቴጂ በመቀጠሉ፣ የኤክስፖርት እንቅስቃሴው በግብርና ምርቶች ላይ ጥገኛ ሆኖ በመቆየቱ፣ የገበሬዎችን አነስተኛ ይዞታ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ተጀምሮ የነበረውን የፓኬጅ አቀራረብና የኤክስቴንሽን መርሃ ግብር እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ

ስራ ላይ እንዲውሉ በማድረጉና በመሳሰሉት ሁኔታዎች ተመሳሳይ ጥረቶች የተደረጉበት ቢሆንም በዓላማ፣ በርዕዮተ ዓለም አመለካከት፣ በአደረጃጀትና በአሰራር ከቀድሞው የተለየ ስር ነቀል ለውጥ የተደረገበት ወቅት ነው። በኢኮኖሚው መስክ ብቻ የነበሩትን ጥቂት መሰረታዊ ለውጦች ብናይ የመሬት ባለቤትነት ሙሉ በሙሉ ወደመንግስት ከመዛወሩም በላይ በሀገር ውስጥና በውጭ ባለሀብቶች የተቋቋሙ ኮሜርሽያል ፋርሞች የፋይናንስና የኢንዱስትሪ ተቋሞች፣ የአገልግሎት መስጫዎችና ከእነሱም ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ ፋሲሊቲዎች ሙሉ በሙሉ በመንግስት ባለቤትነት ስር እንዲሆኑ የተደረገበት ወቅት ነው።

የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ አሰራሮች የተዘጉበትና ሁሉም ዓይነት ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በማዕከላዊ መንግስት እቅድ የሚመራበት ሁኔታ የሰፈነበት ወቅት ነው። አለም አቀፍ ንግድ በርዕዮተዓለም እይታ የተቃኘበትና ከምዕራቡ አለም ጋር ሀገሪቷ የነበራት የኢኮኖሚ ግንኙነት የተዳከመበት ወቅት ነበር። የግል ባለሀብቶች ተሳትፎ የተገደበበትና የግል ኢንቨስትሜንት የወደቀበት ወቅት ነበር።

ይሁን እንጂ በዚህም ወቅት ቢሆን የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ግንባር ቀደም መሪና የልማት አንቀሳቃሽ ሞተር ተደርጎ የተወሰደው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ነበር። በደርግ ዘመን የነበረው በየአምስት ዓመቱ የሚወጣው የአጭር ጊዜ እቅድና የ10 ዓመት መሪ እቅድ በግልፅ እንዳሰፈረው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ግንባር ቀደም ትኩረት የተሰጠውና በዚህ ዘርፍ በሚገኘው ውጤት ወደዘላቂ ልማት መሸጋገር ይቻላል የሚል እምነት ተይዞ ነበር። ከዚህ አመለካከት በመነሳት በመጀመሪያ በንጉሱ ዘመን የነበረው የኮሜርሽያል ፋርም በመንግስት ባለቤትነት ተቀይሮ እንዲቀጥልና የተማሩ ገበሬዎችን እንደሞዴል በመውሰድ በአነስተኛ ገበሬዎች ይዞታ ላይ ይከናወን የነበረውን የአነስተኛ ፓኬጅ አሰራር እ.ኤ.አ እስከ 1985 ድረስ የገበሬ ማህበራትንና የገበሬዎች አምራቾች ሕብረት ሥራ ማህበራትን እንደዋነኛ የኤክስቴንሽን ማስፋፊያ ማዕከል በአደረገ መንገድ ለማስፈፀም ተሞከረ። ከበፊቱ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ሳይቻል በመቅረቱ ሌላ አይነት ሙከራ ተጀመረ።

አዲሱ ሙከራ እ.ኤ.አ ከ1985 በኋላ የተጀመረና የአርሶ አደሮች የግብርና ልማት ፕሮጀክት ሲቀረፅ ቀደም ሲል በፓኬጅ ፕሮጀክቶች የተገኙትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመገምገም ከቀድሞው በተቀሰመው ልምድ ላይ ተመስርቶ በግብርናው ዘርፍ የተሻለ ውጤት ማምጣት ይቻላል የሚል እምነት በመያዝ ነበር። አላማውም ከፍተኛ ፖቴንሽያል ባላቸው የሀገሪቱ ደጋማ አካባቢዎች የግብርናን ምርታማነት ማሳደግ፣ ተጨማሪ የአፈር መሸርሸርና የመሬት መጎዳት እንዳይደርስ የሚረዱ የመከላከያ እርምጃዎችን በመውሰድ የመሬትን ምርታማነት ማሻሻል፣ በግብርና ስራ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸውን የግብርና ሚኒስቴርና የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ተቋማት አቅም ማጠናከር ነበር።

ይኸንኑ ተግባራዊ ለማድረግ ፕሮጀክቱ ወደ ሰባት የሚደርሱና እንደየአካባቢው ልዩ ሁኔታ የተዘጋጁ «የአካባቢ ልማት ፕሮግራም» ወይንም የልማት ቀጠና ፕሮግራሞች ወጥተውለት በስራ ላይ ውለው ነበር። በተለይም ተቋማዊ አቅምን ከማሳደግ አኳያ ብዙ አይነት ሙከራዎች ተደርገዋል። ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ቢያስፈልግ የግብርናውንም ሆነ የሌሎችን ኢኮኖሚ ዘርፎች እንቅስቃሴ በእቅድ የሚመራ የማዕከላዊ ፕላን ጽህፈት ቤትን ከማቋቋም ጀምሮ በርካታ ተቋሞች ተገንብተው ነበር። በሰፊ መዋቅር ከላይ እስከታች የተዘረጋ የግብርና ሚኒስቴር ተቋቁሞ የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ሲመራና ሲያስተባብር ቆይቷል። ለከተማው ሕዝብና ለጦሩ የሚያስፈልገውን የምግብ አቅርቦት ለማሟላት እንዲመች በማሰብ የግብርና ምርቶችን ዋጋ የሚቆጣጠርና ከእያንዳንዱ ገበሬ በኮታ እህል የመግዛት ሞኖፖሊ የነበረው የእርሻ ሰብል ገበያ ኮርፖሬሽን (AMC) በመንግስት ባለቤትነት ተቋቁሞ ነበር። የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ዋነኛ ምንጭና ግንባር ቀደም የኤክስፖርት ምርት የሆነውን ቡናን በመንግስት አማካይነት ወደውጭ ለመላክ እንዲቻል የቡና ገበያ ኮርፖሬሽን (CMC) ተቋቁሞ ነበር። የውጭ ምንዛሬን ለማሳደግ እንዲቻል የቅባት እህሎችና ጥራጥሬ ኤክስፖርት ኮርፖሬሽን (OPEC) ተቋቁሞ ነበር። ለገበሬዎች የግብርና ግብዓቶችንና አገልግሎቶችን ለማቅረብ እንዲቻል የግብርና ግብዓቶችና አገልግሎቶች ኮርፖሬሽን (AISCO)ተቋቁሞ ነበር። የግብርና ምርምር ቴክኒዎሎጂ እንዲስፋፋ ለማድረግ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት (ARI) ተቋቁሞ ነበር። የኢንዱስትሪ እቃዎችንና የተለያዩ ሸቀጦችን ለሕዝቡ ማከፋፈል እንዲቻል የኢትዮጵያ የሀገር ውስጥ ማከፋፈያ ኮርፖሬሽን (EDDC) ተቋቁሞ ነበር።

ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ ተቋማዊ አቅሞች በተፈጠሩበትና ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ በሰው ኃይልና በበጀት አመዳደብ ከሌሎቹ ክፍለ ኢኮኖሚዎች ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ነበር በተባለበት ሁኔታ የተገኘው ውጤት አጥጋቢ ሊሆን እንዳልቻለ ታይቷል።

የግብርና ልማት ፕሮጀክትን ተግባራዊ ለማድረግ በተካሄዱ ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች በገጠር መንገድ ስራ፣ በሰው ኃይል ስምሪትና በመሳሰሉ ጉዳዮች ከንጉሱ ዘመን የተሻለ ውጤት ቢገኝም የግብርናን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ረገድ ከቀድሞው የተለየ ነገር ለመፍጠር አልተቻለም።

ግብርናውን ለማሳደግ የሚረዱ ግብዓቶችን ዋጋ መንግስት እየተሸፈነ ለማዳበሪያና ለመሳሰሉት ወጭዎች ገበሬዎች ድጎማ የሚያገኙበት ሁኔታም ነበር። ይሁን እንጂ በደርግ ዘመን ከርዕዮተ ዓለም አመለካከት በመነጨ ሁኔታ የመሬት ብቸኛ ባለቤት መንግስት እንዲሆን በመደረጉ፣ ከ1976 ጀምሮ በወጣው የገበሬዎች ፈቃደኝነት ሳይኖር፣ በቂ ጥናትና ዝግጅት ሳይደረግ ሰፊ የሰፈራ ፕሮግራም በመካሄዱ፣ የገበሬዎችን የስራ ወቅት፣ የመሬት አጠቃቀም ፍላጎትና የተፈጥሮ ሀብት ስርጭት በዝርዝር የሚያሳይ ጥናት ሳይኖር በችኮላና በግዴታ የመንደር ምስረታ በመከናወኑ ወዘተ. ከበፊቱ በባሰ ሁኔታ የመሬት መጎዳትና የምርታማነት ማሽቆልቆል ተከሰተ። በዚህና በሌሎችም በርካታ ምክንያቶች ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀም የእርሻ እንቅስቃሴ (Labour intensive farm) በመንግስት አማካይነት በተለያየ አቀራረብ ተሞክሮ የሀገሪቱን ግብርና ለማሳደግም ሆነ ወደዘላቂ ልማት ለመሸጋገር የሚያስችል ውጤት ሳያስገኝ ቀረ።

ከላይ እንደተጠቀሰው በመንግስት እርሻ የተደረገው ጥረት በተመሳሳይ ሁኔታ ውጤታማ አልነበረም። እነዚህ እርሻዎች ተጨማሪ መሬት፣ የግብርና ግብዓት፣ ብድር፣ የዋጋ ማበረታቻና ሌሎችንም ሁኔታዎች በማግኘት ረገድ ገደብ የማይደረግባቸው ቢሆኑም ምርታማ ሊሆኑ አልቻሉም። በእነዚህ የመንግስት እርሻዎች አማካይነት ሰፊ በሆነ የሰው ጉልበትና በእንስሳት ጉልበት ከመጠቀም ይልቅ በሰፊ መሬት ላይ የሚካሄድ ሜካናይዝድ ፋርም (capital intensive) በማስፋፋት ግብርናን ለማሳደግ ቢታሰብም አልተሳካም። ለዚህም ከሚጠቀሱት በርካታ ምክንያቶች መካከል ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል በመጀመሪያ ደረጃ አብዛኞቹ በውርስ ወደ መንግስት ንብረትነት ሲዛወሩ ቀደም ሲል የነበራቸውን የማኔጅሜንት ልምድና የአሰራር ዘይቤ በአግባቡ ለመቅሰም ሙከራ ሳይደረግ በችኮላ ብዙም ልምድ በሌለው ማኔጅሜንትና የሰው ኃይል የተተኩ መሆናቸው ነው። አዳዲስ የተጨመሩ የመንግስት እርሻዎች ደግሞ ያለበቂ ጥናትና ዝግጅት የተቋቋሙ ስለነበሩ ምርታማና አትራፊ ለመሆን የሚያስችላቸውን አቅም ለመገንባት ሳይችሉ ቀሩ።

ሌላው ችግራቸው ሜካናይዝድ ፋርም ሊኖረው ከሚችለው የሰው ኃይል መጠን ያለፈ እጅግ በርካታ የሰው ኃይል አከማችተው የሚሰሩ መሆናቸው ነው። የተዛባ ማኔጅሜንት ስለነበራቸውና ንብረትንና ሀብትን በቁጠባ ለመጠቀም ባለመቻላቸው ለከፍተኛ ብክነት የተጋለጡ መሆናቸው ሌላው ችግር ነው። በደርግ ዘመን በሁሉም ነገር ልዩ ድጋፍ የሚደረግላቸው የመንግስት እርሻዎችና የገበሬዎች አምራቾች ሕብረት ስራ ማህበራት የያዙት መሬት ለግብርና ጥቅም ከዋለው ጠቅላላ መሬት ውስጥ እ.ኤ.አ በ1988 አካባቢ ወደ 9% ገደማ ድርሻ ከ10% ብዙም የራቀ አልነበረም። ከ90% በላይ የሚሆነው የግብርና ምርት የሚገኘው በግል እርሻ ከተሰማሩና አነስተኛ ይዞታ በላይ የሆነውን ከሚያንቀሳቅሱትና ከጠቅላላው የግብርና ምርት ውስጥ ከ90% የሚበልጠውን ለሚያገኙት አነስተኛ ይዞታ ላላቸው ገበሬዎች ተገቢው ትኩረት ባለመሰጠቱ የግብርና ምርትና ምርታማነት በማደግ ፋንታ ወደታች አሽቆለቆለ።

የግብርናን ልማት ለማፋጠን ከተደረጉት ጥረቶች መካከል እ.ኤ.አ ከ1985 ጀምሮ ስራ ላይ እንዲውል የተደረገው የእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክት አንዱ ሲሆን ለአራት ዙር የተካሄደ ነበር። ከእነዚህ ውስጥ በከፍተኛ ትኩረት ተካሂደዋል የሚባሉት በሶስተኛውና በአራተኛው ዙር የተከናወኑት የእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክቶች ነበሩ። የእነዚህ ፕሮጀክቶች ዋነኛ ትኩረትም የእንስሳት ሀብት ምርታማነት እንዲሻሻል ማድረግ፣ የእንስሳት መኖ አቅርቦትን ማሳደግ፣ የእንስሳት ጤንነትን ማሻሻል፣ የእንስሳት ሀብት ገበያን ማሻሻል የሚሉት ነበሩ። ይሁን እንጂ በዚህም ፕሮጀክት የተገኘው ውጤት የታሰበውን ያህል አልነበረም። በአጠቃላይ በንጉሱም ሆነ በደርግ ጊዜ በአንዳንድ ጉዳዮች መጠነኛ መሻሻል የታየባቸው ነጥቦች ቢኖሩም የግብርና ልማትን ውጤታማ በማድረግ ሀገሪቱን ወደ ዘላቂ ልማት ለማሸጋገር የሚረዳ ውጤት ተመዝግቧል ሊባል አይችልም።

## 6.2.4.3 ግብርና በህወሓት/ኢህአዴግ ዘመን

*በህወሓት/ኢህአዴግ የተቀየሰው የልማት ስትራቴጂም ከንጉሱና ከደርግ ዘመን ባልተለየ ሁኔታ ግብርናን የልማት መሪና አንቀሳቃሽ ሞተር ያደረገ ነው። የአሁኑ መንግስት ስትራቴጂ «ግብርና ልማት መር ኢንዱስትሪ» (ADLI) ይባል እንጂ በመሰረታዊ አላማዎቹና ይዘቶቹ ካለፉት መንግስታት ሙከራዎች ጋር ተመሳሳይ ነው። በተለያዩ የኢኮኖሚ ሴክተሮች ኤክስፖርት መር ስትራቴጂ ለመከተል የተያዘው የፖሊሲ አቋም ከዚህ በፊት በነበሩት መንግስታትም የተሞከረ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በዋናነት የግብርና ምርቶችን ኤክስፖርት በማድረግ አሰራር ላይ የተመሰረተ ስትራቴጂ መሆኑ ደግሞ ከቀድሞዎቹ መንግስታት የልማት ስትራቴጂ አዲስ ነገር አለመኖሩን ያሳያል። የአድሊ ዓላማዎች የሚባሉት በምግብ ራስን መቻል፣ የሥነምህዳር መጎዳትን መከላከል፣ የሀገሪቱን የግብርና ምርት በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ማድረግና የመሳሰሉት ሲሆኑ የቀድሞዎቹም መንግስታት የልማት ስትራቴጂዎች እነዚህን ዓላማዎች ለማስፈፀም ሙከራ አድርገው አጥጋቢ ውጤት እንዳላመጡ የታወቀ ነው። የአድሊን ዓላማዎች ለማስፈፀም የታሰቡት ስትራቴጂዎችና የአሰራር ዘዴዎች በአንድ በኩል መሬትን፣ የሰው ኃይልንና ካፒታልን በመጠቀም፣ ባህላዊ ተግባሮችን አሻሽሎ በመጠቀም፣ ከምርት በኋላ ያለውን ብክነት በመቀነስ፣ የበለጠ ብቃት ያለው የኤክስቴንሽን ስራና የአመራር ቴክኒክ በመጠቀምና በመሳሰሉት ዘዴዎች የአነስተኛ ገበሬዎችን ይዞታ ምርታማነት ማሻሻል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በገበሬ ያልተያዘ መሬት በባለሀብቶች በሊዝ በማከራየት የግል ኮሜርሺያል ፋርም እንዲስፋፋ ማድረግ ነው። እነዚህ ስትራቴጂዎች ከዚህ በፊት የተሞከሩና ዘላቂ ልማት ያላስገኙ መሆናቸው ቀደም ሲል ተገልጿል።*

*በአነስተኛ ገበሬዎች ይዞታ ላይ ምርታማነትን ለማሳደግም ሆነ የኮሜርሻል ፋርምን ለማስፋፋት የወጣውን ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ በአጭር ጊዜ የታሰበው ዝናብ በሚያገኙ አካባቢዎች ማዳበሪያን በመጠቀምና ያለማዳበሪያም ጭምር የግብርናን ምርታማነት ለማሳደግ መጣርና ጥቅም ላይ ያልዋለ ተጨማሪ የእርሻ መሬት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ነው። በመካከለኛና በረጅም ጊዜ የታሰበው ደግሞ በአነስተኛ ይዞታ ላይ በመስኖ የሚታገዝና የቴክኒዎሎጂ ግብዓቶችን የሚጠቀም ኢንቴንሲቭ የሆነ የእርሻ ስራ መስራት፣ ለኤክስፖርት ጠቃሚ የሆኑ የግብርና ምርቶችን ማምረት፣ ለሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች የሚያገለግሉ የግብርና ጥሬ እቃዎችን ማምረት ወዘተ. ነው። የአሰራር ቅደም ተከተሉም በመጀመሪያ ልማዳዊውን የእርሻ አሰራር ማሻሻል፣ ቀጥሎ ደግሞ የግብርና መሰረተ ልማትን ማስፋፋት፣ ማለትም አነስተኛ መስኖ መዘርጋትና የግብርና ቴክኒዎሎጂን ማስፋፋት ነው። በመጨረሻም ከላይ በተጠቀሱት የግብርና ልማት ቅደም ተከተሎች በሚመዘገበው የግብርና መሬት ምርትና ምርታማነት መሻሻል ላይ ተመስርቶ ፈጣንና ዘላቂ የግብርና መሬት ምርትና ምርታማነት መሻሻል ላይ ተመስርቶ ፈጣንና ዘላቂ የግብርና ልማት ማረጋገጥና ወደ ኢንዱስትሪ ልማት መሸጋገር ነው።*

*በዚህ ስትራቴጂ ውስጥ የታሰቡት የፓኬጅ አቀራረብ፣ የኤክስቴንሽን አሰራር፣ የግብርና ግብዓቶች አጠቃቀም፣ የተማሩ ገበሬዎችን በሞዴልነት መጠቀምና የመሳሰሉት ዘዴዎች አንዳቸውም አዲስ አይደሉም። ከዚህ በፊት የነበሩና የተሞከሩ ናቸው። ወደ ዘላቂ ልማት መሸጋገሪያ ሊሆኑ ቀርቶ የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ እንኳ አስተማማኝ በሆነ መንገድ መሻሻል እንዲያሳይ ያላስቻሉ ናቸው። አሁን በሕወሓት/ኢህአዴግ መንግስት እንደ አዲስ የሚስተጋቡት እነዚህ የልማት ስትራቴጂዎች ከዚህ በፊት በሀገራችን ተሞክረው ፈጣንና ዘላቂ ልማት ማረጋገጥ ይቅርና ድህነትን ለመቀነስም ሆነ የገቢ ልዩነትንና የኑሮ ደረጃን በማቀራረብ ተመጣጣኝ እድገት ለማምጣት ያላስቻሉ ናቸው። የሀገሪቱ ግብርና መሰረታዊ ችግሮች ከሕዝብ ፈጣን እድገትና ከእርሻ መሬት ጥበት ጋር በተያያዘ የሚደርስ የተፈጥሮ ሀብት መመናመንና የመሬት መጎዳት፣ የመስኖና ሌሎች የግብርና መሰረተ ልማት እጥረቶች በመኖራቸው ከፍተኛ ለሆነ የዝናብ ጥገኝነት መጋለጥ፣ የገበሬው የመሬት ባለቤትነት መብት መገፈፍና የመሳሰሉት ቢሆኑም፤ ከሁሉም በላይ ለግብርና ልማት የሚያመች የመንግስት ፖሊሲ አለመኖር ከፍተኛው ችግር ነው። የንጉሱ፣ የደርግና የሕወሓት/ኢህአዴግ መንግስታት ፖሊሲዎች የኢትዮጵያ ገበሬ ነፃ ሆኖ እንዲሰራና ውጤታማ ልማት እንዲያካሂድ እድል የሚሰጡ አይደሉም። ገበሬው ግብር ከመክፈል፣ ለወታደራዊ ግዳጅ ልጆቹን ከመስጠትና የመንግስት ጭሰኛ ከመሆን በስተቀር ሌላ መብት የለውም። የአሁኑ መንግስት ደግሞ ካለፉትም መንግስታት በከፋ ሁኔታ የገበሬውን*

መብት ሙሉ በሙሉ የነጠቀና በከፍተኛ ተፅዕኖ ስር እንዲወድቅ ያደረገ መሆኑን ለመረዳት ብዙ ምርምር የሚጠይቅ ሳይሆን የገበሬውን አደረጃጀት ብቻ በማየት መረዳት ይቻላል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪዎች በነፃነት መርጠው የሚወክሏቸው መሪዎች የሚያንቀሳቅሱት ሕዝባዊ ማህበር መሆኑ ቀርቶ በገዥው ፓርቲ የሚሾሙ የኮር አባላት የሚመሩት የመንግስት አስተዳደር ፖለቲካዊ መዋቅር ሆኗል፡፡ እነዚህ የኮር አባላት በሚመሩት የገበሬ ማህበር ስር ራሳቸው መርጠው የሚሰይሟቸው የመንግስት ቡድኖች አሉ፡፡ በመንግስት ቡድኖች ስር ደግሞ ሴሎች (ሕዋሶች) ያሉ ሲሆን ዋነኛው ተልዕኳቸው ገበሬው ለገዥው ፓርቲ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ድጋፍ እንዲሰጥ ማስገደድ ነው፡፡ በምርጫ ጊዜ የገበሬው ድምፅ ለገዥው ፓርቲ እንዲሰጥ የሚያስገድድ፣ የገዥው ፓርቲ ንግድ ኩባንያዎች የሚያቀርቡትን ብድር፣ ማዳበሪያ፣ የእርሻ መሳሪያና የመሳሰሉትን ግብዓቶች በውድ ዋጋ እንዲገዛ የሚያስገድዱ፣ እዳውን ለመክፈል ያልቻለ ገበሬ ሲኖር ይዞታውን እየነጠቁ፣ ንብረቱን እየሸጡ፣ ባለዕዳውን እያሰሩና እየገረፉ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ረገጣ የሚያካሂዱ እነዚህ አካላት ናቸው፡፡

ገበሬው በሕግ የተፈቀደ የመሬት ባለቤትነት መብት ስለሌለውና የመሬት ባለቤት መንግስት በመሆኑ እነዚህ የገዥው ፓርቲ አባላት ለመንግስት ደጋፊ መሬት እየሰጡ መንግስትን ለማይደግፍ ደግሞ እየከለከሉ ለፖለቲካ ዓላማ ማስፈፀሚያ አድርገውታል፡፡ መሬት ለልማት ተግባር የሚውልበት እድል በመንግስት ፖሊሲ በመዘጋቱ አንድ ሺህ አንድ ጊዜ ስለልማት ስትራቴጂ ቢወራ የሚገኝ ውጤት የለም፡፡

## 6.2.4.4 ማጠቃለያ

በቀድሞዎቹም ሆነ በአሁኑ መንግስት የተቀየሱ ስትራቴጂዎች ውጤት ሊያመጡ ያልቻሉበት ቁልፍ ሚስጥር ከዚሁ ከመሬት ባለቤትነት ፖሊሲና ከገበሬው ነፃ አደረጃጀት አለመኖር ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ የሀገራችን ግብርና ችግሮች ባላፉት መንግስታት የተሞከሩትና በአሁኑ መንግስትም የቀጠሉት ስትራቴጂዎች በራሳቸው መጥፎ ስለሆኑ የተፈጠሩ አይደሉም፡፡ እነዚህን ስትራቴጂዎች በመጠቀም ብቻ የግብርናውን አወቃቀር ለመቀየርም ሆነ ፈጣንና ዘላቂ ወደ ሆነ የኢንዱስትሪ ልማት ለመሸጋገር ይቻላል የሚለው አስተሳሰብ በተግባር ሊረጋገጥ የመቻሉ እድል የጠበበ መሆኑ ካለፉት 40 ዓመታት ልምዳችን በተጨባጭ የታየ ቢሆንም ቢያንስ በግብርናው ዘርፍ መሻሻል እንዲኖርና በምግብ እህል እራሳችንን እንድንችል ሊያግዙ እንደሚችሉ የሚያጠራጥር ነገር አይደለም፡፡ እነዚህን ስትራቴጂዎች በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን በማሻሻል የገበሬውን ገቢ መጨመርና ኑሮውን እንዲያሻሽል ለማድረግ የሚቻልበት እድል የተዘጋ አልነበረም፡፡ ይህ አነስተኛ እድል እንኳ እንዳይኖር የከለከሉት ቀደም ሲል የነበሩት ሥርዓቶች የመሬት ባለቤትነት ፖሊሲ ድክመትና የገበሬው ነፃ አደረጃጀት አለመኖር ናቸው፡፡

እስከአሁን በሶስቱም መንግስታት የተሞከሩትና ከአቀራረብና ከርዕዮተዓለም ቅኝት በስተቀር ከሞላ ጎደል ተቀራራቢ የሆኑት የግብርና ልማት ስትራቴጂዎችም ይሁኑ ሌሎች ከዚህ በፊት ያልተፈተሹ አዳዲስ ስትራቴጂዎች ተደጋግመው ቢወጡ የኢትዮጵያ ገበሬ የመሬት ባለቤትነት መብት በሕግ እስካልተሰጠውና የመንግስትን ከባድ ተፅዕኖ የሚያስቀር ነፃ አደረጃጀት እንዲኖረው ካልተደረገ በስተቀር የሚገኝ ውጤት ይኖራል ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ ከ40 ዓመታት ልምድ የታየው ሀቅ ቢኖር ገበሬውን የመንግስት አገልጋይ የሚያደርግ፣ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚሳድርና የመሬት ባለቤትነቱን የገፈፈ ፖሊሲ እስካለ ድረስ የኢትዮጵያ ግብርና ልማት መንግስታት የፖለቲካ አጀንዳቸውን ለማስፈፀም ይገለገሉበት እንደሁ እንጂ የገበሬውን ኑሮ ለማሻሻል በሚያግዝ ደረጃ ሊለወጥ እንደማይችል ነው፡፡

ሁለተኛውና መሰረታዊው የሀገራችን ግብርና ችግር ደግሞ ለዘላቂ ልማት መረጋገጥ ዋስትና ሊሆን የሚችልበት ተስፋ የመነመነ መሆኑ ነው፡፡ እስካሁን ድረስ ለማየት እንደሞከርነው ወደ 40 ዓመታት ለሚጠጋ ጊዜ ሶስት ተከታታይ መንግስታት ግብርናን ዋነኛው የኢኮኖሚ ልማት መሪና አንቀሳቀሰሽ ሞተር አድርገው በመውሰድ ያደረጉት እንቅስቃሴ ውጤታማ ሊሆን አለመቻሉን ነው፡፡ ቀጥሎ የምንመለከተው ደግሞ የገበሬውን የመሬት ባለቤትነት የሚያረጋግጥና ነፃ አደረጃጀት እንዲኖረው የሚያቅድ ፖሊሲ ኖሮ የግብርና ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ ቢደረግም እንኳ በዚህ የኢኮኖሚ ዘርፍ አማካይነት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ

*መዋቅራዊ ችግሮች ሙሉ በሙሉ በመፍታት ዘላቂ ልማት ወደሚረጋገጥበት የኢንዱስትሪ ደረጃ መሸጋገር ይቻላል የሚለው አመለካከት አሳማኝ በሆነ ማስረጃ ሊደገፍ የሚችል አለመሆኑን ነው። በአጭሩ የግብርናን ኢኮኖሚ ዘርፍ የኢኮኖሚያችን መሪና አንቀሳቃሽ ሞተር አድርገን ለመውሰድ መጠነ ሰፊ ርብርብ ብናደርግ መጨረሻ ላይ ልንደርስበት የምንችለው ግብ በልቶ አደር ሕብረተሰብ መፍጠር ከመሆን የሚዘል አይደለም። የእኛን ሀገር ግብርና የኢኮኖሚያችን መሪና አንቀሳቃሽ በማድረግ ወደ ኢንዱስትሪ ልማት ደረጃ ለመሸጋገር የማያስችሉ በርካታ ነባራዊ ችግሮች አሉ። ከእነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹን ብቻ በአጭሩ በማቅረብ ሁኔታዎችን መረዳት ይቻላል።*

*በቅድሚያ የሚጠቀሰው ቁልፍ ችግር የሀገራችን መሬት በከፍተኛ ደረጃ መጎዳቱ ነው። የመሬታችንን ለምነት እንደገና በመመለስ ምርታማ እንዲሆን ለማድረግ ከፍተኛ ወጪ፣ ረጅም ጊዜና አድካሚ ጥረት ይጠይቃል። በቀላሉ ለማገገም የማይችል የደን ሀብት መመናመን፣ የአፈር መከላትና ለመሬት ምርታማነት አስፈላጊ የሆነው ንጥረ ነገር መሟጠጥ በመድረሱ የግብርና ምርትን ለማሳደግ የሚደረገው ማንኛውም አይነት ጥረት ፈታኝ ነው።*

*በመሬታችን ላይ የደረሰውን ከባድ ጉዳት ለመመለስ የሚያስችል ጥረት ተደርጎ በረጅም ጊዜ ውስጥ የተሳካ ውጤት እስኪገኝ ድረስ የግብርናን ምርታማነት ለማሳደግ ልዩ ልዩ ግብዓቶችንና የቴክኒዎሎጂ ውጤቶችን ብንጠቀም እንኳ ፈጣን ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችል ሁኔታ መፍጠ ር ከባድ ነው። ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘር፣ ፀረ-ተባይና ፀረ-አረም ኬሚካልና የመሳሰሉ የእርሻ ግብዓቶችን የሚጠቀም አንድ የሀገራችን ገበሬ በሄክታር ከ11 - 12 ኩንታል የሚደርስ ምርት መጠን እያመረተ ባለበት ሁኔታ ፈጣንና ዘላቂ ወደሆነ ልማት ለመሸጋገር የሚያስችል አስተማማኝ ዋስትና ለማግኘት ያለን እድል የመነመነ ነው። በሌሎች ሀገሮች አንድ ገበሬ በሔክታር ከ1 ሺህ ኩንታል በላይ እያመረተም ግብርና የዘላቂ ልማት ዋስትና ተደርጎ አይወሰድም። ምክንያቱም ዘላቂ ልማት የግብርናን ምርትና ምርታማነት ከማሳደግ የሰፋ ትርጉም ስላለው ነው።*

*ከዚህ ሌላ ያለብን ችግር የአዳዲስ ቴክኖዎሎጂና ግብዓቶች ችግር ነው። የእህል ምርትን በመጨመር ብቻ የገበሬውን ሕይወት ሙሉ በሙሉ መቀየርም ሆነ በሀገሪቱ ፈጣንና ዘላቂ ልማት ለማምጣት አስቸጋሪ ነው። የግብርናውን ምርት ዋጋ የሚያወጣና ተወዳዳሪ ለማድረግ በሚያስችል ሁኔታ ማምረት ያስፈልጋል። ይኸንን ሁኔታ ለማሟላት ደግሞ በየጊዜው የሚሻሻል የግብርና ቴክኒዎሎጂና ግብዓት መጠቀም ይጠይቃል። የተሻሻለ የግብርና ቴክኒዎሎጂና ግብዓት ደግሞ አንድም በሀገር ውስጥ እንዲመረት ማድረግ አልያም በግዥ ማቅረብ ስለሚያስፈልግ ከፍተኛ የቴክኒክና የፋይናንስ አቅም ይጠይቃል።*

*እንዲህ ዓይነቱ አቅም የሌለን መሆኑ ብቻ ሳይሆን በአጭር ጊዜ ልናሟላው የሚከብድ መሆኑ ደግሞ ሁኔታውን ይበልጥ አስቸጋሪ ያደርገዋል። ሌላም ከባድ ችግር አለብን። ይኸውም የሀገራችን ግብርና የዝናብ ጥገኛ መሆኑ ነው። ተፈጥሮ በቂ ዝናብ ሲቸረን የተሻለ ምርት እናገኛለን። ተፈጥሮ በቂ ዝናብ ሳይለግሰን በሚቀርበት ጊዜ የሰውና የእንስሳት እልቂት በሚያስከትል ድርቅና ረሃብ እንመታለን። በመስኖ የሚካሄድ የግብርና መሰረተ ልማት አልገነባንም። በመስኖ የሚታገዝ ግብርና ከሚያካሂዱ ሀገሮች ልምድ እንደታየው በመስኖ የሚለማ ¼ (ሩብ) ሄክታር መሬት የዝናብ ጥገኛ ከሆነ 25.3 ሄክታር መሬት የበለጠ ምርታማ ነው። የእኛ ሀገር ገበሬ ደግሞ የዝናብ ጥገኛ የሆነ ብቻ ሳይሆን ለምነቱ የተሟጠጠ ½ (ግማሽ) ሄክታር መሬት እያለማ ባለበት ሁኔታ ፈጣንና ዘላቂ ልማት ማረጋገጥ ቀርቶ ለራሱ ምግብ የሚበቃ ምርት ለማምረትም እድል የለውም። ከዚህ በተጨማሪ የሚጠቀሰው ችግር ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት መኖሩ የገበሬውን የይዞታ መጠን ይበልጥ እያሳነሰው መምጣቱ ነው። አሁን ባለው ይዞታ መጠን ራሱን መመገብ ያልቻለ ገበሬ በየጊዜው ፈጣን እድገት እያሳየ በመጣው የሕዝብ መጠን ምክንያት ይዞታው ይበልጥ እያነሰ በሄደ ቁጥር ለባሰ ችግር እንደሚጋለጥ የታወቀ ነው።*

*የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር የዛሬ 23 ዓመት ገደማ አንድ መቶ አርባ ሚሊዮን እንደሚሆን ይገመታል። በግብርና ኢኮኖሚያችን ላይ ፈጣን ለውጥ ማምጣት ካልቻልን ከ23 ዓመት በኋላ ወደ ምን አይነት አሰቃቂ ችግር ውስጥ እንደምንገባ ከወዲሁ መገመት አያዳግትም።*

ሌላው ችግር ደግሞ የገበሬው ይዞታ አንድም ለግብርና ፈጣንና ዘላቂ እድገት በሚያመች መንገድ የተሰባሰበ ሳይሆን የተበታተነና የተበጣጠሰ ነው። አልያም አመራረቱ ለገበያ በሚሆን መልክ የተቃኘና ለሌላው ክፍለ ኢኮኖሚ ድጋፍ እየሰጠ ከፍተኛ ጥቅም በሚገኝበት መንገድ የሚመራ አይደለም። ሌላው የሚጠቀስ ችግር በሀገራችን ግብርና ልማት ጥቅም ላይ እየዋለ ያለው ቴክኒዎሎጂና ግብዓት ሙሉ በሙሉ በብድርና በግዥ ከውጭ የሚገባ ከመሆኑ በተጨማሪ በርካታ ጉዳቶች ያሉት መሆኑ ነው። አንደኛው ጉዳቱ በሀገራችን የነበረውን የተፈጥሮ ማዳበሪያ ፍግ፣ የእፅዋት ብስባሽና የመሳሰለው አጠቃቀም ባህል ያስቀረ መሆኑ ነው። ሌላኛው ጉዳቱ ደግሞ በተፈጥሮ ሀብት ማለትም በብዝሃ ሕይወት፣ በእንስሳትና በሰው ላይ የሚያስከትለው ጠንቅ መኖሩ ነው። እንዲሁም ማዳበሪያውና ሌሎች ኬሚካሎች ከእኛ ሀገር መሬት ፀባይ ጋር እየተጣጣሙ የማይዘጋጁና ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜም መጠኑን በማብዛትና በማሳነስ በሚፈጠር ስህተት ከባድ ችግር ማስከተላቸው ራሱን የቻለ ችግር ነው። ማዳበሪያ መጠቀም ባይችል መሬቱ ምንም ዓይነት ጥቅም የማይሰጥ መሆኑ ሌላ ችግር ነው። በዚህ ዓይነት ብዙ ጠንቆችን መዘርዘር የሚቻል ቢሆንም ዋናው ነገር የግብርና ቴክኒዎሎጂና ግብዓት አጠቃቀማችን ተጨባጭ ሁኔታዎችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እየገመገመ የሚሻሻልና የሚለወጥ አለመሆኑ ከጥቅሙ የበለጠ ጉዳት ማስከተሉ ነው። አሁን እኛ እየተጠቀምንበት ያለው ቴክኒዎሎጂና ግብዓት ከ50ና 60 ዓመታት በፊት ሌሎች ሀገሮች ሲጠቀሙበት የነበረና ጠንቆች እንዳሉት በምርምር ስለደረሱበት እርግፍ አድርገው የተዉት ነው።

ሌላው አለም የናቀውንና የቀየረውን ቴክኒዎሎጂ በብድርና በሽያጭ መልክ እኛ ላይ የሚያራግፍበትን ሁኔታ ለማስቀረት ያላስቻለን ድህነታችንና አቅመቢስነታችን ነው። አንድ የሚጠቅም ነገር ለማግኘት ሲባል ብዙ የሚጎዳ ነገር አብሮ መቀበል የእኛ ብቻ ሳይሆን የማንኛውም አቅመቢስና ድሃ የሆነ ሀገር ሁሉ ችግር ነው። እኛ ራሳችን ልናመርተው ወይንም ተገቢ ጥራትና ውጤታማነት ያለውን ምርትና አገልግሎት በገበያ ተወዳድረን ለመግዛት የሚያስችል ብቃት ልንጨብጥ እስካልቻልን ድረስ የማንፈልገውን ለመቀበልና ሌላው ንቆ የተወውን ውዳቂ ነገር ሁሉ እያግበሰበስን ለመጠቀም ከሚያስገድዱ ተፅዕኖዎች መገላገል አይቻልም። በእነዚህና በሌሎችም ምክንያቶች የተነሳ የሀገራችን ግብርና ፈጣንና ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችል ዋስትና የማይፈጥርልን መሆኑ ግልፅ ነው። ይህ ሲባል እነዚህንና ሌሎችንም የሀገራችን ግብርና ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል ፖሊሲ ማውጣት፣ ስትራቴጂ መቀየስና የተለያዩ የአሰራር ዘዴዎችን መጠቀም አይገባንም ማለት አይደለም። የግብርና ችግሮቻችንን መፍታት ከሀገሪቱ ሕዝብ መካከል 85% የሚሆነውን የገጠር ነዋሪ ብቻ ሳይሆን በከተማ የሚኖረውንና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከግብርና ምርት ጋር የተሳሰረ ሕልውና ያለውን ሕዝብ ሕይወት በአጠቃላይ የሚመለከት ትርጉም ያለው ጉዳይ እንደመሆኑ ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ጥያቄ የሚነሳበት ጉዳይ አይደለም።

ኢዴፓ የኢትዮጵያ ግብርና ችግሮች መፍትሔ እንዲያገኙና ዜጎች ያጋጠማቸውን ከባድ የኑሮ ፈተና ማቃለል እንዲችሉ እስከዛሬ ከታዩት ሙከራዎች የበለጠ ጥረት መደረግ እንዳለበትና እስካሁን በተግባር ተፈትሸው ውጤት አልባ ከሆኑት የግብርና ፖሊሲዎች የተሻለ አማራጭ የግብርና ፖሊሲ መኖር እንደሚገባው ያምናል። በዚህም መሰረት ከሀገራችን ግብርና መሰረታዊ ችግሮች መካከል የገበሬውን የመሬት ባለቤትነት መብት የሚያረጋግጥ ሕጋዊ ዋስትና አለመኖርና አርሶ አደሩ በነፃ የመደራጀት መብቱ ያልተረጋገጠለት መሆኑ ዋነኞቹ ናቸው ብሎ ስለሚያምን ይኸንን ለመለወጥ የሚያስችል አማራጭ በፕሮግራሙ ውስጥ በግልፅ አስቀምጧል። ይኸውም መሬት የመንግስት መሆኑ ቀርቶ በግል ባለቤትነት የሚያዝ፣ ሊሸጥና ሊለወጥ የሚችል፣ የሚከራይ፣ ለብድርና ለዕዳ በመያዣነት የሚያገለግል፣ በስጦታና በውርስ የሚተላለፍ የግል ንብረት እንዲሆን የሚያስችል የመሬት ፖሊሲ መውጣት አለበት የሚል አማራጭ ነው። ነገር ግን መሬት ይሸጥ ይለወጥ ስንል ትልቅ ግምት ሊሰጠው ሊተኮርበት የሚገባው ቁምነገር ከተሟላ የባለቤትነት መብት ጋር ተያይዘው የሚመጡ ኢኮኖሚውን ለማሻሻል ትልቅ ድርሻ የሚኖራቸው መፍትሄዎች መኖራቸው ላይ ነው እንጂ በቁንፅል «መሸጥ መለወጥ» የሚለው ሀረግ ላይ መሆን የለበትም። ከመሸጥ መለወጥ ጋር ይመጣሉ ተብለው የሚታሰቡ ችግሮች የመሸጥ መለወጥ የተሟላ መብት ሲኖር ከሚኖረው ጥቅም ጋር በምንም ዓይነት ተመዛዝነው ሚዛን የሚደፉ አይደሉም። ገበሬው ከኛ በላይ ጥቅሙን የሚያውቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ መሸጥ መለወጥ ሊያስከትል ይችላል ተብሎ የሚታሰበውን ችግር ገበሬውን በማስተማርና በጥቅሙና ጉዳቱ ላይ የሚኖረው ግንዛቤ በማሳደግ መፈታት የማይቻልበት ምክንያት የለም።

ሌላው ነጥብ መሬት ይሸጥ ይለወጥ ሲባል አሁን በእርሻ ጥቅም ላይ የዋለውንና አርሶ አደሩ ሰፍሮ የሚገኝበትን መሬት ማለታችን ነው እንጂ በጥቅሉ ሁሉንም የሀገሪቱን መሬት ማለታችን እንዳልሆነ መታወቅ አለበት። እስካሁን ጥቅም ላይ ያልዋለው መሬት በመንግስት ባለቤትነት እጅ ሆኖ ቀስ በቀስ ወደግል ይዞታ የሚዛወርበት፣ ከብት አርቢው ህብረተሰብ የሚኖርበት አካባቢ ደግሞ የማህበረሰብ የጋራ መሬት ሆኖ መቀጠል የሚገባው መሆኑ ግምት ውስጥ ማስገባት ጠቃሚ ነው።

ይህ አማራጭ መሬት ለመንግስት የፖለቲካ አላማ ማስፈፀሚያ እንዳያውልና ኢኮኖሚያዊ ለሆነ ጥቅም እንዲያገለግል ይረዳል ብሎ ኢዴፓ ያምናል። መንግስት መሬትን እንደመያዣ በመጠቀም በግብርና የተሰማራውን ሕዝብ መብቶችና ነፃነቶች እየገፈፉ ከሚያደርስበት አስከፊ ጭቆና ገበሬው ሙሉ በሙሉ መገላገል የሚችለው የመሬት ባለቤትነት መብቱ በሕግ ሲጠበቅለትና በነፃነት ተደራጅቶ የራሱን ሕልውና በሚመለከት ማንኛውም ጉዳይ ላይ ሀሳቡን በመግለፅ ንቁና የተሟላ ተሳትፎ የማድረግ መብቱ በሕግና በተግባር ሲረጋገጥ ነው የሚል ጠንካራ እምነት ስላለው በፓርቲው ፕሮግራም ውስጥ ይኸንኑ አማራጭ አስፍሯል። ገበሬው መሬትን በግል ባለቤትነት እንዲይዝና በነፃነት እንዲደራጅ የሚያስችለው ሕጋዊ ዋስትና እስካልተሰጠው ድረስ የተፈጥሮ ጥበቃ ለማካሄድም ሆነ የመሬትን ምርታማነት የሚያሳድግ እንክብካቤ ለማድረግ ምንም አይነት ፈቃደኝነትና ተነሳሽነት ሊያሳይ አይችልም። ሁልጊዜ ካለፍላጎቱ በግዳጅና በዘመቻ የሚከናወን የተፈጥሮ ጥበቃ እንቅስቃሴ ደግሞ ዘለቄታ ሊኖረው አይችልም። ገበሬው የመሬት ባለቤትነት ሕጋዊ ዋስትና እንዳለው የሚያረጋግጥ እምነት ሳይኖረው መሬትን ለማልማት፣ ምርትንና ምርታማነትን ለመጨመር የሚወጡ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች መጨረሻቸው ውድቀት እንደሚሆን የ40 ዓመት ገደማ ልምዳችን ከበቂ በላይ ትምህርት ሰጥቶናል። ስለዚህ በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ለሚታሰብ ማንኛውም አይነት ልማት ውጤታማነት በቅድሚያ መፈታት ያለበት የመሬት ባለቤትነት ጥያቄና የገበሬው ነፃ አደረጃጀት ናቸው። የመሬት ባለቤትነት ችግሮች የሚንፀባረቁባቸውን ገፅታዎችና አማራጭ መፍትሔዎች በግብርናው ሴክተር አማራጭ የፖሊሲ መነሻ ሀሳብ ውስጥ በዝርዝር የምንመለስበት ሲሆን በዚህ ርዕስ ስር አጽንኦት ለመስጠት የተፈለገው ግብርናችንን ለማልማት የሚያስችሉ ተገቢ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች መውጣት ያለባቸው መሆኑ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም በዚህ ዘርፍ የሚታቀደውና የሚታሰበው ነገር ሁሉ ውጤት እንዲያስገኝ ከተፈለገ በቅድሚያ ገበሬው የመሬት ባለቤት እንዲሆንና በነፃነት እንዲደራጅ የሚያስችለው ሕጋዊና ተግባራዊ መተማመኛ መፈጠር ይገባል የሚለውን ሃሳብ ነው።

የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ለማልማት የሚጠቅሙ ልዩ ልዩ ስትራቴጂዎችና ስልቶች መውጣት የሚገባቸው በመሆኑ ነጥብ ላይ ኢዴፓ ተቃውሞ የሌለው ቢሆንም ምን አይነት ስትራቴጂና ስልቶች ይውጡ ወይም እነዚህ ስትራቴጂዎችና ስልቶች በማን አማካይነት ይውጡ በሚሉት ጉዳዮች ዙሪያም የተለየ አቋም አለው። ከንጉሱ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ግብርናውን ለማልማት የወጡ ስትራቴጂዎች በመካከላቸው መጠነኛ የአቀራረብና የአጠራር ልዩነቶች ቢታዩም በመሰረቱ ተመሳሳይና እየተደጋገሙ የተሞከሩ ናቸው። ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀም እርሻ፣ የአነስተኛ ገበሬዎችን ይዞታ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችል የኤክስቴንሽን ፕሮግራም፣ በፓኬጅ የሚዘጋጁ የግብርና ፕሮጀክቶች፣ የተማረ ገበሬን ሞዴል ያደረገ የልማት ፕሮግራም፣ በልማት ወኪሎች የቴክኒክ ድጋፍ የሚካሄድ የግብርና ልማት፣ ጥቅም ላይ ያልዋለ ሰፊ መሬት ለባለሀብቶች በኪራይ እያቀረቡ የሚካሄድ የኮሜርሽያል ፋርም፣ ካፒታልን የሚጠቀም ሜካናይዝድ እርሻ፣ በመስኖ የሚታገዝ የግብርና ልማት፣ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኒዎሎጂና ግብዓቶች፣ ብድርና ሌሎች አገልግሎቶች፣ ለገበሬው በወቅቱ እንዲቀርቡለት የሚያስችል ፕሮግራም፣ የግብርና ምርት ኤክስፖርት በማድረግ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ፣ ወዘተ. የሚሉት ጉዳዮች አዲስ ባይሆኑም በተደጋጋሚ ጊዜ ተሞክረው እስካሁን በግብርናው ዘርፍ መሰረታዊ ለውጥ አላስገኙም።

ከፖሊሲ ችግር በመለስ የሚታዩ የስትራቴጂ አወጣጥና የአፈፃፀም መርሃ ግብሮች አነዳደፍ ችግሮችም አሉ። እስካሁን ድረስ በሀገራችን የወጡና ስራ ላይ እንዲውሉ የተደረጉ ስትራቴጂዎች የሕዝቡን ፍላጎት፣ አቅምና ስምምነት መሰረት ያደረጉ አልነበሩም። ሕዝቡ የሚፈልገው ምንድን ነው? ለማድረግ ያለው አቅም ምን ያህል ነው? ለማድረግስ ፈቃደኝነቱንና ስምምነቱን ገልጿል ወይ? የሚሉና የመሳሰሉ ጥያቄዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው አያውቅም። ሁሉንም ጉዳይ የሚወስኑት መንግስታት ናቸው።

በሀገራችን በየጊዜው ስልጣን ላይ የሚወጡ መንግስታት የጉዳዩ ባለቤት ከሆነው ሕዝብ የበለጠ እናውቃለን የሚል አንድ አይነት በሽታ አለባቸው። የልማት ስትራቴጂና መርሃ ግብር ባወጡ ቁጥር ከእነርሱ በፊት የነበረውን መንግስት እያወገዙ ራሳቸውን የሕዝብ ጥቅም ጠባቂ፣ ለሕዝብ ችግር ግንባር ቀደም ተቆርቋሪና አሳቢ መሆናቸውን ከማስተጋባት አልፈው የሕዝቡን መብት ለማክበር የሚያስችል ተጨባጭ እርምጃ ወስደው አያውቁም። በፕሮፓጋንዳ ደረጃ ያለፈውን እየኮነኑ በተግባር ደግሞ ከበፊቱ የከፋ አፈናና ጭቆና አስፍነው ሥልጣናቸውን ማደላደል የተለመደ ነው። ንጉሱ ሁሉን ነገር እርሳቸው ጀምረው እንደጨረሱት አድርገው በማቅረብ የግል ስብዕናቸውንና ራሳቸውን ሲክቡ ከኖሩ በኋላ የተፈጥሮ ሕግ ያመጣባቸውን የእድሜ መግፋት እንኳ ተቀብለው ስልጣን ለባለተራ በወጉ ማስተላለፍ ሲክቡት የቆዩትን የግል ዝናና ክብር የሚቀንስ መስሏቸው ሲያመነቱ መጥፎ አወዳደቅ ወደቁና አረፉት። የደርግ መንግስት ከንጉሱ የተሻለ ነገር መስራቱን ሕዝብ አይቶና አመዛዝኖ ለመፍረድ እስኪችል ድረስ ጊዜ ሳይሰጥ የንጉሱን ዘመን እንከኖች እንዳወገዘ መሸበትና ሕዝቡን ሲያመሰቃቅል ከከረመ በኋላ በመጨረሻም ሀገሪቱን ለከፋ ችግር አጋልጦ ተንኮታኮተ። ሕወሓት/ኢህአዴግም በ12 ዓመታት የሥልጣን ዘመኑ ዜጎች ተስፋ የሚያሳድሩበት ሁነኛ ነገር ሳይሰራ የመበስበስ ችግር ውስጥ ገባ። ህወሓት/ኢህአዴግ ከእርሱ በፊት የነበሩትን መንግስታት እንከኖች ከማውገዝ ቦዝኖ አያውቅም። አሁን ስራ ላይ ያዋለው የግብርና ልማት ስትራቴጂና መርሃ ግብር ግን ከቀድሞዎቹ መንግስታት የተለየ አይደለም።

ስለዚህ ኢዴፓ የግብርናም ይሁን የሌላ ልማት ስትራቴጂና መርሃ ግብር ሲነደፍ ጉዳዩ የሚመለከተው ሕዝብ ሀሳብ እንዲሰጥበት፣ እንዲመክርበትና እንዲከራከርበት እድሉ መሰጠት አለበት ብሎ ያምናል። ማንኛውም ስትራቴጂና መርሃ ግብር ከላይ እየተዘጋጀ ወደታች የሚወረወርበት አሰራር ተቀይሮ የዜጎችን ቀጥተኛ ተሳትፎና ስምምነት ባገኘ መልኩ ከታች ወደላይ የሚዘልቅበትን አቅጣጫ መከተል ይገባል ብሎ ያምናል። የግብርውም ይሁን የሌላ ልማት ስትራቴጂና መርሃ ግብር እንዴት ይዘጋጅ ለሚለው ጥያቄ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ዜጎች ሀሳብና አስተያየት መሰረት ባደረገና የእነርሱንም ንቁ ተሳትፎ ባረጋገጠ መንገድ መዘጋጀት አለበት የሚል አቋም አለው። በማን ይዘጋጅ ለሚለው ደግሞ ጉዳዩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሚመለከታቸው ዜጎች የተሟላ ተሳትፎ፣ በእነርሱ ፈቃድና ውሳኔ ይዘጋጅ የሚል አቋም አለው።

የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ለማሻሻል የሚያስፈልጉ አማራጭ ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና መርሃ ግብሮች ማስፈለጋቸው ያለው ተቀባይነት እንደተጠበቀ ሆኖ ግብርና የሀገራችን ኢኮኖሚ ግንባር ቀደም መሪና አንቀሳቃሽ ሞተር ሊሆን አይችልም የሚለው አቋማችን ከሕወሃት/ኢህአዴግ አቋም የሚለየን መሰረታዊ ነጥብ ነው። ይኸንን አቋም እንድንይዝ ካስቻሉን በርካታ ምክንያቶች መካከል ዋነኛ ናቸው የሚሉትን ሁለት መሰረታዊ ነጥቦች በአጭሩ አቅርበናል። እነዚህም አንደኛው ባለፉት አርባ ዓመታት በግብርና ላይ ተመስርቶ ወደዘላቂ ልማት ለመሸጋገር የተደረጉ ሙከራዎች ውጤት አልባ መሆናቸውና ሁለተኛው ደግሞ የሀገራችን ግብርና ባሉት የተሳሰሩ የረጅምና የቅርብ ጊዜ ነባራዊ ችግሮች የተነሳ ፈጣንና ዘላቂ ለሆነ ልማት መረጋገጥ ዋስትና የመሆን ተስፋው የተመናመነ መሆኑ ናቸው። በኢዴፓ እምነት ፈጣንና ዘላቂ ልማት የማምጣት ተልዕኮ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ሳይሆን የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ መሆን አለበት። የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ጥገኛ ሆነን በኖርንበት በግብርና ላይ ከእንግዲህ ጥገኛ ሆነን መቀጠል እንዳንችል ተፈጥሮ እራሱ አስገዳጅ ሁኔታ እየፈጠረብን ነው። ይህንን እውነት ተገንዝቦ ይኸ ትውልድ አዲስ አቅጣጫና ራዕይ ለማየት መገደድ ያለበት ወቅት ዛሬ ነው። አለበለዚያ ያረጀውንና ያፈጀውን አስተሳሰብ አሁንም ይዘን እንቀጥላለን የምንል ከሆነ ከ20 ዓመታት በኋላ የኢትዮጵያ ህዝብ 140 ሚሊየን በሚሆንበት ወቅት ህዝቡና አገሪቱ መራብ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ህልውናቸውን ሊያጡ እንደሚችሉ ከወዲሁ አርቀን ማሰብ ይኖርብናል።

የሀገራችን ልማት መሪና አንቀሳቃሽ ሞተር መሆን የሚገባው የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ነው ብሎ ኢዴፓ አቋም የያዘው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ይኸንን ተልዕኮ ለመወጣት የማያስችሉ ችግሮች አሉበት ከሚል መነሻ ብቻ አይደለም። ይልቁንም ኢንዱስትሪ ይኸንን ተልዕኮ ለመሸከም የሚያስችል ባህርይ እንዳለው ተቀባይነት ያገኙትን ሳይንሳዊና ተግባራዊ ማስረጃዎች መሰረት በማድረግ ጭምር ነው። ስለሆነም የኢዴፓ የልማት ስትራቴጂ ዋነኛ ይዘት ኢንዱስትሪን ዋነኛ የልማት አንቀሳቃሽ ሞተርና የልማት ውጤት የሚያደርግ ስትራቴጂ መከተል ነው።

## 6.2.5 ኢንዱስትሪን ዋነኛ የልማታችን አንቀሳቃሽ ሞተርና የልማት ውጤት የሚያደርግ ስትራቴጂ መከተል የሚስፈልግበት ምክንያት፣

ኢንዱስትሪን ዋነኛ የልማታችን አንቀሳቃሽ ሞተርና የልማት ውጤት የሚያደርግ ስትራቴጂ መከተል የሚገባን የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ምንም አይነት ጥቅም ሊሰጠን ስላልቻለ አይደለም። ወይንም ለግብርናው ዘርፍ ትኩረት ማድረግ ተገቢ ስለማይሆን አይደለም። እስካሁን ባለው ሁኔታ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ መተዳደሪያና የሕልውና መሰረት የሆነው ግብርና አሁንም ሆነ ወደፊት የሚሰጠን ጥቅም መኖሩን አስመልክቶ ጥያቄ ማንሳትና ክርክር መክፈት አስፈላጊ አይደለም። እጅግ ጠቃሚ ለሆነ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚቻለውን ሁሉ ትኩረት በመስጠት ከፍተኛ ለውጥና መሻሻል እንዲያሳይ ማድረግም አስፈላጊ ነው። ይሁን እንጂ ግብርናችን ሊያደርግ ከሚችለው በላይ ኃላፊነት እንዲሸከም ተገቢ ያልሆነ ጫና መፍጠር ትክክለኛ የልማት ስትራቴጂ አይደለም። የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ እድገትና መሻሻል እንዲያሳይ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ መረባረብ የሚኖረው ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላላ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የመምራት ተልዕኮና ኃላፊነት እንዲሸከም ማድረግ የተሳሳተ የልማት አቅጣጫ ነው። የዚህ አይነቱ የልማት ስትራቴጂ በሀገራችን ውስጥ በተግባር ተፈትሾ ውጤት እንዳላመጣ በተደጋጋሚ ጊዜ ታይቷል።

በሀገራችን ውስጥ ኢኮኖሚያዊ እድገት በፍጥነት ማስመዝገብ ካልተቻለ ከአሁኑ የከፋ ድህነትና ውድቀት እንደሚከተል ከሞላ ጎደል በዜጎች መካከል ስምምነት አለ። ማስመዝገብ የሚገባን ኢኮኖሚያዊ እድገት በፍጥነት መምጣት ካልቻለ ከድህነት የምንወጣበት ጊዜ እንደሚጓተትና በዜጎች ላይ የሚደርሰው ሰቆቃ ይበልጥ አስከፊ እየሆነ እንደሚሄድም በተመሳሳይ መንገድ በዜጎች መካከል ተመሳሳይ ግንዛቤ አለ። ከዚህ በተጨማሪ የምናስመዘግበው ልማት ለአንድ ዓመት ወይንም ለ5 እና 10 ዓመታት እፎይታ ሰጥቶን የሚቆምና እየተመለሰን ወደነበርንበት ድህነት ከመግባት የማይከላከል ሳይሆን ዘላቂና አስተማማኝ ልማት መሆን አለበት። በዚህም አስተሳሰብ ላይ በዜጎች መካከል ሰፊ ልዩነት የለም። ልዩነቱ ያለው ፈጣንና ዘላቂ ልማት በሀገራችን እንዲረጋገጥ ጠቅላላ ኢኮኖሚውን የመምራት ተልዕኮና ኃላፊነት መሸከም የሚገባው ክፍለ ኢኮኖሚ የትኛው መሆን አለበት? በሚለው ነጥብ ላይ ነው። የሀገራችን ግብርና ይኸንን ተልዕኮና ኃላፊነት ለመሸከም የሚያስችለው አቅምና ባህርይ እንደሌለው ቀደም ሲል የታየ ተጨባጭ ልምዶችንና ተገቢ ምክንያቶችን በማብራራት ግልፅ ለማድረግ ተሞክሯል።

ግብርና ይኸንን ኃላፊነትና ተልዕኮ ለመወጣት የሚያስችል አቅምና ባህርይ ከሌለው አማራጩ ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት የሚገባው እንደመሆኑ የኢዴፓ የልማት ስትራቴጂም ይኸንኑ ጥያቄ በሚገባ እንዲመልስ ሆኖ የተዘጋጀ ነው።

ኢዴፓ በሀገራችን ድህነት እንዲወገድና ፈጣን የሆነ ዘላቂ ልማት እንዲመዘገብ ወደ ኢንዱስትሪያላይዜሽን በግድ ማቅናት ይገባናል ብሎ ያምናል። ኢንዱስትሪያላይዜሽን ሲባል አጠቃላይ ኢኮኖሚው ከፍተኛ የእድገት ምጣኔ እንዲያሳይ ለማድረግ የሚያስችሉ የማምረቻ መሣሪያዎችንና የፍጆታ እቃዎችን የማምረት ሂደት ነው። ኢንዱስትሪያላይዜሽን ሲባል የሀገር ውስጥ ኢኮኖሚያዊ መዋቅርን የሰራተኛ ኃይሉንና የአመራረት ዘይቤውን በባህርይው ፈጣን የምርት እንቅስቃሴ ለማድረግ ወደሚችለው የፋብሪካ አመራረት የመቀየር ሂደት ነው። ኢንዱስትሪያላይዜሽን ሲባል ዘመናዊ ሳይንስና ቴክኒዎሎጂን ጥቅም ላይ የማዋል ሂደት እንደመሆኑ ፈጣን ለሆነ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ አስፈላጊ የሆነው ዘመናዊ የፋብሪካ አመራረት በቴክኒክ፣ በአይነትና በመጠን እድገት እንዲያሳይ ከጠቅላላው የሀገር ሪሶርስ ውስጥ ከፍተኛው ድርሻ እንዲመደብለት የማድረግ ሂደት ነው። በሀገራችን ፈጣንና ዘላቂ ልማት ማምጣት ካለብን የልማት አቅጣጫችን ወደዚህ አስተማማኝ ሂደት እንዲያስገባን በሚያስችል መንገድ መነደፍ አለበት።

የሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ አደረጃጀትና እንቅስቃሴ ለዚህ ሂደት ውጤታማነት እንዲያመች ሆኖ እንደገና መቃኘት አለበት። ኢኮኖሚው እርስ በርሱ የሚደጋገፍና የተሳሰረ ሆኖ እንዲያድግ በሚያስችል አኳኋን መደራጀትና መሰራት አለበት። ይኽንን ተልዕኮና ኃላፊነት ሊሸከም የሚችለው ደግሞ ሌላ ሳይሆን ራሱ የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ነው። አጠቃላይ ኢኮኖሚውን የመምራት ኃላፊነትና ተልዕኮ ኢንዱስትሪው መውሰድ አለበት የምንለው ያለምክንያት ሳይሆን ከእርሱ በተሻለ ሁኔታ ይኽንን ተልዕኮ መሸከም የሚችል ሌላ የኢኮኖሚ ሴክተር ስለሌለ ነው። ኢንዱስትሪ በባህርይው ፈጣንና ዘላቂ ልማት እንዲረጋገጥ የሚያስችል ተሰጥኦና ችሎታ ስላለው ነው።

ኢንዱስትሪ ከሌሎች ክፍለ ኢኮኖሚዎች በላቀ መንገድ የእያንዳንዱን ሰው የነፍስ ወከፍ ምርታማነት የማሳደግ ችሎታ ስላለው ፈጣንና ዘላቂ ልማትን ያመጣል። ብሔራዊ ኢኮኖሚው እርስ በርሱ እንዲደጋገፍ ከማድረግ አልፎ ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር ራሱን እንዲያስተካክልና ለአዳዲስ ሁኔታዎች በሚስማማ መንገድ ፈጣን ምላሽ እንዲሰጥ የማድረግ ችሎታ ስላለው ፈጣንና ዘላቂ ልማትን ያስገኛል። የተሳሰረ አወቃቀር እንዲኖረው በማድረግ ብቻ ሳይወሰን ኢኮኖሚው በቅልጥፍናና በማያቋርጥ መንገድ እንዲንቀሳቀስ ስለሚያስችል ፈጣንና ዘላቂ ልማትን ያረጋግጣል። አዳዲስ የልማት ተግባሮች እንዲፈጠሩና ሌሎች ክፍለ ኢኮኖሚዎችም እንዲነቃቁ የማድረግ ባህርይ ስላለው ፈጣንና ዘላቂ ልማትን ያመጣል። በኢንዱስትሪ የማይመራና የማይደገፍ ልማት ፈጣንና ዘላቂ ሊሆን ስለማይችል እኛም ፈጣንና ዘላቂ በሆነ መንገድ የልማት ችግሮቻችንን መፍታት ካለብን ኢንዱሰትሪ መር የልማት አቅጣጫ መከተል ይኖርብናል።

ኢንዱስትሪው ሌሎች የኢኮኖሚ ሴክተሮች እንዲለሙ የማነቃቃትና አጠቃላይ ኤኮኖሚው የተሳሰረና ተደጋጋፊ አደረጃጀት እንዲኖረው ለማድረግ የሚቻልበትን ሁኔታ ይበልጥ ግልፅ አድርጎ ለማሳየት አንድ ቀላል ምሳሌ ማቅረብ ይቻላል። ለምሳሌ የብረት መቅለጫ ፋብሪካዎች በሀገራችን ቢቋቋሙ እነዚህን መሰረት አድርገው የኢኮኖሚ ሴክተሮች ሊስፋፉና የእርስ በርስ ትስስር ሊፈጥሩ የሚችሉበት እድል ይኖራል። ለብረት ማቅለጫ ፋብሪካዎች ጥሬ ዕቃ መገኛ የሆነው የማዕድኑ ክፍለ ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ ሊነቃቃ ይችላል። የብረታ ብረት ውጤቶችን በሰፊው የሚጠቀሙ የመኪና፣ የትራክተር፣ የኮምባይነር ወዘተ. ማምረቻና መገጣጠሚያ ፋብሪካዎች የሚከፈቱበት እድል ይኖራል። በሀገር ውስጥ የሚመረቱና የሚገጣጠሙ መኪናዎችን በሰፊው ማቅረብ ሲቻል የትራንስፖርት አገልግሎቱ ይሻሻላል። ለመኪና ግዥ የሚወጣው የውጭ ምንዛሬ ስለሚድን ለሌላ ልማት ማስፋፊያ ይውላል። በተመሳሳይ ሁኔታ በሀገር ውስጥ በቂ የእርሻ ትራክተር፣ ኮምባይነርና ሌላም ዘመናዊ የእርሻ ማሳዎችን ለማልማት አቅምና ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች በዚህ መስክ ለመስራት ይደፋፈራሉ።

የሰፊ እርሻዎችን መስፋፋት ተከትለው የማዳበሪያ፣ የምርጥ ዘር፣ የተባይ መከላከያ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የሚስፋፉበት እድል ይኖራል። ከሚቋቋሙት እርሻዎች መካከል ጥጥና ሰሊጥ የሚመረቱ ቢሆን የሰሊጥና የጥጥ ምርትን በጥሬ እቃነት ተሚጠቀሙ የዘይት መጭመቂያና የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች ሊቋቋሙ ይችላሉ። ከጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች መስፋፋት ጋር ተያይዘው የክር ማምረቻ ወይም የተሰፋ ጨርቅ ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች ሊቋቋሙ ይችላሉ። በዚህ መንገድ ብዙ አይነት የኢኮኖሚ መነቃቃትና ትስስር እንደሚኖር የሚያሳዩ ምሳሌዎችን አንድ በአንድ እየዘረዘሩ ማስረዳት የሚል ቢሆንም ዋናው ነገር ኢንዱሰትሪ በባህርይው ሌሎች ሴክተሮች እንዲስፋፉ ብቻ ሳይሆን እርስ በርሳቸው እንዲተሳሰሩና እንዲደጋገፉ የማድረግ ልዩ ችሎታ ያለው መሆኑ ነው። አሁን በምሳሌነት በተነሳው ነጥብ ብቻ እንኳ ልዩ ልዩ ኢንዱስትሪዎች ከማዕድን፣ ከግብርናና ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር እንዴት ሊደጋገፉ እንደሚችሉ ወይም አንዱ ለሌላው እድገት ምን ያህል አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ ለማየት ይቻላል። ከዚህ ቀላል ምሳሌ በመነሳት አንዱ የኢኮኖሚ ዘርፍ ከሌላው የኢኮኖሚ ዘርፍ ጋር ብቻ ሳይሆን በአንድ የኢኮኖሚ ዘርፍ ውስጥ እንኳ የምርት ስፔሻላይዜሽን እንደሚፈጠርና ጠ ንካራ ትስስር እንደሚኖር ለመረዳት አያዳግትም። እንዲህ አይነቱን ኢኮኖሚያዊ ትስስርና መደጋገፍ ለመፍጠር ከኢን ዱሰትሪ የተሻለ ሴክተር የለም።

ኢንዱስትሪ መር የልማት አቅጣጫ መከተል የሚገባን የሚደጋገፍ ኤኮኖሚያዊ መዋቅርና ትስስር ለመፍጠር፣ ወይንም የሀገራችንን የእርሻ መሬትና በእርሻ ስራ የተሰማራውን የሰው ኃይል ምርታማነት በማሳደግ የሕዝቡን ገቢና ኑሮ ለማሻሻል ብቻ አይደለም። ይኸንን ማድረግ እጅግ ጠቃሚ መሆኑ ባይካድም ብቻውን በቂ አይደለም። ከዚህ ሌላ ተጨማሪ የስራ እድል በመፍጠር በገጠርና በከተማ ስራ በማጣት ለሚባክነው የሰው እውቀትና ጉልበት፣ በስራ አጥነት ምክንያት በኢኮኖሚያችን ላይ ለሚደርሰው ጫና አስተማመኝ መፍትሔ መፈለግ ይገባናል። በኢትዮጵያ እድሜው ለስራ ከደረሰው መካከል ወደ 97 ከመቶ የሚሆነው ስራ አጥ ነው። በ2002 የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው ለስራ ከደረሱ 44.7 ሚሊዮን ዜጎች መካከል 32.4 ሚሊዮን የሚሆኑት ስራ የላቸውም። ይህ ስሌት ራሱ 72 ከመቶ በላይ ለስራ የደረሱ ዜጎች ስራ አጥ መሆናቸውን ያሳያል። ይኸኛው ስሌት የተሰራው በገጠር ስራ አጥ የለም በሚል ታሳቢና ከከተማው ሕዝብ ውስጥ 20 ከመቶ ስራ አጥ ይኖራል ከሚል መነሻ ነው። ከሌሎች ሴክተሮች ጋር ሲነፃር በተከታታይ በርካታ የሰው ኃይል እየተቀበለ በስራ ላይ ለማሰማራት የሚያስችል ባህርይ ያለው ኢንዱስትሪ ነው። በመሆኑም በገጠርና በከተማ ውስጥ እየተስፋፋ የመጣውን የስራ አጥነት ችግር እንዲቃለል በማድረግ የሰው ኃይላችን ምርታማ ስራ እየሰራ ኑሮው የሚሻሻልበት ሁኔታ መፈጠር ካለበት ለኢንዱስትሪ ልማት ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ይገባናል። በሀገራችን ውስጥ በከተማና በገጠር እየተስፋፋ የመጣው አሳሳቢ የስራ አጥነት ችግር ከኢንዱስትሪ ልማት ውጭ ዘላቂ መፍትሔ ሊያገኝ እንደማይችል በሚገባ ተገንዝበን ካልተንቀሳቀስን ከድህነት የመውጣት ዕድል የለንም።

በሀገራችን ውስጥ ለተንሰራፋው ድህነትና ኋላቀርነት ትልቅ አስተዋፅኦ እያደረገ ያለው ሌላ ችግር የወጪና ገቢ ንግዳችን ሚዛን የተዛባ መሆን ነው። የክፍያ ሚዛን መዛባት ለረጅም አመታት አብሮን የቆየና ሊቃለል ያልቻለ ከፍተኛ ችግር ነው። የዚህ ችግር መሰረታዊ ምንጭ ደግሞ የኢኮኖሚያችን አወቃቀር በግብርና ላይ የተመሰረተና የምርታማነት ደረጃችንም ዝቅተኛ መሆኑ ነው። ለዚህ ችግር መባባስ አስተዋፅኦ የሚያደርግ ወይንም ለታዳጊ ሀገሮች ምርትና አገልግሎት ተወዳዳሪነት የማያመች አለምአቀፋዊ የኢኮኖሚ ስርዓት መኖሩ እንደ አንድ ትልቅ ነጥብ የሚታይ ቢሆንም ዋነኛው ምክንያት ግን የራሳችን ኢኮኖሚ አደረጃጀትና አመራረት ዘይቤ ነው። በብዛት ወደውጭ የምንልከው የግብርና ምርትና ከዚሁ ጋር የተያያዘ ጥሬ ዕቃ ነው። ከምንልከው ምርትና ጥሬ ዕቃ ውስጥ ደግሞ አብዛኛው መጠን በኢንዱስትሪ ውስጥ አልፎ በከፊል እንኳ ያለቀለት ሆኖ የተዘጋጀ ሳይሆን በተፈጥሮ እንደተገኘ ጥሬውን የሚላክ ነው። በዚህ መልክ ወደ ውጭ የምንልከው ጥሬ እቃ በጥራቱ በአለም ገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚችል አይደለም። ከዚህ ሌላ የምንልከው እቃ በአይነትም ሆነ በብዛት አነስተኛ ነው። ለረጅም ጊዜ ቡና፣ የቁም ከብትና ስጋ፣ ቆዳና ሌጦ፣ ቅባትና ጥራጥሬ አበባና ጫት በመላክ ተወስነን የቆየን ሲሆን የእነዚህን መጠን ለመጨመርም ሆነ ሌሎች ነገሮችንም በመላክ አይነቱ እንዲበዛ ለማድረግ የሚያስችል አቅም ሳንገነባ ቆይተናል። በአንፃሩ ከውጭ የምናስገባቸው ምርቶች አገልግሎቶች ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍሉ የኢንዱስትሪ ውጤቶች ናቸው። በዚህም የተነሳ የክፍያ ሚዛን መዛባት አለብን። ይኸንን ለማካካስ ከሀገር ውስጥና ከውጭ አበዳሪዎች የምንወስደው ብድር እየተቆለለ ነው። ያለችንን አነስተኛ አቅም ተጠቅመን የምናገኛትን ውስን ገቢ ለብድር ክፍያ ማዋል ስላለብን ከዚህ ተርፎ ለልማት የሚመደብ ሀብት ልናፈራ አልቻልንም። እንደውም ብድሩን ለመክፈል ሌላ ብድር ከመፈለግ የተሻለ መንገድ ስለጠፋ ተከታታይ ትውልድ እንኳ ከፍሎ የማይጨርሰው ተደራራቢ ብድር ታቅፈን ቁጭ ብለናል። ከዚህ አዙሪት የምንወጣበት መንገድ የኢንዱሰትሪ ልማት ብቻ ነው። ለኢንዱስትሪ ልማት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተን ወደ ውጭ የምንልካቸውን ምርቶችና እቃዎች በከፊልና ሙሉ በሙሉ ያለቀላቸው አድርጎ ለማዘጋጀት ካልተቻለ በጥራታቸውም ሆነ በመጠናቸው በአለም ገበያ ተወዳዳሪ ሊሆኑ አይችሉም። በአንድ በኩል የግብርና ምርቶችን ከተፈጥሮ እንደተገኙ በመላክ እጅግ ርካሽ በሆነ ዋጋ እየሸጥን በሌላ በኩል ደግሞ በውጭ ሀገር ኢንዱስትሪዎች የሚዘጋጁ ምርቶችን በውድ ዋጋ እየገዛን እስከቀጠልን ድረስ ከክፍያ ሚዛን መዛባት ችግር አንድንም።

በኢንዱስትሪ የተመረቱ ምርቶችና አገልግሎቶችን በጥራትና በብዛት ወደውጭ በመላክም ሆነ ከውጭ የምንገዛቸውን በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ እያደረግን የክፍያ ሚዛን መዛባትን ካላስወገድን በስተቀር ለልማት የሚውል ሀብት እያፈራን ወደፊት መግፋት አንችልም። እንደውም በእስከዛሬው መንገድ የብድር መአት እየተሸከምን ከቀጠልን መውጫ በሌለው የድህነት አዙሪት ውስጥ ከመሽጋገር አልፈን እንደ አንድ ነፃ ሀገርና ሕዝብ የራሳችንን ጉዳይ

በራሳችን ለመወሰን የሚያስችል ነፃነት እስከማጣት እንደርሳለን፡፡ አበዳሪዎቻችን የሚሰጡንን ትዕዛዝ ከመፈፀም ውጭ አንድም ጉዳይ በራሳችን ለመወሰን የማንችል ጥገኞች ሆነን ለመኖር እንገደዳለን፡፡ ከዚህ አይነቱ አደጋ ወጥተን በልማት ወደፊት ለመራመድና ነፃነታችንን ጠብቀን ለመኖር የምንችለው ለኢንዱስትሪ ልማታችን ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በዚህ ዘርፍ የሚመራና የሚደገፍ ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ልማት ማምጣት ስንችል ነው፡፡

የሀገራችንን ኢኮኖሚያዊ እድገት አንቆ የያዘው ሌላ ችግር የቁጠባ አቅማችን ዝቅተኛ መሆንና ፈጣን ልማት ለመፍጠር የሚያስችል የካፒታል ክምችት የሌላን መሆኑ ነው፡፡ የሀገር ውስጥ ቁጠባና ለኢንቨስትሜንት የሚሆን የካፒታል ክምችት ካላደጉ ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት አይቻልም፡፡ ቁጠባና የካፒታል ምስረታ የሚኖረው በሀገር ውስጥ በቂ ምርት ሲኖር፣ ገቢ ሲያድግና ከፍጆታ የሚተርፍ ተቀማጭ ሀብት ሲኖር ነው፡፡ የእኛ ሀገር ኢኮኖሚያዊ አደረጃጀትና የአመራረት ሁኔታ ለዚህ የሚመች አይደለም፡፡ ኢኮኖሚያችን ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ግብርናና በኋላቀር የአመራረት ዘይቤ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ለካፒታል ምስረታ የሚገለግል በቂ የሀገር ውስጥ ቁጠባ ስለሌለን ከውጭ በሚገኝ ብድርና እርዳታ ላይ ለመንጠልጠል ተገደናል፡፡ ከዚህ ሁኔታ ለመወጣት የሚያስችለን ዘላቂ የምርት እድገትና የገቢ መጨመር እንዲኖር ማድረግም ሆነ የሀገር ውስጥ ቁጠባን አሳድገን ለልማት የሚውል በቂ የካፒታል ክምችት ማግኘት ካለብን ለኢዱስትሪ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ይኖርብናል፡፡ የሀገር ውስጥ ቁጠባ እንዲያድግና ለካፒታል ምስረታ ያለው ድርሻ በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨመር በማድረግ ለልማት የሚመደብ በቂ ካፒታል ሊኖረን የሚችለው ኢኮኖሚያችን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ከተቀየረ ነው፡፡ ምክንያቱም ከእርሻው ዘርፍ ጋር ሲነፃፀር በኢንዱስትሪ የሚገኘው ትርፍ ድርሻ ከፍተኛ በመሆኑ የተሻለ የቁጠባ ደረጃ እንዲኖረን ስለሚያስችል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከእርሻው ዘርፍ ይልቅ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ለታክስ አሰባሰብ የተመቸ በመሆኑ የመንግስትን ገቢ ለማሳደግም ሆነ ለልማት የሚመደብ ሀብት እንዲጨምር ለማድረግ ያስችላል፡፡ ስለዚህ ፈጣን ቀጣይነት ያለው አስተማማኝ የኢኮኖሚ እድገት እንድናመጣ የሚያስችል ብሔራዊ ቁጠባ እንደኖርና ለልማት የሚውል በቂ ካፒታል እንዲመሰረት ለኢንዱሰትሪ ልማት ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡

ኢንዱስትሪ ዋነኛ የልማት አንቀሳቃሽ ሞተርና የጠቅላላው ኢኮኖሚያችን መሪ መሆን አለበት ሲባል ለዚህ ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠውና በተቻለ ፍጥነት ሊለማ ይገባዋል ማለት ነው፡፡ ኢንዱስትሪ ራሱ የልማት ውጤት እንደመሆኑ ሀገሪቱ በእጇ ያለውንና ከውጭም የሚገኘውን ሁሉ ለኢንዱስትሪ ልማት ማዋል ይኖርባታል ማለት ነው፡፡ ለሀገሪቱ ልማት ሲባል ከውጭ ከሚገባው ብድርና እርዳታ መካከል ከፍተኛው ድርሻ ወደ ኢንዱስትሪ ልማት መዞር አለበት፡፡ ለእርሻ ከሚመደበው የልማት እርዳታና ብድር ውስጥ ከፍተኛው ደርሻ ለተብጣጠሰ እርሻ ከሚውል ለዘመናዊና ለንግድ እርሻ የሚውልበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡ ለኢንዱስትሪ ማስፋፊያ የሚውልበት መንገድ መመቻቸት አለበት፡፡ ይኸንን ማድረግ ካልቻልን በብድርና በእርዳታ የሚገኘውን ገንዘብ ዘላቂና ፈጣን ልማት በማያረጋግጥ ሁኔታ ስንበትን እንኖራለን እንጂ ትርጉም ያለው የኢኮኖሚ ለውጥና እድገት አናመጣም፡፡ ለእለት ችግር ማስታገሻ እንፈጥር ካልሆነ በስተቀር በአጠቃላይ የሀገሪቱን እድገት ልናፋጥን ቀርቶ የግለሰቦችንም ችግር በዘለቄታ መፍታት አንችልም፡፡ የኢኮኖሚ አደረጃጀታችንና የአመራረት ዘይቤያችን ሊሻሻል አይችልም፡፡

ስለዚህ ፈጣንና ዘላቂ ልማት በሀገራችን ለማምጣት ከሁሉም በፊት ለኢንዱስትሪ ልማት ትኩረት መስጠት ይኖርብናል፡፡ ለዚህ ዘርፍ ልማት የሚውል በቂ መዋዕለ ንዋይ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ መሰብሰብ ይገባናል፡፡ የሠራተኛ ኃይላችንን ለዚህ ዘርፍ ልማት በሚያግዝ መንገድ እያስተማርንና እያሰለጠንን ማሰማራት ይገባናል፡፡ የግል ባለሀብቱ እንዲጠናከርና በዘርፉ ሰፊ ተሳትፎ እንዲኖረው መደገፍ ይኖርብናል፡፡ በሀገር ውስጥ ባለሀብቱ አቅም የማይሸፍነውን አንድም በውጭ ባለሀብቶች አልያም በመንግስት ተሳትፎ እንዲሸፈን ማድረግ ይገባል፡፡ በእነዚህና በመሳሰሉት መንገዶች ኢንዱስትሪውን ስናለማ ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ልማትም ይፋጠናል፡፡ የግብርና፣ የማዕድን፣ የኮንስትራክሽንና የሌሎች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘርፎች ትስስር እንዲጨምርና ዘላቂ እድገት እንዲኖር ማድረግ የሚለው የተሳካ የኢንዱስትሪ ልማት ሲኖር ነው፡፡ የኢንዱስትሪ ልማትን ማሳካት ከተቻለ በሌሎች ሴክተሮችም የተሳካ እድገት ለማምጣት ምቹ ሁኔታ ተፈጠረ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ የተሳካ የኢንዱስትሪ ልማት

ስናስመዘግብ በግብርናው ዘርፍ አሁን ያለብንን ፈታኝ ችግሮች ለማቃለል እንደምንችል ጥርጥር የለውም፡፡ ምክንያቱም ኢንዱስትሪ ሲለማ በግብርናው ዘርፍ ከተሰለፈው በርካታ የሰው ኃይል ወደ ኢንዱስትሪው ለማዞር እድል እናገኛለን፣ እንዲህ አይነት ሁኔታ ሲፈጠር ደግሞ በግብርናው ውስጥ ያለውን መጨናነቅ አስወግደን የግብርናውን ውጥረት ከማስተንፈስ በተጨማሪ የገበሬው ይዞታ እንዲጨምርና ገቢው እንዲያድግ በማድረግ የኑሮ መሻሻል እናስገኛለን፡፡ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እንዲጠናከርና የእርሻ መሬት ለምነት እንዲጨምር ምቹ ሁኔታ እንፈጥራለን፡፡ ከዚህ ሌላ ለግብርና ምርት ሰፊና አስተማማኝ ገበያ መፍጠር ስለሚቻል በግብርና መስክ የተሰማራው ኃይል የተሻሻለ ቴክኒዎሎጂ እየተጠቀመ ምርታማነቱን ለማሳደግ፣ ተወዳዳሪ ምርት ወደ ገበያ ለማቅረብና ገቢውን ከፍ ለማድረግ የሚያስችለው አቅም እንዲገነባ እድል ያገኛል፡፡ በዚህ መንገድ የግብርና ምርት እንዲያድግና የገበሬው ኑሮ እንዲሻሻል ማድረግ ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ በሀገራን ፈጣንና ዘላቂ የሆነ አስተማማኝ የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብ፣ የሀገራችንን ኢኮኖሚ አወቃቀር አሻሽለን የተሳሰረና እርስ በርሱ ተደጋግፎ የሚሰራና በማያቋርጥ ሁኔታ የሚያድግ ለማድረግ፣ የስራ አጥነትን ችግር ለማቃለል፣ በወጪና ገቢ ንግድ የሚታየውን የክፍያ ሚዛን መዛባት ለማስቀረት፣ የሀገር ውስጥ ቁጠባን ለማሳደግና ለካፒታል ምስረታ ከፍተኛ ሚና እንዲጫወት ለማድረግ ለኢንዱስትሪ ልማት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተን መረባረብ ይኖርብናል፡፡ ይኸንን ስናደርግና ውጤትም ስናስመዘግብ ኢንዱስትሪያችን በእርግጥም ዋነኛው የልማት አንቀሳቃሽ ሞተርና የኢኮኖሚያችን መሪ ይሆናል ማለት ነው፡፡ በኢንዱስትሪ የሚመራና የሚደገፍ ልማት ማካሄድ ከቻልን ያለ ጥርጥር ለሀገራችን ፈጣንና ዘላቂነት ያለው አስተማማኝ ኢኮኖሚያዊ እድገት እናመጣለን፡፡

ኢንዱስትሪው ይኸንን የመሪነት ሚና በሚገባ እንዲጫወት ከተፈለገ ደግሞ ራሱን ኢንዱስትሪውን በማልማት ረገድ የተወሰነ ርቀት መሄድ ይኖርብናል፡፡ ይኸውም በመጀመሪያ ደረጃ ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት የኢንዱስትሪው ድርሻ እያደገ መሄድ አለበት፡፡ አሁን በሀገራችን ያለው አዝማሚያ ይኸንን የሚያሳይ አይደለም፡፡ በንጉሱ ጊዜ የኢንዱስትሪው ድርሻ 10 በመቶ ገደማ የነበረ ሲሆን በደርግ ጊዜ ወደ 12 በመቶ ገደማ ነበር፡፡ በአሁኑ አገዛዝ ደግሞ ከ10 በመቶ በታች እየወረደ መጥቷል፡፡ ከዚህ ደግሞ የከፍተኛ ኢንዱስትሪው ድርሻ እየጨመረ እንዲሄድ ማድረግ ይገባል፡፡ አንድ ሀገር ኢንዱስትሪያዊ ሆኗል የሚባለው ቢያንስ ከጠቅላለው ብሔራዊ ምርት ውስጥ 25 በመቶ የሚሆነው ከኢንዱስትሪ ዘርፍ መምጣት ሲችል ነው የሚል የሞያተኞች አስተሳሰብ አለ፡፡ የእኛም ሁኔታ ወደዚህ እንዲያመራ ማድረግ አለብን፡፡ በሁለተኛ ደረጃ በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራው የሰው ኃይል እድገት እንዲያሳይ መደረግ አለበት፡፡ አንድ ሀገር ፈጣንና ዘላቂ ወደሆነ የኢንዱስትሪ ልማት እያቀና ነው የሚባለው ቢያንስ ከጠ ቅላላው ሕዝብ ውስጥ ከ10 በመቶ በላይ የሚሆነው በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ መሆን ሲችል ነው የሚል የአንዳንድ ባለሞያዎች አስተያየት መኖሩ ይታወቃል፡፡ የሀገራችን ሁኔታ ሲታይ ከጠቅላላው የስራ ኃይል መካከል በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተቀጠረው ከ8 በመቶ የማይበልጥ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በፋብሪካ ውስጥ የተሰማራው ከጠቅላላው ሰራተኛ ያለው ድርሻ ከ1 በመቶ ያነሰ ነው፡፡

ከዚህም ሌላ ያለን የኢንዱስትሪ ዓይነትና ደረጃም ከቀላልና የጎጆ ኢንዱስትሪ ያላለፈና ፈጣን ለሆነ ዘላቂ ልማት የሚያግዝ አቅም የሌለው በመሆኑ ገና ብዙ መስራት ይጠበቅብናል፡፡ ለምሳሌ ቻይና ሀገሪቱ ካላት ጠቅላላ የስራ ኃይል ውስጥ በኢነዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራው መጠን ከ25 በመቶ የበለጠ ከመሆኑም በላይ የኢንዱስትሪው ዓይነትና ደረጃም ፈጣንና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ከፍተኛ አቅም፣ ዘመናዊ አደረጃጀትና አሰራር ያለው ነው፡፡ በሶስተኛ ደረጃ ፈጣንና ዘላቂ ኢንዱስትሪያዊ ልማት እንዲረጋገጥ ከጠቅላለው የኢንዱስትሪ ምርት ውስጥ የፋብሪካው ድርሻ ከፍተኛ ሊሆን ይገባዋል፡፡ የሀገራችን ሁኔታ ሲታይ ደግሞ የግብርናው ዘርፍ አነስተኛ ይዞታ ባላቸው ገበሬዎች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ከጠቅላላው ኢንዱስትሪ ውስጥ ከ76 በመቶ በላይ የሚሆነው አነስተኛ ኢንዱስትሪ ነው፡፡ የመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ድርሻ የበለጠ እንዲሆን ገና ብርቱ ጥረት የሚጠይቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ፈጣንና ዘላቂ ልማት በሀገራችን እንዲረጋገጥ ከተፈለገ ለኢንዱስትሪ ልማት የተለየ ትኩረት ሰጥቶ ከመንቀሳቀስ የተሻለ ምርጫ የለም፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ ከጠቅላላው ኢንዱስትሪ ምርት ውስጥ የፋብሪካው ድርሻ ከፍተኛ ነው ቢባልም የሀገራችን ፋብሪካ በአብዛኛው የፍጆታ እቃ ከማምረት ያልወጣና የቴክኒዎሎጂ ብቃቱም ሆነ የማኔጅሜንት አቅሙ ደካማ ስለሆነ ፈጣና ዘላቂ ልማት ለማምጣት ወደሚያስችለው ደረጃ እንዲሸጋገር ከፍተኛ ርብርብ መደረግ አለበት፡፡

ኢንዱስትሪው ዋነኛ የልማታችን አንቀሳቃሽ ሞተርና የልማት ውጤት የሚያደርግ ስትራቴጂ እንከተላለን ሲባል ሀገሪቱን በአንድ ጀምበር ወደ ኢንዱስትሪ ደረጃ እናሸጋግራታለን ማለት አይደለም፡፡ ወይንም የሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ አወቃቀር በቀላሉ ወደኢንዱስትሪያዊ ደረጃ ይቀየራል ማለት አይደለም፡፡ ወደ ኢንዱስትሪ ደረጃ ለመሸጋገር ዋነኛው ትኩረታችን ራሱን ኢዱስትሪውን በማልማት ላይ የተመሰረተ ሆኖ አቅማችንን ባገናዘበ መንገድ እንዲከናወን የሚያስችል ስትራቴጂ በያንዳንዱ የኢኮኖሚ ዘርፍ ነድፎ ስራ ላይ ማዋል ይገባል፡፡

# 7. የኢንዱስትሪ ልማታችንን ለማፋጠን የሚረዱ አማራጭ ስትራቴጂዎች

ኢንዱስትሪውንም ሆነ ሌላውን የኢኮኖሚ ዘርፍ ለማልማት ምን አይነት ስትራቴጂ ማውጣት ይገባል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚቻለው ወደፊት ልንደርስበት የምንፈልገውን የልማት ደረጃ ብቻ ሳይሆን አሁን የምንገኝበትንም አቅም በማገናዘብ ነው፡፡ ኢንዱስትሪያችንንም ሆነ ሌላውን የኢኮኖሚ ዘርፍ ለማልማት ካፒታልን በሰፊው የሚጠቅም (Capital intensive) ስትራቴጂ ወይንስ ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀም (labour intensive)ስትራቴጂ እንከተል ብሎ ምርጫ ለማድረግ አሁን ያለን ምንድን ነው? የሚል ግምገማ ማድረግ ይገባል፡፡ አሁን ያለን የተሻለ አቅም የሰው ጉልበት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ስለዚህ ኢንዱስትሪውንም ሆነ ሌሎቹን የኢኮኖሚ ዘርፎች ለማልማት ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀም የልማት ስትራቴጂ መከተል ይኖርብናል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ የኢንዱስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚ ለማልማት ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀም ስትራቴጂ እንከተላለን ሲባል ለአነስተኛ ኢንዱስትሪ የበለጠ ትኩረት ሰጥተን እንንቀሳቀሳለን ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች በባህርያቸው ጉልበትን በሰፊው መጠቀም ያስችላሉ፡፡ ለምርት የሚያስፈልገውን ጥሬ እቃ ከሀገር ውስጥ ለማግኘት የተሻለ እድል ያስገኛሉ፡፡ አዳዲስ ስራ በቀላሉ ለመፍጠርና ተጨማሪ የስራ እድል ለማስገኘት ይረዳሉ፡፡ ለስራቸው የሚያስፈልገውን ያልሰለጠነና በከፊል የሰለጠነ ጉልበት ከሀገር ውስጥ ለማግኘት ያስችላሉ፡፡ በየክልሉ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የኢንዱሰትሪ ስርጭት እንዲኖር ያስችላሉ፡፡ እነሱን ለመገንባት የሚያስፈልገው የመሰረተ ልማት መዋቅርና የውጭ ምንዛሬ ፍላጎታቸውም በተነፃፃሪነት ሲታይ ዝቅተኛ ስለሚሆን በቀላሉ የሚስፋፋበት ሁኔታ አለ፡፡ ስለዚህ የኢንዱስትሪ ልማታችንን ለማፋጠን በቅድሚያ ከፍተኛ ርብርብ መደረግ የሚገባው ጉልበትን በሰፊው ለመጠቀም በሚያስችለው የአነስተኛ ኢንዱስትሪ ልማት ላይ ነው፡፡ አሁን ያለን አቅም ከዚህ እንድንጀምር የሚያስገድድ ቢሆንም ፈጣንና ዘላቂ ልማት የማምጣት ፍላጎታችን ደግሞ በዚህ ብቻ የሚሳካ ስለማይሆን ካፒታልን በሰፊው የሚጠቀም ስትራቴጂም ጎን ለጎን ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ይገባል፡፡ ለዚህም ተፈፃሚነት ሀገሪቱ ለልማት ልታውለው ከሚገባና በሀገር ውስጥ ከምታፈራውም ሆነ ከውጭ በብድርና እርዳታ ከምታገኘው ሪሶርስ አብዛኛውን ለኢንዱስትሪ ልማት መመደብ ይኖርባታል፡፡ ለከፍተኛ ኢንዱስትሪ መስፋፋት አስፈላጊ የሆነ የመሰረተ ልማት ግንባታ ማካሄድ ይገባታል፡፡ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች በከፍተኛ ኢንዱስትሪ ልማት እንዲሳተፉ የሚያደፋፍር የኢንቨስትሜንት ፖሊሲ ማውጣት ይኖርበታል፡፡ በከፍተኛ ኢንዱስትሪ ልማት ሊሰለፍ የሚችል የሰው ኃይል ለማግኘት ሰፊ ስልጠና ማካሄድ ይገባታል፡፡ የቴክኒዎሎጂ ሽግግር እንዲፋጠን፣ የማኔጅመንት አቅም እንዲጠናከር፣ ዘመናዊ የኢንዱስትሪ አደረጃጀትና አሰራር እንዲገነባ የሚያስችል ጥረት ማድረግ አለባት፡፡

ከዚህ ጎን ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት (Import substitution) የሚያስችል ስትራቴጂ በከፍተኛ ጥንቃቄ ልንከተል ይገባል፡፡ ይሽንን መከተል ያለብን በሀገራችን የሚገነቡ ጨቅላ ኢንዱስትሪዎች በተነፃፃሪነት አነስተኛ በሆነ አቅምና አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ ብቃታቸውን ማሳደግ ስለሚቻል፣ አላስፈላጊ ሸቀጦችን ከውጭ ለማስገባት የምናወጣውን ከፍተኛ ወጪ በማዳን ለልማት ጠቃሚ የሆኑ የካፒታል እቃዎችን ለመግዛት የሚረዳ የውጭ ምንዛሬ መቆጠብ ስለሚል፣ በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል ትስስር እንዲጠናከር ስለሚረዳ ነው፡፡ ለሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች አስፈላጊው ጥበቃ ከተደረገላቸው አዳዲስ ተቋሞች የሚከፈቱበት ሁኔታ ስለሚፈጠር የኢንዱስትሪ ግብዓቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ የሚያስችል መነቃቃት ይኖራል፡፡ የእነዚህን ምርቶች በግብዓትነት የሚጠቀሙ ዘርፎች ይስፋፋሉ፡፡ ይኸም ምርት እንዲያድግና ገቢም እንዲጨምር አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ የገቢ ማደግ ደግሞ የኢንዱስትሪ ምርቶች በሀገር ውስጥ ገበያ እንዲያገኙ ይረዳል፡፡ የሀገር ውስጥ ምርቶች ሀገር በቀል ጉልበትን ለማሰልጠንና የቴክኒዎሎጂ መሻሻል እንዲኖር ለማድረግ ይጠቅማሉ፡፡

በእርግጥ እንደማንኛውም ታዳጊ ሀገር የእኛም ኢኮኖሚ ጥገኛ በመሆኑ አሁን ባለው አለም አቀፍ የኢኮኖሚ ስርዓት ውስጥ ተወዳዳሪ ምርትና አገልግሎት በማቅረብ በቀላሉ ውጤታማ ለመሆን ይቻላል የሚል አይደለም፡፡ የተለያዩ የልማት ቲዎሪዎች ለታዳጊ ሀገሮች እድገት ይበጃሉ የሚላቸውን ልዩ ልዩ አማራጮች ለማቅረብ ቢሞክሩም ጉዳዩ እንዲህ ቀላል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ለምሳሌ የአለምን ሕዝብ ዘመናዊና ባህላዊ በሚል ሁለት ምድቦች ከፍሎ የሚመለከተው የዘመናዊነት አመለካከት የ3ኛው አለም የሚሉት ሀገሮች ችግር በውጫዊ ተፅዕኖ ወይም በአለም አቀፉ የስራ ክፍፍልና የኢኮኖሚ ስርዓት መዛባት የተከሰተ ሳይሆን ውስጣዊ ችግር በውጫዊ ተፅዕኖ ወይም በአለም አቀፉ የስራ ክፍፍልና የኢኮኖሚ ስርዓት መዛባት የተከሰተ ሳይሆን ውስጣዊ ችግር ስለሆነ መፍትሔውም ከውስጥ መምጣት አለበት ብሎ ያምናል፡፡ ባደጉትና ባላደጉት ሀገሮች መካከል አሁን ያለው ግንኙነት እንደመጥፎ ነገር ሳይሆን እንደጠቃሚ ነገር መታየት አለበት ብሎ ያምናል፡፡

ይኸንን አስተሳሰብ የሚከተሉት ኒዎ ሊበራሊስቶች 3ኛው አለም የሚለው ፅንሰ ሀሳብ በኢንዱስትሪ ከገፉት ምዕራባዊያን የሪሶርስ ድጋፍ ለማግኘት ሲባል ሆን ተብሎ የተፈጠረ ፖለቲካዊና ርዕዮተ ዓለማዊ ዘዴ እንጂ ትርጉም ያለው ነገር አይደለም ይላሉ፡፡ እንደውም በእርሱ አስተያየት የ3ኛው አለም ሀገሮች የተለየ ባህርይ ወይም ችግር ስለሌላቸው የአደጉትን ሀገሮች ልዩ ድጋፍ ከመጠበቅ ይልቅ በቀጥታ በአለም ነፃ ገበያ ውድድር ስርዓት ውስጥ ገብተው እንደማንኛውም ሀገር ተሳትፎ ቢያደርጉ ለማደግ እድሉ አላቸው ይላሉ፡፡ 3ኛው አለም የሚለው አስተሳሰብ እርዳታ የፈጠረው ስለሆነ ይህ ካልቀረ ልመናቸውን ይቀጥላሉ፡፡ እርዳታ መጠ በቃቸውን ትተው በአለምአቀፍ ነፃ ገበያ ውድድር ውስጥ ከገቡ 3ኛው አለም የሚል ነገር አይኖርም ይላሉ፡፡ በአጭሩ የዘመናዊነት አቀራረብ የ3ኛው አለም ችግር የራሳቸው ውስጣዊ ባህላዊ ስርዓታቸው የፈጠረው ችግር ነው ከሚል አስተሳሰብና የምዕራቡን አለም አንድ መልካም የእድገትና የልማት ምሳሌ አድርጎ ከመቁጠር በመነሳት ለታዳጊ ሀገሮች የሚቀርበው መፍትሔ ከባህላዊ አደረጃጀትና አሰራር ወጥተው ወደ ቴክኒዎሎጂያዊና ኢኮኖሚያዊ ዘመናዊነት፣ ወደሶሲዮ ባህላዊ ዘመናዊነትና ወደ ፖለቲካዊ ዘመናዊነት መሸጋገር አለባቸው የሚል ነው፡፡ ከተበጣጠሰና ከእጅ ወደአፍ ከሆነ የግብርና ኢኮኖሚ ወጥተው ወደ ኢንዱስትሪና ምዕራባዊያን ወደሚገኙበት ዘመናዊ አደረጃጀትና አሰራር መግባት አለባቸው የሚል ነው፡፡

የጥገኝነት ንድፈ ሀሳብ ደግሞ ስለሶስተኛው አለም ችግሮች የሚያደርገው ግምገማና የሚያቀርበው መፍትሔ ከዚህ የተለየ ነው፡፡ የጥገኝነት ቲዎሪ ምንጩ ከማርክሲዝም ቢሆንም ከማርክሲስቶች አመለካከት የሚለይበትም ሁኔታ አለ፡፡ እነማርክስ በካፒታሊዝም ስርዓት ውስጥ በተወሰነ ደረጃ እድገት እንዳለ ያምኑ ነበር፡፡ አንዳንዶቹ የጥገኛ ቲዎሪ አቀንቃኞች ግን ካፒታሊዝምና ኢምፔሪያዝም ማለት ጥገኝነትና በእድገት ወደኋላ መቅረት ማለት ብቻ ነው በሚል ለታዳጊ ሀገሮች ጥገኛ መሆንና ወደኋላ መቅረት ተጠያቂው አሁን በአለም ላይ ያለው የስራ ክፍፍልና የኢኮኖሚ ስርዓት ነው የሚል እምነት አላቸው፡፡ ይህ የጥገኝነት ቲዎሪ በሶሰተኛው አለም በተለይም በላቲን አሜሪካ ምሁራን የተፈጠረ ሲሆን በምዕራባዊያን ከተፈጠ ረው የዘመናዊነት ቲዎሪ የተለየ ግምገማና መፍትሔ የሚያቀርብ አመለካከት ነው፡፡ በዚህ ቲዎሪ መሰረት ጥገኝነትና በዕድገት ወደኋላ መቅረት የሚባሉት አስተሳሰቦች ከኮሎኒሊዝም መከሰት ጋር የተከሰቱ ታሪካዊ ሁኔታዎች ውጤት እንጂ ተፈጥሯዊ ክስተቶች ስላልሆኑ የ3ኛው አለም ሀገሮች እድገት መፋጠንም ሆነ መጓተት ከአሁኖቹ የምዕራብ ሀገሮች እድገት ተነጥሎ መታየት የለበትም የሚለውም አመለካከት ሌላው የጥገኝነት ቲዎሪ ማዕከላዊ ነጥብ ነው፡፡ የጥገኝነት ቲዎሪ በአለም አቀፍ ደረጃ አሁን ያለው የስራ ክፍፍልና ፍትሃዊ ያልሆነ አለም አቀፍ የኢኮኖሚ ስርዓት በ3ኛው አለም ሀገሮች ላይ ያሳደረውን የእድገት መገታት በሚመለከት ጠቃሚ ግምገማዎችንና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ለማቅረብ በመቻሉ ጥሩ አስተዋፅኦ ቢኖረውም አንዳንድ ጉዳዮችን በጥሞና የማየት ድክመቶች ስላሉበት አወዛጋቢ መምሆኑ አልቀረም፡፡

በኢንዱስትሪ የበለፀጉት ሀገሮች የቴክኒዎሎጂ፣ የፋይናንስ፣ የሪሶርስ አጠቃቀም አቅም የመገናኛ ብዙሃንና የአውዳሚ መሣሪያዎች ሞኖፖሊ በመፍጠራቸው በአለም ስርዓት ያልተመጣጠነ እድገትና ግንኙነት መከሰቱ እውነት ነው፡፡

ይሁን እንጂ አሁን ባለው የኢኮኖሚ ስርዓት ውስጥ ሆኖ ልማት ለማምጣትና ስፍራን ለማሻሻል የሚቻልበት ሁኔታ ጨርሶ የተዘጋ አለመሆኑ ደግሞ ሌላው እውነት ነው:: ለምሳሌ ታይዋንና ኮርያ ፈጣን ልማት አስመዝግበው ራሳቸውን ወደ አደጉት ሀገሮች ምድብ ማስገባት ችለዋል:: ቻይናም ወደዚያው እየተጠጋች ሲሆን ሕንድና ሌሎች ሀገሮችም መሻሻል አሳይተዋል:: ብዙዎቹ ታዳጊ ሀገሮች አዲስ አለም አቀፍ የኢኮኖሚ ስርዓት እንዲፈጠር ለሚያነሷቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች ያደጉት ሀገሮች ምላሽ ቀና አዝማሚያ እየታየበት በመምጣቱ ነገሮች ሁሉ ለታዳጊ ሀገሮች ተስፋ አስቆራጭ ሆነው የሚታዩበት አመለካከት ሊሻሻል የሚገባው ነው:: ለታዳጊ ሀገሮች ምቹ የሆነ አለም አቀፍ ንግድ እንዲኖር፣ የእዳ ቅነሳና የእርዳታ ጭማሪ እንዲደረግ፣ ሀገር አቋራጭ በሆኑ ሕብረ ብሔራዊ ኮርፖሬሽኖች ላይ ቁጥር እንዲደረግ፣ አለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ወዘተ. በታዳጊ ሀገሮች ለሚነሱ ጥያቄዎች ከምዕራባዊያን የሚሰጠው ምላሽ ፈጣን ነው ባይባልም በእምቢተኝነት የተዘጋ እንደሆነ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል አይደለም:: ይልቁንም አወንታዊ የሆነ ገጽታው እድገት እያሳየ በመሆኑ ሁኔታዎችን አጨልሞ መመልከት ተገቢነት የለውም:: ያደጉት ሀገሮችም ቢሆኑ ካላደጉት ሀገሮች ጋር የመሰረቱትን ግንኙነት ጠብቀው ማቆየት የሚችሉት ግንኙነቱን ፍትሃዊ በማድረግ እንደሆነ ከምንጊዜውም በተሻለ እያመኑበት የመምጣት ዝንባሌ ማሳየት ጀምረዋል::

ስለዚህ አሁን ባለው አለም አቀፍ የስራ ክፍፍልና የኢኮኖሚ ስርዓት ውስጥ ሆኖ ጥራት ያለው ምርት ለአለም ገበያ እያቀረቡ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚጠይቀው ትግል ቀላል ባይሆንም ያለውን ቀዳዳ ሁሉ እየተጠቀሙ የሀገራችንን ልማት ለማፋጠንና ስፍራዋን ለማሻሻል ጥረት ከማድረግ መቦዘን አይገባም:: ከፍተኛ የብድር እዳ ያለብን በመሆኑና ወደ ውጭ የምንልካቸው ሸቀጦች ሙሉ በሙሉ የእርሻ ጥሬ ምርት ከመሆናቸውም በላይ በአይነትም ውስን ናቸው:: በአንፃሩ ከውጭ የምናስገባቸው በአብዛኛው የተፈበረኩ እቃዎችን ሲሆን እነዚህም በብዛት አላቂ እቃዎች ናቸው በሽያጭና በግዥ እንቅስቃሴዎችን ከፍተኛ ግንኙነት የመሰረትነው በአብዛኛው ከምዕራባዊያን ጋር በመሆኑ በምንሸጠውና በምንገዛው መካከል ያለው የክፍያ ሚዛን የተዛባ ነው:: ስለሆነም በሀገር ደረጃ ጥገኛ ኢኮኖሚ እንዳለን የታወቀ ነው:: በንግድ የተሳሰርናቸው ሀገሮች ከእኛ የበለጠ የማምረትና የመነገድ እውቀት ስላላቸው እኩል ተጠቃሚዎች አይደለንም:: ይሁን እንጂ ፈጣንና ዘላቂ ልማት ለማምጣት አሁን ካለው አለም አቀፍ የኢኮኖሚ ስርዓት ራሳችንን ገለልተኛ በማድረግ ሊመጣ የሚችል ነገር አይደለም:: በዚሁ ሁኔታ ውስጥ እንዳለን ልማት ለማምጣት የሚያስችሉንን አማራጮች ከመጠቀም በስተቀር ሌላ አማራጭ የለም:: አብዮታዊ ዴሞክራቶች እንደመጀሩት በሶሻሊዝምና በካፒታሊዝም መካከል ቆሞ ወለም ዘለም ለማለትና ምንአልባት ሶሻሊዝም ተመልሶ ከመጣ ወደዚያው ለማምራት ይቻል ይሆናል በሚል ስሌት በአንዴ ሁለት ዙር ላይ ለመንጠልጠል ሁኔታችን አይፈቅድም:: ስለዚህ በካፒታሊስት የአመራረትና የግብዓት ስርዓት ከመመራት ውጭ ልንሄድ አንችልም:: ይኸንን መርህ ጨብጠን የእዳ ጫና የሚነሳበትን፣ የንግድ ግንኙነታችን መረብ የሚሰፋበትን፣ ለውጭ የምናቀርባቸው ሸቀጦችና አገልገሎቶች በዓይነትና በጥራት የሚሻሻሉበትን ከውጭ ከምናስገባቸው መካከል የተወሰኑት በሀገራችን ሊመረቱ የሚችሉበትን ሁኔታ መፈጠርና አመራረታችንን ጥራት ያለውና ተወዳዳሪ እንዲሆን ጥረት ማድረግ ይገባናል:: ይኸንን ለማሳካት በኢንዱስትሪው መስክ በቀላሉ ሊለወጥ ወደ ውጭ ገበያ ቀርበው ገቢ ሊያስገኙ በሚችሉት ስትራቴጂያዊ ዘርፎች ላይ ማተኮር ይኖርብናል:: እነዚህን በሀገር ውስጥና በውጭ ባለሀብቶች እንዲለሙ በማድረግ ወደ ውጭ በመላክና ከውጭ የምናስገባውን በመተካት የክፍያ ሚዛናችንን ለማስተካከልና የካፒታል አቅማችንን ለማሻሻል ጥረት ማድረግ አለብን:: ለምሳሌ በጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ይኸንን ተግባራዊ ልናደርግ እንችላለን:: በመገናኛ ቴክኒዎሎጂም በተነፃፃሪነት ዝቅተኛ የኢንቨስትሜንት ወጪ መድበን ከፍተኛ ጥቅም ልናገኝ እንችላለን:: ሕንድ ከመረጃ ቴክኒዎሎጂ ወደ 30 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ታገኛለች:: ከውጭ ካፒታል የሚገባበትን ሁኔታ ፈጥረን በኮንስትራክሽንና በቆዳ ከፍተኛ ገቢ የምናገኝበት እድል አለ:: ጃፓኖችና ኮርያዎች የውጭ ባለሀብቶችን እየተጠቀሙ ካፒታል እያስገቡና የራሳቸውንም አቅም እያሻሻሉ ፈጣንና ዘላቂ እድገት ማስመዝገባቸው ይታወቃል:: እኛም ይኸንን የማንሞክርበት ምክንያት የለም::

ሌላው የክፍያ ሚዛናችንን የሚያስተካክልና የካፒታል ክምችት አቅማችንን ለማሳደግ የሚረዳ ዘርፍ ቱሪዝም ነው:: በኬንያ ከጠቅላለው የሀገር ውስጥ ምርትና ከውጭ ምንዛሬ ግኝት ከፍተኛ ድርሻ ያለው የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ነው:: እኛ ደግሞ ከኬንያ የተሻለ የቱሪዝም ሀብት እያለን ከዚህ ዘርፍ የምናገኘው ጥቅም እጅግ አነስተኛ ነው:: ቱሪዝምን ለማልማት የሚያስፈልገው

የኢንቨስትመንት መጠን በተነፃፃሪነት ሲታይ አነስተኛ ቢሆንም ተገቢ ትኩረት ስላልተሰጠው ከዘርፉ ሊገኝ የሚችለው ጥቅም እየተገኘ አይደለም፡፡ በኢንዱስትሪ፣ በመገናኛ ቴክኒዎሎጂ፣ በቱሪዝም፣ በኮንስትራክሽን በግብርናና በሌላም የኢኮኖሚ ዘርፎች ተወዳዳሪ ምርትና አገልግሎት ማቅረብ እንዳንችል እንቅፋት ይሆናል ተብሎ የሚታሰበው የካፒታል አቅም የሌለን መሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን ይኸንን አቅም ቀስ በቀስ ለማሻሻል የሚያስችል ጥረት እስከተደረገ ድረስ ውጤት ማምጣት ይቻላል፡፡ ለዚህ መፍትሔው በመጀመሪያ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች ተሳትፎ እንዲጨምር የሚያስችል ምቹ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ማውጣት ነው፡፡ በተለይም በውጭ ሀገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሀገር ውስጥ ካሉት ባለሀብቶች ጋር ተቀናጅተው ወይም ከውጭ ባለሀብቶች ጋር በጋራ ሆነው አልያም ራሳቸውን ችለውው ሊሰሩ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ጠቃሚ ነው፡፡ ካፒታልና እውቀት ያላቸው ኢተዮጵያውያን አሉ፡፡ ካፒታል ባይኖራቸውም እውቀትና የልማት ተሞክሮ የቀሰሙ ኢትዮጵያውያን አሉ፡፡ በሀገር ውስጥም የካፒታል አቅማቸው ዝቅተኛ ቢሆንም እውቀት፣ ከፍተኛ የልማት ፍላጎትና የሀገር ፍቅር ስሜት ያላቸው ኢትዮጵያውያን አሉ፡፡ እነዚህን እርስ በርስ ወይንም ከውጭ ባለሀብቶች ጋር ተቀናጅተው እንዲያለው ቢደረግ ከፍተኛ ውጤት ማምጣት ይቻላል፡፡

በግብርናውም መስክ እንደዚሁ ገበያ መር የሆነና ጥራት ያለው ተወዳዳሪ የእርሻ ስራ እነዲሰራ የሚያስችል ስትራቴጂ ልንከተል ይገባል፡፡ በግብርናው ዘርፍ የአካባቢና የምርት ስፔሽያላይዜሽን እንዲኖር በማድረግ እያንዳንዱ አካባቢ ያለውን የአየር ንብረትና የአፈር ፀባይ የተከተለ የልማት ስራ እንዲያካሂድ ልናደርግ እንችላለን፡፡ አንዱ ካሽ ክሮፕ (እንደቡና ፍራፍሬና የመሳሰሉትን) ቢያለማ ሌላው በእንስሳት ልማት ላይ ሊያተኩር ይችላል፡፡ አንዱ በዝናብ ተጠቅሞ ቢያመርት ሌላው በመስኖ እንዲያለማ መደገፍ ይቻላል፡፡ አንዱ በቆሎ ቢያመርት ሌላው በቅመማ ቅመም ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ይቻላል፡፡

በዚህ መንገድ ኤክስፖርትና ገበያ መር ስታራቴጅ እየተከተልን ጥራት ያለው ተወዳዳሪ ምርትና አገልግሎት በአለም ገበያ በማቅረብ ፈጣንና ዘላቂ ልማት ልናመጣ እንችላለን፡፡ የሀገራችንንም ስፍራ ልናሻሽልና ደረጃዋን ከፍ ልናደርግ እንችላለን፡፡ የኤክስፖርት ስትራቴጂያችን ውጤታማ እንዲሆን ከአለም አቀፉ ማህበረሰብ ጋር ያለንን ግንኙነት ጤናማ ማድረግ አንድ ተፈላጊ ነገር ነው፡፡ በልማት የሚሰማሩ ባለሀብቶችን የሚስብ የኢንቨስትሜንት ፖሊሲ ከማውጣት በተጨማሪ ለጋራ ጥቅምና ልማት አጋር ልናፈራ አንችልም፡፡ ከአለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋሞች፣ ከአውሮፓ የልማት ማህበርና ከመሳሰሉት ተቋሞችና መንግስታት ጋር የጋራ ጥቅም ለማራመድ የሚያስችል ፈቃደኝነትና ተነሳሽነት ካለን አስቸጋሪ ሁኔታዎችን በድርድርና በውይይት ለመቀነስ የሚያስችል እድል ይኖረናል፡፡ ስለዚህ አለም አቀፍ ግንኙነታችንን ለጋራ ልማት በሚያግዝ መንገድ መምራት ፈጣንና ዘላቂ ልማት ለማምጣት ያለንን አላማ በማሳካት ትልቅ ትርጉም እንዳለው መረዳት ተገቢ ነው፡፡

በአጠቃላይ ኢንዱስትሪ መር ስትራቴጅያችንን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የፖሊሲ ሀሳቦችን፣ ስትራቴጂዎችንና ስልቶችን በየሴክተሩ በመንደፍ ልማትን ለማፋጠንም ሆነ ዘላቂ ለማድረግ የሚቻልባቸውን በርካታ አማራጮች አንድ በአንድ ማቅረብ ቢቻልም ዋናው ነገር ፈጣንና ዘላቂ ልማት ማምጣት የሚቻለው በግብርና ላይ ተመስርቶ ሳይሆን የኢንዱስትሪ መር አቅጣጫችን እንደተጠበቀ ሆኖ በእርግጥም የመሪነት ሚና እንዲኖረው በቅድሚ ለዘርፉ ትኩረት ሰጥተን ማልማት ይኖርብናል፡፡ ኢንዱስትሪን በማልማት ግብርናውንም ሆነ ሌሎቹን የኢኮኖሚ ዘርፎችና አገልግሎቶች ማልማት እንችላለን፡፡ ኢንዱሰትሪ ሲለማ በእርሻው ዘርፍ አሁን ያለው ውጥረት ይተነፍሳል፡፡ የመሬትና የገበሬ ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ ያድጋል፡፡ የእርሻው ምርት አስተማማኝ ገበያ ያገኛል፡፡ ገበሬው አማራጭ የስራ እድል ይፈጠርለታል፡፡ በዚህም ተጠቅሞ ገቢውን ለማሳደግና ኑሮውን ለማሻሻል ይችላል፡፡ ድህነት ደረጃ በደረጃ ይወገዳል ኢኮኖሚው የተሳሰረና ዘላቂ በሆነ መንገድ የተዋቀረና የሚሰራ ሆኖ ይለማል፡፡ የካፒታል ችግር ለኢንዱስትሪ ብቻ ሳይሆን ለግብርና ልማት የሚረጋግጥም ቢሆንም አሁን ያለንንና ወደፊትም ከተለያየ ምንጭ የምናገኘውን ካፒታል ለግብርና ብናውለው ግፋ ቢል የእለት ጉርሱን እያገኘ የሚኖር ሕብረተሰብ እንፈጥር ይሆናል እንጂ የኢኮኖሚውን አወቃቀርና አሰራር ከመሰረቱ ለውጠን ፈጣንና ዘላቂ ወደ ሆነ የልማት ደረጃ ለመግባት ያለን እድል አነስተኛ ነው፡፡ በኢንዱስትሪ ልማት ላይ ማዋል ከቻልን ግን ያለጥርጥር እርስ በርስ

የሚደጋገፍና የተሳሰረ ኢኮኖሚ ከመፍጠር አልፈን ድህነትን በማሸነፍ ፈጣንና ዘላቂ የሆነ ልማት እናመጣለን። የሕዝባችንን ሕይወት ከመሰረቱ የሚቀይር አስተማማኝ ልማት እናስመዘግባለን። የሀገራችንን ደረጃም በማሳደግ ከድህነትና ከኋላቀርነት ሰልፍ አውጥተን ወደብልጽግና ጎራ እናስገባታለን። የልማት ስትራቴጂያችን ባህርይና አላማ በአጭሩ ይኸው ነው።

# 8. የልማት ስትራቴጂያችን የታለመለትን አላማ እንዲያሳካ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች

ቀደም ሲል በተለያየ ሁኔታ ለመግለፅ እንደተሞከረው የልማት ስትራቴጂያችን ሊያሳካው የሚገባ አላማ የታወቀ ነው። ይኸውም ለልማት የሚመች መልካም አስተዳደር በማስፈን ዜጎችን ከድህነት በፍጥነት ሊያላቅቅ የሚችል ተመጣጣኝ የኢኮኖሚ እድገትና ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል በመላ ሀገሪቱ እውን አድርጎ በአለም አቀፉ የኢኮኖሚ ስርዓት ውስጥ የሀገሪቱን ተሳትፎና ስፍራ በማሻሻል ተጠቃሚነቷን የሚረጋግጥ፣ በሁሉም መመዘኛዎች ብቃት ያለው ዘላቂ ልማትና ብልፅግና የሰፈነበት ፍትህዊ የሆነ ካፒታሊስታዊ የኢኮኖሚ ስርዓት መገንባት ነው። የዚህ ዓላማ ዋና ዋና ገፅታዎች አንደኛ ለልማት አመቺ የሆነ መልካም አስተዳደር ማስፈን፣ ሁለተኛ ዜጎችን በፍጥነት ከድህነት ሊያላቅቅ የሚችል ተመጣጣኝ የኢኮኖሚ እድገትና ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል በመላ ሀገሪቱ ማስፈን፣ ሶስተኛ በአለም አቀፉ የኢኮኖሚ ስርዓት ውስጥ የሀገሪቱን ተሳትፎና ስፍራ በማሻሻል ተጠቃሚነቷን ማረጋገጥ አራተኛ በሁሉም መመዘኛዎች ብቃት ያለው ዘላቂ ልማትና ብልፅግና የሰፈነበት ካፒታሊስታዊ የኢኮኖሚ ስርዓት መገንባት የሚሉት ናቸው። እነዚህን ለማሳካት የሚያስችሉ አገር አቀፍ የስትራቴጂ ሃሳቦች በግልጽ የተቀመጡ ቢሆንም የተለየ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡትን ጉዳዮች እንደገና ለይቶ በማውጣት መጠነኛ ማብራሪያ መስጠት ተገቢ ነው።

## 8.1 ለልማት የሚመች መልካም አስተዳደር መፍጠር

ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ከልማት ጋር ያላቸውን ጥብቅ ዝምድና በተደጋጋሚ ሁኔታ ግልፅ ለማድረግ የተሞከረ በመሆኑ በድጋሚ ወደ ዝርዝር ጉዳዮች መመለስ አስፈላጊ አይሆንም። ዋናው ነገር የዴሞክራሲ ስርዓት ካለ መልካም አስተዳደር እንደሚኖር፣ መልካም አስተዳደር ካለ ደግሞ ፈጣንና ዘላቂ ልማት መፍጠር እንደሚቻል መረዳት ነው። በሀገራችን የዴሞክራሲ ስርዓትና መልካም አስተዳደር ሳንመሰርት ልማት ልናመጣ እንደማንችል የታወቀ ነው። ለምንመኘው ፈጣንና ዘላቂ ልማት የሚጎድለን ትልቅ ነገር ቢኖር የዴሞክራሲ ስርዓትም መልካም አስተዳደርም አለመመስረታችን ነው። አሁን በሀገራችን የነገሰው የጭቆና አገዛዝ በመሆኑ ለልማት አስፈላጊ የሆነው አንድ መሰረታዊ ቅድመ ሁኔታ በሀገራችን አልተሟላም። ኢዴአፓ ያቀረበው ብሔራዊ የልማት ስትራቴጂ የታለመለትን አላማ እንዲያሳካ በቅድሚያ ለልማት የሚመች መልካም አስተዳደር በሀገሪቱ መመስረት እንዳለበት ያምናል። በመሆኑም ሕዝብ የመንግስት ስልጣን ምንጭና ባለቤት የሆነበት፣ የዜጎች መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች የተከበሩበትና የሕግ የበላይነት ሙሉ በሙሉ የተረጋገጠበት ዴሞክራሲያዊ የሆነ ሕገመንግስታዊ ስርዓት በሀገራችን መፈጠር አለበት። አሁን ያለው አገዛዝ ፈጣንና ዘላቂ ልማት ለማምጣት አስፈላጊ የሆኑትን የሲቪል ሰርቪስ፣ የፍትህ አካላትና የመሳሰሉትን ተቋሞች ለሕዝብና ለሕግ የሚገዙ ሳይሆኑ የአንድ ፖለቲካ ቡድን አጀንዳ ማስፈፀሚያ ሆነው እንዲያገለግሉ አድርጎ በአምሳሉ ቀርጿቸዋል። ኢዴአፓ ደግሞ እነዚህ ተቋሞች ከማንኛውም ባለሥልጣንና የፖለቲካ ቡድን ተፅዕኖ ነፃ ሆነው በሚሰሩበት፣ በሕግና ለሕዝብ ተገዥ በሚሆኑበት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነትን ተከትለው በሚደራጁበትና በሚሩበት ሁኔታ ላይ ትኩረት ይሰጣል።

የሀገራችን ሲቪል ሰርቪስ የፓርቲዎች የፖለቲካ አቋምና የመንግስት ፖሊሲ በማይደበላለቁበት መንገድ ገለልተኛነቱንና የሕዝብ አገልጋይነቱን ጠብቆ እንዲደራጅና እንዲሰራ መደረግ አለበት። በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ የሚገቡ ሰዎች የሚመዘኑበት መስፈርት የፖለቲካ ታማኝነት መሆኑ ቀርቶ በብቃትና ችሎታ ብቻ እንዲሆን መደረግ ይገባዋል። የአሁኑ አገዛዝ በፖለቲካ ታማኝነት

መመዘኛ እየተጠቀመ የማይፈልጋቸውን ዜጎች በሰበብ አስባብ ከሲቪል ሰርቪሱ አውጥቶ ለፖለቲካው የሚስማሙትን ሰዎች ካለችሎታቸው በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ቦታ ቦታ አስይዞ በማስቀመጡ ተቋሙ ዴሞክራሲያዊ ባህርይና ይዘት የሌለው የአንድ ፓርቲ ቅርንጫፍ ወደ መሆን ደረጃ ዘቅጧል። ኢዴፓ ይኸንን የተበላሸ ተቋም ዴሞክራሲያዊ ባህርይ የተላበሰ ሆኖ እንዲደራጅና እንዲሰራ ትኩረት ይሰጣል። ማንም ዜጋ በግሉ ያለው ፖለቲካዊ እምነት እየተከበረለት በመንግስት ሲቪል ሰርቪስ ሕግና ስርዓት እየተመራ ሞያውና ችሎታው በሚፈቅድለት በየትኛውም የስራ መስክ ተሰማርቶ በነፃነት እንዲሰራ የሚያስችል ማስተካከያ ይደረጋል። ከፖለቲካ ተሿሚዎች በስተቀር ማንኛውም የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኛ የሚመራው በሲቪል ሰርቪሱ ሕግ ብቻ እንዲሆን ይደረጋል። የሲቪል ሰርቪሱ አደረጃጀትና አሰራር ግልፅነትና ተጠያቂነትን መሰረት ያደረገና በገለልተኝነት ለሕዝቡ አገልግሎት ለመስጠት እንዲችል ሆኖ ይደራጃል።

የፍትህ ተቋሙም ያጋጠመው ችግር ከሲቪል ሰርቪሱ ያለተለየ ነው። በሀገራችን ነፃ የፍትህ ተቋምና የዳኝነት ስርዓት ጠፍቶ ሁሉም ነገር በፖለቲካ ካድሬዎች የሚወሰንበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ስለዚህ ኢዴፓ የፍትህና የዳኝነት ተቋማቱ የአንድ ፖለቲካ ድርጅት አገልጋይ ከሆኑበት ሁኔታ ወጥተው በነፃነት እንዲደራጁና እንዲሰሩ የሚያስችል ሁኔታን ይፈጥራል። በእነዚህ ተቋሞች የሚመደቡ ሰዎች በሞያ ብቃታቸው፣ በስራ ልምዳቸውና በስነምግባራቸው የተመሰገኑ መሆናቸውን በሚያረጋግጥ ግልፅ አሰራር እንዲመደቡ በማድረግ የአሰራር ነፃነታቸው እንዲከበር፣ ለአገልገሎታቸው ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያና ማበረታቻ እንዲያገኙ፣ ስራቸውን በሚሰሩበት ጊዜ ለሕግና ለሕሊናቸው ብቻ ታማኝ ሆነው እንዲሰሩ የሚያስችል ምቹና ሕጋዊ ሁኔታ ይፈጠርላቸዋል። በስራ ላይ የሚፈፅሙት ጉድለት ሲኖር የፖለቲካ ግምገማን ተከትሎ በሚሰጥ ፖለቲካዊ ውሳኔ ሳይሆን ግልፅነትንና ተጠያቂነት መሰረት አድርጎ በተዘጋጀ ግልፅ የሕግ አሰራር ብቻ ውሳኔ የሚገኙበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት።

በሕግ አውጭው፣ በሕግ አስፈፃሚውና በሕግ ተርጓሚው መካከል ግልፅ የሆነ የስራ ክፍፍልና የእርስ በርስ ቁጥጥር እንዲኖር በማድረግ በአሁኑ አገዛዝ ህግ አስፈፃሚው አካል ብቸኛው አድራጊና ፈጣሪ የሆነበት ሁኔታ መቀየር ይኖርበታል። አስፈፃሚው አካል የሕግ አውጭውንም የሕግ ተርጓሚውንም ኃላፊነት ጠቅልሎ የያዘበት አሰራር እንዲቀየር ተገቢ ሕጋዊ እርምጃ መወሰድ ይገባዋል። አስፈፃሚው ሁሉንም ጉዳዮች እንደፈለገው በሚወስንበት ሁኔታ የቢዝነስ ጥቅሞቹን የሚጠብቅለት ሕጋዊ ሥርዓት እንደሌለ በማየት ባለሀብቱ በሙሉ ልብ ወደ ልማት የሚገባበት ሁኔታ ስለማይኖር ይኸንን እምነት የሚሸረሽሩ የፖለቲካ አሰራሮች መቀየር አለባቸው። እነዚህንና የመሳሰሉትን የዴሞክራሲ ስርዓትና የመልካም አስተዳደር ሁኔታዎች አሟልተን የተረጋጋ የፖለቲካ ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ ካልቻልን ፈጣንና ዘላቂ ልማት በሀገራችን ለማረጋገጥ አንችልም። በመሆኑም ለልማት የሚመች መልካም አስተዳደር መኖሩ የሚረጋገጥባቸው ዴሞክራሲያዊ የመንግስትና የሲቪል ተቋሞች በሀገራችን እንዲመረቱ ትኩረት ሰጥተን መረባረብ ግድ ነው።

## 8.2. ሰብአዊ ልማት

ሌላው ትኩረት የምንሰጠው ጉዳይ የሰው ኃይላችንን ለተፋጠነና ዘላቂ ልማት እንዲመች አድርጎ ማዘጋጀት ነው። በማንኛውም ሕብረተሰብ የመንግስት የኢኮኖሚ አመራር ግብና ዓላማ መሆን ያለበት የሕዝብን የኑሮ ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ ማሻሻል ነው። ሰብአዊ ሁኔታ ፈርጀ ብዙ ገፅታዎች ያሉት ሲሆን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው። የአንድ አገር ሕዝብ የኑሮ ደረጃ መሻሻልና ማደግ የሚችለው ልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ሲመቻቹ ነው። እነዚህ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችም ከፍተኛ ምጣኔ ያለው የኢኮኖሚ እድገት፣ ሰፊ የስራ እድል፣ ፍትሃዊ የገቢ ክፍፍል፣ የገበያ ዋጋ መረጋጋትና የውጭ እዳ ክፍያ ሚዛንን ለመጠበቅ የሚያስችል አቅም ናቸው። የአንድ አገር ሕዝብ የኑሮ ደረጃ ይዞታም በእነዚህ በተዘረዘሩት ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች እንደሚገኙበት ደረጃ ይወሰናል።

በአንድ አገር የሰብአዊ ልማት ይዞታ ምን እንደሚመስል ለመገንዘብ የአገሪቱን ሰብአዊ ልማት ፈለግ ወይም አዝማሚያና ደረጃ ለይቶ መረዳት ያስፈልጋል። የሰብአዊ ልማት ፅንሰ ሃሳብ አራት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት። እነዚህም ምርታማነት፣ እኩልነት፣ ዘላቂነትና በውሳኔ ተሳትፎ ማድረግ ናቸው።

አንደኛ፣ የአንድ አገር ሕዝብ የኑሮ ደረጃ የሚሻሻለው ብዙ ለማምረትና በቂ አገልግሎቶች ለማግኘት ሲቻል ነው፤ ስለዚህም ሕዝቡ ገቢ በሚያስገኙ የምርት ተግባራት ሙሉ በሙሉ የመሳተፍ፣ እንዲሁም ምርታማነትን የማሳደግ ግዴታ አለበት፤ ይህ መሆን ሲችልም ኢኮኖሚያዊ እድገት የሰብአዊ ልማት አንድ አካል ይሆናል። ሁለተኛ፣ ሰዎች በማንኛቸውም ነገር እኩል እድል ሊኖራቸው ይገባል፤ ሕዝቡ በኢኮኖሚውና በፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርግና የተገኙ የልማት ውጤቶች ተጠቃሚ ለመሆን እንዲችልም አድልዎና ማበላለጥ መወገድ አለባቸው። ሶስተኛ፣ በልዩ ልዩ እድሎች እኩል የመጠቀም መብት በዘመኑ ለሚኖረው ትውልድ ብቻ ሳይሆን ለመጪዎቹም ትውልዶች የሚተላለፍና ዘላቂነት ያለው መሆኑ መረጋገጥ አለበት፤ በየዘመኑም አገልገሎት ላይ የዋሉት ልዩ ልዩ አካላዊ፣ ሰብአዊና አካባቢያዊ ጥሪቶች መተካት አለባቸው። አራተኛ፣ ልማት ለሕዝብ ብቻ ሳይሆን በሕዝብ መደገፍም አለበት፣ ስለዚህም ሕዝቡ የልማት እቅዶችን በመንደፍና ተግባራዊ በማድረግ ሂደቶች ሙሉ በሙሉ በቀታተ ወይም በወኪሎቹ አማካይነት የመሳተፍና የመወሰን መብት ሊኖረው ይገባል።

ከላይ በተጠቀሱት መስፈርት መሰረት፣ የኢትዮጵያ ሰብአዊ ልማት ደረጃ 25 በመቶ ገደማ እንደሚሆን ይገመታል። ይህ ነጥብ ከዓለም አማካይ ነጥብ አንድ ሶስተኛ፣ እንዲሁም ከታዳጊ አገሮች አማካይ ነጥብ ከግማሽ የሚያንስና በጣም ወደኋላ የቀሩና ያልለሙ የሚባሉ አገሮች ካገኙት አማካይ ነጥብ ደግሞ በሶስት አራተኛ ዝቅ ያለ ነው። ስለዚህ የሰው ኃይል ልማታችንን ማሳደግ ለአጠቃላይ የልማት ስትራቴጂያችን ውጤታማ መሆን ቁልፍ ጉዳይ በመሆኑ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተን መስራት ይጠበቅብናል።

በሰው ኃይል ልማት ልዩ ትኩረት የምንሰጠው የሕዝቡን ሁለገብ ተሳትፎ ከማሳደግ ጎን ለትምህርትና ስልጠና ነው። አሁን በሀገራችን ያለው የትምህርት ስርዓት ነፃ አስተሳሰብና የሞያ ብቃት ያለው ዜጋ ለማፍራት ሳይሆን «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» የሚገባውን የአንድ ፖለቲካ ቡድን ርዕዮተዓለማዊ ግንዛቤ የጨበጠ የፖለቲካ ካድሬ ለማፍራት ዓላማ የተዘጋጀ ነው። በመሆኑም የስራ ብቃት፣ በራስ የመተማመን መንፈስና ነፃ አስተሳሰብ ያለው ዜጋ ለማፍራት የሚያስችል ስርዓተ ትምህርት ከማዘጋጀት ጀምሮ የስራ ላይ ስልጠናዎችንና የሞያ ብቃት ማሻሻያ ፕሮግራሞችን በሰፊው እስከመጠቀም የሚደርስ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል።

## 8.3 ድህነትን መቀነስ

ፈጣንና ዘላቂ ልማት ለማምጣት በምናደርገው ጥረት ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው ድህነትን መቀነስ ነው። ድህነት ውስብስብና ዘርፈ ብዙ ነው። ኢትዮጵያ በልማት ወደኋላ መቅረቷን የምንረዳው የሕዝቧን የኑሮ ሁኔታ ስንመለከት ነው። በግምት ከግማሽ በላይ የሚሆነው ሕዝብ ፍፁም ድህነት በሚባለው ደረጃ ላይ ያለ ነው። ከሚወለዱት ሕፃናት ውስጥ ከአስር ከመቶዎቹ በላይ አንድ ዓመት ሳይሞላቸው ይሞታሉ። እንደገናም ከሚወለዱት ስምንት ከመቶ በላይ የሚሆኑት አምስት ዓመት ሳይሞላቸው ይሞታሉ። ብዙዎቹ የሚሞቱት አስቀድሞ መከላከያ ሊደረግላቸው በሚችሉ ምክንያቶች ነው።

የአገሪቱን ፖሊሲ በመንደፍ በኩል ዋና ትኩረት የሚያስፈልገውና ከባዱ ጉዳይ ድህነትን መቀነስ ነው። ይህ ተግባር አጣዳፊ ነው ቢባል ማጋነን አይደለም። አስቸጋሪነቱንም አቃሎ መናገር አይቻልም። መንግስት ተስማሚ ፖሊሲዎችን ለመቅረፅ ከተነሳ፣ አመቺ ሁኔታዎችን ካመቻቸና ሕዝብን በማስተባበርና በማንቀሳቀስ ረገድ ንቁ አመራር ከሰጠ ይህ ተግባር ሊከናወን ይችላል። በእንዲህ ዓይነቱ ፖሊሲ መንደፍ ሂደት ውስጥ መንግስትና ህብረተሰቡ እጅ ለእጅ ተያይዘው አንድ ላይ ሆነው ተግተው መስራት ይኖርባቸዋል።

የአገሪቱ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በእጅጉ አሳሳቢ ናቸው። ቀጣይነት ያለው ዘርፈ ብዙ ስትራቴጂ ለመንደፍና የተነደፉትን የልማት ስትራቴጂዎች በተግባር ለመተርጎም የሚበቃ ችሎታ መኖር አለበት። ይህ ካልሆነ ግን አስተማማኝ ውጤት ማግኘት አይታሰብም። እዚህን ችግሮች በብቃት ለመቅረፍ ከመሪዎች ጥበብና ራዕይ ይጠበቃል። አገሪቱ የምትፈልገውን

ሰብአዊ ሀብት ብዛትና ብቃት በተመለከተም ሆነ ያለውን የተመናመነ ሀብት ለተፈላጊው ትክክለኛ ጉዳይ ለማዋል የምሁራንን ምክር ማዳመጥ ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪም ርዕዮተ ዓለማዊ አጀንዳ ለመፈፀም ከሚያስቡ ሳይሆን የአገሪቱን ፍላጎቶችና ችግሮች ለማቃለል ሲሉ ከሚተባበሩ የዓለም አቀፍ ማህበረሰቦች ድጋፍ ማግኘት ጠቃሚ ነው፡፡ በሌላ አባባል ድህነትን የመቅረፍ ተግባር ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ ይፈልጋል፡፡ አገሪቱ ያሉዋትን የሀብት ምንጮች ሁሉ፣ በተለይም ሰብአዊ ሀብትን በብቃት መጠቀምን ይጠይቃል፡፡

# 8.4 **የሕዝብን ተሳትፎ ማሳደግ**

ፈጣንና ዘላቂ ልማት ከሕዝብ ተሳትፎ ውጭ የሚታሰብ አይደለም፡፡ በቅርብ ዘመን ተቀባይነት እያገኘ የመጣው የልማት አስተሳሰብ በተቀናጀ ፖለቲካና የኢኮኖሚ አመለካከት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህ አመለካከትም የኢኮኖሚ ችግሮች በኢኮኖሚ ለውጦች ብቻ የሚሰኑ እንዳልሆኑ ያሳያል፡፡ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ችግሮችን ለመፍታት ለመዋቅራዊ ጉዳዮች ትኩረት የሚሰጥ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲ፣ ብቃት ያለውና ከሙስና የነፃ ቢሮክራሲ፣ ተጠያቂነት ያለበት መስተዳድራዊ መዋቅር፣ የተረጋጋ ፖለቲካና ከሁሉም በላይ በሁሉም ሕብረተሰብ ውስጥ ሰፊ የልማት ትብብር መመስረት አስፈላጊ ናቸው፡፡ እዘኒህን መሰል ትብብሮች ለማካሄድ ከሚመለከታቸው አጋሮች ጋር በፖሊሲ ጉዳዮች፣ ቀረፃዎችና ትግበራዎች እንደልብ ሊወያይና ሊመካከር የሚፈቅድ መንግስት መኖር አስፈላጊ ነው፡፡

በፖሊሲ አሰራር ሂደት ውስጥ የመመካርን አስፈላጊነት ደግመን ደጋግመን የምናነሳው ያለምክንያት አይደለም፡፡ አገራችን ያለባት የልማት ችግሮች ጥቂት «አዋቂዎች» እንደሚገምቱት ሳይሆን ማንኛውም ወገን ብቻውን ሊሸከማቸው የሚከብዱ፣ ማንኛውም ምሁራዊ የእውቀት ዘርፍ በተናጠል ሊረዳቸው የማይችሉና ውስብስቦች ናቸው፡፡ ስለዚህም የፖሊሲ አወጣጡ ሂደት ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚያሳትፍ ልዩ ልዩ ፅንሰ ሃሳቦች የሚንፀባረቁባቸውና ልዩ ልዩ ፖለቲከዊና ርዕዮተ ዓለማዊ አቋሞችን የሚያካትት መሆን አለበት፡፡

ተሳትፎ የዜጎች ሁሉ መብትም ግዴታም ነው፡፡ በአገራችን ጉዳይ አለመሳተፍ ወይም ጉዳዩ እንደማይመለከተን መቆጠር የሚጥረውን ችላ የመባል የስጋትና የመገለል ስሜት ያህል አስከፊ ነገር የለም፡፡ ተሳትፎ ሲኖር ቀደም ሲል ያለመጠንና ከእኛ ተፅዕኖ ውጭ የመሰለንን ጉዳይ ሁሉ በቁጥጥራችን ስር እንዳደረግነው ይሰማናል፡፡ ተሳታፊነት ማለት ዜጎች በቤት፣ በስራ ቦታና ማህበራዊ ሕይወታቸውን በሚመለከቱ ሁሉም ዓይነት ውሳኔዎች ላይ መካፈልን ይጨምራል፡፡ የተጠናከረ ሕዝባዊ ተሳትፎ ካለ ሕዝብ ራሱ በራሱ ጉዳይ ላይ ሃሳብ ያፈልቃል፣ ፖሊሲ ይነድፋል፣ ይፈፅማል፣ ያስተዳድራል እንዲሁም ውጤታቸውን ይገመግማል ማለት ነው፡፡

በተጨማሪ ስልጣንን ወደ ሕዝብ መውረድ ለሕዝባዊ ተሳትፎ ወሳኝና እንዲያውም አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ ይህ ማለት በአካባቢው ለተመረጡና ተጠያቂነት ላለባቸው ተወካዮች እውነተኛ ውሳኔ የማድረግን ስልጣን ማዛወር ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ስልጣንን ወደ ሕዝብ ማውረድ የመንግስት ወጪ ለገጠሩም ለከተሞችም ሚዛናዊ እንዲሆን ማከፋፈልንና ለሕዝብ ፍላጎት መልስ የሚሆን አገልግሎት በቀጥታ ለሕዝብ ማውረድ ማለትም ነው፡፡ ይህ መርህ ውሳኔ አሰጣጥና አፈፃፀም በተቻለ መጠን እስከ ታች ድረስ መውረዱን የሚያረጋግጥ በመሆኑ በከፍተኛ ደረጃ ተመራጭነትን አትርፏል፡፡

በአገራችን የድህነት መባባስ ዋነኛው ምንጩ መልካም አስተዳደርን ሊያስገኝ የሚችል የተረጋጋ የፖለቲካ ስርዓት መፍጠር ባለመቻሉ ነው፡፡ ስለሆነም በአገራችን ሕዝባዊ ስልጣንን መሰረት ያደረገ ፖለቲካዊ ስርዓት መመስረት ለዘላቂና አስተማማኝ የሆነ የድህነት መቀነሻ ቁልፍ ነው፡፡ የፖለቲካው ችግር ባግባቡ ከልተፈታና ሁሉም ዜጎች በአገራችን ጉዳይ ካልተሳተፉ ድህነትን መቀነስ አይቻልም፡፡ በአገራዊ ፖሊሲ ቀረፃና ትግበራ ሂደት ውስጥ መመካከረ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የአገራዊ ፖሊሲ አወጣጥ ሂደት ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በማሳተፍ የተለያዩ ሃሳቦችንና አመለካከቶችን ማካተት ይኖርበታል፡፡

## 8.5 የመንግስት ፋይናንስና በጀት፣ አስተዳደርና አጠቃቀም ፍትሃዊ እንዲሆን ማድረግ

*የምንኖረው ሁሉ ነገር እንደልብ በማይገኝበት ውስን ዓለም ውስጥ ነው:: የአንድ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ተገቢነት የሚወሰነው፣ ፖሊሲው ተግባራዊ በሚሆንበት አካባቢ ያሉ ማነቆዎችን ለማቃለል በሚያቀርባቸው አማራጮች ነው:: መንግስታት ብዙ ነገሮችን ለማከናወን ላላቸው ምኞት በእጅጉ የሚያሰናክላቸው (የፋይናንስ ምንጮችን በማግኘት ረገድ ማነቆ የሚሆንባቸው) የበጀት ፖሊሲ ነው:: በዚህም ምክንያት መንግስታት ብዙ ጊዜ ገቢያቸውን በየትኛው አገልግሎት ላይ እንደሚያውሉት ለመምረጥ ይቸገራሉ:: ልዩ ልዩ መርሀ ግብሮችን ለማስፈፀም የሚያስችል ገንዘብ የማግኛ ምንጮችን ለመፈለግም ይገደዳሉ:: በእርግጥ ብዙ የፖለቲካ ሰዎች፣ በተለይም በምርጫ ሰሞን ብዙ መርሀግብሮችን ለማከናውን ለሚመርጣቸው ሕዝብ ቃል ይገባል:: ሆኖም ስልጣን ሲይዙ  መርሀ ግብሮቻቸው ከፍ ያለ ጠቀሜታ ያላቸው መሆናቸውን ቢያውቁም እንኳ ሁሉንም ለማስፈፀም የሚያበቃ በጀት ሊገኝ እንደማይቻል ይረዳሉ:: ለዚህም ነው ብዙ ጊዜ ኢኮኖሚስቶች የፖለቲካ ሰዎች ልብ የት እንዳለ ለመረዳት የፈለገ ሰዎቹ ስለ አገራቱ በጀት ያላቸውን ግንዛቤ በቅድሚያ ማወቅ አለበት እያሉ የሚናገሩት:: ኢትዮጵያን በመሰሉ አገሮች ብዙ ጊዜ የመንግስት ባለስልጣኖች ስለፖሊሲ ጉዳዮች ከሚሰጡት መግለጫ ይልቅ የመንግስትን ገቢ እና ወጭ ፖሊሲ በጥንቃቄ መመርመር የመንግስትን ፍላጎትና መመሪያ ለመረዳት ያስቻላል::*

*የመንግስትን ፋይናንስ በጥልቀት መመርመር የሚያስፈልግበት ምክንያት አለ:: አንደኛ ሕግና ደንብን፣ ትምህርትና ስልጠናን፣ የጤና እንክብካቤ አገልግሎትን፣ መሰረተ ልማትን ብሔራዊ መከላከያን፣ የመረጃ አቅርቦት አገልግሎትን፣ ምርምርና ልማትን የመሳሰሉት በአብዛኛው ለነፃ ገበያው ብቻ የማይተው በመንግስት ጭምር የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው:: ከዚህም በተጨማሪ የተረጋጋ ማክሮ-ኢኮኖሚ ለመፍጠር የገበያዎችን ውድቀት በመከላከልና በመሳሰሉት የመንግስት ጣልቃ መግባት አስፈላጊ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ የመንግስትን ገቢና ወጪ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዲመራ በማድረግ ሀብትን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ  በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ማሰራጨት ስለሚገባ ለዚህ ጉዳይ ትኩረት መስጠት ከፍትሃዊነት ጥያቄ ጋር የተያያዘ ነው::*

*በመንግስት ወጪዎችና ገቢዎች መካከል የሚታዩት ክፍተቶችን ለማጥበብ ከሚያስችሉ መንገዶች አንዱ ወጭን መቀነስ ነው:: በዚህም ምክንያት የሀብት ምንጮች ከመከላከያ ዘርፍ ወደ ማህበራዊ ዘርፍ (ትምህርትና ጤናን ለመሳሰሉት) እና ወደ ኢኮኖሚ መሰረተ ልማት እንዲዛወሩ የሚደረገው ጥረት ተቀባይነት አለው:: ነገር ግን በሀገራችን ለመከላከያ የሚመደበው ወጪ አሁንም ዝቅተኛ ነው የባሚል አይደለም::*

*ከመንግስት ገቢ ውስጥ ትልቁን ድርሻ የሚሸፍነው ከግብር የሚሰበሰበው ነው:: ከ*1974 *እስከ* 1990 *ዓ.ም በአገር ውስጥ ከተገኘው ጠቅላላ ገቢ ከቀረጥ የተሰበሰበው* 70 *በመቶ ያህል ነበር:: ከዚህም ውስጥ* 40 *በመቶ ያህሉ ከቀጥተኛ ቀረጥ* 30 *በመቶ ቀጥተኛ ካልሆነ ቀረጥ እና* 30 *በመቶ ደግሞ ከውጭ ንግድ ቀረጥ የተገኘ ነው:: ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርት የቀረጥ ገቢ ሲታሰብ በአማካይ ከ*12 *ከመቶ በላይ ይሆናል:: ሌላው ከመንግስት የአገር ውስጥ ገቢ* 30 *ከመቶ የሚሆነው የሚገኘው ከቀረጥ ውጭ የሆኑ ልዩ ልዩ ገቢዎች ነው:: ከዚህም በተጨማሪ ከውጭ እርዳታ የሚገኘው ገቢ ባለፉት ዓመታት በዓመት ከአገር ውስጥ ከሚገኘው ገቢ እስከ* 50 *በመቶ ያህል ደርሶ ነበር:: የግብር አሰባሰብ ስርዓቱ የመክፈል ብቃትንና ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ካለመሆኑም ሌላ መጠኑ ከፍተኛ ነው:: የታክስ ቤዙ ጠባብ በመሆኑ የታወቁትን ግብር ከፋዮች ብቻ የሚያሳድድ ሲሆን የአሰባሰብ ስርዓቱም ችግር ያለበት ነው::*

*የመንግስት ወጪዎች የሚባሉት የስራ ማስኬጃና የካፒታል ወጪዎች ተቀናጅተው ነው:: የስራ ማስኬጃዎች የመንግስትን ልዩ ልዩ አካላት ለማንቀሳቀስ የሚውሉና በባህሪያቸውም ተመላላሽነት ያላቸው ናቸው:: የካፒታል ወጭዎች የሚባሉት ደግሞ ቋሚ ጥሪቶችን ለመግዛት የሚውሉ ሲሆኑ የመንግስት የልማት ወጪዎች ሊባሉ ይችላሉ::*

እዘኒህ ወጪዎች የሚሸፈኑት ከፍ ብለው የተገለፁትን የበጀት እርምጃዎች ለማንቀሳቀስ ከሚሰበሰቡ ገቢዎች ነው። የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅና ኢኮኖሚውን ለማቀላጠፍ የገቢ ምንጮችን በተገቢው ጥንቃቄ ማስተዳደርና በዝቅተኛ ወጭ ከፍተኛ ተግባር ለማከናወን መጣር አስፈላጊ ሁኔታዎች ናቸው።

የስራ ማስኬጃ ወጭ በ1974 ከነበረበት የ2.6 ቢሊዮን ብር መጠን በ1990 ወደ 7.1 ቢሊዮን ሊያድግ ችሏል። የስራ ማስኬጃ ወጪዎች በአራት ዋና ዋና ፈርጆች ሊዋቀሩ ይችላሉ። እነሱም፤ አንደኛ፣ አጠቃላይ ሕዝባዊ አገልግሎት (ልዩ ልዩ የመንግስት አባላትና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ፣ ለፍትሕ፣ ለመከላከያ ወዘተ.) ሁለተኛ፣ ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት (የግብርና፣ የኢንዱስትሪ፣ የትራንስፖርትና መገናኛ፣ ወዘተ.) ሶስተኛ፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች (የትህምርትና ስልጠና፣ የጤና አገልግሎት፣ ወዘተ.) አራተኛ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች (የጡረታ ክፍያዎች፣ የእዳ አገልግሎት፣ ድጎማዎች፣ ወዘተ.) ለመሰሉ ተግባራት የሚውል የስራ ማስኬጃ ወጪ ነው። ከ1984 ዓ.ም እስከ 1990 ዓ.ም የነበረውን የስራ ማስኬጃ ብንመለከት፣ ለጠቅላላ ሕዝባዊ አገልግሎት 34 በመቶ፣ ለኢኮኖሚያዊ አገልግሎት 10 በመቶ፣ ለማህበራዊ አገልግሎት 25 በመቶ እና ለልዩ ልዩ አገልግሎት 31 በመቶ ነበር። ከ1986 እስከ 1990 የመከላከያ ወጪ እያደገ ሄዶ ከኢትዮ- ኤርትራ ግጭት በፊት 2.1 ቢሊዮን ደርሶ ነበር።

የካፒታል ወጪ በ1974 ከነበረበት የ1.2 ቢሊዮን ብር ደረጃ በ1990 ዓ.ም 4.2 ቢሊዮን ብር ደርሶ ነበር። ከ1984 ዓ.ም እስከ 1990 ዓ.ም የነበረውን የካፒታል በጀት ብንመለከት፣ ለኢኮኖሚያዊ አገልግሎት 75 በመቶ፣ ለማህበራዊ አገልግሎት 20 በመቶ እና ለጠቅላላ ልማት 5 በመቶ ነበር። የካፒታል ወጪያችንና የልማት ፍላጎታችን እጅግ የተራራቁ በመሆናቸው ይኸንን ክፍተት ደረጃ በደረጃ ለማጥበብ የሚያስችል ልማት ማጠናከር ይገባናል።

እዚህ ላይ ሳይነሳ መታፍ የሌለበት ጉዳይ የመከላከያ በጀት ጉዳይ ነው። ከጎረቤት አገሮች ጋርም ይሁን የእርስ በርስ ግጭት መቀነስ ብሎም መወገድ ለአገራችን ልማት ወሳኝነት ያለው የበጀት መሸጋሸግ ሊፈጥር እንደሚችል ነው። ስለዚህ እዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባ ጉዳይ በአገራችን ሰላም እንዲሰፍን ሳንታክት መስራት ከሚያስገኘው የመንፈስ መረጋጋት በተጨማሪ ለአጠቃላይ እድገታችን ወሳኝ መሆኑን ነው።

## 8.6 የግሉን ዘርፍ በአጋርነት መመልከትና ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት

በአገራችን አንዳንድ ጊዜ ጤናማ የማክሮ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ካስገኙት ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል ከበጎ አድራጊዎች የተገኙ ድጋፎችና ተፈጥሯዊ ሁኔታዎች ተስተካክለው ጥሩ ዝናብ መኖር ነው። ሆኖም ዝናብም ሆነ ረድኤት አድራጊዎች በመለዋወጥ ባህሪያቸው ምክንያት አስተማማኝና ዘላቂነት የላቸውም።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት በኢትዮጵያ በኢንቨስትመንት ረገድ የተሰበሰቡት መረጃዎች በሙሉ በግልፅ እንደሚያመለክቱት በአብዛኛው ለአገሪቱ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴና ለኢኮኖሚ እድገት ነዳጅ የሆነው የአገር ውስጥ የግሉ ዘርፍ ነው። የአገር ውስጥ የግሉ ዘርፍ ይህን ማድረግ የቻለው አያሌ ማነቆዎችን በመቋቋም ነው። የሻገተው የመንግስት ቢሮክራሲ ከአገር ውስጥ የግሉ ዘርፍ ይልቅ ለውጭ አገር ሰዎች ቅድሚያ የሚሰጥ ይመስላል። የካፒታል እጥረት ያለበት የአገር ውስጥ የግሉ ዘርፍ ከውጭ አገር ሰዎች በመወዳደር የወረቱን ብዙ እጅ መሬት ለማግኘት እንዲከፍል ይገደዳል። ከዚህም ሌላ መሬት ለማግኘት አነሰ ቢባል የብዙ ወራት ወይም የዓመታት ድካም ይጠይቃል። ማስተዋል በተሳናቸው መስተዳድሮችም ያለምንም ጥቅም ካፒታልን ለመሬት አፍስሶ እንዲቆይ ይደረጋል። ለምሳሌ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የጣለው ከልክ ያለፈ የኪራይ ጭማሪም ብዙ የአገር ውስጥ ነጋዴዎች ከንግድ ስራ እንዲወጡ አድርጓል። የመንግስት ኢንተርፕራይዞችን ለመግዛት የሚደረገው «ነፃ ውድድርም» የአገራችን የግል ዘርፍ ወደ ዘመናዊ አምራችነት እንዳይገባ አድርጎታል። በመሆኑም በግሉ ዘርፍ የተሰማራው ብሔራዊ ባለሀብት ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዳያደርግ ቀስ በቀስ ከዚህ አዳጊ

ዘርፍ እየተገፋ እየወጣ ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ችግሮች እያሉም የአገር ውስጥ የግሉ ዘርፍ አሁንም ከፍተኛው ኢንቨስተርና የኢኮኖሚ እድገት አንቀሳቃሽ ነው፡፡ ይህ ዘርፍ ከመንግስት ብዙ ድጋፍ ሊሰጠው የሚገባ ቢሆንም እስካሁን ግን ምንም ድጋፍ ያላገኘ ነው፡፡

ዘርፉ ከመንግስት ብዙ ድጋፍ ሊያገኝ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በገዢው ፓርቲ በኩል እየተደረገ ያለው በተቃራኒው ነው፡፡ በግሉ ዘርፍ የተሰማሩትን «ኪራይ ሰብሳቢ»፣ «ጥገኞች»፣ «ቁማርተኞች»፣ ወዘተ. የሚል ቅፅል በመስጠት እንኳን ሊደግፋቸውና ሊያበረታታቸው ጭራሹኑ እንዲዳከሙ አጥብቆ እየሰራ ነው፡፡ ከጥገኝነት ቲዎሪ መረዳት እንደሚቻለው የእኛን ሀገር ጨምሮ የታዳጊ ሀገሮች ኢኮኖሚ ጥገኛ መሆኑን ነው፡፡ በእኛ ሀገር ለብቻው ጥገኛ የሚልና ጥገኛ ያልሆነ ባለሀብት ማግኘት ቀርቶ ጥገኛ ያልሆነ መንግስት እንኳ እንደሌለን የታወቀ ነው፡፡ ስለዚህ የአሁኑ አገዛዝ «ጥገኛ» የሚል ተቀጥላ ያወጣላቸው በፖለቲካ የሚጠላቸውን «የልማት ባለሀብት» የሚላቸው ደግሞ በፖለቲካ የሚስማሙትን ብቻ ካልሆነ በስተቀር ሳይንሳዊና ሚዛናዊ መመዘኛ የለውም፡፡ ስለዚህ አንዱን ባለሀብት ወዳጅ ሌላውን ጠላት አድርጎ መፈረጅ ለልማት የሚጠቅም አስተሳሰብና ከነፃ ገበያ መርህ ጋር የማይሄድ በመሆኑ መወገድ የሚገባው ነው፡፡ ባለሀብቶች መመዘን የሚገባቸው እኩል የተሳትፎ እድል አግኝተው በሚያደርጉት ውድድር ውጤታማ ሆኖ በመገኘትና ተሸንፎ ከውድድሩ በመውጣት ነው፡፡ ማንም ባለሀብት በፖለቲካ አመለካከቱ በዘሩና በትውልድ ቦታው እየተለየ ጥገኛና አልሚ ሊባል አይገባውም፡፡ ይኸንን የሚወስነው ገበያው መሆን አለበት፡፡

# 8.7 ሙስናን መዋጋት

ሌላው የግሉን ዘርፍ አንቆ የያዘው መቅሰፍት ሙስና ነው፡፡ አሁን ባለንበት ወቅት በአገራችን ሙስና «በአይነትም ሆነ በጥራት» አድጎ በስርጭቱም ተስፋፍቶ መገኘቱ ሊሸፋፈን የማይችል ግዙፍ ሀቅ ሆኗል፡፡ ይህች ድሃ አገር ትሸከመዋለች ተብሎ የማይታሰብ የሙስና ቅሌት በራሱ በአገዛዙ መገናኛ ብዙሃን መስማት ከጀመርን ውሎ አደረ፡፡ የሙስናው ባህርይ ደግሞ በግልና በድብቅ የሚካሄድ መሆኑ ቀርቶ ይፋና ተቋማዊ እየሆነ መጥቷል፡፡

በአገራችን ሙስና እዚህ ደረጃ ሊርስ ከቻለባቸው ምክንያቶች መካከል፣ 1ኛ. በሕግ አውጪው፣ ሕግ አስፈፃሚውና በሕግ ተርጓሚው አካሎች መካከል መኖር የሚባው ሚዛን የተዛባ መሆን፣ 2ኛ. የባስልጣኞች ግልፅነትና ተጠያቂነት መጥፋት 3.ኛ የሲቪል ሰርቪስ ስራ አቀጣር፣ አመዳደብ፣ እድገት የመሳሰሉት እርምጃዎች በችሎታ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን በጎሣ (ብሔረሰብ) ላይ ማተኮር፣ 4ኛ. በመንግስት ገንዘብና ንብረት አስተዳደር፣ አሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀም ላይ ግልፅነትና ተጠያቂነት መጥፋት፣ 5.ኛ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ኃይል ተሰባስቦ ባብዛኛው በመንግስትና በሕወሓት/ኢሕአዴግ የንግድ ድርጅቶች እጅ መውደቅና በድምሩ ኢሕአዴግ በብቸኝነት የሚቆጣጠረው በመሆኑ በውጤቱም ነፃ የገበያ ውድድር መዳከም ይገኙበታል፡፡

ሕወሓት/ኢህአዴግ ሕግን በሚጥስ መንገድ ያቋቋማቸው የንግድ ተቋማት በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው፡፡ የነፃ ኢኮኖሚውን እድገት ቀፍድደው ይዘዋል፡፡ ኢሕአዴግ በተለይም ወያኔ የንግድ ተቋማቱን ወረት ያፈራሁት በትጥቅ ትግል ወቅት ነው ይለናል፡፡ ለመሆኑ ሕወሓት ብዙ ንብረት ያፈራሁት በትጥቅ ትግል ጊዜ ነው ሲል ምን ማለቱ ነው? በእርሻው፣ በኢንዱስትሪው በንግዱ መስክ ተሰማርቶ ነው ንብረት ያፈራው? ከመንግስት፣ ከማህበራትና ከግለሰቦች ንብረት አልተወሰደም? በርሃብ ከሞት አፋፍ በደረሰው በትግራይ ሕዝብ ስም ተለምኖ ከመጣው እርዳታ ውስጥስ አልወሰደም? እነዚህን ተቋሞች የምናወግዝበት ምክንያት ከግል ጉዳይና ከፖለቲካ ትርፍ ጋር በተያያዘ መንገድ አይደለም፡፡ ሕገወጥነትን ለመሸለም ካለመፈለግ ቁርጠኛ እምነት በመነሳት ነው፡፡ የሕወሓት የንግድ ኩባንያዎች የገንዘብና የሀብት ምንጫቸው ሕገወጥ ነው ብለን እናምናለን፡፡ አደረጃጀታቸውና አሰራራቸውም እንደዚሁ ሕገወጥ ነው፡፡ የእነዚህን ተቋሞች ሕገወጥነት ባንቃወምና ባንታገል ጠመንጃና ጉልበት ዘላለማዊ ስልጣን እንዲኖቸው እውቅና እንደመስጠት የሚቆጠር ነው፡፡ ማንም ጠመንጃ ያለው ወደበረሃ እየገባ በጉልበት ሀብትና ንብረት ቢዘርፍ የሚጠየቅበት ሁኔታ ስለማይኖር ዝርፊያ አንደኛው የሀብት ማፍሪያ መንገድ እንዲሆን ከመፍቀድ ተለይቶ የሚታይ አይደለም፡፡ ይህ አንደኛውና መሰረታዊው ምክንያት ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የሕዋሓት ንግድ

ኩባንያዎች በተደራጁበትና በሚሰሩበት መንገድ እስከቀጠሉ ድረስ የነፃ ገበያና የመድብለ ፓርቲ ስርዓት እዚህች ሀገር ተግባራዊ የሚሆኑበት እድል የሌለ በመሆኑ ነው። ስለዚህ እነዚህ ተቋሞች የኢትዮጵያ ሕግ በሚደነግገው መሰረት ኢንዶውሜንት ለመሆንም፣ ለትርፍ የሚሰራ የአክሲዮንም ሆነ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለመሆን የሚያስችላቸው ህጋዊ መሰረት ስለሌላቸው ከንግዱ መስክ መውጣት ይገባቸዋል። ኢንዳውሜንት እንዳይሆኑ ለትርፍ የሚሰሩ ሆነው እንዳይቀጥሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ንግድ እንዳያካሂድ የሚከለክለውን የሀገሪቱን ሕግ ይጥሳሉ። ስለዚህ ሕጋዊና አሳማኝ ምክንያት ሳኖራቸው ሕገወጥ በሆነ ስራ ተሰማርተው ስለሚገኙ በሀገሪቱ የፍትሀብሔር ሕግ ከአንቀፅ 463-467 እንዲሁም በዚሁ ሕግ አንቀፅ 506 በተደነገገው መሰረት መፍረስ ይኖርባቸዋል። ከመንግስት፣ ከግልና ከማህበራት ተወስደው የሕወሓት ንግድ ኩባንያዎች የካፒታል መሰረት የሆኑት ንብረቶችና ገንዘብ ለሕጋዊ ባለቤቶቹ መመለስ ይገባዋል።

ሕወሓት/ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ለቡድናዊ ፍላጎቱ በማሰብ ለእነዚህ ሕገወጥ ኩባንያዎች የሰጠው ልዩ ድጋፍ በሌሎች ዜጎችና በሀገሪቱ ጥቅም ላይ ያደረሱት ጉዳት በገለልተኛ ወገን ተጣርቶ ለፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል። ኩባንያዎቹ የመንግስትና የሕዝብን ጥቅም በመጉዳት ያካበቱት ሀብትና ንብረት ያልከፈሉት የብድር፣ እዳና ልዩ ልዩ ክፍያ በገለልተኛ ኦዲተሮች ወይንም የዋናው ኦዲተር በሚወክላቸው መርማሪዎች ተጣርቶ ለሕዝብ ይፋ መደረግ ይገባዋል። ይኸንን ሪፖርት መሰረት አድርጎ አቃቤ ሕግ ክስ ሊመሰርትና በፍርድ ቤት ብይን እንዲሰጥበት ሊደረግ ይገባዋል የሚል እምነት አለን።